# ሸ

**ሸ** ከ "ሰ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ሸህ(ሼህ)** ስ የቁርአን ትምህርት ያለው፥ የቁርአን ምሁር::

**ሸሆና (ሸኮና፥ ሰኮና)** ስ የእንስሳት እግር ወይም መርገጫ ፤ ኮቴ::

**ሸለለ** ግ 1. በዜማና በግጥም የሰራውን ጀብዱ እየጠቃቀሰ አቅራራ:: 2. አጌጠ፥ ተሽቀረቀረ፥ ተሸሞነሞነ::

**ሽለላ** ስ 1. የሚያቅራራ (ሰው):: ቅ 2.ውብ፥ ሽቅርቅር፥ ያማረ::

**ሸለለበት** ኮራበት፥ ዘነጠበት፤ተጀነነበት ::

**ሸላይ** ስ 1. የሚያቅራራ (ሰው):: ቅ 2.ውብ፥ ሽቅርቅር፥ ያማረ::

**ሽለላ** ስ 1.ቀረርቶ:: 2. መጊያጊያጥ፥ መሽቀርቀር::

***ሸለለ**

**ሸለሊት** ስ "እንሽላሊት" ን ተመ.

**ሸለል አለ** ግ ሸረር አለ፤ ፈጠን ብሎ ሄደ (እንደ እንሽላሊት፥ እባብ ያለ ተሳቢ እንስሳ)::

**ተንሻለለ** ግ ሸለል አለ::

**ሸለመ** ግ 1. አስጌጠ፥ አስቆነጀ፥ አስዋበ፥ አሸሞነሞነ:: 2. ቅርፅ አወጣ፥ አዥጎረጎረ፥ ጌጥ አበጀ፥ (በቀለም፥ በቅርፅ ማውጫ ወይም በመንቀሻ መሳሪያ)::3. ለፈፀመው ስራ ማበረታቻ የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥...ሽልማት ሰጠ:: 4. ሳይጎዳ በቀላሉ ለቀቀ (ኩፍኝ፥ ፈንጣጣ)::

**ሽልም** ቅ ጌጥ ወይም ንቅሳት ያለበት::

**ሽልማት** ስ 1. የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥...ስጦታ፥ ዳረጎት:: 2, ጌጥ እንዲሆን ተብሎ የተሰራ እንደ ንቅሳት፥ ሽንትራት ያለ ነገር::

**ሽልምልም** ቅ ዝጉርጉር (ዥጉርጉር)::

**ተሸለመ** ግ 1. ሽልማት፥ ስጦታ ተሰጠው:: 2. ተጌጠ፥ ተሸሞነሞነ፥ ቅርፅ ተበጀለት፥ ተዥጎረጎረ::

**ተሸላሚ** ቅ ለሽልማት የቀረበ ወይም ሽልማት ያገኘ::

**ተሸላለመ** ግ ተጊያጊያጠ፥ ተነቀሰ፥ ተሸሞነሞነ::

**ሸለም** ስ የዘንባባ፥ የኮባ፥ የሙዝ ሙ ሽ ራ ፤ ውልብልቢት::

**ሸለምጥማጥ** ስ 1.ረዥም ጅራት ያለውና በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ፥ በተቦረቦረ ግንድ ወይም በጥሻ ውስጥ የሚኖር ድመት የሚመስል የዱርአውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.):: 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ጥቁር::

**ሸለሸለ** ግ 1. ሰነጠቀ፥ ሰነተረ፥ ገመሰ (እርሻን):: 2. በዝቶ የበቀለን አገዳ ነቀለ (በማረሻ)::

**ተሸለሸለ** ግ በማረሻ ተሰነጠቀ፥ ተሰነተረ፥ ተገመሰ::

**ሸለሸል** ስ በዱር የሚገኝ የደረቀ የከብት እበት፤ ኩበት::

**ሸለቀቀ** ግ 1. ላጠ፥ ገለፈፈ፥ ገፈፈ፥ ቀረፈ:: 2. (ከኪስ፥ ከቦርሳ ብርን) መዘዘ፥ አወጣ::

**ሽልቃቂ** ስ ልጣጭ፥ ግልፋፊ::

**ተሸለቀቀ** ግ ተላጠ፥ ተገለፈፈ፥ ተገፈፈ::

**ሸለቆ** ስ በሁለት ተራሮች ወይም ከፍተኛ ስፍራዎች መካከል የሚገኝ ረባዳ ወይም ጎርጓዳ ቦታ::

***ሸለበ**

**ሽልብታ** ስ ቀላል እንቅልፍ::

**ሸለብ አደረገ** ግ ለትንሽ ጊዜ አንቀላፋ::

**አሸለበ** ግ 1. አንቀላፋ፥ ለትንሽ ጊዜ ተኛ:: 2. (ዘይ.) ሞተ:: *እንደተኛ በዚያው አሸለበ::*

**ሸለተ** ግ 1. ላጨ፥ መደመደ (ፀጉርን):: 2. ጠረበ፥ ላገ፥ ቀረፀ:: 3.(ዘይ.) ሀ - አታለለ፥ አሳተ፥ ሸነገለ:: ለ- ሸረደደ፥ አሸሟጠጠ::

**ተሸለተ** ግ ተላጨ፥ ተመደመደ፥ ፀጉሩ ተነሳለት::

**አሸለተ** ግ ዳነ፥ አገገመ፥ አማረ (ታሞ የነበረ ሰው)::

**ሸለገ[1]** ግ አሰበ፥ አሰላ፤ ለካ፥ ገመተ፥ መዘነ፥ መጠነ::

**ሸለገ[2]** ግ ሆዱን ወደ ውስጥ አስጠጋ፥ አጣበቀ::

**ሸለገ[3]** ግ አታለለ::

**አሸልግ** ቅ አታላይ::

**ሸለፈት** ስ 1. ልንቡጥ፥ ወሸላ:: 2. ልጣጭ፥ ግልፋፊ::

**ሸለፈታም** ቅ (ስድብ) ያልተገረዘ (ወንድ)::

**ሸለፈፈ** ግ ገለፈፈ፥ ላጠ፥ ቀረፈ፥ ገረፈ::

**ሽልፋፊ** ስ ግልፋፊ::

**ተሸለፈፈ** ግ ተገለፈፈ፥ ተላጠ፥ ተቀረፈ፥ ተገረፈ::

**ሸመለለ** ግ ጠቀለለ፥ ሸበለለ::

**ሸመሸመ** ግ 1.ከረተፈ፥ ሸረከተ፥ በቀላሉ ፈጨ:: 2. በብዛት ቃመ፥ በላ (ፈረስ፥ በቅሎ፥... እህልን)::

**ሸመቀ** ግ አደባ፥ ደፈጠ፥ ተደበቀ (አደጋ ለመጣል)::

**ሽማቂ** ስ የደፈጣ ተዋጊ::

**ሽመቃ** ስ የደፈጣ ውጊያ::

**ሽምቅ ተዋጊ** ስ የደፈጣ ተዋጊ።

**ሽምቅ ውጊያ** ስ በማድፈጥና አደጋ በመጣል የሚካሄድ የውጊያ ስልት።

**አሸመቀ** ግ አደባ፥ አደፈጠ፥ ሸመቀ።

**ሸመቀቀ** ግ 1. በሽምቀቆ አስተሳሰር ሳብ አድርጎና አጥብቆ አሰረ፤ አነቀ። 2. ጨምድዶ ያዘ፥ አኮማተረ። *እግሩን ሽምቅቆ ይዞት አላስኬድ አለው።*

**ሽምቀቆ** ስ 1. የከረጢት አፍ ማሰሪያ ጥብጣብ፥ ገመድ፥...። 2. ከጭራ፥ ከጠፍር፥... የተበጀ የወፍ፥ የአውሬ መያዣያ ወይም ማነቂያ ወጥመድ። 3. አንደኛውን ጫፍ ሳብ ሲያደርጉት እንደሚጠብቅ ወይም አንቆ እንደሚይዝ ሆኖ የታሰረ ወይም የተቋጠረ ገመድ።

**ተሸመቀቀ** ግ ተሰበሰበ፥ ተሸበሸበ፥ ተጨማደደ።

**ተሸማቀቀ** ግ አፈረ፥ ደነገጠ፥ ፈራ። *በጥገኝነት ስለሚኖር ሁሌ እንደተሸማቀቀ ነው።*

**አሸማቀቀ** ግ አስፈራ፥ አስደነገጠ፥ አስጨነቀ።

**ሸመቃ "ሸመቀ"** ስር ተመ.

**ሸመተ** ግ 1. ገዛ፥ ገበየ (ብዙውን ጊዜ እህልን)። 2. (ዘይ.) ያዘ፥ አተረፈ። *ጥንቃቄ ባለማድረጉ በሽታ ሸመተ።*

**ሸመታ** ስ ግዥ (ብዙውን ጊዜ የወር አስቤዛ)።

**ሸማች** ስ እህልን ለንግድ ሳይሆን ለምግብነት የሚገዛ በላተኛ።

**ሸመተረ** ግ ሸነቆጠ፥ ገረፈ።

**ሸመታ "ሸመተ"** ስር ተመ.

**ሸመነ** ግ ሸማ ሰራ።

**ሸማኔ** ስ እንደኩታ፥ የአገር ልብስ፥ ጃኖ የመሳሰሉትን የሚሰራ ጥበበኛ።

**[የ]ሸማኔ መወርወሪያ የሚያህል** (የን.አነ.) በጣም አጭር የሆነ (ሰው)።

**[የ] ሸማኔ እቃ** ስ የሸመና ስራ የሚከናወንባቸው እንደ መን፥ መወርወሪያ የመሳሰሉት።

**የሸማኔ ዘንግ** ስ ሸማኔ የሚሰራውን ሸማ የሚለካበትና የተወሰነ መጠን ያለው የርዝመት መለኪያ።

**የሸማኔ ጉድጓድ** ስ ሸማኔ እግሩን አስገብቶ የሚሰራበት እመሬት ውስጥ ያለ ጉድጓድ።

***ሸመደመደ**

**ሸመድማዳ (ሽምድምድ)** ቅ ውልክፍክፍ፥ ጥምልምል፥ ልፍስፍስ፥ ለዋሳ።

**ሽምድምድ አለ** ግ ተሸመደመደ።

**ተሸመደመደ** ግ 1.ተልፈሰፈሰ፥ተጥመለመለ። 2. አቅም፥ ጥንካሬ አጣ (መንግስት፥ ኢኮኖሚ፥..)።

**አሸመደመደ** ግ 1. አጥመለመለ፥ አልፈሰፈሰ። 2. አቅም፥ ጥንካሬ አሳጣ፤ አዳከመ (መንግስትን፥ ኢኮኖሚን፥...)።

**ሸመደደ** ግ 1. ጨልጦ ጠጣ። 2. ቃል በቃል አጠና፥ በቃሉ ያዘ።

**ሽምዳጅ** ቅ ሁሉንም ቃል በቃል የሚያጠናና በቃሉ የሚይዝ።

**ሸመድማዳ "*ሸመደመደ"** ስር ተመ.

**ሸመገለ** ግ 1. አረጀ፥ በእድሜ ገፋ። 2. አስታረቀ፥ ገላገለ፥ አስማማ።

**ሽምጋይ** ስ አስታራቂ፥ አስማሚ።

**ሽማግሌ** ስ 1.በእድሜ የገፉ አዛውንት። 2. አስታራቂ፥ ገላጋይ።

**ሽማግሌ ተላከበት** የሚማልድ አስታራቂ፥ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ወደ እርሱ ሄደ ወይም ተላከ።

**ሽምግልና** ስ 1. እርጅና። 2. የማስታረቅ፥ የማስማማት፥ የማማለድ ተግባር።

**ሸመጠረ** ግ ኮመጠጠ።

**ሽምጣራ** ቅ ኮምጣጣ።

**ሸመጠጠ**[1] ግ 1. ዠመገገ፥ መዠረገ፥ ለቀመ(ፍሬን፥ እሸትን)። 2. ዥው አድርጎ ጠጣ፥ ጨለጠ። 3. በፍጥነት ሮጠ፥ ጋለበ። 4.(ዘይ.) ዋሸ፥ አበለ። 5. ገረፈ፥ ቆነደደ። 6. ወደ ሂላ አስተኛ (እንስሳ ጆሮውን)።

**ሽምጥ** ስ ፈጣን የፈረስ ግልቢያ።

**ሸመጠጠ**[2] ግ ተርታውን በተተከሉ ቋሚ የአጥር እንጨቶች ላይ እንደ አጋም፥ ክትክታ፥ ቀጨሞ ያሉ ጨፈቃዎችን እያወሳሰበ ወይም እያጠላለፈ አጠረ።

**ሽምጥ** ቅ በጨፈቃ ተጠላልፎ ወይም ተወሳስቦ የታጠረ (አጥር)።

**ሸሚዝ** ስ ቀለልና ሳሳ ካለ የጨርቅ አይነት የሚሰራና እጀ ሙሉ ወይም ጉርድ ወይም ኮሌታ ያለው ወይም የሌለው፥ አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች ከካኒተራ በላይ ከኮት ስር የሚለብሱት የልብስ አይነት።

**ሸማ** ስ እንደኩታ፥ ነጠላ፥ ጃኖ፥ ጋቢ ያለ ከድርና ከማግ የሚሰራ ልብስ።

**ሸማሜ** ስ ራስ ትልቅ ስንዴ።

**ሸማቂ "ሸመቀ"** ስር ተመ.


**ሸማች "ሸመተ"** ስር ተመ.

**ሸማኔ "ሸመነ"** ስር ተመ.

**ሸማዳ** ቅ ወልጋዳ፥ ወሸማዳ።

**ሽምቀቆ "ሸመቀቀ"** ስር ተመ.

**ሽምቃቃ** ዝ.ከ.
**ሽምበቆ** "ሸንበቆ" ን ተመ.
**ሽምዳጅ** "ሸመደደ" ስር ተመ.
**ሽምጋይ** "ሸመገለ" ስር ተመ.
**ሽምጣራ** "ሸመጠረ" ስር ተመ.
***ሸሞነሞነ**
**ሽሙንሙን** ቅ በአኳኋኑ ኩንስንስ፥ በአለባበሱ መጊያጊያጥ የሚያበዛ::
**ሽሙንሙን አለ** ግ ተሸሞነሞነ::
**ተሸሞነሞነ** ግ ተሽፋፈነ፥ ተከናነበ፤ ተኩነሰነሰ፥ አጌጠ፥ ተቆነጃጀ::
**አሸሞነሞነ** ግ አኩነሰነሰ፥ አስጌጠ፥ አሳመረ፥ አቆነጀ፥ አስዋበ::
***ሸሞጠጠ**
**ሽሙጥ** ስ የሽርደዳ፥ የአሽሙር፥ የአግቦ ንግግር::
**ሽሙጥጫ** ዝ.ከ.
**አሽሟጠጠ** ግ ሸረደደ፥ አንጓጠጠ፤ አሽሙር፥ አግቦ ተናገረ::
**አሽሟጣጭ** ቅ ሽርዳጅ::
**ሸረሞጠ** ግ አመነዘረ፥ ሴሰነ::
**ሽርሙጣ** ስ (ስድብ) 1. አመንዝራ:: 2. ሴተኛ አዳሪ:: 3.(ዘይ.) በባህርዩ አንዴ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ከሌላው የሚሆንና ነገር የሚያወላስብ ወረተኛ::
**ሽርሙጥና** ስ 1. አመንዝራነት:: 2.ሴተኛ አዳሪነት:: 3. (ዘይ.) በአንድ አቋም አለመርጋት፥ ከሁሉም ጋር አለሁ ማለት:: *የፖለቲካ ሽርሙጥና::*
**ተሸራሞጠ** ግ 1. ሸረሞጠ፤ የብልግና ንግግር ተናገረ:: 2. (ዘይ.) ጠባዩ መጥፎና ተለዋዋጭ ሆነ::
***ሸረረ**
**ሽረር አለ** ግ 1. ፈቀቅ፥ ዘወር አለ:: 2. (በሽታ) ተወት አደረገ፥ ፋታ ሰጠ:: 3. ተንሻሎ ሄደ:: 4.ሿ ብሎ ወረደ፥ ፈሰሰ(ቀጭን ተቅማጥ)::
**ሽረር አደረገ** ግ እንደ ውሃ ያለ ተቅማጥ ተቀመጠ::
**ተንሻረረ** ግ ፈጥኖ አለፈ፥ ተንሻለለ፥ ተወረወረ፥ ሽር ብሎ ሄደ::
**አንሻረረ** ግ ወረወረ፥ አንሻለለ::
**ሸረሪት** ስ ትናንሽ ከሆኑና 8 እግር ካላቸው ፍጥረታት አንዱ የሆነችና በምግብነት የሚያገለግሏትን ነፍሳት ለማጥመጃ ድር የመሰለ ነገር የምታደራ ነፍሳት::



ሸረሪት

**የሸረሪት ድር** ስ ሸረሪት የምታደራው ድር::
**ሸረሸረ** ግ በረበረ፥ ሰረሰረ፥ ፈለፈለ::
**ሽረሸር** ስ ፈረፈር፥ ፈፋ፥ ጉድባ፥ የተሸረሸረ ቦታ::
**ተሸረሸረ** ግ ተበረበረ፥ ተሰረሰረ፥ ቀስ በቀስ ተበላ፥ ተናደ::
***ሸረሸረ**
**ሽርሽር** ስ ለመዝናናት፥ ለመደሰት የሚደረግ ጉዞ::
**ተሸራሸረ** ግ 1. የተበላ ምግብ በቀላሉ በጨጓራ ተፈጨ:: 2. ተሽጋሸጎ ተቀመጠ::
**ተንሸረሸረ** ግ ሰገረ፥ ፈጥኖ ተራመደ (በቅሉ)::
**ተንሸራሸረ** ግ ተዘዋወረ፥ ተናፈሰ፥ ለመዝናናት ወዲያና ወዲህ ሄደ::
**አንሸረሸረ** ግ አሰገረ (በቅሉን)::
**አንሸራሸረ** ግ 1. ለማዝናናት፥ ለማስደሰት፥ ወደ መንገድ ይዞ ሄደ፤ አናፈሰ፥ ነፋስ እንዲቀበል አደረገ:: 2. የተበላ ምግብ በቀላሉ በጨጓራ እንዲፈጭ አደረገ (መጠጥ):: 3. አሸጋሸገ::
**ሽረሽር** "ሸረሸረ" ስር ተመ.
**ሸረቆጠ** ግ ቀለጠፍ፥ ሽንቀጥ አለ፥ ተሰበሰበ (በአለባበስ፥ በአካሄድ፥ በአቀማመጥ)::
**ሽርቋጣ (ሽርቁጥ)** ቅ ሽንቃጣ::
**ሸረበ** ግ 1. ሶስት ወይም አራት የሚሆኑ ገመዶችን፥ ክሮችን፥... በአንድነት ደበለ፥ እየደረበ ገመደ:: 2. ሹርባ ሰራ፥ ጎነጎነ፥ አሸመ:: 3. (ዘይ.) ነገርን፥ ሴራን አውጠነጠነ፥ ዶለተ::
**ሹሩባ (ሹርባ)** ስ የራስ ፀጉር ጉንጉን:: (ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)
**ሹሩባ ሰሪ** ስ የሴት ፀጉር የምትጎነጉን ወይም የምትቆነድድ ሴት::
**ሹርቤ ብርሌ** ስ አንገቱ ቀጭንና ረዥም የሆነ ሽልም ብርሌ(ስእሉን ብርሌ ስር ተመ.)::
**ሽርቦሽ** ስ የተፈተለ ገመድ ወይም ጅራፍ::
***ሸረተተ**

**ሸርተቴ(ሸተቴ)** ስ 1. ቁልቁለት ወይም ተዳፋት ከሆነ ቦታ ላይ ሆነው ወደታች እየተንሸራተቱ የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ:: 2. የተቅማጥ በሽታ::

**ሸርታታ** ቅ (ዘይ.) ወላዋይ፥ በቃሉ የማይረጋ::

**ተንሸራተተ** ግ 1. ወደታች እየተንፏቀቀ ወረደ፥ ተንሻተተ:: 2. (ዘይ.) ወላወለ፥ ከዳ፥ በቃሉ ሳይረጋ ቀረ::

**አንሸራተተ** ግ አዳለጠ፥ አዳጠ፥ አንሻተተ::

**አንሸራታች** ቅ የሚያንሸራትት፥ የሚያዳልጥ (ቦታ)::

**ሸረኛ** "**ሸር**" ስር ተመ.

***ሸረከ**

**ሸሪክ(ሸርካ፥ ሸርክ)** ስ 1. በጋራ ወይም በአንድነት የሚሰራ ወይም የሚነግድ:: 2. ወዳጅ፥ ባልንጀራ፥ ጓደኛ::

**ሸርክና** ስ 1. የህብረት ስራ ወይም ንግድ:: 2. ወዳጅነት፥ ጓደኝነት::

**ተሻረከ** ግ ተባበረ፥ ተወዳጀ፥ ጓደኛ ሆነ፥ ተስማማ::

**አሻረከ** ግ አብሮት እንዲሰራ ወይም እንዲነግድ ተስማማ::

***ሸረከረከ**

**ሸረክራካ (ሸርክርክ)** ቅ ወላዋይ::

**ተሸረከረከ** ግ ተፍረከረከ፥ ወላወለ::

**ሸረከተ** ግ 1. ቀደደ፥ ተረተረ፥ ዘረከተ:: 2. ሳያደቅ ፈጨ፥ ገረደፈ፥ ከካ:: 3. (በጦር፥ በጩቤ) ወጋ፥ ዘነጠለ::

**ሸርካታ** ቅ (ዘይ.) ውሸታም::

**ሸርክት** ስ 1. ያልደቀቀ፥ ያልላመ (ዱቄት) :: 2. (ዘይ.) ውሸታም::

**ተሸረከተ** ግ 1. ተቀደደ፥ ተተረተረ:: 2. ሳይደቅ ተፈጨ፥ ተገረደፈ፥ ግርድፍ ሆነ:: 3. (ዘይ.) ዋሽቶ ተናገረ፥ ዘባረቀ::

**ሸረክራካ** "***ሸረከረከ**" ስር ተመ.

**ሸረደደ** ግ 1. አሽሟጠጠ፥ አሾፈ፥ አላገጠ፥ ፎተተ:: 2. ያልሆነውን ነገር እንዲህ ነው እያለና በውሸት እያጋነነ ተናገረ::

**ሸርዳጅ** ቅ አሽሟጣጭ፥ ፎታች::

**ሸርደዳ** ስ የአሽሙር፥ የሽሙጥ ንግግር::

***ሸረጠ**

**ሸርጥ** ስ 1. ከወገብ በታች የሚውል ግልድም:: 2. ቆሻሻን ለመከላከል በልብስ ላይ የሚለበስ የስራ ልብስ:: 3. ለሃዘን ተብሎ ተዘቅዝቆየተለበሰ ነጠላ::

**ተሸረጠ** ግ (ከፋ፥ መጥፎ መንፈስ፥...) ለቀቅ አደረገ፥ ገለል አለ፥ ተወ::

**ተሸረጠለት** (ዛር፥ ቁጣ) ተወገደለት፥ ጠፋለት፥ ወደ ቀድሞው ጤናማ ሁኔታ ተመለሰ::

**አሸረጠ** ግ አገለደመ፥ አደገደገ::

**አሸረጠች** በሃዘን ጊዜ ነጠላዋን ዘቅዝቃ ለበሰች::

**ሸረፈ** ግ 1. በትንሹ ቆረሰ፥ ሰበረ:: 2.(ከብት) ጥርሱን ነቀለ:: 3. መነዘረ፥ ዘረዘረ፥ ወደ ቅንስናሽ ገንዘብ ለወጠ:: 4. ቀነሰ፥ ቆነጠረ::

**ሸራፋ** ቅ 1. የተሰበረ (እቃ፥ ጥርስ፥...):: 2. (ስድብ) ጥርሱ የተሸረፈ:: 3. በጣም አጭርና ኮሳሳ የሆነ (ሰው)::

**ሸርፍ** ስ ምንዛሪ::

**ሸራፊ** ቅ ተሰብሮ፥ ተቆርሶ የወጣ ነገር፥ ስባሪ::

**ሸርፍራፊ** ቅ 1. ስብርባሪ:: 2. ምንዛሪ፥ ቅንስናሽ ገንዘብ::

**ተሸረፈ** ግ ከላዩ ላይ ትንሽ ተቆረሰ ወይም ተሰበረ::

**ተሸራረፈ** ግ 1. ጫፍ ጫፉ ብዙ ቦታ ላይ ተሰበረ:: 2. ከላዩ ላይ ተቀነሰለት::

**አሸረፈ** ግ (ገንዘብን) ዘረዘረ፥ መነዘረ::

**ሸሪራ**[1] ስ 1. ኮርኒስ ላይ የሚመታ ቀጭን እንደ ማስመሪያ ያለ እንጨት:: 2. ከመጋረጃ ጨርቅ ጋር ተያይዘው ወደ ግራና ቀኝ እየተንሸራተቱ መጋረጃውን መክፈትና መዝጋት የሚያስችሉት ባለ ሃዲድ ትናንሽ ቀለበቶች የሚንሸራተቱበት ጠፍጣፋ ባለሃዲድ ዘንግ ወይም ብረት::

**ሸሪክ** "***ሸረከ**" ስር ተመ.

**ሸራ** ስ ድንኳን፥ ቦርሳ፥ ሻንጣ፥...ለመስራት ወይም በላዩ ላይ ስእልን ለመስራት የሚያገለግል ጠንካራና ሻካራ የሆነ ጨርቅ::

**ሹራ [ጫማ]** ስ ከሸራ የሚዘጋጅ ጫማ::

**ሸራፋ** "**ሸረፈ**" ስር ተመ.

**ሸር** ስ ተንኮል፥ ክፋት፥ ደባ::

**ሸር ሰራ** ተንኮል፥ መጥፎ ድርጊት ፈፀመ::

**ሸረኛ** ቅ ተንኮለኛ፥ ክፉ፥ መሰሪ፥ ሴረኛ::

**ሸርሙጣ** "**ሸረሞጠ**" ስር ተመ.

**ሸርተቴ** "***ሸረተተ**" ስር ተመ.

**ሸርታታ** ዝ.ክ.

**ሸርካታ** "**ሸረከተ**" ስር ተመ.

**ሸርዳጅ** "**ሸረደደ**" ስር ተመ.

**ሸርጣን** ስ ብዙ እግር ያለው የባህር ነፍሳት፥ ጎርምጥ::



ሸርጣን

**ሽርጣን [ውሃ]** ስ በሰኔ ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪም **"ኮከብ ቆጠራ"**ን ተመ.

**ሸሸ** ግ 1. ከፍርሃት የተነሳ ወደ ሃላ ተመልሶ ሮጠ፥ ፈረጠጠ። 2. ራቀ፥ ተለየ። *በገዛ ጥፋቱ ከጓደኞቹ ሸሸ*፡ 3. መገኘቱ ቀረ፥ ጠፋ። *ሃብት ሸሸው*። 4. (በሽታ፥ ነገር፥...) እንዳያጋጥመው፥ እንዳያገኘው ተጠነቀቀ። 5. ቦታውን ለቀቀ፥ ዘመመ፥...።

**ሽሽት** ስ ከአደጋ ወይም ከሌላ ነገር ለማምለጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ፥ ስደት፥ ፍርጠጣ።

**መሸሻ** ስ መጠጊያ፥ መከለያ፥ መደበቂያ።

**አሸሸ** ግ 1. አገለለ፥ ሰወረ፥ ሸሸገ፥ ደበቀ። 2. አራቀ።

**ሸሸገ** ግ (እንዳይታይ፥ እንዳይታወቅ) ደበቀ፥ ሸፈነ፥ ከለለ፥ ጋረደ።

**ሽሽግ** ቅ ድብቅ፥ ስውር።

**ተሸሸገ** ግ ተደበቀ፥ ተሰወረ፥ ተከለለ።

**ሸቀለ** ግ ተሸከመ፥ የጉልበት ስራ ሰራ።

**ሸቃይ** ስ ተሸካሚ፥ ኩሊ።

**ሽቀላ** ስ የጉልበት ስራ (በአብዛኛው ሸክም)።

**ሸቀሸቀ** ግ 1. ሰቀሰቀ፥ መሳልሶ ወጋ። 2. ጠዘጠዘ፥ አመመ፥ ነዘነዘ (ህመም)።

**አሸቀሸቀ** ግ 1.ተንጠለጠለ፥ አዘበዘበ፥ ሊወድቅ ወይም ሊፈርስ ደረሰ። 2. በህመም ምክንያት ቆዳው ሊገፈፍ ወይም ሊቀረፍ ደረሰ፤ አፈከፈከ።

***ሸቀሸቀ**

**ተንሸቀሸቀ** ግ ፈራ፥ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ።

**አንሸቀሸቀ** ግ አስፈራ፥ አራደ፥ አንቀጠቀጠ።

**ሸቀበ** ግ 1. ('በሽያጭ ላይ) አታለለ፥ አሞኘ። 2. (የአራዳ አነ.) ለከፈ፥ በነገር ነካ።

**ሸቃባ** ቅ (ስድብ) የሚሸቅብ፥ አታላይ፥ ገደቢስ።

**ሸቀን** ስ በሰውነት ላይ የተጋገረ እድፍ።

**ሸቀናም** ቅ (ስድብ) እድፋም፥ ጭቅቅታም፥ ቆሻሻ።

**ሸቀጠ** ግ ሸጠ፥ ለወጠ፥ ቸረቸረ፥ ነገደ።

**ሸቀጥ** ስ ለራስ ፍጆታ ሳይሆን ለትርፍ የሚሸጥና ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም እቃ።

**ሸቀጣሸቀጥ** ስ በአይነት የተለያዩና ብዛት ያላቸው ለሽያጭ የሚቀርቡ እቃዎች።

**ሸቃጭ** ስ ቸርቻሪ ነጋዴ።

**ሸቁራራ(ሸቆረር)** ቅ አይን አፋር።

**ሸቃባ "ሸቀበ"** ስር ተመ.

***ሸቆመቆመ**

**ሽቁምቁም** ቅ.ግድርድር፥ አይን አፋር።

**ተሸቆመቆመ** ግ ተግደረደረ።

**ተሽቆምቋሚ** ቅ ሽቁምቁም።

**አሸቆመቆመ** ግ አግደረደረ።

**ሸቆረር "ሸቁራራ"** ን ተመ.

***ሸቆጠቆጠ**[1]

**ሽቁጥቁጥ (ሽቆጥቋጣ)** ቅ ደግ፥ ትሁት፥ ታዛዥ፥ ለሰው የሚጨነቅ ወይም የሚቸገር፥ ርግብግብ።

**ተሽቆጠቆጠ** ግ 1. አክብሮትን፥ ፍቅርን በማሳየት ታዛዥ ሆነ፤ ደግነትን፥ ትህትናን፥ አሳየ። 2. ተለማመጠ፤ ፈራ፥ ተርበደበደ።

**አሽቆጠቆጠ** ግ አስፈራ፥ አርበደበደ፥ አስጨነቀ።

***ሸቆጠቆጠ**[2]

**ተሸቆጠቆጠ** ግ አጌጠ፥ ተዋበ፥ አማረ። *በወርቅ የተሸቆጠቆጠ ካባ ለብሷል*።

**አሸቆጠቆጠ** ግ አስጌጠ፥ አስዋበ።

**ሸቆጥቋጣ"*ሸቆጠቆጠ[1]"** ስር **"ሽቁጥቁጥ"**ን ተመ.


**ሸበለለ** ግ ጠቀለለ።

**ሽብልል (ሽብል)** ቅ 1. ጥቅልል። ስ 2. ወፈር ተደርጎ የተዘጋጀ የገብስ ሊጥ።

**ተሸበለለ** ግ (ወረቀቱ፥ ብራናው) ተጠቀለለ።

**ሸበለቀ** ግ 1. ጫፉን አሾለ። 2. በጦር፥ በአንካሴ፥ በሽብልቅ ወጋ።

**ሽብልቅ** ስ ውሻል፥ ቅርቃር፥ ሹል እንጨት ወይም ብረት።




***ሸበለበለ**

**ሽብልብል** ቅ ሽፍንፍን፥ ጥቅልል።

**ተሸበለበለ** ግ 1. ተሸፋፈነ፥ ተጠቀለለ። 2. (ዘይ.) አማረ፥ ተሽሞነሞነ።

**አሸበለበለ** ግ 1. ሸፋፈነ፥ ጠቀለለ። 2. (ዘይ.) ሀ•አሳመረ፥ አሽሞነሞነ። ለ•አባበለ፥ አቆላመጠ፥ ተለማመጠ።

**ሸበላ** ስ 1. የእንስት፥ የኮባ፥...ሙሽራ። 2.

አቋቋመ መልክም፥ ውብ፥ መዘዞ።

*ሸበረ

**ሽብር** ስ ረብሻ፥ ሁከት፥ ብጥብጥ።

**ሽብር ፈጣሪ** ቅ 1. ረባሽ፥ አዋኪ፥ ሰላምን አደፍራሽ፥ በጥባጭ። 2. (ድርጅት ወይም የድርጅት አባል) በመሳሪያ ሃይል አላማውን ለማስፈፀም የሚሞክር ሽብርተኛ።

**ሽብርተኛ** ቅ ሽብር ፈጣሪ።

**ተሸበረ** ግ 1. ተረበሸ፥ ታወከ፥ ተበጠበጠ፥ ፀጥታ ደፈረሰ። 2. ፈራ፥ ደነገጠ፥ ባባ፥ ተጨነቀ።

**ተሸባሪ** ቅ በቀላሉ የሚደነግጥ፥ የሚረበሽ።

**አሸበረ** ግ 1. አወከ፥ በጠበጠ፥ ፀጥታ ነሳ። 2. አስፈራ፥ አስጨነቀ።

**አሸባሪ** ቅ በጥባጭ፥ አዋኪ፥ ሰላምን አደፍራሽ።

*ሸበረቀ

**ሽብርቅ አለ** ግ 1. አማረ፥ ተዋበ። 2. አንፀባረቀ።

**አሸበረቀ** ግ አማረ፥ ተዋበ፥ አጌጠ።

**አሸብራቂ** ቅ ያማረ፥ የተዋበ፥ የሚያንፀባርቅ።

*ሸበረከ

**ሽብራካ** ቅ ወልጋዳ፥ አሻዳ።

**ሽብረክ አለ** ግ 1. በርከክ አለ። 2. (ዘይ.) እሺ አለ፥ ከቁጣው በረደ፥ ለስለስ አለ።

**አሸበረከ** ግ በርከክ አለ።

**ሸበሸበ** ግ 1. አጨማደደ፥ አኮማተረ። 2. (ቀሚስን) ሸነሸነ።

**ሽብሽባት** ስ የቀሚስ ወገብጌ ወይም የእጅጌ ሽንሽን።

**ሽብሽቦ** ስ ሽንሽን ቀሚስ።

**ተሸበሸበ** ግ ተጨማደደ፥ ተኮማተረ።

*ሸበሸበ

**ሽብሽባ** ስ 1. በመንፈሳዊ ዜማ የታጀበ ውዝዋዜ። 2. ዘፈንን ለማድመቅ የሚደረግ ጭብጨባ፥ ጭፈራ፥ ውዝዋዜ።

**አሸበሸበ** ግ 1. በመንፈሳዊ ዜማ እየታጀበ አረገደ፥ ተወዛወዘ። 2. በዘፈን እየታጀበ ጨፈረ፥ ተወዛወዘ፥ አጨበጨበ።

**አሸብሻቢ** ቅ በመንፈሳዊ ዜማ እየታጀበ የሚያረግድ፤ አስረጋጭ (ካህን)፥...። 2. እያጨበጨበ፥ እየተወዛወዘ ዘፈንን የሚያዳምቅ። 3. (ዘይ.) አጨብጫቢ፥ አሸቃባጭ።

**ሸበበ** ግ (በገመድ፥ በጠፍር) የበሬን፥ የበቅሎን አፍ አሰረ፥ ለጎመ።

**መሸበቢያ** ስ የበሬን፥ የበቅሎን አፍ ማሰሪያ፥ መለጎሚያ።

**ሽብ አደረገ** ግ ሳይጠብቅ ላላ አድርጎ አሰረ።

**ተሸበበ** ግ 1. ዝናብ፥ ብርድ እንዳይገባ የቤቱ ዙሪያ ተጋረደ።2. (አፉ) ተለጎመ፥ ታሰረ።

**ሸበተ** ግ 1. (አብዛኛውን ጊዜ ከእርጅና የተነሳ) ነጭ ፀጉር አወጣ። 2. (ለእንጀራ፥ ለጠላ፥...) ሻገተ።

**ሸበቶ** ቅ 1. ነጭ ፀጉር ያወጣ። 2. በእድሜ የገፋና ሽበት ያወጣ።

**ሽበት** ስ አብዛኛውን ጊዜ ከእድሜ መግፋት የተነሳ የሚወጣ ነጭ ፀጉር።

**ሽበታም** ቅ (ሰው) ሽበት ያወጣ።

**ሸበድ** ስ ከበገርድ ግራና ቀኝ ያለ የጭንና የሆድ መጋጠሚያ ቦታ።

**ሸበጥ** ስ ነጠላ ጫማ።

**ሽብራካ "*ሸበረከ"** ስር ተመ.

**ሸተ** ግ 1. ጎመራ፥ ደረሰ፥ በሰለ። 2.(ዘይ.) አማረ፥ ተዋበ።

**እሸት** ስ ለመበላት የደረሰ ለጋ የእህል ዛላ፥ ዘለላ፥ እንቡጥ ፍሬ።

**አሸተ** ግ ጎመራ፥ ደረሰ፥ በሰለ፥ ፍሬ ያዘ።

**ሸተተ** ግ 1. ጠረኑ ወይም ሽታው ለአፍንጫ ተሰማ፥ አወደ። 2. ገማ፥ ከረፋ፥ ቆነሰ።

**ሽታ** ስ 1. የአንድ ነገር ጠረን፥ መአዛ (ለአፍንጫ የሚሰማ)። 2. በተፈጥሮ ገላ ላይ የሚወጣ ጥቁር ምልክት።

**ለሽታ ያህል** በትንሹ ወይም በመጠኑ ለአመል ያህል።

**ሽቶ (ሽቱ)** ስ መልካም መአዛ ካላቸው እፅዋትና ዝባድ የተሰራ ጥሩ ሽታ ያለው ፈሳሽ።

**ተሻተተ** ግ ትንሽ ትንሽ ተዳረሰ (ምግብ፥ መጠጥ)።

**አሸተተ** ግ 1.የአንድን ነገር መአዛ ወይም ጠረን በአፍንጫ ማገ፥ ሳበ። 2.እንዲገማ፥ እንዲከረፋ አደረገ። *ስጋውን አሸተተከው።*

**አሻተተ** ግ ትንሽ ትንሽ አዳረሰ (ምግብ፥ መጠጥ)።

**ሸተቴ "*ሸረተተ"** ስር **"ሸርተቴ"** ን ተመ.

**ሸነሸነ** ግ 1. ሸበሸበ፥ ሽንሽን እንዲሆን አደረገ። 2. ከፋፈለ፥ቆራረሰ። 3. (እንጨትን) በቀጭኑ ሸነታተረ፥ ሰነጣጠቀ፥ ፈለጠ።

**ሽንሽን** ስ የተሸበሸበ ቀሚስ።

**ተሸነሸነ** ግ 1. ተሸበሸበ። 2. ተከፋፈለ፥ በትንሽ በትንሹ ተዳረሰ።

**ሸነቀረ** ግ 1. ቀረቀረ፥ ሸጎጠ። 2. (የሱሪን፥ የቀሚስን ጫፍ ውሃ ወይም ጭቃ እንዳይነካው)

ሰበሰበ፥ ቀነፈ፥ ከፍ አድርጎ ሻጠ::

**ሽንቅር** ቅ የተወተፈ፥ የተቀረቀረ::

**ተሽነቀረ** ግ ተቀረቀረ፥ ተሸጎጠ፥ ተወተፈ::

**ሽነቀጠ** ግ ቀልባጫ፥ ቀልጣፋ ሆኖ አማረ፥ ተዋበ::

**ሽንቃጣ(ሽንቅጥ)** ቅ ከወገቡ ቀጠን ያለ፥ ሸበላ::

**ሽነቆረ** ግ ቀደደ፥ ነደለ፥ በሳ::

**ሽንቁር(ሽንቋራ)** ቅ ብስ፥ ቀዳዳ::

**ተሽነቆረ** ግ ተቀደደ፥ ተነደለ፥ ተበሳ::

**ሽነቆጠ** ግ 1.በአርጩሜ፥ በአለንጋ፥... መታ፥ ሾጥ አደረገ፤ ገረፈ:: 2. (ዘይ.) አሰቃየ፥ ጎዳ (ብርድ፥ ችግር...)::

**አሽንቋጠ** ስ መግረፊያ፥ አርጩሜ፥ አለንጋ::

**ሽነተረ** ግ በጣ፥ ቀደደ፥ ሰነበጠ::

**ሽንትር** ቅ 1. የተሰነበጠ፥ ብጥ:: 2. እንደሰንበር ወይም እንደንቅሳት ያለ መስመር፥ ጌጥ፥ ሽልማት::

**ሽንትራት** ስ እንደሰንበር ወይም ንቅሳት ያለ መስመር ወይም ጌጥ::

**ተሽነተረ** ግ 1. ተበጣ፥ ተቀደደ:: 2. ሰንበር ወይም መስመር አወጣ::

**ሽነተፈ** ግ በጣ፥ ቆረጠ::

**ሽነከፈ** ግ 1. የአህያን፥ የበግን፥...አንዱን የፊት እግር አጥፎ ወይም ኮርትሞ አሰረ፥ ሰነከለ፥ ቀየደ:: 2. በጣም ሳያጠብቅ ላላ አድርጎ አሰረ::

**ሽንካፋ(ሽንክፍ)** ቅ (ስድብ) እግሩ ወይም እጁ ስንኩል የሆነ::

**ሽነገለ** ግ 1. ደለለ፥ አሞኘ፥ አታለለ:: 2. አባበለ፥ ተለማመጠ፥ ለመነ:: 3. አለከፈ፥ በመጠኑ አበላ::

**መሽንገያ** ስ ማባበያ፥ መደለያ፥ ማ ታ ለ ያ የሚሆን አነስተኛ ስጦታ::

**ሽንጋይ** ቅ አታላይ፥ ሰውን የሚያሞኝ::

**ሽንገላ** ስ ድለላ፥ ለማባበል ሲባል የሚነገር ወይም የሚደረግ ነገር::

**ተሽነገለ** ግ በትንሽ ነገር ተደለለ፤ እሺ አለ፥ መሽንገያ ተቀበለ::

***ሽነገረ**

**ሽንጋራ** ቅ (ስድብ) ሸውራራ::

**ውሽንግር** ዝ.ከ.

**ተሸናገረ** ግ 1. ተንሸዋረረ፥ ተጠናገረ:: 2.ተወላገደ፥ ተጣመመ::

**አሸናገረ (አወሸናገረ)** ግ 1. አይንን አንሸዋረረ:: 2. አወላገደ፥ አጣመመ::

**ሽነጎ** ግ በጉባኤ ፥ በስብሰባ መከረ ወይም ዶለተ::

**ሽንጎ** ስ 1. ህዝብ የሚሰበሰብበት ወይም ዳኛ የሚያስችልበት ቦታ፥ አደባባይ:: 2. ጉባኤ፥ ስብሰባ:: 3. በሽንጎ ላይ የተሰበሰበ ህዝብ:: 4. የሽንጎው ሰብሳቢ የሆኑት ሽማግሌዎች ወይም የጉባኤው የበላይ አካላት::

**ሽንጎኛ** ስ በሽንጎ ላይ እየተገኘ የሚከራከር፥ የሽንጎ ሰው::

**ሽነጠ** ግ የጀግንነትን ስሜት ወይም ወኔን ቀሰቀሰ (ቀረርቶው)::

***ሽነፈ**

**ሽንፈት** ስ መረታት፥ ድል መሆን::

**ተሽነፈ** ግ 1. ድል ሆነ፥ ተረታ:: 2. አቃተው፥ ደከመው:: 3. (ዘይ.) እንቢታውን ተወ፥ እሺ አለ፥ ተቀበለ::

**ተሸናፊ** ቅ በውድድር ወይም በጦርነት የተረታ::

**አሸነፈ** ግ 1. ድል መታ፥ ረታ:: 2. አቃተ፥ አልቻል አለ:: 3. እሺ አሰኘ፥ የተባለውን እንዲቀበል አደረገ::

**አሸናፊ** ቅ (በውድድር፥ በግጥሚያ፥...) ድል አድራጊ::

**ሸና** ግ 1. ሽንቱን ለቀቀ ወይም አፈሰሰ:: 2. (ለምሳሌ ባትሪ ድንጋይ) ፈሳሽ ነገርን ከአካሉ ውስጥ አመነጨ፥ አወጣ፥ ርጥበት አሳየ::3. (ዘይ.) ፈራ::

**ሽንት** ስ ከሰውነት ውስጥ በብልት በኩል የሚወጣ ቆሻሻ ፈሳሽ::

**ሽንትህን ይባርከው** ዘርህን ይባርከው::

**ሽንተ መልካም** ጥሩ ዘር ያፈራ፥ ጥሩ ልጆች ያሉት::

**ሽንት ማጥ** ስ ሽንትን በቀላሉ ለመሽናት የሚከለክልና የሚያስምጥ ህመም::

**ሽንት ቤት** ስ መፀዳጃ ቤት::

**የሽንት ቤት ወረቀት** ስ ሽንት ቤት የሚሄድ ሰው በመፀዳጃ ጊዜ የሚገለገልበት ስስና ለስላሳ ወረቀት::

**የሽንት ጨርቅ** ስ ለህፃናት ሽንትና አይነ ምድር መቀበያ እንዲሆን ከወገብ በታች የሚጠቀለሉበትና በትንንሹ ተቆራርጦ የተዘጋጀ ጨርቅ::

**ሽንታም** ቅ 1. ሽንቱን በላዩ ላይ የሚለቅ:: 2. (ዘይ.+ ስድብ) ፈሪ፥ ቦቅቧቃ::

**ሽንቋራ** "ሽነቆረ" ስር "ሽንቁር" ን ተመ.

**ሽንበቆ(ሽምበቆ)** ስ መቃ::

**የሽምበቆ ምርኩዝ** የማያዋጣ፥ አምኖ የተጠጋውን ሊረዳ ወይም ሊደግፍ የማይችል::

**ሽንተረር** ስ ግራና ቀኙ ገደል ወይም ተዳፋት፥

የሆነና መካከሉ ከላይ እስከታች እንደሰንበር ሆኖ የሚወርድ የመሬት ቅርፅ።

**ሸንከኛ** "ሸንከ" ስር ተመ.

**ሸንካፋ** "ሸነከፈ" ስር ተመ.

**ሸንኬሎ** "ሰንኬሎ" ን ተመ.

**ሸንከ** ስ ተንኮል።

**ሸንከኛ** ቅ ተንኮለኛ።

**ሸንኮራ [አገዳ]** ስ ሲጨመቅ ለስኳር መስሪያ የሚያገለግል ጣፋጭ ፈሳሽ የሚሰጥና በቆላማ አካባቢ የሚበቅል የአገዳ ተክል።

**ሸንኮሬ** ስ ሴቶች የሚጠሩበት የተዛምዶ ወይም የአክብሮት ስም።

**ሸንኮር** ስ በሸንኮራ አገዳ አምሳያ የተቀረፀ ወይም የታነፀ የአልጋ እግር።

**ሸንኮፍ** "ሰንኮፍ" ን ተመ.

**ሸንዳራ** ቅ (ስድብ) አይነ ሸውራራ፥ ጠንጋራ።

**ሸንጋራ** "*ሸነገረ" ስር ተመ.

**ሸንጋይ** "ሸነገለ" ስር ተመ.

**ሸንጎ** "ሸነኀ" ስር ተመ.

**ሸንጎበት** ስ የአገጭ ላይ ጢም።

**ሸንጎበታም** ቅ ጢማም።

**ሸንጎኛ** "ሸነኀ" ስር ተመ.

**ሸንጥሮ** ስ ሸለቆ።

**ሸኘ** ግ 1. አሰናበተ። 2. መንገደኛን በማጀብ ጥቂት መንገድ ወይም የተወሰነ ርቀት አብሮ ሄደ። 3. (ባለጉዳይን) አስተናግዶ ጉዳዩን ፈፅሞ እንዲሄድ አደረገ።

**መሸኛ** ስ 1. ዘመድ፥ ወዳጅ፥...ለመሸኘት የሚደረግ ግብዣ። 2. ሸኚ ደብዳቤ።

**ሸኚ** ቅ አጃቢ።

**ሸኚ ደብዳቤ (መሸኛ ደብዳቤ)** ስ አንድ ሰው፥ እቃ፥ ጉዳይ፥...ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ በሚላክበት ጊዜ ስለሁኔታው እንዲገልፅ በአጭሩ ተዘጋጅቶ ከተላኪው ጋር አብሮ የሚሄድ ደብዳቤ ወይም ፅሁፍ።

**ተሸኘ** ግ 1. ተሰናበተ፥ ሄደ። 2. መሸኛ ተደረገለት።

***ሸከመ**

**ሸክም** ስ 1. በሰው ጀርባ፥ ትከሻ፥ ራስ፥... ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የሚጓጓዝ እቃ ወይም ጭነት።2.ክብደት፥ ጫና፥...ያለውና የሚያስቸግር ወይም የሚያስጨንቅ ማንኛውም ጉዳይ። 3. (ዘይ.) ራሱን ያልቻለ፥ የሌላ ሰው ጥገኛ ሆኖ የሚኖር (ሰው)።

**ሸክም ነው** ብዙ ነው። *በሃያ አምስት ሳንቲም የገዛችው ሸንኩርት ሸክም ነው።*

**ተሸከመ** ግ 1.ክብደት ያለውን ነገር በራሱ፥ በትከሻው፥ በጀርባው፥ ያዘ። 2. (ዘይ.) ተቀበለ፥ ቻለ፥ ታገሰ። *ይህን ሁሉ ችግር ተሸክሞ ኖሯል።*

**ተሸካሚ** ስ እቃ በጫንቃው ይዞ የሚያጓጉዝ፤ ኩሊ።

**አሸከመ** ግ 1. እቃን በተሸካሚው ትከሻ ወይም ራስ፥... ላይ አደረገ። 2. በብዛት ሰጠ።

***ሸከረከረ**

**ሽክርክር** ስ ተሽከርካሪ ነገር።

**ሽክርክሪት** ስ 1. ከገል፥ ከቅል፥ ከቀንድ ወይም ከእንጨት ክብ ሆኖ የሚሰራ የእንዝርት ራስ። 2. በሞተር ወይም በነፋስ ሃይል የሚሽከረከር ውልብልቢት ወይም ክብ ሆኖ የተሰራና እንደ ጎማ የሚሽከረከር ነገር።

**ተሽከረከረ** ግ 1. ዞረ፥ ሾረ። 2.(ዘይ.) ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዘዋወረ፥ ሄደ። *አርፈህ ተቀመጥ አትሽከርክርብኝ።*

**ተሽከርካሪ** ስ መኪና ወይም እንደ መኪና በጎማ አማካይነት የሚንቀሳቀስ መጓጓዣ።

**አሽከረከረ** ግ 1. አሾረ፥ አዞረ። 2. (መኪናን፥ ብስክሌትን፥...) ነዳ። 3. (ዘይ.) በሚፈልገው አቅጣጫ አስኬደ።

**አሽከርካሪ** ስ መኪና ነጂ፤ ሹፌር።

**ሸከሸከ** ግ 1. ገለባን፥ ቂንድን ወይም አሰርን ከፍሬው ለመለየት እህልን በሙቀጫ ላላ አድርጎ ወቀጠ። 2. (ማግን፥ ሹራብን፥...) ጥብቀት እንዳይኖረው ዘርዛራ አድርጎ ሰራ። 3. በሳሳ፥ ወጋጋ።

**ሽክሻካ** ቅ 1. ዘርዛራ፥ ሳይጠብቅ ተራርቆ የተሰፋ፥ ሰግሳጋ(ልብስ)። 2. (ዘይ.) ወሬኛ፤ ምስጢር የማይቋጥር፤ ቁምነገር የሌለው።

**ሽክሽክ** ቅ 1. ሳይደርቅ የተወቀጠ፥ ገለባውና ቂንዱ የተለየለት (እህል)። 2. ሳይጠብቅ ዘርዛራ ሆኖ የተሰፋ ወይም የተሰራ (ልብስ፥ ዳንቴል፥...)።

**ተሸከሸከ** ግ 1. በሙቀጫ ላላ ተደርጎ ተወቀጠ። 2. ሳይጠብቅ ዘርዛራ ሆኖ ተሰራ ወይም ተሰፋ (ልብስ)።

**አሸከሸከ** ግ ሸከሸከ፤ ላላ አድርጎ ወቀጠ።

**ሸከኛ** "ሽክ[1]" ስር ተመ.

**ሸከከ** ግ ፈራ፥ ተጠራጠረ።

**ሽክ** ስ 1.ፍርሃት፥ ጥርጣሬ።2.ክፋት፥ ተንኮል።

**ሸከፈ** ግ የተበታተነውን ነገር ባንድ ላይ ሰበሰበ።

**ሽክፍ** ቅ 1.የተሰበሰበ።2. ጠንቃቃ።

**ሸካራ** "ሻከረ" ስር "ሻካራ" ን ተመ.

**ሽክ[1]** ስ ክፋት፥ ተንኮል።

**ሸከኛ** ቅ ክፋተኛ፥ ተንኮለኛ።

**ሽክ²** "ሽክክ" ስር ተመ.

***ሽክ**

**ሽክ አደረገ** ግ ቀረጠ፥ ጎመደ (በስለት)።

**ሸክላ** ስ 1. እንደ ጀበና፥ ገበር ምጣድ፥ እንስራ፥...ያለ የቤት ቁሳቁስን ለመስራት የሚያገለግል የተለያዩ የአፈር አይነቶች ውሁድ። 2. ከሸክላ አፈር የሚሰራ እንደ ጀበና፥ ምጣድ ያለ እቃ። 3. ለቤት ህንፃና ለወለል ንጣፍ የሚያገለግል ጡብ። 4. ድምፅ የሚቀረፅበትና የተቀረፀውም ድምፅ በሸክላ ማጫወቻ አማካኝነት ተመልሶ የሚደመጥበት ክብና ዝርግ ነገር። 5. (ዘይ.) በቀላሉ የሚሰበር፥ ጥንካሬ የሌለው።

**ሸክላ ማጫወቻ** ስ በሸክላ ላይ የተቀረፀን ድምፅ ወይም ሙዚቃ ለማዳመጥ የሚያስችል በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ።

**ሸክላ ሰሪ** ስ እንደ ጋን፥ ምጣድ ያሉትን የሚሰራ ሰው።

**ሸክላ ሳህን** ስ ከሸክላ የሚሰራ ዝርግ ወይም ጎድጓዳ ሳህን።

**ሸክላ ስራ** ስ የሸክላ ዕቃዎችን የማምረት፥ ስራ።


**[የ]ሸክላ እቃ** እንደ የቡና ጀበና፥ የእንጀራ ምጣድ ያለ ከሸክላ የሚሰራ እቃ።




1. ጋን
2. እንስራ
3. ማሰሮ
4. ጣባ
5. ጊርጊራ
6. ጀበና
7. ሸክላ ድስት
8. ምጣድ

**ሽክላ በቅሎ** ስ ቀይ በቅሎ::
**ሽክላ ቤት** ስ ግድግዳው በጡብ የተሰራ ቤት::
**ሽክም "*ሽከመ"** ስር ተመ.
**ሽክሻካ "ሽከሸከ"** ስር ተመ.
***ሽከመከመ**
**ሽኩምኩም** ቅ ተሸከርማሚ፥ አይን አፋር::
**ተሸከመከመ** ግ 1. ተሸከረመመ:: 2. ተግደረደረ::
**አሽከመከመ** ግ1. አሸከረመመ፥ አቆላመጠ:: 2. (አውራዶሮ) በአፉ ምግብ ይዞ ክንፉን በእግሩ አጓያ ዘርግቶ በእንስቷ ዶሮ ዙሪያ ተሸከረከረ::
***ሽከረመመ**
**ተሽከረመመ** ግ በአይን አፋርነት ጠባይ አይኑን ሰበር አንገቱን ዘንበል አደረገ፥ ተቅለሰለሰ::
**አሽከረመመ** ግ 1.አቆላመጠ፥ አሳሳቀ፥ አቃበጠ፥ ተጻራ፤ በጥቅሻ፥ በቀልድ፥... አጨዋወተ:: 2. አይኑን ሰበር አንገቱን ዘንበል አደረገ፥ አቅለሰለሰ::
***ሽከተ**
**ሽኩቻ** ስ 1. ተወዳዳሪዎች በእጅ ጣቶቻቸው አማካይነት የተለያየ ቅርፅ እየሰሩ (የወስፌ፥ የመቀስ፥...) ሁሉም በአንድ ጊዜ ብቅ አድርገው በማሳየት የሚያካሂዱት የቁማር ጨዋታ አይነት (ለምሳሌ መቀስ ወስፌን፥ ሰይፍ መቀስን፥... ይረታል):: 2. (አንዱ ሌላውን ለመጣል፥ ለማሸነፍ የሚደረግ) ፉክክር፥ ውድድር፥ ትግል፥ ሽሚያ::
**ተሻኮተ** ግ 1. ተወዳደረ፥ ተፎካከረ:: 2. አጋና ተማታ::
**አሻኮተ** ግ 1. አወዳደረ፥ አፎካከረ:: 2. አጋና አማታ::
**ሽኮና "ሽሆና"** ን ተመ.
**ሸወረረ** ግ ጠነገረ፥ ሸነደረ (አይን)::
**ሸውራራ** ቅ ጠንጋራ፥ አይኖቹ ወደሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመለከቱ የሚመስሉ::
**ሸውረር አለ** ግ ተጠናገረ፥ ተንሸዋረረ (አይኑ)::
**ሸውረር አደረገ** ግ አጠናገረ፥ አንሸዋረረ (አይኑን)::
**ተንሸዋረረ** ግ አይኖቹ ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ መሰለ::
**አንሸዋረረ** ግ አጠናገረ፥ አይኖቹን ወደተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ አስመሰለ::
**ሸወከ** ግ ሰበቀ፥ አዋሸከ::
**ሸውክ** ስ ሰብቅ::
**ሸውከኛ** ቅ ሰብቀኛ፥ አዋሻኪ::
**አዋሸከ** ግ አሳበቀ፥ አጣላ::
**ሸወደ** ግ (የአራዳ አነ.) አታለለ፥ አሞኘ::
**ሸዋጅ** ቅ አታላይ::
**ሸወዳ** ስ ማታለል፥ ማሞኘት::
**ተሸወደ** ግ ተታለለ፥ ተሞኘ::
**ሸውራራ "ሸወረረ"** ስር ተመ.
**ሸውሸዌ** ስ ንፋስ ሲነካው ሸው ሸው የሚል የዛፍ አይነት::
**ሸውሻዋ** ቅ ከአንድ የማይረጋ፥ ወላዋይ፥ ከውካዋ::
**ሸውከኛ "ሸወከ"** ስር ተመ.
**ሸውክ** ዝ.ከ.
**ሸዬ (ሾዬ)** ስ ከታች ሰፋ፥ ከጫፉ ሾጠጥ የሚልና የሚበላ ፍሬ ያለው ትልቅ የዛፍ አይነት:: "እሼ"ም ይባላል::
**ሸደሸደ** ግ 1. ሰፋ፥ ወሰወሰ፥ ሸከሸከ፥ ዘርዛራ አድርጎ ሰራ:: 2. አፋጠነ፥ አጣደፈ:: 3. አስቀመጠ፥ ነዳ (ተቅማጥ)::
**ተሸደሸደ** ግ ተሸከሸከ፥ ዘርዛራ ተደርጎ ተሰራ ወይም ተሰፋ::
***ሸገሸገ**
**ሽግሽግ** ስ ማጠጋጋት፥ማቻቻል፥ ማብቃቃት::
**ተሸጋሸገ** ግ ተጠጋጋ፥ ተቻቻለ፥ ተብቃቃ::
**አሸጋሸገ** ግ አጠጋጋ፥ አቻቻለ፥ አብቃቃ::
**ሸገነ** ግ አማረ፥ ተዋበ::
**ሽግና** ቅ መልከ መልካም፥ ሸጋ::
**ሸጋ** ቅ ያማረ፥ ቆንጆ፥ ውብ የሆነ::
**አሸገነ** ግ አሳመረ፥ አስዋበ::
**ሸጉራ (ሻጉራ)** ቅ አመሉ ከሰው የማይገጥም፥ አመለ ወልጋዳ::
**ሸጎረ** ግ 1. ቀረቀረ፥ ሸጎጠ፥ ደነቀረ:: 2. ቆለፈ፥ ዘጋ::
**መሸጎሪያ** ስ (የበር፥ የሳጥን) መቀርቀሪያ::
**ተሸጎረ** ግ 1. ተቀረቀረ፥ ተሸጎጠ:: 2. (በሩ) ተቆለፈ፥ ተዘጋ::
**ሸጎበ** ግ 1.(ውሻ) ጅራቱን ወደ ጉያው ከተተ፥ ወይም ሸጎጠ:: 2. (ዘይ.) በትንሹ፥ ሰወር አድርጎ ሰጠ (ገንዘብን ለዘመድ፥ ጉቦ)::
**ሸጎጠ** ግ 1. ሻጠ፥ ወተፈ፥ አገባ:: 2. ሰወረ፥ ደበቀ፥ ሸሸገ::
**ሽጉጥ** ስ 1.ከወገብ ላይ ወይም ከብብት ስር የሚታጠቁትና በአንድ እጅ የሚተኮስ አነስተኛ የጦር መሳሪያ::2. ግማሽ ሊትር የሚይዝ ትንሽ

ጠርሙስ፣ ቢራ ጠርሙስ።




ሽጉጥ

**ሽጉጡን ጠጣ** በሽጉጥ ራሱን ገደለ።

**ሽጉጥ ታጠቀ** ሽጉጥ አገነደረ፥ አነገበ (በወገብ፥ በብብት ስር)።

**ሽጉጥ አለ** ግ ተሸጎጠ፥ ተጠጋ (ተገን፥ ረዳት ፍለጋ)።

**ተሸጎጠ** ግ 1. ተሻጠ፥ ተወተፈ። 2. ተሰወረ፥ ተደበቀ፥ ተሸሸገ።

**ሸጠ** ግ 1. አንድን ነገር ወይም እቃ በገንዘብ ለወጠ። 2. (ዘይ.) ለጥቅም ሲል አሳልፎ ሰጠ። *የሃገሩን ምስጢር የሚሸጥ ከሃዲ ነው*።3. (የአራዳ አነ.) አታለለ፥ አሞኘ።

**መሸጫ** ስ 1. አንድ ነገር ወይም እቃ የሚሸጥበት ዋጋ። 2. እቃ ወይም ሌላ ነገር የሚሸጥበት መደብር።

**ሻጭ** ቅ አንድን ነገር ወይም እቃን በገንዘብ የሚሸጥ ወይም የሚለውጥ።

**ሽያጭ** ስ 1. አንድ ነገር ወይም እቃ የሚሸጥበት ዋጋ። 2. የአሻሻጥ ሁኔታ።

**ተሸጠ** ግ 1. በገንዘብ ተለወጠ። 2. (የአራዳ.አነ.) ተታለለ፥ ተሞኘ።

**አሸጠ** ግ አንድን ሰው ንብረቱን፥ እቃውን እንዲሸጥ አደረገ ወይም ገፋፋ።

**አሻሻጠ** ግ ገገርን በማምጣት፥ በመደለል፥ በማግባባት እቃው ወይም ንብረቱ እንዲሸጥ አደረገ።

**አሻሻጭ** ስ 1. ደላላ። 2. ቡና ቤት የምትሰራ ሴት።

**ሸጠሸጠ** ግ በፍጥነትና በብዛት ሰራ፥ አደረገ፥ ፃፈ፥ አዘጋጀ፥...።

**ሸጥ** ስ ፈፋ፥ ፈረፈር።

**ሸፈሬ** ስ በቆላ አካባቢ የሚበቅል የዛፍ አይነት።

**ሸፈሸፈ** ግ በመደዳ አጨደ፥ ቆረጠ፥ ከመከመ፥ አስተካከለ፥ ከረከመ።

**ሽፍሻፊ** ስ 1. ፍቅፋቂ፥ ቁርጥራጭ፥ ትርፍራፊ። 2. መናኛ ሳንቃ፥ ጠርብ።

**ሸፈተ**[1] ግ አመፀ፥ ከዳ፥ ተለየ፤ ወደ ዱር ወይም ወደ በረሃ ገባ ወይም ለመንግስት አልገዛ አለ።

**ሽፍታ** ስ አመፀኛ፥ ወንበዴ፥ ቀማኛ።

**አሸፈተ** ግ አሳመፀ፥ አስከዳ።

**ሸፈተ**[2] ግ (በሚናጥ ውተት ላይ) ቅባቱ ከላይ ሰፎ እንደ ጤፍ ፍሬ ጉብጉብ ብሎ ታየ።

**ሽፍታ** ስ በሚናጥ ወተት ላይ ሰፎ የሚታይ ጤፍ የሚያካክል ቅባት።

**ሸፈነ** ግ 1. አለበሰ፥ ከለለ፥ ጋረደ፥ እንዳይታይ አደረገ። 2. ደበቀ፥ ሰወረ። 3.ተክቶ ሰራ። *እሱ በሌለበት ጓደኞቹ ስራውን ሸፈኑለት*። 4. ቻለ፥ አጠቃለለ፥ ከፈለ። *ለትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ወጪ ሸፈነለት*።

**መሸፈኛ** ስ የመሶብ፥ የሳህን፥...ልብስ።

**ሽፋን** ስ 1. ልባስ፥ ክዳን፤ ከለላ። 2. ሰበብ፥ ምክንያት።

**ሽፍን** ቅ የተከደነ፥ ድብቅ።

**ሽፍን ጫማ** ስ እግርን ሙሉ ለሙሉ የሚያለብስ ጫማ።

**ሽፍንፍን** ስ 1. ድብቅ። 2. እንጀራ ለብሶ የሚቀርብ የስጋ ወጥ።

**ሸፋፈነ** ግ እንዳይታወቅ ወይም እንዳይጋለጥ ደበቀ።

**ተሸፈነ** ግ 1. ጨርቅን በመልበስ ተከለለ፥ ተጋረደ። 2. ተደበቀ፥ ተሰወረ፥ እንዳይታወቅ ሆነ። 3. (ስራው በሌላ ሰው) ተካሄደ፥ ተከናወነ። 4. (ወጪ) ተከፈለ፥ ተጠቃለለ።

**ተሸፋፈነ** ግ1. ለበሰ፥ ተከናነበ። 2. (ገበናው፥ ምስጢሩ) ተለባበሰ፥ ተደበቀ፥ እንዳይታወቅ ተደረገ።

**ሸፈጠ** ግ 1. ከዳ፥ ካደ፥ አበለ፥ ዋሸ።2. (ቁስሉ) የዳነ መስሎ እንደገና ተባባሰ።

**ሸፋጭ** ቅ አጭበርባሪ፥ አታላይ።

**ሽፍጥ** ስ 1. ክህደት፥ እብለት፥ ውሸት። 2. ማጭበርበር።

**ሽፍጠኛ** ቅ 1. ከዳተኛ። 2. አጭበርባሪ።

**ሸፈፈ** ግ ተወላገደ፥ ተጣመመ።

**ሸፋፋ** ቅ (ስድብ) እግረ ወልጋዳ፥ ጠማማ፤ በትክክል የማይረግጥ።

**ሸፎ ገመዱ** (ስድብ) እግሩን እያወላገደ ወይም እያጋመደ የሚሄድ።


**ሸፈፍ አለ** ግ ጠመም አለ፥ ወልገድ አለ።

**ሸፈፍ ሸፈፍ አለ** ግ ወልገድ ወልገድ እያለ ሄደ።

**ተንሻፈፈ** ግ ተወላገደ፥ ተጣመመ፤ በትክክል የማይረግጥ ሆነ።

**አንሻፈፈ** ግ አጣመመ፥ ሸፋፋ አደረገ።

**ሸፋፈነ** "ሸፈነ" ስር ተመ.
**ሸፋፋ** "ሸፈፈ" ስር ተመ.
**ሸፋጭ** "ሸፈጠ" ስር ተመ.
**ሸፍት** ስ የበሬ የሽንት መሽኛው (የቀጻጻው) ዙሪያ።
**ሸፍጠኛ** "ሸፈጠ" ስር ተመ.
**ሸፍጥ** ዝ.ከ.
**ሸፎ ገመዳ** "ሸፈፈ" ስር ተመ.
**ሹ** የ'ሸ' ፊደል ካእብ ዘር።
**ሹሉዳ** "ሹልዳ" ን ተመ.
**ሹል** "ሾለ" ስር ተመ.
**ሹልክልክ** "ሾለከ" ስር ተመ.
**ሹልውልዊት** ስ ጅራተ ጎፍላ የሆነችና በዛፍ ላይ የምትኖር አይጥ የምትመስል አውሬ።
**ሹልዳ(ሹሉዳ)** ስ በታናሽ የስጋ ብልት ላይ የሚገኝ ገርጣ ያለ ቀይ የስጋ ብልት።
**ሹመት** "ሾመ[1]" ስር ተመ.
**ሹም** ዝ.ከ.
**ሹም ሽር** ዝ.ከ.
**ሹሩባ** "ሾረበ" ስር ተመ.
**ሹራብ** ስ ከጥጥ፥ ከሱፍ፥...ክር የሚሰራና ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል የሚያለብስ፥ ባለ እጅጌና ባለኮሌታ ወይም ያለእጅጌና ኮሌታ የሚዘጋጅ የልብስ አይነት።
**ሹርባ** "ሸረበ" ስር "ሹሩባ"ን ተመ.
**ሹርቤ ብርሌ** "ሸረበ" ስር ተመ.
**ሹሮ** "ሽሮ"ን ተመ.
**ሹሻይ** ስ ቡላ ወይም የቢጫና ቡላ ድብልቅ መልክ ያለው፥ በመጠን ጨረባ የሚያክልና የሚመገባቸውን ነፍሳት እሾክ ላይ ከሰካ በሂላ የሚበላ ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።
**ሹካ** ስ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ፥ ሶስት ወይም ከሶስት የበለጠ መውጊያ ጣት ያለውና ምግብን ለመጉረስ የሚያገለግል ባለ እጀታ እቃ።



ሹካ

**ሹክ**
**ሹክታ** ስ በቀስታ ወይም በጆሮ የተነገረ ምስጢር፥ ወሬ፥ ሰብቅ።
**ሹክሹክታ** ስ 1. ሹክታ። 2. በአነስተኛ ድምፅ የሚደረግ ንግግር። 3. በአደባባይ ያልተነገረና ያልተረጋገጠ ወሬ።
**ሹክ አለ** ግ ሰው ሳይሰማ በቀስታ በጆሮ ወሬን ነገረ።
**ተንሾካሾከ** ግ ቀስ እያለ በምስጢር አወራ፥ ተነጋገረ።
**አሾከሾከ** ግ 1. ሌላ እንዳይሰማበት ቀስ ብሎ በለሆሳስ አወራ። 2.አሳበቀ።
**አሾክሿኪ** ቅ አሳባቂ፥ ወሬኛ።
**አንሾካሾከ** ግ ቀስ ብሎ በምስጢር ነገረ፥ አወራ።
**ሹግ (ሽግ)** ስ ችቦ።
**ሹጥ** ስ (ፀያፍ) የኮሶ ትል።
**ሹጣም** ቅ (ፀያፍ፥ ስድብ) ሹጥ ያለበት (ሰው)።
**ሹፌር** "ሾፈረ" ስር "ሾፌር" ን ተመ.
**ሺ** የ"ሸ" ፊደል ሳልስ ዘር።
**ሺህ (ሺ)** ስ 1. ከዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ቀጥሎ የሚመጣ ቁጥር፤ በአሃዝ ሲፃፍ ፲፻ ፥1000 ነው። ቅ 2. መጠኑ አስር መቶዎችን የሆነ።*ሺህ ብር።*
**ሻ[1]** የ"ሸ" ፊደል ራብእ ዘር።
**ሻ[2]** ግ ፈለገ፤ አሰኘው። *ለመሄድ ይሻል።*
**ሲሻኝ** ስፈልግ፥ ሲያሰኘኝ።
**ቢሻው** ቢፈልግ። *ቢሻው ይምጣ፡*
**አሻ** ግ አስፈለገ፥ አሰኘ። *ምን ላሻህ ? ምንም ኣልሻም።*
**ምን አሻህ** 1. ምን ቸገረህ፥ ምን አገባህ። 2. ምን አሰኘህ፥ አስፈለገህ።
**ኣያሻም** አያስፈልግም። *እንዲህ ያለ ነገር ኣያሻም።*
**ያሻው ቢሆን** የፈለገው ቢሆን፥ የመጣው ቢመጣ።
**ሻሁራ** "ሻኩራ" ን ተመ.
**ሻህላ** "ሻክላ" ን ተመ.
**ሻህኝ** ስ ብዙውን ጊዜ አፍንጫ ላይ የሚወጣ የቁስል አይነት።
***ሻለ**
**ሻል አለ** ግ ከበፊቱ የበለጠ ጥሩ ሆነ።
**ሻል አለው** አገገመ፤ በመጠኑ በጎ ወይም ደህና ሆነ፤ ከህመሙ ዳነ።
**ተሻለ** ግ 1. በለጠ፥ ላቀ። 2. ህመሙ ለቀቀ፥ በመጠኑ ተወገደ። *መድሃኒት ወስጄ ህመሙ ተሻለኝ።*
**የማይሻል** የማይበልጥ፥ ከበፊቱ ለውጥ

የሌለው:: *አዲስ የመጣው እቃ ከበፊቱ የማይሻል ነው::*

**ተሻሻለ** ግ 1. የተሻለ ሆነ፥ ጥሩ ለውጥ አሳየ:: 2. በኑሮ፥ በስልጣኔ፥ በሃብት አደገ፥ በለፀገ:: 3. ተለወጠ፤ መጠኑ፥ ጥራቱ፥ ደረጃው ከፍ ወይም ዝቅ አለ:: *ዋጋው ተሻሽሏል::*

**አሻለ** ግ በሽ አደረገ፥ አዳነ፥ ህመሙን አስታገሰ::

**አሻሻለ** ግ 1. ለወጠ፥ ጥሩ አደረገ፥ አሳመረ:: 2. መጠኑን፥ ጥራቱን፥ ደረጃውን ከፍ ወይም ዝቅ አደረገ::

**ማሻሻያ** ስ 1. ማስተካከያ፥ እርምት:: 2. (የትምህርት፥ የደሞዝ፥ የዋጋ፥...) ደረጃን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረጊያ::

**ሻለቃ** ስ 1.ከሻምበል በላይ ቀጥሎ ያለው ወታደራዊ ማእረግ:: 2. የተወሰነ ብዛት ያለው ሰራዊት የሚገኝበት የወታደር ክፍል::

**ሻል** ስ ብዙውን ጊዜ ከለስላሳና ከሚሞቅ የጨርቅ አይነት ወይም ከሱፍ ክር የሚሰራና ሴቶች ትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት አነስ ያለና እንደነጠላ የሚያገለግል ልብስ::

**ሸሚት** ስ ገፈራ፥ መኖ::

**ሻማ**[1] ስ 1. ከሰምና ከክር የሚሰራና ሲለኮስ ብርሃን የሚሰጥ ወፍራም የጧፍ አይነት:: 2. የኤሌክትሪክ አምፑሎች የብርሃን መጠን ወይም አቅም መለኪያ:: *ባለስልሳ ሻማ አምፑል::*

**ሻማ**[2] ስ ናይለንነት ያለው ጨርቅ::

***ሻማ**

**ሽሚያ** ስ አንድን ነገር ለማግኘት፥ ለመውሰድ፥ለመንጠቅ መሽቀዳደም፥ መረባረብ::

**ተሻማ** ግ 1. አንድን ነገር ለመውሰድ፥ ለመያዝ ከሌላው ጋር ተወዳደረ፥ ተሽቀዳደመ፤ ተናጠቀ:: 2. ተጋራ::

**አሻማ** ግ 1. አናጠቀ፤ የቀደመ፥ የቻለ፥ ያጋጠመው እንዲወስድ አወዳደረ:: 2. ግልፅ አልሆን አለ፤ እቅጩን የማይገልፅ፥ አጠራጣሪ ሆነ::

**አሻሚ** ቅ ግልፅ ያልሆነ፥ ከአንድ በላይ አማራጭ ያለው (ነገር)::

**ሻሜ** ስ የዶቃ አይነት::

**ሻሜታ** ስ ከበሶ የሚዘጋጅ ጌሾና ብቅል የሌለው ወፍራም መጠጥ::

**ሻሜት** ስ አጥሚት::

**ሻምላ** ስ ከነሃስ፥ ከብር ወይም ከሌላ ማእድን የሚሰራና ለክብር፥ ለጌጥ የሚያዝ ጎራዴ::

**ሻምበል** ስ 1. ከመቶ አለቃ ቀጥሎ የሚገኝ ወታደራዊ ማእረግ:: 2. የተወሰነ ብዛት ያለው ሰራዊት የሚገኝበት የወታደር ክፍል::

**ሻምፒዮን** ስ የስፖርት ወይም የሌላ ውድድር የሁሉም አሸናፊ::

**ሻምፓኝ** ስ ብዙውን ጊዜ በሰርግ ወይም በሌላ ልዩ ዝግጅት ላይ ለእንግዳ ልዩ የክብር ወይም የደስታ መግለጫ ሆኖ የሚቀርብ ከወይን የሚዘጋጅና አልኮልነት ያለው መጠጥ::

**ሻረ** ግ 1. ዳነ፥ ተፈወሰ:: 2. ተወ፥ አስቀረ፥ አፈረሰ:: *የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሻረ::* 3. የመድሃኒት ሃይልን አጠፋ፥ ደመሰሰ፥ ቀነሰ:: 4. ጣሰ፥ አፈረሰ:: *ህጉን ሽሮ ወንጀል ሰራ::* 5. ከስልጣን አወረደ ወይም አስወገደ:: 6. (ዘይ.) የሚበቃውን፥ የሚያረካውን ያህል አገኘ::

**ሽረት** ስ 1. ፈውስ፥ ደህንነት:: 2. ከስልጣን መውረድ ወይም ማውረድ:: 3. ከጠበቁት በላይ ማግኘት፥ መርካት (የውሳኔ፥ የፍርድ፥...)::

**ተሻረ** ግ 1. ከስልጣን ወረደ ወይም ተወገደ:: 2. ተተወ፥ ቀረ፥ ፈረሰ:: 3. ፈረሰ፥ ተገደፈ (ፆም)::

**አሻረ** ግ 1. አዳነ፥ ፈወሰ (የኮሶ መድሃኒት):: 2. ከተጠበቀው በላይ ሰጠ፥ አስደሰተ::

**አሻረ** ግ አስቀረ፥ አስለወጠ፥ አስገለበጠ (ውሳኔን፥ ፍርድን፥...)::

**ሻሲ(ሻንሲ)** ስ የመኪና የተለያዩ አነስተኛ ክፈሎች የሚገጣጠሙበትና ዋና ተሸካሚ የሆነ የራሱ መለያ ቁጥር ያለው ትልቅ የመኪና አካል::

**የሻሲ ቁጥር** ስ በሻሲ ላይ የታተመ መለያ ቁጥር::

**ሻሽ** ስ 1. ወርዱ ጠበብ ቁመቱ ረዘም ያለ፥ ከጥጥ የተሰራና ስስ የሆነ ነጭ የራስ ማሰሪያ፤ ጥምጥም:: 2. ከጥጥ፥ ከሃር፥... የሚሰራ የተለያየ ቀለማትና መጠን ያለው የሴቶች የራስ ማሰሪያ ወይም ሽፋን::

**ሻሽ የመሰለ** በጣም ነጭ የሆነ::

**ሻሾ** ቅ የነጭ በሬ፥ ፈረስ፥... የቅፅል ስም::

**ሻቀለ** ግ 1. ጓጓ፥ ሰየ፥ ቋመጠ፥ ጎመጀ:: 2.ቸኮለ፥ ተጣደፈ::

**አሻቀለ** ግ አጓጓ፥ አቋመጠ፥ አስጎመጀ::

***ሻቀበ**

**ሽቅብ** መዋ. አቀበት፥ ወደላይ፥ ዳገት፤ የቁልቁል ተቃራኒ::

**ሽቅብ ቁልቁል አለ** 1. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተሯሯጠ፤ ለፋ፥ ደከመ፥ ኳተነ:: 2. በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ አስመለሰ፥ አስቀመጠ::

**ሽቅብ አለ** አስታወከ::

**ሽቅብ ወጣ** ወደ ላይ አቅጣጫ ወይም ከፍ ወዳለ ቦታ ሄደ::

**ሽቅበት** ስ ዳገትማ፥ ከፍ ያለ ቦታ::

**አሻቀበ** ግ ወደላይ፥ ወደ ዳገት ወጣ ወይም ሄደ።

**አሻቅቦ ተሳደበ** ታላቁን ፥ የበላዩን ሰደበ።

***ሻተተ**

**ሸተቴ** ስ ተቅማጥ።

**ተንሻተተ** ግ ተንሸራተተ፥ እየተንፏቀቀ ሄደ።

**አንሻተተ** ግ 1. አንሸራተተ፥ አዳለጠ። 2.(ተቅማጥ) አስቀመጠ።

**ሻታ** ስ 1.ተቅማጥ 2. (የአራዳ አነ.) ትውከት።

**ሻንሲ** "ሻሲ"ን ተመ.

**ሻንቅላ** ቅ ጥቁር።

**ሻንቆ** ቅ በጣም ጥቁር የሆነን በቅፅል ስም መልክ ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

**ሻንቆ ጋሻ** ስ ጌጥ የሌለውና ልሙጥ የሆነ ጥቁር ጋሻ።

**ሻንኩራ** ስ ባለ አንድ ጆሮ ማድጋ።

**ሻንጣ** ስ ከቆዳ፥ ከሸራ፥...የሚሰራ ቀላል ሳጥን።

**ሻኛ** ስ ከማጅራት ሧላ የሚገኝ ጉብ ያለ የበሬ ፥ የላም ... ትከሻ።

**ሻከረ** ግ 1. ኮሰኮሰ፥ ጎረበጠ፥ ቆረቆረ፥ ልስላሴ አጣ። 2. (ዘይ.) ደስ የማይል ሆነ፥ መጥፎ አዝማሚያ ያዘ። *በሁለቱ መሃል የነበረው ግንኙነት ሻክሯል።*

**ሻካራ** ቅ ለስላሳ ያልሆነ፥ የሚኮሰኩስ፥ የሚጎረብጥ።

**አሻከረ** ግ 1. ልስላሴ አሳጣ። 2.(ዘይ.) አስቀየመ፥ ቅር አሰኘ።

**ሻኩራ (ሻሁራ)** ስ 1. ከነሃስ፥ ከመዳብ፥... የሚሰራና የሚቅጨለጨል ወይም የሚንሿሿ መርገፍ ያለው የቤት ጉልላት ወይም በመሶብ ወርቅ ወይም በመረሻት ላይ ያለው የሚንሿሿ ዘርፍ።2. የቤተክርስቲያን የማእጠንት እቃ፤ ፅንሃህ።

**ሻካራ** "ሻከረ" ስር ተመ.

**ሻክላ (ሻህላ)** ስ 1. ከብዙ አገልግሎት በሧላ የሚፈጠር የሸክላ እቃ የውስጠኛ ክፍል መቦርቦር ወይም መቀረፍ። 2.የደረቀ የጥርስ ልግም ወይም ቆሻሻ።

**ሻክላ በላው** ሻክላ አበላሸው፥ ቦረቦረው፥ ቀረፈው።

**ሻወር** ስ ውሃ በዝናብ መልክ እንዲወርድ የሚያደርግ ወንፊት መሰል ማውረጃ ከጫፉ ላይ የተገጠመበት የገላ መታጠቢያ ቧንቧ።

**ሻይ** ስ 1. ሞቃትና ርጥብ በሆነ አካባቢ የሚበቅል ቁጥቋጦ መሰል ተክል። 2. ሻይ ከሚባለው ተክል የሚገኘው ቅጠል ከውሃ ጋር ተፈልቶ፥ ብዙውን ጊዜ ስኳር ተጨምሮበት በትኩሱ የሚጠጣ፥ ቀላ ያለ መልክ ያለው መጠጥ።

**የሻይ ማንኪያ** ስ ሻይ ለማማሰል የሚያገለግል ትንሽ ማንኪያ(ስእሉን ማንኪያ ስር ተመ.)።

**ሻይ ቅጠል** ስ ደርቆና ደቆ የተዘጋጀ የሻይ ቅጠል።

**ሻይ ቤት** ስ ሻይ፥ ለስላሳ መጠጦችና ዳቦ፥... የሚሸጡበት የንግድ ቤት።

***ሻገረ**

**ሽግግር** ስ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ እስኪገባ ድረስ ያለው ጊዜ፥ ሁኔታ፥ ሂደት።

**[የ]ሽግግር መንግስት** ስ ቋሚ መንግስት እስኪመሰረት ድረስ በጊዜያዊነት የሚቋቋም መንግስት።

**የሽግግር ወቅት** ስ ከአንድ ደረጃ ወይም ሁኔታ ወደ ሌላ እስኪገባ ድረስ ያለው ጊዜ።

**ተሻገረ** ግ 1.(ወንዝን፥ ሸለቆን፥ ባህርን፥...) አቋርጦ ሄደ። 2. ተራመደ። 3. አለፈ። 4. ወደ ሌላ ገባ፥ ተላለፈ። 5. (በሽታ) ተጋባ፥ ተላለፈ።

**ተሻጋሪ ግስ** ስ ተሳቢ የሚያስፈልገው ግስ።

**ተሸጋገረ** ግ 1. አለፈ፥ ሄደ፥ አቋረጠ። 2. ካንዱ ወደ ሌላ ተላለፈ። 3. እድገት፥ ለውጥ አሳየ። 4. (ከዘመን ወደ ዘመን) አለፈ፥ ተሻገረ። 5. (በውርስ) ተላለፈ።

**መሸጋገሪያ** ስ መተላለፊያ፥ መረማመጃ፥ ድልድይ፥ ርብራብ።

**ተሸጋጋሪ** ስ የቤትን ጣራ የሚሸከም ወፍራምና ረዥም እንጨት፤ ሰረገላ።

**አሻገረ** ግ 1.ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ አጓጓዘ ወይም ወሰደ። 2. (ድልድይ፥ መንገድ) መረጋገጫ ሆኖ አሳለፈ፥ አስኬደ። 3. ከአንዱ ወደ ሌላው አስተላለፈ። 4. ከአንዱ መነሻ ቦታ ወደ ሌላው ለመሄድ መተላለፊያው ወይም መንገዱ ችግር የሌለበት ሆነ።

**ባሻገር** 1. ወዲያ፥ በሧላ፥ ሌላ፥ በተጨማሪ። *ከዚህም ባሻገር ሌላ አገልግሎት ይሰጣል።* 2. በርቀት ወይም ማዶ። *ባሻገር የሚታየው የሰውየው ቤት ነው።*

**ባሻጋሪ** በርቀት።

**አሻግሮ ተመለከተ** በርቀት ያለውን ተመለከተ።

**አሻጋሪ** ስ ወንዝን የሚያሻግር ዋናተኛ።

**አሸጋገረ** ግ 1. አስተላለፈ። 2. አደረሰ። *ጽንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረም*። 3. (ገመድን፥ ወራጅ እንጨትን) ከወዲህ ወደዚያኛው ዳር አስተላለፈ (ለማሰር፥ ለመምታት፥...)።

**ሻገተ** ግ 1. ሸበተ፥ ከመቆየት፥ ከሙቀት የተነሳ ተበላሸ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)። 2. ብዙ ኖረ ቆየ፥

ወይም አረጀ።

**ሻጋታ** ቅ 1. የታመከ፥ ጥጥ የመሰለ፥ የተበላሸ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)። 2. (ስድብ) አሮጌ፥ የተበላሸ፥ ንፅህና የጎደለው።

**ሻጉራ** "ሽጉራ" ን ተመ.

**ሻግያ** ቅ በጣም ጥቁር የሆነ፥ ጠቋራ።

**ሻጠ** ግ ሰካ፥ ተከለ፥ ሽጎጠ፥ ሳገ።

**ተሻጠ** ግ ተሰካ፥ ተሽጎጠ።

**ሻጠረ** ግ 1. አዋዋለ፥ አስማማ፥ አገበያየ። 2.ተብለጠለጠ፤ ተንኮል፥ ሸር ሰራ።

**ሻጥር** ስ ተንኮል፥ ሸር።

**ሻጥረኛ** ቅ ተንኮለኛ፥ ሸረኛ።

**አሻጠረ** ግ ተንኮል፥ ሸር ሰራ፤ ደባ ፈፀመ።

**አሻጥር** ስ ተንኮል፥ ሸር፥ ሴራ፥ ደባ።

**አሻጥረኛ** ቅ ተንኮለኛ፥ ሸረኛ፥ ደባ የሚፈፅም።

**ሻጭ** "ሻጠ" ስር ተመ.

**ሻፈደ** ግ (ነውር) ቋመጠ፥ ፈለገ፥ ጓጓ (ለወሲብ)።

**ሻፋዳ** ቅ (ስድብ) ቅንዝረኛ፥ ሴሰኛ።

**አሻፈደ** ግ (ነውር) ለወሲባዊ ግንኙነት አግባባ፥ ቀሰቀሰ፥ አነሳሳ።

**ሻፎ** ቅ ስለት ያለው ሹል (ድንጋይ፥ ሴፋጭ፥ ባልጩት)።

**ሼ** የ"ሸ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ሼህ** "ሸህ" ን ተመ.

**ሽ** የ"ሸ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**–ሽ** ከግሳዊ ቃል በስተመጨረሻ በኩል እየገባ ፥ የግሱ ባለቤት ወይም ተሳቢ መደቡ 2ኛ፥ ቁጥሩ ነጠላ ፆታው አንስታይ መሆኑን የሚያመለክት ምእላድ። ለምሳሌ "መፅሃፉን ወሰድሽ?" በሚለው ግሳዊ ቃል ውስጥ "–ሽ" "አንቺ" የሚለውን የግሱን ባለቤት ያመለክታል። "ጠሩሽ" በሚለው ግሳዊ ቃል ውስጥ "–ሽ" "አንቺን" የሚለውን ተሳቢ የሚያመለክት ምእላድ ነው። ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች (መደብ፥ ቁጥር፥ ፆታ) በተጨማሪ የአንድ ነገር ባለቤት ወይም ባለ ይዞታ መሆንን የሚያሳይ ምእላድ ነው። ለምሳሌ "መኪናሽ" በሚለው ቃል ውስጥ "–ሽ" "ያንቺ" የሚለውን የባለቤትነት ይዞታ ያሳያል።

**ሽህር** ስ መሲና፤ የደለበች የስጋ ላም።

**ሽሉዳ** "ሹልዳ" ን ተመ.

**ሽላን** ስ እንስላል።

**ሽል** ስ 1.ፅንስ።2. (ዘይ.፥ ስድብ) ልፍስፍስ፥ ደካማ፥ አቅመቢስ(ሰው)።

**ሽለሙቅ** ቅ ቶሎ ቶሎ የምትፀንስና የምትወልድ (ሴት)።

***ሽል**

**ሽል አለ** ግ 1. ሰለለ፥ ቀጠነ። 2. (ተራ አነ.) ተደብቆ፥ ተሸሽጎ ሄደ።

**ሽልማት** "ሸለመ" ስር ተመ.

**ሽልም** ዝ.ከ.

**ሽልምልም** ዝ.ከ.

**ሽልብታ** "*ሸለበ" ስር ተመ.

**ሽልጦ** ስ እንደጠቢኛ ያለ ወፈር ያለ ቂጣ።

**ሽልፋ** ቅ 1. የማይረባ፥ አቅመቢስ። 2. በአይነቱ በጣም ዝቅተኛና ተራ የሆነ፥ መናኛ።

**ሽመለኛ** "ሽመል" ስር ተመ.

**ሽመላ** ስ እግረ ቀጭንና ረዥም የሆነ በየወንዙ ዳር የሚታይ የአሞራ አይነት ( ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ሽመል** ስ 1. እንደመቃ አንጓ ያለው ውስጠ ድፍን የሆነ የእፅዋት አይነት። 2. በትር፥ ዱላ።

**ሽመለኛ** ቅ ዱለኛ፥ ተደባዳቢ።

**ሽሙንሙን** "ሽሞነሞነ" ስር ተመ.

**ሽሙጥ** "*ሸሞጠጠ" ስር ተመ.

**ሽሙጥጫ** ዝ.ከ.

**ሽሚያ** "*ሻማ" ስር ተመ.

**ሽማት(ሽማያት)** ስ የቅማያት አባት ወይም እናት፤ አራተኛ አያት።

**ሽማግሌ** "ሸመገለ" ስር ተመ.

**ሽምብሩት** "ሽንብራ" ስር "ሽንብሩት"ን ተመ.

**ሽምብራ** "ሽንብራ" ን ተመ.

**ሽምድምድ** "*ሸመደመደ" ስር ተመ.

**ሽምግልና** "ሸመገለ" ስር ተመ.

**ሽምጥ**$^1$ "ሸመጠጠ$^1$" ስር ተመ.

**ሽምጥ**$^2$ "ሸመጠጠ$^2$" ስር ተመ.

**ሽረት**$^1$ "ሻረ$^1$" ስር ተመ.

**ሽረት**$^2$ "ሻረ$^2$" ስር ተመ.

**ሽር**

**ሽር አለ** ግ 1. ፈጠነ፥ ቀለጠፈ (ለስራ)። 2. ዘነጠ፥ ተሽቀረቀረ።

**ሽር ጉድ አለ** (ስራ ለመስራት፥ ለማስተናገድ) ወዲያ ወዲህ አለ።


**ሽር ጉድ አበዛ** አጉል ታዛዥነት፥ አለሁ አለሁ ባይነት አሳየ።

**ሽርሙጥና** "ሸረሞጠ" ስር ተመ.

**ሽርሽር** "ሸረሸረ$^2$" ስር ተመ.

ሽርቁጥ "ሽረቆጠ" ስር "ሽርቋጣ"ን ተመ.
ሽርቦሽ "ሽረበ" ስር ተመ.
ሽርካ "*ሽረከ" ስር "ሽሪክ" ን ተመ.
ሽርክ ዝ.ከ.
ሽርክርክ "*ሽረከረከ" ስር ተመ.
ሽርክት "ሽረከተ" ስር ተመ.
ሽርክና "*ሽረከ" ስር ተመ.
ሽርደዳ "ሽረደደ" ስር ተመ.
ሽርጥ "ሽረጠ" ስር ተመ.
ሽርፍ "ሽረፈ" ስር ተመ.
ሽርፍራፊ ዝ.ከ.
ሽሮ (ሹሮ) ስ ከተቆላ አተር፥ ባቄላ፥ ሽንብራ፥...ተፈጭቶ የሚዘጋጅ ለወጥ የሚሆን ዱቄት:: 2. ከሽሮ ዱቄት የሚሰራ ወጥ::
ሽሽት "ሸሸ" ስር ተመ.
ሽሽግ "ሸሸገ" ስር ተመ.
ሽቀላ "ሸቀለ" ስር ተመ.
ሽቁምቁም "*ሸቆመቆመ" ስር ተመ.
ሽቁጥቁጥ "*ሸቆጠቆጠ[1]" ስር ተመ.
ሽቅበት "*ሻቀበ" ስር ተመ.
ሽቅብ ዝ.ከ.
ሽበታም "ሸበተ" ስር ተመ.
ሽባ ስ 1.እግሩ ወይም እጁ እንደልብ ሊታዘዝለት የማይችል፥ ሰላላ፥ ልምሾ፥ አካለ ስንኩል::2. (ዘይ.) ልፍስፍስ፤ አቅም ወይም ጥንካሬ የሌለው (ሰው)::
ሽባጥ ስ በጣልቃ ወይም በጎደለ ቦታ የሚገባ ስርዋፅ::
ሽብልል (ሽብል) "ሸበለለ" ስር ተመ.
ሽብልቅ "ሸበለቀ" ስር ተመ.
ሽብልብል "*ሸበለበለ" ስር ተመ.
ሽብር "*ሸበረ" ስር ተመ.
ሽብርተኛ ዝ.ከ.
ሽብሽባ "*ሸበሸበ" ስር ተመ.
ሽብሽባት "ሸበሸበ" ስέ ተመ.
ሽብሽቦ ዝ.ከ.
ሽቦ ስ እንደ ክር፥ ሲባጎ፥...ቀጭን ሆኖ የተሰራ ብረት፥ መዳብ...::
ሽቦ ራስ (ስድብ) ቁርንድድ ፀጉር::
ሽቦ አልጋ ስ ከብረትና ሽቦ የተሰራ አልጋ::
ሽቱ "ሸተተ" ስር "ሽቶ" ን ተመ.
ሽታ "ሸተተ" ስር ተመ.

ሽቶ ዝ.ከ.
ሽንሽና ስ በወንዝ ዳር የሚበቅልና የማይነቅዝ የዛፍ አይነት::
ሽንሽን "ሸነሸነ" ስር ተመ.
ሽንቁር "ሸነቆረ" ስር ተመ.
ሽንቅር ዝ.ከ.
ሽንቅጥ "ሸነቀጠ" ስር "ሽንቃጣ" ን ተመ.
ሽንብራ(ሽምብራ) ስ በጫፉ ላይ ሾል ያለ አፍንጫ መሰል ጉጥ ያለው ፍሬ የሚያፈራ የአበባ እህል፤ ፍሬውም "ሽንብራ"ይባላል::
ሽንብራው ፈሰሰ ህፃን በወደቀ ጊዜ እንዳያለቅስ ሃሳቡን ወደ ሌላ ለመውሰድ የሚባል የማባበያ ቃል::
ሽንብሩት (ሽምብሩት) ስ ሽንብራ የምትመስል የንብ አይነት::
ሽንብራ ዱቤ ስ ፍሬው ትልልቅ የሆነ ሽንብራ::
ሽንታም "ሸና" ስር ተመ.
ሽንት ዝ.ከ.
ሽንትራት "ሽነተረ" ስር ተመ.
ሽንትር ዝ.ከ.
ሽንኩርት ስ ቀላ ወይም ነጣ ያለ መልክ ያለው ከብ ሆኖ በመሬት ውስጥ የሚያፈራና የሚፋፋ፥ የተነባበረ ቆዳ ያለው ተክል::


ቀይ ሽንኩርት


ነጭ ሽንኩርት

ሽንክ ስ ነጭ አባ ወጓሬ የሚመስል ነፍሳት::
ሽንክላ ስ የውሃ፥ የጠላ፥...መያዣ ማድጋ::
ሽንገላ "ሸነገለ" ስር ተመ.
ሽንጥ ስ 1. በጀርባ አጥንት ግራና ቀኝ በኩል ከትከሻ ግርጌ እስከ ዳሌ አካባቢ ያለው የሰውነት ክፍል(ሰእሉን ሰውነት ስር ተመ.):: 2. ከሻኛ ግርጌ እስከ ጅራት አካባቢ የሚደርስ የቀንድ ከብት የስጋ ብልት::
ሽንጣም ቅ ቁመቱ ረዥም የሆነ::
ሽንጥ ራስ ስ የሽንጥ ጫፍ ስጋ::
ሽንፈት "*ሸነፈ" ስር ተመ.
ሽንፍላ ስ 1. ፈርስ የሚቀመጥበት፥ ሲያጥቡት ቶሎ የማይጠራ የተነባበረና ትንንሽ ከረጢት

ያለው ጨጓራ መሰል የሆድ እቃ። 2. (ዘይ.) የማይጠራ፥ እንከን የማይታጣበት።
**ሽኩምኩም** "*ሽኮመኮመ" ስር ተመ.
**ሽኩቻ** "ሽኮተ" ስር ተመ.
**ሽክ**
**ሽክ አለ** ግ ተዋበ፥ አጌጠ።
**ሽክርክሪት** "*ሽከረከረ" ስር ተመ.
**ሽክርክር** ዝ.ከ.
**ሽክሽክ** "ሽከሸከ" ስር ተመ.
**ሽክና** ስ ከቅል የሚዘጋጅ የውሃ፥ የጠላ፥... መቀጃ ወይም መጠጫ እቃ።
**ሽክፍ** "ሽከፈ" ስር ተመ.
**ሽኮኮ** ስ በየጎሬው፥ በየቋጥኙ የሚኖር፥ ድመት የሚያክልና ቅርፁም ሆነ መልኩ አይጥ የሚመስል እግረ አጭር የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።
**ሽወዳ** "ሸወደ" ስር ተመ.
**ሽው**
**ሽውታ** ስ 1. የምች፥ የግርፋት ህመም። 2. የነፋስ እንቅስቃሴ (ፍጥነት)። 3. (ዘይ.) ጭምጭምታ ወሬ።
**ሽው አለ** ግ ሹው፥ ጭልጥ ብሎ ሄደ። 2. በፍጥነት በሮ አለፈ። 3. ነፈሰ፥ የነፋስ እንቅስቃሴ ተሰማ።
**ሽው አለበት** 1. በትንሹ ተጨመረበት። 2. ዞር አለበት፥ እንደመበሳሸት አለ (ጠላ፥ ጠጅ፥...)።
**ሽው አለው** 1. ጨረፍታ ወሬ ሰማ። 2.በመጠኑ አመመው።
**ሽው ሽው አለ** ግ 1.መሳልሰ ነፈሰ። 2. ከነፈ፥ ወዲያና ወዲህ አለ፥ ተንከወከወ። 3. በነፋስ ሃይል ተንቀሳቀሰ፥ ተወዛወዘ (ዛፍ፥ ቅጠል)።
**ሽያጭ** "ሸጠ" ስር ተመ.
**ሽጉጥ** "ሸጎጠ" ስር ተመ.
**ሽግል** ስ የአባለ ዘር በሽታ፣ ጨብጥ።
**ሽግሽግ** "*ሸገሸገ" ስር ተመ.
**ሽግግር** "*ሻገረ" ስር ተመ.
**ሽፋል** ስ ከግንባር በታች ያለው የቅንድብ ፀጉር (በጎጃምና በጎንደር ቅንድብ እየተባለ ይጠራል) (ስእሉን አይን ስር ተመ.)።
**ሽፋሽፍት** ስ በአይን ዙሪያ ያለ ፀጉር። ቅንድብ እየተባለም ይጠራል(ስእሉን አይን ስር ተመ.)።
**ሽፋን** "ሸፈነ" ስር ተመ.
**ሽፋፍ** ስ የስለት (የጦር፥ የቢላዋ፥ የቀስት፥...) ማህደር።
**ሽፍ**
**ሽፍታ** ስ ሽፍ ወይም እጅብ ብሎ የሚወጣ እከክ መሰል ነገር።
**ሽፍ አለ** ግ እጅብ ብሎ ወጣ፥ ታየ፥ በቀለ፥ አለበሰ (እንደ ቡቃያ ወይም እከክ ያለ ነገር)።
**ሽፍሻፌ** "ሸፈሸፈ" ስር ተመ.
**ሽፍታ**[1] ስ ቀጭን ሹሩባ።
**ሽፍታ**[2] "ሸፈተ[1]" ስር ተመ.
**ሽፍታ**[3] "ሸፈተ[2]" ስር ተመ.
**ሽፍታ** "ሽፍ" ስር ተመ.
**ሽፍት** ስ ፈረቃ።
**ሽፍን** "ሸፈነ" ስር ተመ.
**ሾ** የ "ሸ" ፊደል ሳብእ ዘር።
**ሾለ** ግ ከወደ ጫፉ ቀጠነ፥ እንደ ወስፌ ሆነ፥ ሾጠጠ።
**ሹል** ቅ ከጫፉ የቀጠነ፥ የሾጠጠ።
**ሹል አፍ** ቅ (ስድብ) ነገረኛ፥ ሞጥሟጣ።
**አሾለ** ግ ከጫፉ አቀጠነ፥ አሾጠጠ።
**ሾለቅ** ስ ምንቃሩ ትልቅ የሆነ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።
**ሾለከ** ግ 1.በቀዳዳ ወጣ፥ ተፈተለከ፥ ወለቀ፥ አልፎ ሄደ። 2. ሳይታይ ቀስ ብሎ ሄደ፥ ጠፋ፥ አመለጠ። 3.ተረፈ፥ ዳነ፥ አመለጠ፥... (ከሞት፥ ከአደጋ፥...)።
**መሹለኪያ** ስ መውጫ፥ ማለፊያ፥ ቀዳዳ።
**በሹልክታ** ተው.ግ. ሳይሰማ፥ ሳይታይ፥ ሳይታወቅ።
**ሾላካ** ቅ 1. (ስድብ) ቀትረ ቀላል፥ ከውካዋ። 2. ሰላይ።
**ሹልክልክ** ቅ (ስድብ) የማይያዝ፥ የማይጨበጥ፥ እርጋታ የሌለው።
**ሹልክ አለ** ግ ድምፁን ሳያሰማ፥ ሳይታይ ፈጥኖ ወጣ ወይም ሄደ።
**ሹልክ አደረገ** ግ አሾለከ።
**ተሾለከ** ግ ቀስ ብሎ ወይም ተደብቆ ወጣ ወይም ሄደ።
**ተሽሎከሎከ** ግ ውስጥ ለውስጥ ተጓዘ፥ አለፈ።
**መሽሎክሎኪያ** ስ ውስጥ ውስጡን መተላለፊያ መንገድ።
**መሿለኪያ** ስ ለመተላለፊያ የሚያገለግል ቀዳዳ ወይም ከፍተት።
**አሽሎከሎከ** ግ ውስጥ ለውስጥ አስኬደ፥ አሳለፈ።
**አሾለከ** ግ አስወጣ፥ አሳለፈ።

**አሾለከ** ግ እንዲሾልክ አደረገ።
**ሾላ** ስ ፍሬው የሚበላ ትልቅ ዛፍ፤ ፍሬውም ሾላ ይባላል።
**ሾላ በድፍን** ነገሩ ወይም ምስጢሩ ሳይገለጥ እንዳለ ይሁን ለማለት የሚነገር አባባል።
**ሾሌ** ስ አፋና ከንፈሩ አካባቢ ነጭ የሆነ ፈረስ፤ አፈ ሾሌም ይባላል።
**ሾመ**[1] ግ ስልጣን ሰጠ።
**ሹም** ስ ባለስልጣን፥ አለቃ፥ አዛዥ፥ ሃላፊ።
**ሹም ሽር** ስ በስልጣን የነበረውን የማውረድና ሌላ አዲስ ባለስልጣን የመተካት ተግባር።
**ሹመት** ስ የበላይ ሃላፊነት፥ የአዛዥነት፥ የአለቅነት፥ የአስተዳዳሪነት ማእረግ ወይም ስልጣን።
**ሹመት አይደንግጥ** ከስልጣን ለተሻረ ሰው የሚቀርብ የማፅናኛ አነጋገር።
**ሹመት አገኘ** ስልጣን አገኘ፥ ሃላፊነት ተሰጠው።
**ሹመት ያዳብር** (ምር.) ሹመቱ ይፅና፥ እያደገ ወይም ከፍ እያለ ይሂድ፥ ይጨምር (አዲስ ለተሾመ የሚቀርብ የደስታ መግለጫ)።
**የሹመት ደብዳቤ** ስ አንድ ሰው ለአንድ የስራ ሃላፊነት የተመደበ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ።
**ሿሚ** ቅ ስልጣን መስጠት የሚችል ከፍተኛ ባለስልጣን።
**ተሾመ** ግ ስልጣን፥ ሹመት አገኘ ወይም ተሰጠው።
**ተሿሚ** ቅ ከፍተኛ ማእረግ ወይም ስልጣን ያገኘ (ሰው)።
**አስሾመ** ግ ስልጣን አስገኘ። *የሚያሾም ስራ ሰርቷል።*
**ሾመ**[2] ግ ሞላ፥ አንቸረፈፈ፥ ጢም አደረገ። *ጠላውን በጋን ሾመ።*
**ተሾመ** ግ ተሞላ፥ ተንቸረፈፈ፥ ጢም አለ (ጠጁ ወይም ጠላው በማድጋ፥ በጋን፥...)። 2. በሽታ፥ ዛር፥...በላዩ አደረ። *የተሾመበት ዛር ላለናገር ላለው።*
**ሾረ** ግ 1. ተሽከረከረ፥ ዞረ፥ ተንሻረረ። 2. (ዘይ.) ሀ. ታረመ፥ ተስተካከለ፥ ልክ ገባ። ለ.ሰለጠነ፥ ቀለጠፈ።
**አሾረ** ግ 1. አሽከረከረ፥ አዞረ፥ አንሻረረ። 2.(ዘይ.) ሀ. አረመ፥ አስተካከለ፥ ልክ አገባ።ለ. ቀልጣፋ አደረገ።
**ሾርባ** ስ በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።
**የሾርባ ማንኪያ** ስ ከሻይ ማንኪያ ከፍ የሚልና ሁለት የሻይ ማንኪያ ያህል የሚይዝ ማንኪያ (ስእሉን ማንኪያ ስር ተመ.)።
**የሾርባ ሳህን** ስ ለሾርባ ማቅረቢያ የሚያገለግል ጎድጓዳ ሳህን።
**ሾርኒ** ስ የጎን፥ የእጅ አዙር፥ የተዘዋዋሪ መንገድ። *በሾርኒ ሰደበው።*
**ሾቀ** ግ 1.በመጠኑ ተቀቀለ፥ ተንገረገበ። 2. ራሰ፥ ረጠበ። *ልብሱ በዝናብ ሾቀ።* 3. በሙሉ አለቀ ወይም ሞተ። *ሰራዊቱ እንዳለ ሾቀ።*
**ተሾቀ** ግ ተንገረገበ፥ እንዲርስ፥ ተደረገ (በመጠኑ በመቀቀል)።
**አሾቀ** ግ 1. በመጠኑ ቀቀለ፥ አንገረገበ። 2. አራሰ፥ አረጠበ (ለምሳሌ ዝናብ ልብስን)።
**አሹቅ** ስ ተቀልቶ በፈላ ውሃ የተንገረገበ ባቄላ ወይም አተር።
**ሾተላይ** ስ የወንድና የሴት የደም አይነት ቅንጅት ተስማሚ ባለመሆኑ ሽሉ እንደተፀነሰ ወይም ህፃኑ እንደተወለደ እንዲሞት ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት የወሊድ ችግር።
**ሾተሌ** ስ እንደ ጭልፊት ያለ የአሞራ አይነት።
**ሾተል** ስ በሁለት ወገን ስለት ያለው ቀጥ ያለ ቀጭን ሰይፍ።



ሾተል

**ሾተል አፍ** ቅ (ስድብ) ተሳዳቢ፥ ምላሰኛ።
***ሾከከ**
**ሾካካ** ቅ 1. (ስድብ) አሳባቂ፥ ወሬኛ። 2. ጥላ ቢስ፥ ቀላል።
**ተንሿከከ** ግ 1. ጥላ ቢስ ሆነ። 2. አሳበቀ፥ ወሬ አቀበለ።
**አንሿከከ** ግ አሳበቀ፥ ነገር አቀበለ።
**ሾኬ** ስ ሰውን በእግር ጠልፎ የመጣል ዘዴ።
**ሾዬ** "ሸዬ" ን ተመ.
**ሾጠጠ** ግ ከወደ ጫፉ ቀጠነ፥ ሞለለ፥ ሾለ።
**ሾጣጣ** ቅ ቀጭን ወይም ጠባብ፥ ሞላላ፥ ሹል የሆነ።
**አሾጠጠ** ግ ሞላላ፥ ሾጣጣ አደረገ።
**ሾጤ** ቅ ወገበ ቀጭን።
**ሾጤ በርበሬ** ስ ቀጭንና ረዥም የሆነ ቃሪያ፥ በርበሬ።
**ሾጥ**
**ሾጥ አደረገ** ግ በልምጭ፥ በአለንጋ፥...

ሽንቆጠ፥ ገረፈ፥ መታ።

*ሾፈ

**ተሾፈ** ግ ተቀለደ፥ ተዘበተ፥ ተፌዘ።

**አሾፈ** ግ 1. አፌዘ፥ ቀለደ። 2. ናቀ፥ አቃለለ።3. ለገመ፥ ዳተኛ ሆነ (በስራ)።

**አሿፊ** ቅ 1. ቀላጅ፥ ፌዘኛ። 2. በስራ ላይ የሚቀልድ፥ ልግመኛ።

**ሾፌረ** ግ መኪና ነዳ ወይም አሽከረከረ።

**ሾፌር(ሹፌር)** ስ መኪና ነጂ ወይም አሽከርካሪ።

**ሿ** የ "ሽ" ፈደል ፍንዕቅ ዘር።

**ሿሚ** "ሾመ" ስር ተመ.

*ሿሿ

**ሿሿቴ** ስ 1. የገደል ላይ የውሃ ፏፏቴ ድምፅ። 2.የፅንሃህ፥ የፀናፅል፥ የሻኩራ፥ የመረሸት፥ የጉልላት፥... አጫዋች ወይም መርገፍ፥ ቅሰቃሴ የሚፈጠረው ድምፅ።

**ሿ አለ** ግ ተንሿሿ፤ የመፍላት፥ የመፍሰስ ድምፅ ሰጠ።

**ሿ አደረገ** ግ በተነ፤ አስገባ። *ጋዝ ያለበት ውሃ መጠጣት ሆድን ሿ ያደርጋል።*

**ተንሿሿ** ግ 1. ፈሰሰ፥ ገነፈለ። 2. የመፍሰስ፥ የመፍላት ድምፅ አሰማ። 3. ተቅጨለጨለ።

**አንሿሿ** ግ 1. አቅጨለጨለ። 2. የመፍሰስ፥ የመፍላት ድምፅ አሰማ።

# ቀ

**ቀ** ከ "ሸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)፡፡

**ቀለሀ (ቀለሃ)** ስ ጥይቱ ከተተኮሰ በሂላ ወይም በሌላ ምክንያት ያለባሩድና ያለ እርሳስ የሚቀረው ባዶው ቀፎ(ስእሉን ጥይት ስር ተመ.)፡፡

**ቀለሀ ራስ** ቅ (ስድብ) ባዶ፥ የማያስብ፥ የማያመዛዝን (ሰው)፡፡

**ቀለለ** ግ 1. አነሰ፥ ቀነሰ፥ ክብደት አጣ፡፡ 2. ተዋረደ፥ አፈረ፡፡ *ውሸት ተናግሮ በህዝብ ፊት ቀለለ፡፡* 3. የማያስቸግር ሆነ፥ ገራ፡፡ *ፈተናው ቀለለ፡፡* 4. ተሻለ፡፡ *ህመሙ ከትናንት ዛሬ ቀለለው፡፡* 5. ኮሰሰ፥ ዝቅ ብሎ ታየ፡፡

**ቀላል** ቅ 1. ከባድ ያልሆነ፡፡ 2.(ስድብ) ወራዳ፥ ክብሩን የማይጠብቅ፥ ባለጌ፡፡

**በቀላሉ** ተው.ግ. ያለብዙ ችግር፥ ድካም፡፡ *ችግሬን በቀላሉ ተወጣሁት፡፡*

**ቅለ ት** ስ የመቅለል፥ ከባድ ያለመሆን ሁኔታ፡፡

**ቅሌት** ስ ውርደት፣ የሚያሳፍር፥ ነውር ስራ፡፡

**ቅሌታም** ቅ (ስድብ) ወራዳ፥ ነውረኛ፡፡

**ተቃለለ** ግ 1. ቀስ በቀስ ከላዩ እየተነሳለት አነሰ፥ ቀነሰ፡፡ 2. ተጣፋ፥ ተካፈለ፡፡ *2/4ኛ ሲቃለል ½ ይሆናል፡፡* 3. መፍትሄ አገኘ፥ ችግሩ ተወገደ፡፡

**አቃለለ** ግ 1. አዋገደ፥ አገባደደ (ስራን)፡፡ 2. (ሂሳብን)አጣፋ፥ አካፈለ፡፡ 3. መፍትሄ ሰጠ፥ አስወገደ (ችግርን)፡፡ 4. ናቀ፥ አኮሰሰ፥ አዋረደ፡፡

**ቀለመ**[1] ግ ቀለም ያዘ፥ ነካ፥ በቀለም ተነከረ፡፡

**ቀለም** (ብ.ቁ.**ቀለማት**) ስ 1. ከእፀዋት ወይም ከአፈርና ከሌሎችም ልዩ ልዩ ነገሮች በፈሳሽ ወይም በዱቄትና በጭቃ መልክ የሚዘጋጅና ለማቅለሚያ ወይም ለመፃፊያ የሚያገለግል እንደ አረንጓዴ፥ቢጫ፥ ቀይ፥ ሰማያዊ፥ ጥቁር፥...ያለ መልክ ያለው ነገር፡፡ 2. መልክ፡፡ *የሲትሮዋ ቀለም ተበላሽቷል፡፡* 3.አይነት፡፡ *ቀለሙ ነጭ ነው፡፡* 4.(ዘይ.) ትምህርት፡፡ *ቀለም ይገባዋል፡፡*

**ቀለም አገባ** በቀለም ነከረ፡፡

**ቀለም ይይዛል** ትምህርት ይገባዋል፡፡

**ቀለም ገባው** ትምህርት ገባው፡፡

**ቀለም ቀቢ** ስ ስራው የቤት ግድግዳዎችን፥ በርና መስኮቶችን፥... ቀለም መቀባት የሆነ ሙያተኛ፡፡

**ቀለም ቅብ** ስ በሸራ፥ በሰሌዳ፥ በወረቀት፥...ላይ በቀለም የሚሰራ የስእል ጥበብ፡፡

**የቀለም ልዩነት** ስ ነጮች በጥቁሮች ላይ የሚያደርጉት የዘር መድልዎ፡፡

**የቀለም ሰው** ስ 1. የትምህርት ወይም የእውቀት ሰው፥ ሊቅ፥ ምሁር፡፡ 2. ብሩህ አእምሮ ያለው፥ ትምህርት የሚገባው ሰው፡፡

**የቀለም ቀንድ** ስ 1. ቀለም የሚበጠበጥበትና የሚቀመጥበት ከቀንድ የተሰራ የቀለም መያዣ፡፡ 2. (ዘይ.) ምሁር፥ ሊቅ፡፡

**የቀለም ትምህርት** ስ ሙያ ነክ ያልሆነ ትምህርት፡፡

**የቀለም አባት** ስ አስተማሪ፥ መምህር፡፡

**ቀለማም** ቅ ቀለሙ ደማቅ የሆነ፡፡

**አቀለመ** ግ ቀለም አገባ ወይም ቀለም ውስጥ ነከረ፡፡

**ቀለመ**[2] "**ቀለበ**[2]"ን ተመ.

***ቀለመ**

**ቀለም** ስ ቀሰም፥ ቀጭን መቃ፡፡

**ተቀለመ** ግ ተዳወረ፡፡

**አቀለመ** ግ አዳወረ፥ አጠነጠነ፥ በቀሰም ላይ ፈትልን ጠቀለለ፡፡

**አቅላሚ** ስ አዳዋሪ፡፡

**ቀለማም** "**ቀለመ**[1]" ስር ተመ.

**ቀለም**[1] "**ቀለመ**[1]" ስር ተመ.

**ቀለም**[2] "***ቀለመ**" ስር ተመ.

**ቀለሰ** ግ 1. አጎበጠ፥ አስጎነበሰ፡፡ 2. በአሂዶ ጊዜ ቀላሹ በሬ አዞረ፥ አሟረ፣ ሌሎቹ ከብቶች እሱን እየተከተሉ ክብ በመዞር ነዶውን እንዲረግጡ መራ፡፡

**ቀላሽ** ስ አሟሪ፥ ፊት መሪ በሬ (በአሂዶ ጊዜ)፡፡

***ቀለሰለሰ**

**ቅልስልስ(ቀለስላሳ)** ቅ 1.ደካማ፥ ዝልፍልፍ፥ ልፍስፍስ፡፡ 2. አይንአፋር፥ ተሽኮርማሚ፡፡

**ተቅለሰለሰ** ግ 1. ደከመ፥ ተዝለፈለፈ፥ ተልፈሰፈሰ፡፡ 2. እንደማፈር፥ እንደመሽኮርመም አለ፡፡

**አቅለሰለሰ** ግ 1. አደከመ፥ አዝለፈለፈ፥ አልፈሰፈሰ፡፡ 2. በመሽኮርመም፥ በማፈር አይነት ራሱን ዘንበል ቀና አደረገ፡፡

***ቀለሸለሸ**

**ቅልሽልሻ** ስ ማጥወልወል፡፡

**ቅልሽልሽ አለ** ግ 1. አጥወለወለ፥ ልውጣ ልውጣ አለ (ትውከት)፡፡ 2. (ዘይ.) ሰለቸ፥ አንገፈገፈ፡፡

**አቅለሸለሸ** ግ 1. አጥወለወለ፥ ልውጣ ልውጣ አሉ (ትውከት)፡፡ 2. (ዘይ.) ሰለቸ፥ አንገፈገፈ፡፡

***ቀለቀለ**

**ቀልቃላ (ቀለቀል)** ቅ ቀዥቃዣ፥ ከውካዋ፥ ቀውቃዋ።

**ቅልቅል አለ** ግ ተንቀለቀለ፥ ተንቀዠቀዠ፥ ተንከወከወ፥ ተንቀወቀወ።

**ቅልቅል አደረገ** ግ አንቀለቀለ፥ አንቀዠቀዠ፥ አንከወከወ፥ አንቀወቀወ።

**ነቀልቃል** ስ የእሳት ወላፈን፥ ነበልባል።

**ተንቀለቀለ** ግ 1. ተንቀዠቀዠ፥ ተንከወከወ፥ ተንቀወቀወ። 2. ተንበለበለ፥ ተንቦገቦገ፥ በሃይል ነደደ (እሳት)።

**አንቀለቀለ** ግ 1.አንቀዠቀዠ፥ አንከወከወ፥ አንቀወቀወ። 2. አንበለበለ፥ አንቦገቦገ (እሳትን)።

**ቀለቀንጻ (ቃለቀንጻ)** (ስድብ) ቅ 1. አፈኛ፥ ነገረኛ፥ ለፍላፊ። 2. አሳባቂ።

**ቀለበ**[1] ግ 1. አዘውትሮ ምግብንና መጠጥን እያዘጋጁ ለተቀላቢ መገበ፥ አበላ። 2. እየመገበ አወፈረ፥ አደለበ (ሙክትን፥ ሰንጋን፥...)።

**ቀለብ** ስ 1. በየጊዜው እየተዘጋጀ ለተጠቃሚው የሚቀርብ ምግብና መጠጥ። 2. ለተወሰነ ጊዜ የሚበቃ እህል፥ የምግብ ፍጆታ። 3. በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ፤ ደመወዝ።

**ቀለብ ሰፈረ** ቀለብ ሰጠ (በወር፥ በአመት፥...)።

**ቀለብተኛ** ስ 1. ከአንድ ግለሰብ፥... ዘንድ ምግብን፥ መጠጥን፥ ....እያገኘ የሚኖር ጥገኛ፥ ተረጅ፥ በላተኛ ሰው። 2. ስ ከአንድ ግለሰብ፥ ቤተሰብ፥...ጋር ባለው የስራ ወይም የሌላ ነገር ግንኙነት ምክንያት በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ፥ እህል፥... የሚሰጠው ወይም የሚከፈለው ደመወዝተኛ።

**ቀላቢ** ስ ምግብና መጠጥን እያዘጋጀ ገንዘብ በማስከፈል ወይም በነፃ በቋሚነት ተቀላቢውን የሚያበላና፥ የሚያጠጣ።

**ቅልብ** ቅ ወፍራም፥ ድልብ።

**ተቀለበ** ግ በተወሰነ ቦታ በቋሚነት ተመገበ፥ በላ። 2. በሚገባ እንዲመገብ ተደረገ፥ ወፈረ፥ ደለበ።

**ተቀላቢ** ስ በአንድ በተወሰነ ቦታ በቋሚነት የሚበላ ተመጋቢ፥ የምግብ ደንበኛ።

**ቀለበ**[2] **(ቀለመ)** ግ የተወረወረን ነገር ምድር ሳይነካ ያዘ፥ በእጁ አደረገ።

**ቅልቦሽ (ቅልሞሽ)** ስ ልቅሞሽ።

**ቅልልቦሽ (ቅልልሞሽ)** ስ ልጆች ኳስን ምድር ላይ እያነጠሩ በመቅለብ የሚጫወቱት ጨዋታ።

***ቀለበለበ**

**ቅልብልብ(ቀለብላባ)** ቅ 1. ችኩል፥ ከላባ፥ ከልብልብ። 2. ምላሰኛ።

**ቅልብልብ አለ** ግ ተቅለበለበ።

**ተቅለበለበ** ግ ቸኮለ፥ ተከለበለበ፥ ተጣደፈ። 2. አፈቸለ፥ ቀባጠረ።

**አቅለበለበ** ግ 1. አስገበገበ፥ አስቸኮለ፥ አከለበለበ፥ አጣደፈ።2. አስቀባጠረ፥ አናገረ።

**ቀለበሰ** ግ 1. ወደ ውስጥ ወይም ወደ ውጪ አጠፈ፥ ገለበጠ፥ ቀነፈ (የጨርቅንና የመሳሰለውን ጫፍ)። 2. ወደ ሗላ መለሰ። *ኳሷን ቀልብሶ መታ።*

**ቀልባሽ** ቅ አድሃሪ፥ ጎታች፥ አደናቃፊ።

**ቅልበሳ** ስ የአንድን አዲስ ስርአተ ማህበር እርምጃ ለማጨናገፍ የሚደረግ እንቅስቃሴ።

**ቅልብሳት** ስ እጥፋት፥ ቅንፋት።

**ተቀለበሰ** ግ ወደሗላ ተመለሰ።

***ቀለበሰ**

**ተንቀላበሰ** ግ አልብሱኝ፥ አንተርሱኝ፥ አንሱኝ ደግፉኝ አለ (በድሎት፥ በመቀማጠል ወይም በህመም ምክንያት)።

**አንቀላበሰ** ግ ተንከባከበ፥ በጥንቃቄ ያዘ።

**ቀለበት** ስ 1. ከብር ወይም ከወርቅ ወይም ከነሃስ፥...የሚሰራ ክብና ክፍት የሆነ የጣት ጌጥ። 2. ማንኛውም ዙሪያ ክብነት ያለው ውስጠ ክፍት ነገር። 3. የጋብቻ ውል መፈራረሚያ ቀን፤ ፍጥምጥም።

**ቀለበት አሰረ** 1. የጋብቻ ቃልኪዳን ምልክት የሆነውን ቀለበት አደረገ። 2. የጋብቻ ውል ተፈራረመ።

**ቀለበት አደረገ** ቀለበት አሰረ።

**ቀለበት ውስጥ ገባ** በማያመልጥበት፥ መፈናፈኛ በማያገኝበት ሁኔታ ውስጥ ገባ።

**የቀለበት ጣት** ስ በትንሽ ጣትና በመሃል ጣት መካከል የሚገኝ (የቃል ኪዳን ወይም የጋብቻ ቀለበት የሚደረግበት) የግራ እጅ ጣት።

***ቀለበጨ**

**ቀልባጫ** ቅ 1. እጥር ምጥን ያለ። 2. ቀልጣፋ።

**ቅልብጭ (ቀልበጭ) ያለ** ዝ.ከ.

**ቀለብ** "ቀለበ[1]" ስር ተመ.

**ቀለብላባ** "*ቀለበለበ" ስር "ቅልብልብ" ን ተመ.

**ቀለብተኛ** "ቀለበ[1]"ስር ተመ.

**ቀለተ** ግ ረዳ፥ አገዘ፥ ረጠበ (ለተቸገረ፥ ንብረት ለጠፋበት፥ እዳ ለገባ፥...)።

**ቀለታ(ቀለት)** ስ እርጥባን፥ እርዳታ።

**ቀለንጅ (ቀሌንጅ)** ስ መጠኑ ትንሽ የሆነ የገዘፍ ጥርስ::

***ቀለወ**

**ቀላዋ** ቅ ከላባ፥ ከላፋ፥ ቀዥቃዣ::

**ቀለው ቀለው አለ** ግ ተንቀዠቀዠ::

**ቀለዋ (ቀላዎ)** ስ ፍሬው የእከክ መድሃኒት ነው የሚባል መጠኑ አነስተኛ የሆነ የዛፍ አይነት::

**ቀለደ** ግ 1. አባለተ፥ ተረበ፥ ዋዛ ፈዛዛ ተናገረ:: 2. አላገጠ፥ አሾፈ፥ አፌዘ:: *በስራ ይቀልዳል::*

**ቀላጅ** ቅ 1. አባላች፥ ተራቢ:: 2. አላጋጭ፥ አሿፊ:: 3. ተጫዋች፥ ጨዋተኛ::

**ቀልድ** ስ 1. ባልት፥ ተረብ፥ ፌዝ፥ ጨዋታ:: 2. ውሸት፥ የምር ያልሆነ ነገር::

**የቀልድ** የእውነት፥ የምር ያልሆነ::

**ቀልደኛ** ቅ 1. ባልተኛ፥ ተረበኛ፥ ፌዘኛ፥ ተጫዋች:: 2. አላጋጭ፥ አሿፊ::

**ተቀለደ** ግ ተላገጠ፥ ተሾፈ፥ ተፌዘ::

**ተቀላለደ** ግ በቀልድ ተጨዋወተ::

**ተቃለደ** ዝ.ከ.

**ተቃላጅ** ቅ ቀልደኛ፥ ተጫዋች::

**አቃለደ** ግ አዋዛ፥ አጫወተ:: *እያቃለደ ስራዬን አዘናጋኝ::*

**ቀለጠ** ግ 1. ሟሟ፥ ወደ ፈሳሽነት ተለወጠ (ከሙቀት የተነሳ):: 2. ደራ፥ ደመቀ፥ ሞቀ (ዘፈኑ፥ እልልታው፥...):: 3. ተሸበረ፥ ተደበላለቀ (እሪታ፥ ጩሀት፥ ኡኡታ፥...):: 4.(ዘይ.) ሀ.ጠፋ:: *ገንዘቤ ቀለጠ::* ለ.ከሰረ:: 5. ተመታ፥ ተደበደበ:: *ሌባው በጥፊ ቀለጠ::* 6.ወፈረ፥ ደነደነ፥ ሰባ፥ ጮማ ሆነ:: *ሙክቱ ቀለጠ::* 7.ተናደ፥ ፈረሰ፥ ወደቀ:: *ዝናብ ስለበዛበት ኮረብታው ቀለጠ::* 8. ከህመም፥ ከከባድ ስራ፥... የተነሳ ደከመ፥ ተዝለፈለፈ:: 9 . ተሞላቀቀ:: *ልጅህ ቀልጧልና ስነስርአት አስተምረው::*

**ቀለጤ** ቅ ቅብጠት የሚያበዛ፥ ሞልቃቃ (ለልጅ)::

**ቅልጣን** ስ 1. ምቾት፥ ድሎት:: 2. ቅብጠት፥ መሞላቀቅ::

**ቅልጥልጥ** ቅ ወዛም፥ ስብነት ያለው::

**ቅልጥ አለ** ግ 1. ሄዶ ቀረ፥ ጥፍት አለ:: 2. ቀለጠ::

**ቅልጥ ያለ** 1. በጣም የደመቀ:: *ቅልጥ ያለ ከተማ::* 2. በጣም የሰባ:: *ቅልጥ ያለ ሰንጋ::* 3. በጣም የተሞላቀቀ:: *ቅልጥ ያለ ልጅ::*

**ተቃለጠ** ግ ተማታ፥ ተደባደበ (እርስ በእርስ):: *ጎረምሶች በዱላ ተቃለጡ::*

**ተቅለጠለጠ** ግ 1. ወዛ፥ ቅባት የተቀባ መሰለ:: 2. ሰባ፥ ጮማ ሆነ::

**አቃለጠ** ግ 1. አዳመቀ:: 2. አጫረሰ (ሃብትን አብሮ በማባከን)::

**አቃልጣ** ቅ ወሬ አዳማቂ::

**አቅልጥ (አቅላጭ)** ቅ አክሳሪ::

**አቅለጠለጠ** ግ አወዛ፥ ቅባት የተቀባ አስመሰለ::

**አቅለጥልጥ** ቅ አቃልጣ::

**ቀለጠመ** ግ መታ፥ ሰበረ፥ አነከተ (ለምሳሌ እጅን፥ እግርን)::

**ቀልጣማ** ቅ በቀላሉ የሚሰበር፥ አቅመ ቢስ::

**ቅልጥም** ስ 1. ከጉልበቷ እስከ ጫማ ያለው የእግር ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.):: 2. በሁለት አንጓዎች መካከል የሚገኝ፥ በውስጡ ቅባት ወይም መቅኒ የሚይዝ፥ መለል ያለ ውስጠ ክፍት አጥንት:: 3. በሁለት አንጓዎች መካከል የሚገኝ መለል ያለ አካል:: *የሸንኮራ አገዳ ቅልጥም::* 4. ከቅልጥም አጥንት ውስጥ የሚገኝ ቅባት፥ መቅን ወይም መቅኒ::

**ቅልጥሙ ፈሰሰ** ዛለ፥ ደከመ፥ ተብረከረከ::

**ቅልጥም አለ** ግ እንክት አለ፥ ተሰበረ::

**ቅልጥም አወጣ** 1. አደገ፥ በረታ፥ ጎለበተ:: 2. አደገ፥ አንጓ ለየ፥ አበጀ (የአገዳ እህል)::

**ቅልጥማም** ቅ ረዣዥም ቅልጥም ያለው::

**ቀለጣጠመ** ግ ሰባበረ::

**ተቀለጠመ** ግ ተሰበረ::

**ተቀለጣጠመ** ግ ተሰባበረ::

***ቀለጠጠ**

**ቀልጣጣ (ቀለጠጥ)** ቅ 1. ግልጥ ወይም ከለላ አልባ የሆነ (ቦታ):: 2. በልጣጣ፥ አይኑ የሚንቀዠቀዥ፥ ሃፍረተ ቢስ::

**ቅልጥጥ** ዝ.ከ.

**ቅልጥጥ አለ** ግ 1. ግልጥ አለ፥ ወለል ብሎ ታየ፥ ከለላ አልባ ሆነ:: 2. ተንበላጠጠ፥ አይኑ ተንቀዠቀዠ::

**ቅልጥጥ አደረገ** ግ ገለጠጠ፤ ወለል፥ ግልጥ አድርጎ አሳየ::

**ተንቀለጠጠ** ግ 1. ተከፈተ፥ ተገለጠ፥ ወለል ብሎ ታየ:: 2. ሃፍረተ ቢስ ሆነ:: 3. ተንገለጠጠ፥ ተንተረከከ፥ ጋመ (ፍም)::

**ቀለጠፈ** ግ 1.በፍጥነት፥ በቶሉ ተከናወነ፥ ተደረገ፥ ተሰራ:: 2. ፈጠነ::

**ቀልጣፋ** ቅ አንድን ነገር በፍጥነት መስራት የሚችል፤ ፈጣን::

**ቅልጥፍና** ስ በፍጥነት የመስራት ችሎታ፤ ፍጥነት::

**ቅልጥፍጥፍ ያለ** ዝርክርክ ያልሆነ፥ ጥንቅቅ

ስብስብ ያለ።

**ተቀላጠፈ** ግ 1. በፍጥነት ተከናወነ። 2. በፍጥነት አከናወነ።

**ተቀለጣጠፈ** ዝ.ከ.

**አቀላጠፈ** ግ በፍጥነት አከናወነ፥ ቶሎ ፈፀመ፥ ሰራ።

**አቀላጥፎ ይናገራል** በደንብ፥ በትክክል ይናገራል። *አማርኛ አቀላጥፎ ይናገራል።*

**ቀለጤ** "ቀለጠ" ስር ተመ.

**ቀላ[1]** ግ 1. ቀይ ሆነ። 2. በሰለ፥ ጎመራ (ለፍራፍሬ)።

**ቀያቴ** ቅ ቀይነት ያለው (ለአፈር)።

**ቀይ**(ብ.ቁ.**ቀያይ**) ቅ 1.ግምጃ፥ በርበሬ፥ ደም የሚመስል። ስ 2. ከጠይም ፈካ የሚል የሰው መልክ። 3. በርበሬ፥ ደም፥...የሚመስል ቀለም።

**ቀይ መስቀል** ስ የጦርነት ወይም የተፈጥሮ አደጋ ባጋጠመበት ቦታ ፈጥኖ እየተገኘ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ አስፈላጊውን ሰብአዊ እርዳታ የሚያደርግ አለማቀፋዊ የእርዳታ ድርጅት።

**ቀይ ስር** ስ ደም የሚመስል ቀለም ያለውና ስሩ እንደድንች ያለ የሚበላ ተክል።



ቀይ ስር

**ቀይ ሽብር** ስ በሶሻሊስት ስርአተ ማህበር ውስጥ የስርአቱ አራማጆች፥ ፀረ አብዮተኞች ናቸው በሚሏቸው ላይ የሚያካሂዱት የግድያ ተግባር።

**ቀይ ሽንኩርት** ስ ቅርፁ ክብ ሆኖ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚያድግ፥ የተነባበረ ልጣጭ ያለው፥ ለምግብ ማጣፈጫነት የሚያገለግል ተክል።

**ቀይ አፈር** ስ ቀይነት ያለው አፈር፥ ቦረቦር።

**ቀይ ወጥ** ስ በርበሬ የገባበት ወጥ።

**ቀይ ዳማ** ስ ቀለሙ በጠይምና በቀይ መካከል የሆነ የሰው መልክ።

**የቀይ ጥቁር ሆነ** ቀይ የነበረው በጉስቁልና ምክንያት ጠቆረ።

**የቀይ ጥቁር ነው** መልኩ እንደ መልአክ ቀይ ቢሆንም ክፉ፥ ተንኮለኛ ነው።

**ቅላት** ስ ቀይነት፥ ግምጃ መልክ።

**ቀላ[2]** ግ መታ፥ ለጋ (እሩርን፥ ጥንግን፥ ኳስን፥...)።

**ቅሌ** ስ እሩር፤ ጥንግ።

**ቀላ[3]** ግ ቆረጠ። *አንገቱን በጎራዴ ቀላው።*

**ቀላል** "ቀለለ" ስር ተመ.

**ቀላመደ** ግ ዘላበደ፥ ቀሳፈተ፥ ዘባረቀ፥ የሆነ ያልሆነውን ቀባጠረ፥ ውሸትና እውነትን ቀላቅሎ ተናገረ።

**ቀልማዳ(ቀላማጅ)** ቅ 1. ዋሾ፥ ወሸካታ፥ ቀሳፊች። 2. ዘባራቂ፥ ዘላባጅ።

**አስቀላመደ (አቀላመደ)** ግ 1. አስዋሸ፥ አስቀሳፈተ፥ አስቀባጠረ። *ምን ያስቀላምድሃል።* 2. አስዘላበደ፥ የሆነ ያልሆነውን አስቀባጠረ።

**ቀላሸ** "ቀለሰ" ስር ተመ.

**ቀላቀለ** ግ 1. ቀየጠ፥ ዘነቀ። 2. አገናኘ፥ ደባለቀ።

**ቅልቅል** ቅ 1.ድብልቅ፥ ቅይጥ። ስ 2. አልኮለነት ያለው የመጠጥ አይነት። 3. የወንዱና የሴቷ ሙሽራ ቤተሰቦች ሙሽራው ቤት በአንድነት ተገናኝተው ራት የሚጋበዙበትና የሚተዋወቁበት ቀን።

**ተቀላቀለ** ግ 1. ተደባለቀ፥ ተቀያየጠ። 2.ገባ፥ አብሮ ሆነ፥ ተደባለቀ።

**አቀላቀለ** ግ 1. አገናኘ (ዘመድ ከዘመድ)። 2. (ነውር) ዘመዳሞችን በወሲብ ተገናኘ።

**ቀላቢ** "ቀለበ[1]" ስር ተመ.

**ቀላባ** ቅ ከላባ፥ ቀለብላባ።

**ቀላወጠ** ግ 1. ሳይጠራ፥ ሳይጋበዝ፥ ሳይፈለግ በየቤቱ እየሄደ በላ፥ ጠጣ። 2. ለመነ፥ ቀፈፈ፥ ቧገተ። 3. ከጀለ፥ ፈለገ፥ ሻ፥ ጓጓ። *አይቶ ቀላወጠ።*

**ቀላዋጭ** ስ ሳይጠሩት፥ ሳይጋብዙት፥ ሳይፈልጉት በየቤቱ እየዞረ የሚበላ፥ የሚጠጣ።

**ቅልውጥ** ስ 1.ባልተጋበዙበት፥ ባልተፈለጉበት ቦታ እየተገኙ የመብላትና የመጠጣት ድርጊት። 2. ልመና፥ ቀፈፋ።

**አቀላወጠ** ግ ለቀላዋጭ ሰጠ፥ አበላ።

**ቀላዋ** "*ቀለወ" ስር ተመ.

**ቀላዎ** "ቀላዋ" ን ተመ.

**ቀላይ** (ብ.ቁ..**ቀላያት**) ስ ጥልቅና ሰፊ የሆነ ባህር፤ ውቅያኖስ።

**ቀላድ** ስ 1. ርዝመቱ 150 ክንድ ሆኖ ከቃጫ ወይም ከእንሰት ወይም ከጭረት፥... የተሰራ ገመድ፥ ወደሮ። 2. በቀላድ የተለካ፥ የተሰፈረ መሬት።

**ቀላድ ወደቀ/ተጣለ** በቀላድ ተለካ፥ ተሰፈረ

(መሬት፥ እርስት)።

**ቀላድ ጣለ** 1. መሬትን በቀላድ ለካ፥ ሰፈረ። 2. በቀላድ እየለካ ሰጠ(መሬትን)።

**ቀላድ ጣይ** ስ መሬትን በቀላድ እየለካ ለታዘዘለት ሰው ይሰጥ የነበረ የመንግስት ሰራተኛ።

**ቀላጅ** "ቀለደ" ስር ተመ.

**ቀላጤ (ቃለአጤ)** ስ 1. አቤት ባይ ወይም ተበዳይ ከበላይ አካል የሚያመጣው የውሳኔ ማገኛ ወይም ማፍረሻ ትእዛዝ። 2. የንጉስን ወይም የባለስልጣንን ትእዛዝ በቃል ተቀብሎ በቃል ለሚመለከተው ወገን ያደርስ የነበረ መልእክተኛ።

**ቀላጥም** ስ የቃሬዛ፥ የመሰላል፥...አግዳሚ እንጨት።

**ቀላጥቤ** "ቅላጥቤ" ን ተመ.

**ቀሌንጅ** "ቀለንጅ" ን ተመ.

**ቀልማዳ** "ቀላመደ" ስር ተመ.

**ቀልቀሎ** ስ ስልቻ።

**ቀልቃላ** "*ቀለቀለ" ስር ተመ.

**ቀልበቢስ** "ቀልብ" ስር ተመ.

**ቀልባሽ** "ቀለበሰ" ስር ተመ.

**ቀልባጫ** "ቀለበጨ" ስር ተመ.

**ቀልቤ** ስ ከሽፋል በላይ በግንባር ዙሪያ በቀጭን ታስሮ ጫፍና ጫፉ በማጅራት በኩል የሚወርድ ሻሽ።

**ቀልብ** ስ ማስተዋል፥ ማስታወስ የሚያስችል አእምሮ፥ ልብ።

**ቀልቡ ጠፋ** 1. ረሳ፥ ዘነጋ (አንድን ነገር ማድረግ፥ መፈፀም፥..ን፡ 2. ማስተዋል ተሳነው፤ ልቡ ጠፋ።

**ቀልብ ገዛ** አስተዋይ ሆነ፥ ጨመተ።

**ቀልበ ቢስ** ቅ 1. ልበ ቢስ፥ ዝንጉ፥ ቶሎ የሚረሳ። 2. ጥላ ቢስ፥ ከውካዋ።

**ቀልበ ደረቅ** ለዛ ቢስ።

**ቀልደኛ** "ቀለደ" ስር ተመ.

**ቀልድ** ዝ.ከ.

**ቀልጣማ** "ቀለጠመ" ስር ተመ.

**ቀልጣጣ** "*ቀለጠጠ" ስር ተመ.

**ቀልጣፋ** "ቀለጠፈ" ስር ተመ.

**ቀመለ** ግ 1. ቅማልን ለቀመ፥ አነሳ፥ ገደለ። 2. ቅማል፥ አፈራ።

**ቅማል** ስ በሰው ልብስና በፀጉር ንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚፈጠርና ደም እየመጠጠ የሚኖር ጥቁር ወይም ነጭ ተባይ።



ቅማል

**ቅማላም** ቅ 1. (ስድብ) ዘወትር ቅማል የማይለየው። 2- (ዘይ.ስድብ) ምንም ሃብት የሌለው፥ ችግረኛ። *ቅማላም ድሃ።*

**ቀመመ** ግ ልዩ ልዩ ነገሮችን መጥኖ በመደባለቅና በማዋሃድ እንደመድሃኒት፥ መርዝ፥ ቅመም፥...ያሉትን አዘጋጀ።

**ቀማሚ** ቅ 1. መድሃኒትን፥ መርዝን፥ ቅመምን፥...የሚያዘጋጅ። 2. የቅመማ ተግባር ባለሙያ።

**ቅመማ** ስ ቅመም የማዘጋጀት ተግባር።

**ቅመም** ስ 1. ከተለያዩ ተክሎች ፍሬፍሬ ወይም ስራስር ወይም ቅርፊት፥... የሚዘጋጅና ለምግብ ማጣፈጫነት የሚያገለግል እንደ ነጭና ጥቁር አዝሙድ፥ ጅንጅብል፥ ሽንኩርት፥ ቀረፋ ያለ ነገር። 2. አንድን ነገር ለመስራት አስፈላጊ የሆነ ንጥረ ነገር። *መድሃኒቱን ለመስራት አስፈላጊ የሆኑት ቅመሞች ተዘጋጅተዋል።* 3. (ዘይ.) ባለሙያ። *ልጅቷ ቅመም ናት።*

**ቅመማ ቅመም** ስ የተለያዩ የቅመም አይነቶች።

**ቅምም** ቅ በቅመም የተዘጋጀ፥ የተከሸነ፤ የተቀመመ።

**ቀመረ** ግ 1. ቆጠረ። 2. አዘጋጀ፥ አከናወነ።

**ቀመር** ስ ቁጥር፥ ስሌት።

**ቀመር**[1] ስ ፍሬው ትንንሽ የሆነ አደንጓሬ።

**ቀመር**[2] ስ ዋልታ፤ የባጥ ገበታ።

**ቀመር**[3] "ቀመረ" ስር ተመ.

**ቀመሰ** ግ 1. በጥቂቱ በላ፥ ጠጣ፥ ለከፈ። 2. ጣእሙን ለማወቅ በጥቂቱ ጎረሰ፥ ፉት አለ፥ ላሰ። 3. አየ፥ ተቀበለ (ችግርን፥ መከራን፥...)። 4. (ዘይ.) ሀ-ከዚህ በፊት ተገናኝቷት የማያውቃትን ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ በግብረ ስጋ ተገናኘ። ለ-ተመታ፥ ተደበደበ። *ዱላ ቀመሰ።*

**-ቀመስ** -ነክ፥ በትንሹ ያለበት ወይም ከ-ጋር ግንኙነት ያለው። *ታሪክ ቀመስ/ አሸዋ ቀመስ/ ከተማ ቀመስ።*

**ቀማሽ** ቅ በቤተ መንግስት ይደረግ በነበረ ግብዣ ላይ፥ የተዘጋጀው ምግብ ለንጉሱ ወይም ለተጋባዡ ከመቅረቡ በፊት ምግቡና መጠጡ ደረጃውን የጠበቀና ተስማሚ መሆኑን በመቅመስ ይቆጣጠር የነበረ ባለሟል።

**ቅምሻ** ስ አነስተኛ ምግብ ወይም መጠጥ፤ ለመቅመስ ያህል የቀረበ።

**ተቀማመሰ** ግ 1. በጥቂቱ ተከፋፈለ፥ ተጻረሰ። 2. ተደባደበ፥ ተማታ (አንዱ ከሌላው ጋር)።

**ተቃመሰ** ግ ተቀማመሰ።

**አቀመሰ** ግ 1. መታ። 2. አዋጠ፥ አበላ፥

አጠጣ፥ (መድሃኒትን)፡፡3. በትንሹ አበላ፥ አጠጣ፥...፡፡

**አያቀምስም (አያስቀምስም)** ምንም አይሰጥም፡፡

**አቀማመሰ** ግ ለዚህም ለዚያም በትንሽ በትንሹ አቀመሰ፥ አዳረሰ (ለምሳሌ ምግብን)፡፡

**አቃመሰ** ዝ.ከ.

**አላስቀምስ አለ** ከለከለ፤ አልሰጥ፥ አላስነካ አለ፡፡

**አይቀመስም** አይደፈርም፥ አይበገርም፥ አይነካም፡፡

**ቀመቀመ**[1] ግ 1. የልብስን ጠርዝ በትንሹ አጥፎ ወይም ሌላ ማሬኛ ክፈፍ አስገብቶ ዳር ዳሩን ሰፋ፤ ዘመዘመ፡፡ 2. የልብስ ቁልፍ ማስገቢያ ቀዳዳዎችን ዙሪያ በክር ዘመዘመ፡፡

**ቅምቅማት** ስ የልብስ ጠርዝ፤ ዝምዝማት፡፡

**ቀመቀመ**[2] ግ በትንሹ ወጣ፥ በቀለ፥ ብቅ ብቅ አለ፡፡

**ቀምቀሞ** ስ በትንሹ የወጣ፥ የበቀለ፥ ብቅ ብቅ ያለ ጠጉር፡፡

**አቀመቀመ** ግ ፀጉር አወጣ፥ አበቀለ፡፡

**ቀመቀመ**[3] ግ ብዙ ጠጣ (የሚያስክር መጠጥ)፡፡

**ቀምቃሚ** ቅ አዘውትሮ የሚጠጣ፤ ጠጪ፡፡

**ቀመቀመ**[4] ግ ፀጉርን ፥ ተክልን፥...አስተካከለ፥ ቆረጠ፡፡

**ቀምቃሚ** ስ ፀጉር አስተካካይ፡፡

***ቀመቀመ**

**ተቀማቀመ** ግ ህፃኑ ልጅ ወይም ገመምተኛው ምግብ ለመብላት ሞከረ፥ ጣረ፡፡

**አቀማቀመ** ግ ምግብ መብላት እንዲለምድ ገፋፋ፥ ረዳ (ህፃንን፥ በሽተኛን)፡፡

***ቀመደመደ**

**ቀመድማዳ (ቅምድምድ)** ቅ ሽምድምድ፥ ዝልፍልፍ፥ አቅመቢስ፥ ጥምልምል፡፡

**ተቅመደመደ** ግ አቅም አጣ፥ ተዝለፈለፈ፥ ተሽመደመደ፡፡

**አቅመደመደ** ግ አሽመደመደ፥ አዝለፈለፈ፥ አጥመለመለ፥ አቅም አሳጣ፡፡

***ቀመጠ**

**ቅሟጭ** ስ ተቅማጥ፡፡

**ቅማጫም** ቅ (ስድብ፥ ነውር) ተቅማጣም፡፡

**ቅምጥ** ቅ 1. የተቀመጠ፥ ቁጭ ያለ ወይም የተደረገ፡፡ ስ 2. ቁጭታ፥ በቁም ያልሆነ፡፡ *ከቅምጥህ ሳትነሳ አቀብለኝ፡፡* 3. በአንድ ሰው ተወስና በውሽምነት የተቀመጠች ሴት፤ እቁባት፡፡

**ቅምጠሽ (ቅምምጠሽ)** ስ ልጆች አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እየተቀመጡ፥ ኳስ እየወረወሩና እያነጡ በመቅለብ የሚጫወቱት ጨዋታ፡፡

**ተቀመጠ** ግ 1. ቁጭ አለ፡፡ 2. ቁጭ ተደረገ፡፡ 3. ቆየ፥ ሰነበተ፥ ኖረ፡፡ *አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተቀመጠ*፡፡ 4. ከበቅሎ፥ ከፈረስ፥ ጀርባ ላይ ቁጭ አለ፡፡ 5. አይነምድርን ተፀዳዳ፡፡

**ተቀማጭ** ቅ 1. ቁጭ ያለ ወይም የሚል፥ የተቀመጠ፡፡ *ተቀማጭ ስልፈኛ*፡፡ 2. ነዋሪ፡፡ 3. ለልዩ ልዩ ጉዳዮች መጠባበቂያ እንዲሆን የሚጠራቀም ወይም የተቀመጠ (ገንዘብ)፡፡

**መቀመጫ** ስ 1. ቁጭ የሚባልበት፥ ማረፊያ (ወንበር፥ በርጩማ፥ መደብ፥ ድንጋይ፥...)፡፡ 2. መኖሪያ (ቤት፥ አገር፥ ቦታ፥...)፡፡ 3. ቂጥ፡፡

**ተቅማጥ** ስ 1. የሚያስቀምጥ፥ የሚያስቀዝን በሽታ፡፡ 2. ቀጭን አይነ ምድር፤ ቅዘን፡፡

**ተቅማጥ ነዳው** (ነውር) በብዛት አስቀዘነው፥ አስቀመጠው፡፡

**ተቅማጣም** ቅ (ስድብ፥ ዘይ.) ፈሪ፡፡

**አቀማመጥ** ስ 1. አደራደር፥ ቦታ አያያዝ፡፡ *የእቃዎቹ አቀማመጥ አልተስተካከለም*፡፡ 2. አኗኗር፡፡ *ከዚህ አገር አቀማመጥህ እንዴት ነው?* 3. የተፈጥሮ ሁኔታ (የመሬት፥ የአገር፥ የከተማ፥...)፡፡ *የቦታው አቀማመጥ ለእርሻ አይሆንም፡፡*

**አስቀመጠ** ግ 1. ቁጭ አድርጎ፥ ይዞ፥ ጠብቆ አቆየ፥ አኖረ (እቃን)፡፡ 2. ቁጭ አደረገ፡፡ 3. ቁጭ አሰኘ፥ ቁጭ እንዲል አደረገ፡፡ 4. አኖረ፥ መኖሪያ ሰጠ (ለሰው)፡፡ *ወንድሜ ከቤቱ አስቀምጦኝ ነበር፡፡* 5.መቀመጫ ቦታ ሰጠ፡፡ *እንግዳውን አስቀምጡት፡፡* 6. ቦታው በቂ ሆነ (ለሚቀመጠው ነገር)፡፡ *ይሄ ቦታ ቁምሳጥኑን ሊያስቀምጠው ይችላል፡፡* 7. አጠራቀመ፥ ተቀማጭ አደረገ(ገንዘብን)፡፡ 8. እቁባት ያዘ፥ አኖረ፡፡9. አስቀዘነ (መድሃኒቱ፥ በሽታው፥...)፡፡

**አላስቀምጥ አለው** አስቸገረው፥ ነተነተው፥ ፋታ ነሳው፡፡

**ቀመጠለ** ግ 1. ጎመደ፥ ጎረደ፥ ቀነጠሰ፥ ቆረጠ፡፡ 2. ገመደለ፥ ቆረሰ፥ ከፈለ፡፡ 3. አሳነሰ፥ አጎደለ፥ ከተገመተው በታች ዝቅ አደረገ፡፡

**ቅምጥል አለ** ግ 1. የታሰበውን ያህል ሳይሆን ቀረ፥ በረከት አጣ፡፡ *ምርቱ ቅምጥል አለ፡፡*

**ተቀመጠለ** ግ አነሰ፥ ጎደለ፥ ከተገመተው በታች ዝቅ አለ፡፡ 2. ተጎመደ፥ ተቀነጠሰ፥ ተቆረሰ፡፡

**ተቀመጣጠለ** ግ ተቆራረሰ፡፡

**ቀመጠል** "*ቀማጠለ" ስር "ቅምጥል" ን ተመ.

**ቀሚስ** ስ 1. ቁመቱ እስከተረከዝ ሊደርስ የሚችል፥ የአንገትና የእጅ ማስገቢያ ያለው

ወይም ልቅ የሴቶች ልብስ። 2. ርዝመቱ እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ፥ ጎኑ ሰፊ የሆነ፥ በእጀጠባብ ቅርፅ የተዘጋጀ የካህናት ልብስ። 3. ፈረስና በቅሎ ከተጫኑ በሂላ ኮርቻውንና አካላቸውን በረዥሙ የሚሸፍን የወግ ልብስ። 4. የመሶብ ልብስ፣ መሸፈኛ። 5. በቀድሞ ጊዜ ባለስልጣን የሆኑ የቤተመንግስት ሰዎች የሚለብሱት የእጀጠባብ ቅርፅ ያለው የማእረግ ልብስ። 6. በቅዳሴ ጊዜ ከሌሎች ዲያቆናት ይልቅ ዋናውን የመሪነት ቦታ ይዞ የሚቀድሰው ዲያቆን (ገባሬ ሰናይ ዲያቆን)።

**ቀማ** ግ 1. በሃይል ወይም በጉልበት ወሰደ። 2. ነጠቀ፥ መነጨቀ (አንድን ነገር ከእጅ ላይ)። 3. ዘረፈ፥ ገፈፈ (ሃብትን፥ ንብረትን)።

**ቀማኛ** ስ ነጣቂ፥ ዘራፊ፥ ወንበዴ።

**ቅሚያ** ስ ዝርፊያ፥ ንጥቂያ፥ የውንብድና ተግባር።

**ተቃማ** ግ ተሻማ፥ ተናጠቀ።

**አቃማ** ግ አሻማ።

**አስቀማ** ግ በጥንቃቄ ጉድለት፥ በንዝህላልነት አስወሰደ፥ አስነጠቀ።

**ቀማሚ** **"ቀመመ"** ስር ተመ.

**ቀማሽ** **"ቀመሰ"** ስር ተመ.

**ቀማኛ** **"ቀማ"** ስር ተመ.

***ቀማጠለ**

**ቅምጥል(ቀምጣላ፥ ቀመጠል)** ቅ 1. በድሎት፥ በምቾት፥ በእንክብካቤ የሚኖር። 2. ቀብራራ።

**ተቀማጠለ** ግ 1. በድሎት፥ በምቾት ተያዘ፥ በእንክብካቤ ኖረ። 2. ተሞላቀቀ፥ ተንቀባረረ።

**አቀማጠለ** ግ 1. በድሎት፥ በምቾት ያዘ፥ ተንከባከበ። 2. አሞላቀቀ፥ አንቀባረረ።

**ቀምቀሞ** **"ቀመቀመ[2]"** ስር ተመ.

**ቀምቃሚ[1]** **"ቀመቀመ[3]"** ስር ተመ.

**ቀምቃሚ[2]** **"ቀመቀመ[4]"** ስር ተመ.

**ቀምበር** **"ቀንበር"** ን ተመ.

**ቀምበጥ** **"ቀንበጥ"** ን ተመ.

**ቀረ** ግ 1. የመጣ ተቃራኒ፣ አልመጣም ለማለት ሲፈለግ የሚነገር። *ይመጣል የተባለው ሰው ቀረ።* 2. የሄደ ተቃራኒ፣ አልሄደም ለማለት ሲፈለግ የሚነገር። *ይሄዳል የተባለው ሰው ቀረ።* 3. ቆመ፥ ታገደ፥ ተሰረዘ፥ ተተወ፥ ተከለከለ። *ጢሰኝነት ቀረ።* 4. ቆየ፥ ዘገየ። *ምነው ቀረህ ቶሎና እንጂ!* 5. ተረፈ። *ስንት ቀረህ?* 6. ጎደለ፥ አነሰ። *ለፍራው ሊሞላ ትንሽ ይቀረዋል።* 7. ዳነ ፥አመለጠ፥ ተረፈ። *ከሞት የሚቀር የለም።* 8. በዚያው ፀና፥ ረጋ። *አሜሪካ ሄዶ ቀረ።* 9. አለመሳካትን፥ አለመፈፀምን፥ አለመደረግን፥... ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ሳያይ ቀረ/ሳይሰማ ቀረ/ሳያገኝ ቀረ።* 10. አልተገኘም፥ ጠፋ። *ቀለበቴ ወድቆ ቀረ።*

**ቀረበት** አመለጠው (ጥሩ ነገር)።

**በቀረ (በተቀረ፥ በስተቀር)** አለበለዚያ። *ብታጠና ይሻልሃል በቀረ ትወድቃለህ።*

**ከ__በስተቀር (በተቀር፥ በቀር)** መዋ. 1. ከ _____ ሌላ፥ በላይ፥ በተረፈ። *ከዚህ በስተቀር ምንም አላገኘሁም።* 2. ሳይጨምር፥ ሲቀር። *ከአባትየው በስተቀር ሌሎቹ ሰምተዋል።*

**የቀረው (የተቀረው)** ሌላው። *ይህን ሰምቻለሁ፣ የቀረው ምንድን ነው?*

**የቀረው ቢቀር** ሌላው ተትቶ፥ ቢያንስ ቢያንስ። *የቀረው ቢቀር በሩ መገጠም አለበት።*

**ይቅር አለ** ምህረት አደረገ፣ ቅሬታውን፥ ቂሙን ተወ።

**ይቅር ባይ** መሃሪ።

**ይቅር ተባባለ** ታረቀ፥ ተስማማ።

**ይቅርታ** ስ 1.ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይኖር፥ በዳይ ተበዳይን ምህረት የሚጠይቅበት የልመና ቃል። *ይቅርታ! ሳላይ ገፋሁህ።* 2. በደልን፥ ቂምን መተው፥ ይቅር ማለት፥ ምህረት ማድረግ። *ለእስረኞች ይቅርታ ተደረገላቸው።* 4. በንግግር መሃል ጣልቃ ገብቶ ለመናገርም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ ሲፈለግ የአድማጭን ፈቃድ ማግኘት እንዲቻል በቅድሚያ የሚነገር የትህትና ቃል። *ይቅርታ! በጨዋታችሁ መካከል አንድ ነገር ልናገር።*

**ይቅርታ አደረገ** ማረ፣ ቅሬታውን፥ ቂሙን ተወ።

**ቀሪ** ቅ 1. የቀረ፥ ያልመጣ ወይም ያልሄደ። 2. ተራፊ። 3. ያለ፥ የሚኖር። *የሞተስ ሞተ ይብላኝ ለቀረው።*

**ቅሪት** ቅ 1. እርጉዝ፥ ነፍሰጡር፥ የፀነሰች (ሴት)። ስ 2. ርዝራዥ (ለምሳሌ ሃብት)።

**ቅሪተ አካል** ስ ጥንት ህይወት የነበራቸው፥ አሁን ግን ደርቀው በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ጠጣር ነገሮች።

**ቀረት አለው/ብሎታል** ገና ነው፡ እንደተፈለገው አልሆነም፥ መጠነኛ ጉድለት አለው (ለመብሰል፥ ለመድረስ፥ ለመሙላት፥...)።

**ቅርት አለ** ግ 1. በጣም ቆየ፥ ዘገየ። 2. ድንገት ትንፋሹ ተቋረጠ፣ ድብን አለ፥ ሞተ። 3.ዛለ፥ መራመድ አልቻል አለ (እግር)። *እግሬ ወደሂላ ቅርት አለብኝ።*

**አስቀረ** ግ 1. ወሰደ፥ ለራሱ አደረገ። 2. ከለከለ፥ ሳይመልስ ቀረ።3. እንዳይሄድ ወይም እንዳይመጣ አደረገ።

***ቀረመተ**

**ቅርምት** ስ የስጋ ክፍፍል፣ ቅርጫ።
**ተቀረማመተ** ግ 1. ተካፈለ፣ ተቃረጠ። 2. ተሻማ፣ ተቧጨቀ።
**ተቀራመተ** ዝ.ከ.
**አቀራመተ** ግ 1. አካፈለ፣ አቃረጠ። 2. አሻማ፣ አቧጨቀ።
**ቀረረ** ግ 1. ጠራ፣ ጠለለ። 2.አዘለ፣ ያዘ(አይኑ እንባን)። *እንባው ቀረረ።*
**ቀረራ** ስ ሊጥ ተቦክቶ ኩፍ ካለ በኋላ ከእናቱ ላይ ጠልሎ የሚታይና እርሾነት ያለው ኮምጣጣ ፈሳሽ።
**ቅራሪ** ስ 1. ቀረራ፣ የቀረረ፣ ጥላይ። 2. ጠላው ተጠጥቶ ወይም ተቀድቶ ካለቀ በኋላ አተላው ላይ ውሃ ተሞልቶ የሚገኘው መናኛ ጠላ፤ አሰር ውሃ።
**ቀረር አደረገ** ግ የጠራው፣ የጠለለው እንዳይደፈርስ ቀስ አድርጎ ቀዳ።
**አቀረረ** ግ 1. የጠራውን፣ የጠለለውን ቀስ አድርጎ ቀዳ። 2. አጠለለ፣ ውሃ ከላይ ያዘ፣ አዘለ። 3. ያዘ፣ ቋጠረ፣ አዘለ (አይን እንባን)።
**አንቃረረ** ግ 1. ከዚህም ከዚያም አጯለጠ፣ ጠጣ፤ አጠረቃቀመ (መጠጥን)። 2. አጥለሉ፣ አቅረሮ ቀዳ።
**አንቃራሪ** ቅ ጠጪ፣ ሰካራም።
***ቀረረ**
**ቀረርቶ (ቀረርቱ)** ስ ሽለላ፤ የጦር፣ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማ።
**አቅራራ** ግ ሸለለ፤ የጦር፣ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማ አዜመ።
**አቅራሪ** ስ የጦር፣ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማን የሚያዜም ሰው፤ ሽላይ።
**አንቃረረ** ግ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮሀ።
**ቀረራ "ቀረረ"** ስር ተመ.
**ቀረርቱ "ቀረረ"** ስር"**ቀረርቶ**"ን ተመ.
**ቀረሮ (ቀራሮ)** ስ እንጨቱ ጠንካራ የሆነና ለተለያየ አገልግሎት የሚውል የዛፍ አይነት።
**ቀረሸ** ግ የጠባውን፣ የተጋተውን እንደማስታወክ አይነት ፍልቅ አደረገ (ህፃን ልጅ)።
**ቅርሻት** ስ በትውከት አምሳያ ሆኖ ከህፃን ልጅ ሆድ በመጠኑ ፍልቅ ብሉ የሚወጣ ፈሳሽ።
**ቅርሻታም** ቅ 1. ቅርሻት የሚበዛበት። 2. (ስድብ) በስካር ምክንያት ተገቢ ያልሆነ ንግግር የሚናገር፣ የሚሳደብ፣ ባለጌ።
**አቀረሸ** ግ ቀረሸ።
**እስኪአቀረሸው** እስኪያንገፈግፈው፣ እስኪሰለቸው። *እስኪአቀረሸው ነው የነገርኩት።*

**ቀረሸመ** ግ 1.ከረሸመ፣ ቆረጠመ፣ ጎረደመ። 2. ሰበረ፣ አነከተ።
**ቅርሽም አለ** ግ እንክት፣ ስብር አለ።
**ቀረሻሸመ** ግ 1. ከረሻሸመ፣ ቆረጣጠመ፣ አደቀቀ። 2. ሰባበረ፣ አነካከተ።
**ቅርሽምሽም አለ** ግ ስብርብር አለ።
**ቀረሻሽንቦ (ቀረሻሽምቦ)** ስ እንደጉሎና እንደሽንበቆ ውስጠ ክፍት የሆነ፣ በቀላሉ የሚሰበር የእፀዋት አይነት፡
**ቀረቀረ** ግ 1. በርን ወይም መስኮትን እንዳይከፈት በመወርወሪያ፣ በመቀርቀሪያ ዘጋ፣ ሸጎረ፣ ከረቸመ። 2. አስገባ፣ ጨመረ፣ ደነጎረ፣ ከተተ። 3. ደበቀ፣ እማይታይ ቦታ አስቀመጠ፣ ሰወረ።
**መቀራቅር(መቀራቅርት)** ስ ለመውጣትና ለመግባት የሚያስቸግር ጠባብ ቦታ።
**መቀርቀሪያ (ቅርቃር)** ስ በርና መስኮት እንዳይከፈት የሚያግድ መሸጎሪያ፤ ቅርቃር ወይም መወርወሪያ።
**ቀርቀሬ** ስ በጣም ጎድጓዳና ሸለቋማ የሆነ የቆላ መሬት።
**ቀርቀር** ስ ገደል።
**ቅርቃር "መቀርቀሪያ"**ን ተመ.
**ቅርቅር አለ** ግ ተቀረቀረ፣ ገብቶ ቀረ፣ ተወሸቀ።
**ተቀረቀረ** ግ ገብቶ ቀረ፣ አልወጣ አለ።
**ቀረቀበ** ግ 1. ሁለት ተመጣጣኝ ሸክምን (ጭነትን) በአህያ፣ በአጋሰስ፣... ጀርባ ግራና ቀኝ እንዲውል አድርጎ አሰረ፣ አቆራኘ፣ ወደነ። 2. እቃን፣ ልብስን፣...ሰብስቦ፣ ጠቅልሎ በአንድነት አሰረ። 3. (ዘይ.) በጣም እስኪጠግብ በላ።
**መቀርቀቢያ** ስ ቀርቃባን ለማሰር የሚያገለግል ጠፍር።
**ቀርቃባ (ቅርቃብ)** ስ 1. በአህያ፣ በአጋሰስ፣...ጀርባ ላይ ለመጫን እንዲያመች ተመጣጣኝ ሆኖ የታሰረ ወይም የተቆራኘ መንታ ጭነት፣ ሸክም።
***ቀረቀበ**
**ቀርቀቦ** ስ 1. ማንቀርቀቢያ፣ ሰፌድ። 2. "**ቀርበቦ**"ን ተመ.
**ተንቀረቀበ** ግ 1. ግርድፉ ከደቃቁ እንዲለይ ሆኖ በሰፌድና በመሳሰለው እቃ ተበጠረ፣ ተንገዋለለ። 2. ተናወጠ፣ ተንቀጠቀጠ፣ ራደ (ምድር፣...)። 3. ደጋግሞ ነጠረ (ኳስ እግር ላይ)።
**አንቀረቀበ** ግ 1. ግርድፉ ከደቃቁ እንዲለይ አድርጎ በሰፌድና በመሳሰለው አበጠረ፣ አንጠረጠረ፣ አንገዋለለ። 2. አናወጠ፣

አንቀጠቀጠ፥ አራደ (ምድርን፥...)፡፡3. ደጋግሞ አነጠረ፥ ጢብ ጢብ አደረገ (ኳስን በእግር)፡፡

**ማንቀርቀቢያ** ስ ለማንጠርጠር፥ ለማበጠር የሚያገለግል እቃ፤ ሰፌድ፡፡

**እንቅርቃቢ** ስ ከተፈጨ ወይም ከተወቀጠ ነገር ውስጥ በሰፌድ ተንገዋሎ፥ ተንጠርጥሮና ተለይቶ የሚወጣው ያልደቀቀው ክፍል፡፡

**ቀረበ** ግ 1. ተጠጋ፤ ቅርብ፥ አጠገብ ሆነ፡፡ 2. ደረሰ፡፡ *ዓመት በዓሉ ቀረበ፡* 3. መጣ፥ በቦታው ላይ ተገኘ፡፡ *ወንጀለኛው ቀረበ፡* 4.ዝግጁ ሆነ፥ ተሰራ፡፡ *ገበታው ቀረበ፡* 5. ይበልጥ ተጠጋ፥ ተዛመደ፥ ተግባባ፡፡ *ከአንተ የቀረበ ጓደኛ የለኝም፡፡* 6. ተነገረ፥ ተሰጠ፥ ተሰነዘረ፡፡ *ሃሳብ ቀረበ፡፡*

**ቀረቤታ** ስ ቅርበት (የዝምድና፥ የወዳጅነት)፡፡

**ቅርብ** ቅ 1. አጠገብ ያለ፥ የተጠጋ፥ ሩቅ ያልሆነ፡፡ 2. የጠበቀ፥ በጣም የተጠጋ (ለዝምድና፥ ለወዳጅነት)፡፡

**ቅርብ ለቅርብ** የተጠጋጋ፥ ያልተራራቀ፥ አጠገብ ለአጠገብ ያለ፡፡

**[በ]ቅርብ ቀን** በዚህ ሰሞን፥ በቅርቡ፡፡

**የቅርብ ሩቅ** 1. ቅርብ ሆኖ የሩቅን ያህል የሚያደክም(መንገድ)፡፡ 2- አጠገብ ለአጠገብ ሆኖ የማይገናኝ፥ የማይጠያየቅ፡፡

**ቅርበት** ስ 1. አጠገብነት፡፡ 2. የጠበቀ ግንኙነት (ለወዳጅነት፥ ለዝምድና)፡፡

**ተቀራረበ** ግ 1. ተጠጋጋ፥ ቅርብ ለቅርብ ሆነ፡፡ 2. ተግባባ፥ ተስማማ፡፡ 3. ተመሳሰለ፥ ተመጣጠነ፡፡

**ተቀራራቢ** ቅ ተመሳሳይ፥ ተመጣጣኝ፡፡

**ተቃረበ** ግ 1. ተዳረሰ (ጊዜው)፡፡ 2. ተጠጋ፥ ወደ አካባቢው ቀረበ፡፡

**መቃረቢያ** ስ 1. መዳረሻ፡፡ 2. ዋናው ቤተክርስቲያን እስኪሰራ ድረስ ለጊዜው እንደቤተክርስቲያን ሆኖ የሚያገለግል አነስተኛ ቤት፥ የታቦት ማረፊያ፤ መቃኞ፡፡

**አቀረበ** ግ 1. አስጠጋ፥ አጠገብ አደረገ፡፡ 2. ቶሎ እንዲደርስ አደረገ፥ አሳጠረ (የቀጠሮ ጊዜውን) 3. አመጣ፡፡ 4. (ዝግጅቱን) ሰጠ፥ አበረከተ፥ አሳየ፡፡ 5. ዘመድ ወዳጅ አደረገ፡፡ 6. ሰጠ፡፡ *ሰላምታ አቀረበ፡፡* 7. ሰነዘረ፡፡ *ወቀሳ አቀረበ፡፡*

**ማቅረቢያ** ስ 1. ማምጫ፥ ማስቀመጫ፥ ማጓጓዣ(እቃ)፡፡ 2. ማባበያ፥ መማለጃ፥ ስጦታ፥...፡፡

**አቅራቢ** ቅ ልዩ ልዩ ነገሮችን ወደሚያስፈልገው ቦታ የሚያቀርብ (ሰው፥ ድርጅት)፡፡

**አቅራቢያ** ስ 1. በቅርብ ያለ ቦታ፡፡ 2. አካባቢ፡፡ *ሊነጋጋ አቅራቢያ እቦታው ደረስን፡፡*

**አቅርቦት** ስ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የተፈለገውን ሸቀጥ የማቅረብ አቅም፡፡

**አቀራረበ** ግ አመጣ፥ አዘጋጀ፥ ደረደረ (የተለያዩ ነገሮችን)፡፡

**አቀራረበ** ግ 1. አጠጋጋ፡፡ 2. ግንኙነት፥ ስምምነት እንዲፈጠር አደረገ፥ አግባባ፡፡

***ቀረበበ**

**ቀርባባ(ቀረበብ)** ቅ ከርፋፋ፥ ጎርባባ፡፡

**ቀርባባ ጆሮ** ስ ትልቅ ጆሮ፡፡

**ተንቀረበበ** ግ ተንከረፈፈ፥ ተንጎረበበ፡፡

**አንቀረበበ** ግ አንከረፈፈ፥ አንጎረበበ፡፡

**ቀረባ** ስ እሾሀንና የመሳሰለውን ቆንጥጦ ለመንቀል የሚያስችል መቆንጠጫ፤ ወረንጦ፡፡

**ቀረቤታ "ቀረበ"** ስር ተመ.

**ቀረቦ "ቀርበቦ"** ን ተመ.

***ቀረነ**

**ቅራኔ** ስ 1. አለመስማማት፥ አለመግባባት፥ ቅዋሜ፡፡ 2. ጥል፥ ግጭት፡፡

**ተቃረነ** ግ 1.ተቃወመ፥ አልስማማ አለ፡፡ 2. እርስ በእርስ ተጣላ፥ ተጋጨ፡፡

**ተቃራኒ** ቅ 1. ተፃራሪ፥ አፍራሽ፡፡ 2. ጠላት፥ ተቃዋሚ፡፡ 3. እርስ በርስ የማይስማማ፡፡ 4. ለአንዱ ቃል ፍቺ ተፃራሪ ፍቺ ያለው ቃል፡፡*"መጣ" የ"ሄደ" ተቃራኒ ነው፡፡*

**ተቃራኒ ፆታ** ስ በፆታ የማይመሳሰል (እንስትና ተባእት)፡፡ የተባእት ተቃራኒ ፆታ እንስት ስትሆን የእንስቷም ተቃራኒ ፆታ ተባእት ነው፡፡

**ቀረነተ (ቀረነጠ)** ግ ጠረነቀ፥ ጥፍር አድርጎ አሰረ፡፡

**ቀረና** ግ 1. ቀንድ፥ ቆዳ፥ ፀጉር፥...ሲቃጠል እንደሚፈጠረው ያለ ሽታ ሸተተ፡፡ 2. ገማ፥ ከረፋ፡፡ 3. ጎረና (ለወጥና ለመሳሰለው)፡፡

**ቅርናት** ስ 1. ከተቃጠለ ቀንድ ወይም ቆዳ ወይም ፀጉር የሚወጣ መጥፎ ሽታ፡፡ 2. ክርፋት፥ ግማት፡፡

**ቅርናታም** ቅ (ስድብ) ግማታም፥ ክርፋታም፡፡

**አቀረና** ግ መታ (በዱላ፥ በጥፊ፥...)፡፡

**ቀረንጠሎ** ስ የተበጣጠሰና ያደፈ ልብስ፤ ጭርንቁስ፥ ቅርንጥስ፡፡

**ቀረንጠሷም** ቅ (ስድብ) የተበጣጠሰና ያደፈ ልብስ የሚለብስ፤ ቅርንጥሳም፥ ቡትቷም፡፡

**ቀረዋ[1] "ቀራዎ[1]"** ን ተመ.

**ቀረዋ[2] "ቀራዎ[2]"** ን ተመ.

**ቀረደደ** ግ 1. ቆረጠ፥ ሸረከተ፡፡ 2. ቀረጠፈ፥

ሰነጠቀ። 3. (ዘይ.) ሳያፍር ዋሸ፥ ወሸከተ።

**ተቀረደደ** ግ 1.ተቀደደ፥ ተቆረጠ፥ ተሸረከተ፤ ተሰነጠቀ። 2. (ዘይ.) ሳያፍር ዋሸ፥ ወሸከተ።

**ተቀራደደ** ግ በስለት ተሸራከተ።

***ቀረደደ**

**ቀረደድ(ቀርዳዳ)** ቅ ከረፈፍ፥ ቀረፈፍ፥ ከርፋፋ፥ ቀርፋፋ።

**ተንቀረደደ** ግ ተንከረፈፈ፥ ተንቀረፈፈ (ለአካሄድ)።

**አንቀረደደ** ግ አንከረፈፈ፥ አንቀረፈፈ።

**ቀረጠ** ግ ግብር ተቀበለ ወይም አስከፈለ (ከሽያጭ ወይም ከሌላ ገቢ፥ ጥቅም)።

**ቀረጥ** ስ 1. ከሽያጭና ግዢ ወይም ከሌላ ነገር ለተገኘ ገቢ ወይም ጥቅም ለመንግስት የሚከፈል ግብር፤ ታክስ፤ አሹራ። 2. በፊደል ተ ራ ው ተመ.

**የቀረጥ ቴምብር** ስ ለመንግስት ገቢ እንዲያስገኝ ባለጉዳይ እየገዛ በማመልከቻ፥ በልዩ ልዩ የፈቃድና የምስክር ወረቀት፥ የንግድ እቃ፥... ላይ የሚለጠፍ ቴምብር።

**ቀራጭ** ስ በገበያ መግቢያ በሮች፥ በመንገድ ኬላዎች ላይ እየተገኘ ቀረጥ የሚያስከፍል የመንግስት ሰራተኛ።

**ቅርጫ** ስ ክፍፍል፥ ቅርምት (የስጋ)።

**ተቃረጠ** ግ ተከፋፈለ፥ ተቀራመተ (ስጋን)።

**አቃረጠ** ግ አከፋፈለ፥ አቀራመተ (ስጋን)።

**ቀረጠፈ** ግ 1. ከጫፍ ከጫፉ ላይ በአጭር በአጭሩ ቆረጠ፥ ከረተፈ (ጌሾን ወይንም ሌላ ነገርን)። 2. ጎመደ፥ ቆረጠ። 3. አጣበቀ፤ ቆነጠጠ፥ ቆረጠ። *መዝጊያው እጄን ቀረጠፈኝ።* 4. በላ፥ አነከተ። *ጅብ ቀረጠፈው።* 5. አመመ (ቁርጥማት)።

**መቀርጠፊያ** ስ አነስተኛ መጥረቢያ።

**ቀረጥ**[1] ስ ቅጠሉ ለቁርበት ማቅለሚያ፥ ላልተሟሸ ወይም ለአዲስ ቅል ማሟሻ የሚሆን አነስተኛ የዛፍ አይነት።

**ቀረጥ**[2] "**ቀረጠ**" ስር ተመ.

***ቀረጨ**

**አንቀራጨ** ግ ቅርጭው ቅርጭው አደረገ፥ ቆረጠመ።

**ቀረጨመ** "**ቆረጨመ**" ን ተመ።

**ቀረጨጨ** ግ በሃይል ነከሰ (በጥርስ)።

**ቀረፀ (ቀረጠ)** ግ 1. አነፀ፥ አበጀ፥ ቅርፅ ሰራ። 2. አሾለ። *እርሳሱን ቀረፀ።* 3. ቀዳ፥ መዘገበ፥ አነሳ (ድምፅን፥ ምስልን፥... በቴፕ፥ በፊልም፥...)። 4. ፈጠረ፥ ሳለ (አንድን ስሜት በአእምሮ ውስጥ)። 5. ሰራ፥ አበጀ (ለምሳሌ ፊደልን)።

**መቅረጫ** ስ በውስጡ ስለት ያለው የእርሳስ ማሾያ።

**ቀራጭ (ቀራፂ)** ስ ሃውልት፥ ምስል ሰሪ።

**ቅርፅ** ስ 1. ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፥...የተሰራ የአንድ ነገር ምስል። 2. የአንድ ነገር ውጫዊ ገፅታ፥ መልክ። 3. የሰውነት አቋም፥ ቁመና።

**ቅርፃ ቅርፅ** ስ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፥...የተሰሩ የልዩ ልዩ ምስሎች፥ እቃዎች፥... አሰራርና አይነት።

**ቀረፈ** ግ 1. አነሳ፥ ላጠ፥ ገለፈፈ (ቅርፊትን፥ ምርጊትን፥...)። 2. ተወ፥ አስወገደ (ቂምን፥ ችግርን)።

**ቀራፊ** ቅ የሙጋድ እንጨት ሰባሪ፥ ፈላጭ፥ አቅራቢ።

**ቀራፎ** ስ 1. የቅል፥ የአንኮላ ጉማጅ፤ ፋጋ። 2. (ዘይ፥ ስድብ) ከርፋፋ፥ ቂል።

**ቅራፊ** ቅ ተቀርፎ፥ ተገልፍፎ ከላይ የተነሳው የእንጨት ወይም የሌላ ነገር ቅርፊት።

**ቅርፊት** ስ ከላይ ተቀርፎ፥ ተልጦ የተነሳ የእንጨት፥ የዳቦ፥... ልባስ፥ ሽፋን።

**ቅርፊት ያዘ/አበጀ** ቅርፊት ለበሰ፥ ደረቀ (ቁስል)።

**ቅርፍርፍ** ቅ ስንጥቅጥቅ፥ ፍርክርክ።

**ተቀረፈ** ግ ተነሳ፥ ተላጠ፥ ተገለፈፈ።

**ተቅረፈረፈ** ግ ተሰነጣጠቀ፥ ተፍረከረከ።

**ቀረፈተ** ግ ቀረፈ፥ ላጠ፥ ገሸለጠ።

**ተቀረፈተ** ግ ተቀረፈ፥ ተላጠ፥ ተገሸለጠ።

**ቀረፈፈ** ግ ላጠ፥ መለጠ፥ ገፈፈ፥ ገለፈፈ፥ ቀረፈ።

***ቀረፈፈ**

**ቀረፈፍ(ቀርፋፋ)** ቅ ከረፈፍ፥ ከርፋፋ።

**ተንቀረፈፈ** ግ 1. ዝግ አለ፥ ተንከረፈፈ፥ ፍጥነት አጣ። 2. ረዘመ፥ ተንቀረበበ።

**ተንቀራፈፈ** ዝ.ከ.

**አንቀረፈፈ** ግ አንከረፈፈ፥ አረዘመ፥ አንቀረበበ።

**አንቀራፈፈ** ዝ.ከ.

**ቀረፋ** ስ በቅመምነት የሚያገለግል ጥሩ ጣእምና ሽታ ያለው የእንጨት ቅርፊት።

**ቀረቦ** ስ ጌሾ የሌለውና በጠላ መልክ የሚዘጋጅ መጠጥ።

**ቀራ**[1] ግ ከብቶችን ሌሊት ጠበቀ።

**ቅራት** ስ የሌሊት ከብት ጥበቃ። *ቅራት ወጣ።*

**ቅራተኛ** ስ ሌሊት ከብት የሚጠብቅ ሰው።

**ቀራ**[2] ግ ቁርአን ተማረ።
**ቀራሮ** "**ቀረሮ**" ን ተመ.
**ቀራዎ**[1] **(ቀረዋ)** ስ መስፈሪያ ቁና። (ሃረር)
**ቀራዎ**[2] **(ቀረዋ)** ስ የጎራዴ አይነት።
**ቀራጭ**[1] "**ቀረጠ**" ስር ተመ.
**ቀራጭ**[2] "**ቀረፀ**" ስር ተመ.
**ቀራጺ** "**ቀረጠ**" ስር "**ቀራጭ**" ን ተመ.
**ቀራፊ** "**ቀረፈ**" ስር ተመ.
**ቀራፎ** "**ቀረፈ**" ስር ተመ.
**ቀርም** "**ቃረመ**" ስር "**ቃርሚያ**" ን ተመ.
**ቀርቀም** ስ ፌጦ የሚመስልና ፍሬው የማይበላ ወንዝ ዳር የሚበቅል የእፀዋት አይነት።
**ቀርቀሬ** "**ቀረቀረ**" ስር ተመ.
**ቀርቀር** ዝ.ከ.
**ቀርቀቦ** "**ቀርበቦ**" ን ተመ.
**ቀርቃሃ** "**ቀርከሃ**" ን ተመ.
**ቀርቃባ** "**ቀረቀበ**" ስር ተመ.
**ቀርበቦ (ቀረቦ÷ ቀርቀቦ)** ስ ከላም ወይም ከበሬ ግምባር ቆዳ የሚሰራ ወታቦ መሰል ቅርጫት ወይም ቁና መሰል ትንሽ እቃ።
**ቀርበታ** ስ 1. ለውሃ መቅጃ የሚያገለግል ስልቻ። 2. (ዘይ.÷ ስድብ) ሆዳም፤ ቀፈታም።
**ቀርባባ** "***ቀረበበ**" ስር ተመ.
**ቀርን** ስ ቀንድ።
**ቀርከሃ (ቀርቃሃ)** ስ አንድ ቦታ እጅብ ብሎ የሚበቅል እንደሸንበቆ ያለ ግን ትልልቅና ጠንካራ የሆነ የእፀዋት አይነት።
**ቀርዳዳ** "***ቀረደደ**" ስር "**ቀረደድ**"ን ተመ.
**ቀርጥ** ስ ስፋቱ ሃምሳ ሜትር በሃምሳ ሜትር ወይም 50 መረባ የሆነ መሬት።
**ቀርጫ**
**ቀርጫ ቀርጫ አለ** ግ ሲበሉት ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ ሰጠ።
**ቀርፋፋ** "***ቀረፈፈ**" ስር "**ቀረፈፍ**"ን ተመ.
**ቀሰመ** ግ 1. ጣፋጭ ፈሳሽን ከአበባ ውስጥ ወሰደ÷ ሰበሰበ÷ ለቀመ (ንብ÷ቢራቢሮ)። 2. ተማረ÷ ወሰደ። *ዝበዝ ተማሪ እውቀትን ከመምህሩ ይቀስማል።*
**ቀሰም** ስ ከቀጭን መቃ ወይም ሸንበቆ ባጭር ባጭሩ ተቆርጦ የተዘጋጀ የማግ ማዳወሪያ÷ መጠቅለያ።
**ቀሰረ** ግ 1. አቆመ÷ ገተረ (ጭራን÷ ጣትን÷...)።
**ቀሳራ (ቅስር)** ቅ ገታራ÷ የተቀሰረ።
**ቅስር ቅስር አለ** ግ ግትር ግትር አለ (ለአካሄድ)።
**ተቀሰረ** ግ ተገተረ÷ ቆመ።
**ቀሰሰ**[1] ግ የቅስናን ማእርግ ወይም ስልጣነ ክህነትን ተቀበለ፤ ቄስ ሆነ።
**ቀሲስ** ስ ስልጣነ ክህነት ያለው የቤተክርስቲያን አገልጋይ÷ ካህን።
**ቄስ (ብ.ቁ. ቀሳውስት)** ዝ.ከ.
**ቄስ ገበዝ** "**ገበዝ**" ን ተመ.
**ቄስአጤ** ስ በቀድሞ ዘመን የንጉስ ነፍስ አባት÷ ዘውድ አጣኝ÷ ማእድ ባራኪ የነበረ ካህን።
**የቄስ በቅሎ** እየሄደ ሳለ መንገድ ላይ ሰው ባገኘ ቁጥር በየቦታው የሚቆም÷ የሚገተር።
**የቄስ ተማሪ** ስ 1. ከፊደል ቆጠራ እስከ ዳዊት ደገማ ያለውን ትምህርት በቄስ ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ። 2. የቆሎ ተማሪ።
**የቄስ ትምህርት ቤት** ስ ህፃናት በመጀመሪያ ከፊደል ቆጠራ እስከ ዳዊት ደገማ የሚማሩበት በየመንደሩና በየቤተክርስቲያኑ የሚገኝ ትምህርት ቤት።
**ቅስና** ስ የቄስነት ማእርግ÷ ስልጣን።
**አቀሰሰ** ግ ቅስና ሰጠ፤ ቄስ አደረገ።
**ቀሰሰ**[2] ግ ፈዘዘ÷ ቀዘዘ።
**ቀሰስተኛ** ቅ በበሽታ÷ በተፈጥሮ÷...ምክንያት አቅም ያጣ÷ ዝግ ብሎ የሚራመድ። 2. ፈዛዛ።
**ቀሳሳ** ቅ ቀዛዛ÷ ፈዛዛ።
**ቅስስ አለ** ግ ፍዝዝ÷ ቅዝዝ አለ።
**ቀሰቀሰ** ግ 1. አስነሳ÷ አነቃ (ከእንቅልፍ)። 2. አስተማረ÷ አነቃ÷ አነሳሳ (አንድ ነገር ለመስራት)። 3. እንደገና እንዲነሳ÷ እንዲታወስ አደረገ። *ትዝታውን ቀሰቀሰበት*። 4. ጀመረ÷ አጫረ። *ጠቡን የቀሰቀሰው ልጅየው ነው*። 5. በረበረ÷ ፈተሸ÷ ፈለገ (እቃን)። 6. ነካካ÷ አወከ (ቦታውን እንዲለቅ)። *ንቡን ከቀፎው ቀሰቀሰው*። 7. አጫረ÷ አነሳሳ። *የወጡ ሽታ የምግብ ፍላጎቴን ቀሰቀሰብኝ።*
**ቅስቀሳ** ስ ሰዎችን ለአንድ አላማ ወይም ስራ ለማሰለፍ የሚሰጥ ማነቃቂያ÷ ማነሳሻ÷ መጎትጎቻ ትምህርት።
**ቀስቀስ አለ** ግ በጥቂቱ ተንቀሳቀሰ÷ ተላወሰ።
**ቅስቅስ አለ** ግ ንቅንቅ አለ። *ቅስቅስ አንዳትል።*
**ቅስቅስ ብሎ ወጣ** በጠቅላላ÷ በብዛት ወጣ።
**ተቀሰቀሰ** ግ እንደገና ተነሳ÷ ተጀመረ።
**ተቀስቅሶ ወጣ** በብዛት ወጣ።
***ቀሰቀሰ**
**ቅስቃሴ** ስ ንቅናቄ÷ እንቅስቃሴ።

**ተንቀሳቀሰ** ግ 1. ተንቃነቀ፥ ተላወሰ:: 2 ጉዞ ጀመረ፥ ተነሳ:: 3. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዘዋወረ (ከቦታ ወደ ቦታ)::

**መንቀሳቀሻ** ስ መነሻ፥ መጀመሪያ የሚሆን ገንዘብ (ለንግድ ስራ)::

**ተንቀሳቃሽ** ቅ 1. ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወር የሚችል:: 2. የሚላወስ፥ ህይወት ያለው ነገር::

**ተንቀሳቃሽ ሂሳብ** ስ ወለድ የማይኖረውና በተፈለገ ጊዜ በቼክ ሊወጣ የሚችል በባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ::

**አንቀሳቀሰ** ግ 1. አነቃነቀ፥ አላወሰ:: 2. አስጀመረ፥ አስነሳ (ሞተርን፥...):: 3. አካሄደ፥ መራ:: *ድርጅቱን የሚያንቀሳቅሰው ማነው?* 4. ገንዘብን ወጪ ገቢ አደረገ፥ በስራ ላይ አዋለ::

**እንቅስቃሴ** ስ 1. የመነቃነቅ፥ የመላወስ ሁኔታ:: 2. አንድን ስራ ለመስራት የሚደረግ መሯሯጥ:: 3. የተቃውሞ ርምጃ፥ ንቅናቄ፥ አመፅ::

**ቀሰብ** ስ ማንኛውም እንደ መቃ ያለ ውስጠ ክፍት እንጨት ወይም ብረት::

**ቀሰተ** ግ 1. ቅስት ሰራ፥ አበጀ፤ አጎበበ፥ እንደ ደጋን አደረገ::

**ቀስት** ስ 1. በደጋን አይነት ወይም ቅርፅ የተሰራና ገመዱን ለጥጠው ሲለቁት ፍላፃ የሚያስፈነጥር የጦር መሳሪያ:: 2. ጫፉ ሹል የሆነና በደጋን አውታር የሚስፈነጠር፥ለጦር መሳሪያነት የሚያገለግል ብረት፤ ፍላፃ:: 3. በፍላፃ ምስል የተሰራ የአቅጣጫ ማመልከቻ ምልክት::

**ቀስተደመና** ስ የተለያዩ ቀለማት (አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ፥...) ያለውና በተለይ ካፊያ በሚኖርበት ጊዜ በደጋን ቅርፅ ከሰማይ ወደመሬት ተተክሎ የሚታይ የፀሃይ እንፅብራቂ፤ የማርያም መቀነትም ይባላል::

**ቀስተኛ** ስ በቀስት የሚዋጋ፥ የሚያድን ሰው::

**ቅስት** ስ 1. በበር፥ በመተላለፊያ፥ በድልድይ ላይ እንደ ደጋን ጎብጦ ወይም በአራት ማእዘን ቅርፅ ሆኖ የሚሰራ እንጨት፥ ብረት ወይም ግምብ:: 2. እንደ ጠረጴዛ እግር ወይም የግድግዳ ቋሚ እንጨት የመሳሰለ ነገር እንዳይዋልልና እንዳይወድቅ ወጥሮ የሚይዝ ሰያፍ ማገር::

**ቀሰንዲ** ቅ ቆሽማዳ፥ ወልጋዳ::

**ቀሰጠ** ግ 1. ቆንጠር አድርጎ ሰረቀ፤ ቀንሶ ወሰደ:: 2. አበለ፥ ቀጠፈ፥ ዋሸ::

**ቀሳጢ** ቅ 1. ሌባ:: 2. አባይ፥ ዋሾ::

**ቀሰፈ** ግ 1. ያለጊዜው ገደለ፥ ቀጠፈ፥ ቀጨ:: 2. ሰቀዘ፥ ወጠረ፥ አስጨነቀ (ውጋትና የመሳሰለው)::

**ቀስፎ ያዘ** ወጥሮ፥ አስጨንቆ፥ ወግቶ ያዘ::

**መቅሰፍት** ስ እልቂትን የሚያስከትል እንደተላላፊ በሽታ፥ ጎርፍ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ቸነፈር የመሳሰለ ከባድ አደጋ፤ መአት::

**መቅሰፍታም** ቅ መቅሰፍት፥ በሽታ የሚበዛበት (ቦታ፥ ጊዜ)::

**ቀሳፊ** ቅ ገዳይ፥ አጥፊ:: *የቀሳፊው ኤድስ ሰለባ ላለመሆን ከልቅ ወሲብ መቆጠብ ያስፈልጋል::*

**ቅሰፈት** ስ 1. በአጭር መቀጨት፥ በድንገት መሞት:: 2. ሞት የሚያስከትል አደጋ፥ መአት፥ በሽታ፥...::

**ተቀሰፈ** ግ ያለጊዜው ሞተ፥ ተቀጨ፥ ተቀጠፈ:: 2. ፋታ አጣ፥ ተወጥሮ ተያዘ:: *ተቀስፎ ተይዟል::*

**ቀሲስ** "ቀሰሰ[1]" ስር ተመ.

**ቀሳ** ስ ተላላፊ በሽታ ወደ ጤናማው ሰው እንዳይተላለፍ ከሰፈር ራቅ ብሎ በሚገኝ ገለልተኛ ቦታ ላይ ለበሽተኛው መታመሚያ የሚሰራ ጊዜያዊ ቤት::

**ቀሳ ወጣ** ገለል ወዳለ ቦታና ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ (በሽታ የያዘው ሰው)::

**ቀሳራ** "ቀሰረ" ስር ተመ.

**ቀሳሳ** "ቀሰሰ[2]" ስር ተመ.

**ቀሳውስት** "ቀሰሰ[1]" ስር ተመ.

**ቀሳጢ** "ቀሰጠ" ስር ተመ.

**ቀሳፈተ** ግ ቀላመደ፥ ዘላበደ፥ አበለ፥ ዋሸ::

**ቀሳፋች** ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፥ ለፍላፊ፥ ውሸት የሚያበዛ::

**ቀስፋታ** ዝ.ከ.

**አስቀሳፈተ** ግ አስዋሸ፥ አሳበለ፥ አስቀባገረ::

**ቀሳፊ** "ቀሰፈ" ስር ተመ.

**ቀሳፋች** "ቀሳፈተ" ስር ተመ.

**ቀስ** ዝግ፥ ረጋ::

**ቀስ በቀስ** ተው.ግ. በጊዜ ብዛት፥ በዝግታ፥ ቀስ እያለ:: *ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል::*

**ቀስታ** ስ ዝግታ፥ ርጋታ::

**በቀስታ** ተው.ግ. 1. በዝግታ፥ በርጋታ:: 2.በዝቅተኛ ድምፅ ፥ በሹክሹክታ፥ በለሆሳስ:: *የተኛችን እንዳትቀሰቅሱ በቀስታ ተነጋገሩ::*

**ቀስተኛ** ቅ ዝግተኛ፥ ዘገምተኛ::

**ቀስ አለ** ግ 1. ዝግ አለ፥ ረጋ አለ፥ ከመጣደፍ ተቆጠበ:: *ቀስ እያለ ተራመደ*:: 2. ከፍ ያለ ድምፅ ሳያሰማ ወይም ጮክ ሳይል ወይም ሃይል ሳያበዛ፥... አደረገ:: *ቀስ ብለው ይናገሩ እባክዎ* /ምስማሩን በመዶሻ ቀስ እያለ ቀጥቅጦ አቃናው::

**ቀስ አደረገ** ግ 1.ፍጥነት ቀነሰ፥ ዝግ አደረገ:: 2. በዝግታ፥ በእርጋታ፥ በጥንቃቄ-፥... አደረገ:: *በሽተኛውን ከአልጋው ላይ ቀስ አድርጎ*

*ሳስተኛው።* 3. በትንሹ፥ ሃይል ሳይጨምር ሰራ ወይም አደረገ። *ጓሉን ቀስ ሳድርገህ ምታ።*

**ቀስተኒ(ን)ቻ** ስ መጠኑ ከፅጌረዳ የማይበልጥ፥ ግንዱ ውስጠ ክፍት፥ የሚለመጥ፥ ለቀስት የሚሆን የእፀዋት ኣይነት፤ ሰሪቴ።

**ቀስተኛ "ቀሰተ"** ስር ተመ.

**ቀሰተደመና "ቀሰተ"** ስር ተመ.

**ቀስታ "ቀስ"** ስር ተመ.

**ቀስት "ቀሰተ"** ስር ተመ.

**ቀስፋታ "ቀሳፈተ"** ስር ተመ.

**ቀሸመ** ግ (የኣራዳ ኣነ.) ኣንድን ነገር የመስራት፥ የማድረግ ዘዴው፥ እውቀቱ፥ ችሎታው፥ ብልሃቱ ቀነሰ።

**ቀሽም** ቅ 1. ኣንድን ነገር በሚገባ መስራት ወይም ማድረግ የማይችል፤ በቂ ሙያ የሌለው። *ጸግር ኳስ ሲጫወት ቀሽም ነው።* 2. ኮሾ፥ የማይረባ፥ ጥራት የሌለው። *ያደረገችው ጫማ ቀሽም ነው።*

**ቀሸመደ** ግ 1. ሰበረ፥ ኣነከተ። 2. መታ፥ ኣዘረጠ (በብትር)።

**ቀሽማዳ (ቀሸመድ)** ቅ ሰባራ፥ ደካማ፥ ኣቅመቢስ፥ ተልካሻ።

**ቅሽምድምድ** ቅ ውልክፍክፍ፥ ልፍስፍስ፥ ኣቅመቢስ።

**ቀሸረ** ግ 1. ከሸነ፥ ኣሳመረ። 2. በመውቀጥ ወይም በመከካት ፍሬውን ከገለባ ለየ (ብዙውን ጊዜ ለቡና)።

**ቀሸር(ቅሸር)** ስ ገለባው ወይም ቆዳው ከላዩ ላይ የተነሳለት ቡና፤ የተፈለፈለ ቡና።

**ተቀሸረ** ግ ተከሸነ፥ ኣማረ።

**ቀሸረረ** ግ ከሳ፥ ደረቀ።

**ቀሸራራ (ቀሸረር)** ቅ ከሲታ፥ ደረቅ።

**ተንቀሸረረ** ግ ከሳ፥ ደረቀ።

**ኣንቀሸረረ** ግ ኣከሳ፥ ኣደረቀ (ሰውነትን)።

***ቀሸቀሸ**

**ተንቀሸቀሸ** ግ ተነካከተ፥ ተሰባበረ።

**ኣንቀሻቀሸ** ግ ሰባበረ፥ ኣነካከተ።

**እንቅሽቅሽ ኣለ** ግ እንክትክት፥ ስብርብር ኣለ።

**እንቅሽቅሽ ኣደረገ** ግ ኣነካከተ፥ ሰባበረ።

**ቀሸመሪ (ሬ)** ስ የቀድሞ ጊዜ ጌጠኛ ጥብጣብ፥ መታጠቂያ።

**ቀሽማዳ "ቀሸመደ"** ስር ተመ.

**ቀሽም "ቀሸመ"** ስር ተመ.

**ቀሸራራ "ቀሸረረ"** ስር ተመ.

**ቀሸር**[1] **"ቀሸረ"** ስር ተመ.

**ቀሸር**[2] ስ ያለሻይ ቅጠል በዝንጅብል ብቻ የተፈላ ሻይ።

**ቀቀለ** ግ 1. በውሃ ውስጥ ኣድርጎ በሙቀት ሃይል ኣበሰለ፥ ኣሞከከ፥ ኣነፈረ (ብዙውን ጊዜ ለምግብ)። 2. ኣቃጠለ፥ ለበለበ፥ (በረሃው፥ ሙቀቱ፥...)።

**መቀቀያ** ስ የሚቀቀልበት፤ እንደድስት፥ ማሰሮ፥ ብረት ድስት፥ ሰታቴ ያለ እቃ።

**ቀቃይ** ስ ኣብሳይ።

**ቅቅል** ስ 1.ተቀቅሎ የበሰለ ስጋ ከነመረቁ። 2.የተቀቀለ (በቆሎ፥...)።

**ተቀቀለ** ግ 1. በሰለ፥ ሞከከ፥ ነፈረ (በውሃና በሙቀት)። 2. ተቃጠለ፥ ተለበለበ (በፀሃይ፥ በበረሃ ሙቀት፥...)።

**ቀቀረ** ግ ጆሮውን ጣለ፤ ለማዳመጥ፥ ለመስማት ጆሮውን ኣቆመ። *ጆሮውን ቀቅሮ ያዳምጥ ነበር።*

**ቀቀተ** ግ ነፈገ፥ ሰሰተ።

**ቅቅት (ቀቀት)** ስ ንፍገት፥ ስስት።

**ቅቅታም** ቅ (ስድብ) ንፉግ፥ ስስታም።

**ቀቃይ "ቀቀለ"** ስር ተመ.

**ቀቅ**[1] ስ በማሳ ላይ ያለ እህልን የሚያበላሽ ውርጭ፤ ዋግ።

**ቀቅ**[2] ስ ለተመታና ለቆሰለ ሰው የሚሰጥ ኣነስተኛ ካሳ። *ጸገሌ የቀቅ ከፈለ።*

***ቀበለ**

**ቀበሌ** ስ የሰውን ድምፅ ተቀብሎ የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶ።

**ቅበላ** ስ የፆም ዋዜማ፥ ፆም ከመግባቱ በፊት ቀደም ብሎ ያለው ቀን ወይም ሰሞን።

**ቅብብል** ስ ኣንዱ ለሌላው የሚያደርገው የመስጠት፥ የማቀበል፥ የማሻገር ድርጊት። *ኢቃው የተጓጓዘው በቅብብል ነው።*

**ቅብብሎሽ** ዝ.ከ.

**ተቀበለ** ግ 1. ወሰደ፥ እጁ ኣደረገ፥ ተረከበ። 2.ተስማማ፥ ፈቀደ፥ እሺ ኣለ። *የቀረበውን ሃሳብ ኮሚቴው ተቀበለው።* 3. ኣመነ፥ የራሱ ኣደረገ። *ክርስትናን ተቀበሉ*።4. የመጣን እንግዳ ኣስተናገደ። 5. ተስማሚ ሆነ፥ ኣማረ። *የለበሰው ልብስ ተቀብሎታል*። 6.ኣየ፥ ደረሰበት፥ ተሸከመ። *መከራ ተቀበለ/ስቃይ ተቀበሉ*። 7. ኣገኘ፥ወሰደ(ስልጣንን፥ማእረግን፥ ሃላፊነትን፥...)። *ዲቁና ተቀበለ።* 8. በዘፈን፥ በሙሾ፥... ጊዜ ኣውራጁን በድምፅ ኣጀበ፥ ኣደመቀ፥ ኣዝማቹን ኣለ፥ ኣዜመ።

**ተቀባበለ** ግ 1. ኣንዱ ለሌላው እየሰጠ ኣስተላለፈ፥ ኣሸጋገረ። 2. ጠመንጃው ወይም ሽጉጡ ጥይት ጎርሶ ለተኩስ ተዘጋጀ፥ ከቃታው ወደ ጋኑ ገባ።

**አቀበለ** ግ ሰጠ፥ አሻገረ፥ አሳለፈ።

**አቀባበለ** ግ ጠመንጃውን አጉርሶ ለተኩስ አዘጋጀ፤ ጥይቱን ወደ ጋኑ አስገባ።

**ማቀባበያ** ስ የጎረሰን ጥይት ለተኩስ ማዘጋጃ፤ ወደ ጋኑ ማስገቢያ።

**አቀባበል** ስ 1. እንግዳን የመቀበልና የማስተናገድ ስነ ስርአት። *ዛሬ ከውጭ የመጡት እንግዳ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው።* 2. መስተንግዶ። *ሴትየዋ እንግዳ አቀባበል ያውቃሉ።*

**ቀበሌ** ስ 1. ሰፈር፥ መንደር፥ አጥቢያ። 2. ነዋሪዎች በማህበር ተደራጅተው የሚተዳደሩበት የተወሰነ ክልል የያዘ ቦታ፥ አካባቢ። 3. ያንድ ከፍተኛ ከተማ ንኡስ ክፍል። 4. የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ፅህፈት ቤት።

**ቀበሌ ገበሬ ማህበር** ስ በተወሰነ ክልል(ብዙውን ጊዜ በየሃያ ጋሻ) ክልል ውስጥ የሚገኙ ገበሬዎች በማህበር ተደራጅተው የሚገኙበትና የአስተዳደር፥ የኢኮኖሚ፥ የሶሻልና የፖለቲካ ጉዳዮችን በአጠቃላይ የመከታተልና የማስተባበር ተግባር የሚያከናውን ማህበራዊ ድርጅት። ገበሬ ማህበር እየተባለም ይጠራል።

**ቀበሌ "*ቀበለ"** ስር ተመ.

**ቀበረ** ግ 1. ሬሳን ወይም ሌላን ነገር ጉድጓድ ውስጥ አስገብቶ በአፈር፥ በድንጋይ፥... ጉድጓዱን ሞላ፥ ደፈነ። 2. በቀብር ስነ ስርአት ላይ ተገኘ። 3. ደበቀ፥ ሰወረ፥ ሸሸገ። 4.(ዘይ.) ጨቆነ፥ እድገት ከለከለ (የደመወዝ፥ የስልጣን፥...)። 5. ኳስን ወደተጋጣሚው ወገን በኩል አክርሮ ቁልቁል መታ (የመረብን፥ የጠረጴዛ ቴኒስን ኳስ፥...)።

**መቃብር** ስ የሬሳ ማኖሪያ ጉድጓድ፥ ቦታ።

**መቃብር ቆፋሪ** ስ የመቃብር ቦታን እየቆፈረ የሚያዘጋጅ (ሰው)።

**መቃብር ቤት** ስ ብዙውን ጊዜ መነኮሳት፥ የቆሎ ተማሪዎች፥...የሚኖሩበትና በቤተክርስቲያን ክልል ውስጥ የሚገኝ፥ በሙታን መቃብር ላይ የተሰራ ቤት።

**ቀባሪ** ስ 1. ወደ መቃብር ቦታ ሬሳን አጅቦ የሚሄድ ለቅሶኛ። 2. ጉድጓድ ቆፍሮ ሬሳውን አፈር የሚያለብስ።

**ቀባሪ አታሳጣኝ** የክፉ ቀን ወገን፥ ዘመድ አታሳጣኝ ለማለት የሚነገር አባባል።

**ለቀባሪው አረዱት** ጉዳዩን በይበልጥ ለሚያውቀው ሰው እንደማያውቅ አድርገው ነገሩት።

**ቀብር** ስ 1. ሬሳን ለመቅበር የሚደረግ ስነስርአት፤ ስርአተ ቀብርም ይባላል። 2. አስከሬን የሚቀበርበት ቦታ፥ ጉድጓድ፤ መቃብር።

**ተቀበረ** ግ 1. ወደ መቃብር ገባ፥ አፈር ለበሰ። 2. ተደበቀ፥ ተሸሸገ፥ ተሰወረ። 3.እድገት አጣ፥ ተከለከለ (የደመወዝ፥ የስልጣን፥...)።

**አያቀባብርም** ያቀያይማል፥ ያጣላል፥ ያጨካክናል (ነገሩ፥ ጉዳዩ፥ ድርጊቱ)።

**አቀበረ** ግ የዳኑ መስሎ መግል ያዘ፤ ለገመ (ቁስል)።

**አቃበረ (አቀባበረ)** ግ 1. ሬሳን ለቀብር አጅቦ ወሰደ። 2. በቀብሩ ስነስርአት ላይ ተገኘ፥ አገዘ፥ ረዳ።

**አስቀበረ** ግ በቀብሩ ስነስርአት ላይ ተገኘ።

***ቀበረረ**

**ቀብራራ (ቀበረር)** ቅ 1. ደልቃቃ። 2. ሞልቃቃ፥ ልቅ ሆኖ ያደገ።

**ቅብርር አለ** ን ተንቀባረረ።

**ቅብርር አደረገ** ግ አንቀባረረ።

**ተንቀባረረ** ግ 1. ተቀማጠለ፥ ተንደላቀቀ። 2.ተሞላቀቀ፥ ተኩራራ።

**አንቀባረረ** ግ 1. አቀማጠለ፥ አንደላቀቀ። 2. አሞላቀቀ፥ አኩራራ።

**ቀበርቾ** ስ ብዙውን ጊዜ በደጋ የሚበቅል፥ እሾህ ያለውና ስሩ ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

**ቀበሮ** ስ በብዛት ቀይ ዛጎልማና ወርቅማ መልክ፥ ሾጣጣ ጆሮዎችና ረዥም እግር ያለው፥ ጅራቱ ረዥምና በጣም ፀጉራም የሆነ፥ ትናንሽ የቤት እንስሳትንና እንቁላል የሚመገብ ስጋ በል የዱር እንሰሳ(ስእሉን የዱር እንሰሳ ስር ተመ.)።

**የቀበሮ ባህታዊ** ቅ አስመሳይ፥ አታላይ፥ አሳሳች፤ የዋህ፥ ደግ መስሎ በመጠጋት የሚያጠፋ፥ የሚጎዳ።

**የቀበሮ ጉድጓድ** ስ በጦርነት ጊዜ ወታደሮች ለመከላከያ ወይም ለመሸሸጊያ የሚጠቀሙበት ጉድጓድ፥ ጉድብ፥ ምሽግ።

**ቀበቀበ**[1] ግ መሬትን ደጋግሞ አረሰ፥ አለሰለሰ።

**ቅብቅብ** ስ ተደጋግሞ የታረሰ፥ ልስልስ እርሻ።

**ቀበቀበ**[2] ግ 1. የደነዘን ብረት አሾለ፥ አሰላ፥ አተባ። 2. ቸከለ፥ ተከለ፥ ወጋ፥ ወደ ውስጥ አስገባ (ችካልን)። 3.መታ፥ ቆረቆረ፥ አንኳኳ (በርን)።

**ቅብቃብ** ስ ችካል።

***ቀበቀበ**

**ቀብቃባ(ቀበቀብ)** ቅ ገብጋባ፥ ስስታም፥ ቅቅታም፥መስጠት ወይም ማውጣት የማይፈልግ፥ ቆንቋና።

**ቅብቅብ አለ** ግ ተንቀበቀበ።

**ተንቀበቀበ** ግ ተንገበገበ፥ ሰሰተ፥ ቀቀተ።

**አንቀበቀበ** ስ አንገበገበ፥ አሰሰተ፥ አቀቀተ።


**ቀበተተ** ግ ነፋ፣ ወጠረ:: *የበላሁት ምግብ ሆዴን ቀበተተኝ::*

**ቀብታታ (ቀበተት)** ቅ የተነፋ፣ የተወጠረ፣ ያበጠ (ሆድ፣ ስልቻ...)::

**ቅብትት** ዝ.ከ.

**ተቀበተተ** ግ ተነፋ፣ ተወጠረ::

**ቀበቶ** ስ 1. ከቆዳ ወይም ከሸራ ወይም ከጨርቅ፣... የሚሰራና ወገብ ላይ የሚውል መታጠቂያ፤ ስቅ:: 2. በበረራ፣ በጉዞ ላይ ከአደጋ ለመከላከል እንዲረዳ በመኪና ወይም በአውሮፕላን ወንበር ላይ ሆኖ ተሳፋሪው ወይም ነጂው የሚታጠቀው ቀበቶ መሰል ሸራ፣ ቆዳ::



*ቀበቶ 1ኛ ፍቺ*

**ቀበቶህን አጥብቅ** በርታ፣ ጥና፣ ጠንክር::

**ቀበኛ** ስ 1. ልብስና የመሳሰለውን የሚበላ ክብት:: 2. (ዘይ.) (ልብስ + እህል) ተሉ የሚጨርስ፤ የማይበረክትለት::

**ቀበዝባዛ** "ቃበዘ" ስር ተመ.

**ቀበደደ** ግ 1. ነፋ፣ ወጠረ፣ ቀበተተ:: 2. መታ፣ ደበደበ::

**ቀብዳዳ (ቀበደድ)** ቅ ዘርጣጣ፣ ሆዱ የተነፋ::

**ቅብድድ** ዝ.ከ.

**ተንቀበደደ** ግ ሆዱ ገፋ፣ ተነፋ፣ ተንዘረጠጠ::

**አንቀበደደ** ግ አንዘረጠጠ፣ ነፋ፣ አሳበጠ (ሆድን)::

**እንቅብድ** ቅ ዘርጣጣ፣ ሆደ ትልቅ::

**ቀበጠ** ግ 1. ተቀናጣ፣ ባለገ፣ ማድረግ የማይገባውን ነገር አደረገ:: 2. (ዘይ.) ምቾት አገኘ፣ ዘበነ:: *የቀበጠ ጌታ::*

**ቀበጢና** ቅ ቀበጥ::

**ቀበጥ** ቅ 1. ቅልብልብ፣ ክልፍልፍ:: 2. እረፍተ ቢስ፣ ማድረግ የማይገባውን የሚያደርግ:: 3. ቅንጡ::

**የቀባጭ** ስ አያገባው ገብቶ የተናገረ ወይም የሰራ የሚከፍለው መቀጮ::

**ቅብጠት** ስ 1. በመቀናጣት የሚፈፀም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት:: 2. ልፊያ::

**ቅብጥብጥ (ቀበጥባጣ)** ቅ 1. ቀንጥንጥ፣ አርፎ የማይቀመጥ፣ ቅልብልብ:: 2. ብስጩ፣ ነጭናጫ:: *ሆዱ ከመታመሙ የተነሳ ቅብጥብጥ ሆነ::* 3. (ዘይ.) ዘበናይ፣ ቅንጡ::

**ተቃበጠ** ግ ተላፋ፣ ተዳራ::

**አቀበጠ** ግ ቀበጥ አደረገ፣ አሞላቀቀ::

**ተቅበጠበጠ** ግ 1. ተቁነጠነጠ፣ ተወራጨ:: 2. አመሉ ቢስ ሆነ፣ ተበሳጨ፣ ተነጫነጨ::

**አቅበጠበጠ** ግ 1. አቁነጠነጠ፣ አወራጨ:: 2. አበሳጨ፣ አነጫነጨ::

**ቀቢፀ ተስፋ** ስ ተስፋ መቁረጥ::

**ቀባ** ግ 1. አንድን ነገር ለማራስ፣ ለማለስለስ፣ ለማውዛት፣ መልክ ለመስጠት፣... በቅባት ወይም በቀለም፣...ለቀለቀ፣ አበሰ:: 2. የንጉስነት ወይም የነቢይነት ወይም የክህነት፣... ስልጣን ሰጠ፣ ወይም የተፀለየበትን ቅባት በመቀባት ባረከ:: 3. (ዘይ.) ሃጢአተኛ፣ በደለኛ አስመሰለ፣ ስም አጠፋ:: *ስሙን ቀቡት::*

**ቅባት** ስ 1. ከስብ፣ ከወተት ወይም ከሌሎች ነገሮች የሚገኝና ዘይትን፣ ቅቤን፣ ሞራን፣ ቅልጥምን የመሳሰለ ሁሉ:: 2. ከዘይት፣ ከስብ፣ ... ነገሮች ጋር ተቀምሞ በፈሳሽ ወይም በጭቃ መልክ የሚሰራ መድሃኒት ወይም የሰውነት ቆዳን፣ ፀጉርን ማበሻ፣ ማለስለሻ፣ ማውዣ::

**የቅባት እህሎች** ስ እንደ ኑግ፣ ሰሊጥ፣... የመሳሰሉና ዘይት ሊወጣቸው የሚችል የእህል አይነቶች::

**ቅቤ** ስ ከወተት የሚገኝ ቅባት::

**ቅቤን አነገሰ** ቅቤን አንጥሮ ለረዥም ጊዜ አቆየ::

**ቅቤው በሰለ** ቆየ፣ ጠነከረ::

**ቅቤ አንጓች/ጠባሽ** እወደድ ባይ፣ አድር ባይ፣ አሽቃባጭ፣ አዛኝ መሳይ::

**የቅቤ ቅል** ስ 1. ቅቤ መያዣ፣ ማስቀመጫ:: 2. (ዘይ.) አዘውትሮ ቅቤ የሚቀባ::

**የቅቤ ቅል መሰለ** ወዛም ሆነ፣ ወዙ ተቅለጠለጠ::

**የቅቤ አር** ስ ቅቤ ተነጥሮ ሲጠለል ከስሩ የሚቀረው ዝቃጭ፣ አተላ::

**ቅብ** ቅ የተቀባ:: *ወርቅ ቅብ ሰአት አለኝ::*

**ቅብአ መንግስት** ስ ንጉስ ወይም ንግስት ዘውድ ሲጭኑ (ሲነግሱ) በቤተክህነት ሰዎች የሚቀቡት የተፀለየበት ቅባት (ዘይት)::

**ቅብአ ቅዱስ (ቅባቅዱስ)** ስ ከወይራ ፍሬ የሚዘጋጅ የተፀለየበትና ሀፃናት ክርስትና

ሲነሱ፥ ታቦት በሚባረክበት እለት የሚቀቡት ዘይት:: ቅብአ ሜሮንም ይባላል::

**ቅብአ ኑግ (ቅባኑግ)** ስ ከኑግ የሚወጣ ቅባት፥ ዘይት::

**ቅብአክህነት** ስ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ስልጣነ ክህነት በሚቀበሉበት ጊዜ የሚቀቡት የተፀለየበት ቅባት (ዘይት)::

**ተቀባ** ግ የነቢይነት ወይም የካህንነት፥...ስልጣን ተቀበለ፥ ተሾመ ወይም የተፀለየበትን ቅባት በመቀባት ተባረከ::

**ተቀብኦ** ስ ተሰጥኦ::

**ተቀባባ** ግ 1. ተነካካ፥ ተዳረሰ፤ እርስ በርስ አንዱ ባንዱ ላይ ላከከ (ነገርን)::

**ቀባ (ቃባ)** ስ በዋሻ ወይም በገደል ወይም በውስጠ ክፍት ግንድ ውስጥ የሚገኝ ማር ከነንቡ::

**ቀባቆራጭ** ስ የቀባ ማር የሚቆርጥ ሰው::

**ቀባሪ "ቀበረ"** ስር ተመ.

**ቀባዠረ(ቀባጀረ)** ግ ቀባጠረ፥ ዘባረቀ፥ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ::

**ቀባዣሪ** ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፥ ዘባራቂ፥ የሆነ ያልሆነውን የሚናገር::

**አስቀባዠረ** ግ አስቀባጠረ፥ አስዘባረቀ፥ የሆነ ያልሆነው አናገረ::

**ቀባጠረ** ግ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ፥ ለፈለፈ::

**ቀባጣሪ** ቅ (ስድብ) የሆነ ያልሆነውን የሚናገር፥ ለፍላፊ::

**አስቀባጠረ** ግ የሆነ ያልሆነውን አናገረ፥ አስለፈለፈ::

**ቀብራራ "*ቀበረረ"** ስር ተመ.

**ቀብር "ቀበረ"** ስር ተመ.

**ቀብቃባ "*ቀበቀበ"** ስር ተመ.

**ቀብታታ "ቀበተተ"** ስር ተመ.

**ቀብዳዳ "ቀበደደ"** ስር ተመ.

**ቀብድ (ቃብድ)** ስ እቃን ለመግዛት ወይም ለማሰራት በቅድሚያ የሚከፈል ገንዘብ፥ መያዣ::

**ቀተረ[1]** ግ ነፋ፥ አሳበጠ፥ ቀበተተ፥ ወጠረ:: *የቂል በትር ሆድ ይቀትር::*

**ቅትር** ቅ የተነፋ፥ ያበጠ፥ ውጥር::

**ተቀተረ** ግ ተነፋ፥ ተወጠረ፥ አበጠ፥ ተቀበተተ::

**ቀተረ[2]** ግ ቀረቀረ፥ ሸጎረ::

**ቅትርት** ስ ሞፈሩንና በሞፈሩ ግራና ቀኝ ያሉትን ድግሮች አጣምሮ እንዲያያይዝ በተጠቀሱት እቃዎች ቀዳዳ ውስጥ የሚሰካ ቀጭን እንጨት(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

**ተቀተረ** ግ ተቀረቀረ፥ ተሸጎረ::

**ቀተረ[3]** ግ ገተረ፥ ቀሰረ፥ አቆመ::

**ተቀተረ** ግ ተገተረ፥ ተቀሰረ፥ ቆመ::

***ቀተረ**

**ተቀታተረ** ግ ተወዳደረ፥ተፎካከረ፥ ተከራከረ:: *ከባለቀትር አትቀታተር::*

**አቀታተረ** ግ አወዳደረ፥ አፎካከረ፥ አከራከረ:: *ያለአቅሙ ምን አቀታተረው::*

**ቀትር[1]** ስ ቁመና፥ የሰውነት ቅርፅ::

**ቀትረ ቀላል** ቅ ቀጠን ያለና ለአይን ጎላ ብሎ የማይታይ (ሰው)::

**ቀትር[2]** ስ እኩለ ቀን፥ የቀን አጋማሽ::

**የቀትር እባብ** ስ 1. አደገኛ፥ መርዘኛ እባብ:: 2. (ዘይ.) በጣም ተንኮለኛና መርዘኛ የሆነ (ሰው)::

**ቀነሰ** ግ 1. አሳነሰ፥ አጎደለ፥ ከላዩ ላይ አነሳ፥ ዝቅ አደረገ (ብዛትን፥ ክብደትን፥ ቁመትን፥ መጠንን):: 2. ቀድሞ ከነበረው አነሰ፥ መነመነ፥ ዝቅ አለ፥ ጎደለ:: *ከታመመ ወዲህ ሰውነቱ ቀነሰ::* 3. በረድ አለ፥ ታገሰ፥ ሻል አለ (ህመሙ፥ ንዴቱ፥...):: 4. ዝቅ አደረገ፥ አረከሰ (ዋጋን):: 5. ቀድሞ ከነበረው በታች ሆነ፥ ረከሰ (ዋጋ):: 6. ዝግ አደረገ (ፍጥነትን):: 7. ዝግ አለ(ፍጥነት)::

**መቀነስ** ስ ከተወሰነ ቁጥር ወይም መጠን ላይ የተወሰነ ቁጥር ወይም መጠን በማንሳት የሚሰራ የሂሳብ ስሌት መንገድ፤ ከአራቱ የስሌት መደቦች አንዱ::

**መቀነሻ** ስ ከአንድ ነገር ላይ እያነሱ ወደሌላ መገልበጫ፥ ማዛወሪያ እቃ፤ ማቀናነሻም ይባላል:: ለምሳሌ ከጋን የሚቀነስ ጠላ የሚቀመጥበት እንስራ ወይም ገንቦ::

**ቅናሽ** ስ 1. አነስተኛ ወይም ርካሽ ዋጋ:: *በቅናሽ የተገዛ እቃ ነው::* 2. ጠላ ሲሞላ ከላዩ ተቀንሶ የቀረ፤ ሰለልታ::

**ቀናነሰ** ግ ከዚህም ከዚያም ቀነሰ፥ አነሳ::

**ቅንስናሽ** ስ ጋን ሲሞላ ተቀንሶ የቀረ፥ የተረፈ ጠላ::

**ቅንስናሽ ገንዘብ** ስ ዝርዝር፥ ሽርፍራፊ ገንዘብ::

**ተቀነሰ** ግ ከተወሰነ መጠን ወይም ቁጥር ላይ ተነሳ፥ ዝቅ አለ::

**ተቀናሽ** ቅ ከተወሰነ መጠን ወይም ቁጥር ላይ የሚቀነስ ወይም የሚነሳ::

**ተቀናነሰ** ግ ተቀነሰ::

**ተቀናናሽ ሂሳብ** ስ ከተለያዩ መጠኖች ላይ ተቀንሶ የቀረ ሂሳብ::

**አቀናነሰ** ግ ቀነሰ፥አንዱን ከአንዱ ላይ አነሳ ::

**ማቀናነሻ** "መቀነሻ" ን ተመ.

**ቀነቀነ**[1] ግ 1. ነቀዘ፥ ጠነጠነ። 2. በላ፥ አሳከከ።

**ቅንቅን** ስ 1. ነቀዝ፤ የእንጨት፥ የእህል ትል። 2. በጣም ትንንሽ የሆነ ቅጫም መሰል ተባይ (ብዙውን ጊዜ ዶሮ ላይ የሚገኝ)።

**ቅንቅናም** ቅ (ስድብ) 1. ቅንቅን ያለበት፥ የበዛበት። 2. (ዘይ.) ስስታም፥ ንፉግ፥ ቆንቋና።

**ቀነቀነ**[2] ግ መረመረ፥ ፈተሸ፥ ፈተነ።

**ቅንቀና** ስ 1. ምርመራ፥ ፍተሻ (ለጥናትና ምርምር ተግባር የሚደረግ)። 2. ዜማ ማውረድ።

**አቀነቀነ** ግ 1. አዜመ፥ ዘፈንን አወረደ። 2. አራመደ (አላማን፥ ሃሳብን)።

**አቀንቃኝ** ስ 1. የዜማ፥ የዘፈን፥... አውራጅ። ቅ 2. አንድን አላማ አራማጅ።

**ቀነበረ** ግ በእሳት፥ በፀሃይ ተንቃቅቶ ደረቀ፥ ጠና፥ በሰለ (እንጀራ፥ ዳቦ)።

***ቀነበረ**

**ቅንብር** ስ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣም፥ አብሮ እንዲሄድ አድርጎ የማስተካከል ስራ ወይም ውጤት፤ ቅንጅት፥ ጥንቅር። *የሙዚቃ ቅንብር።*

**ተቀናበረ** ግ ተቀናጀ፥ ተጠናቀረ፥ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣምና አብሮ እንዲሄድ ሆኖ ተዘጋጀ፥ ተደራጀ።

**ተቀነባበረ** ዝ.ከ.

**አቀናበረ** ግ አቀናጀ፥ አጠናቀረ፥ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣምና አብሮ እንዲሄድ አድረጎ አዘጋጀ፥ አደራጀ።

**አቀናባሪ** ቅ አዘጋጅ። *ዜና አቀናባሪ።*

**አቀነባበረ** ግ አቀናበረ።

**ቀነበበ** ግ ከበበ፥ ክብ አደረገ።

**ቅንብብ** ቅ መሃሉን ትቶ ዙሪያውን የተላጨ (የራስ ፀጉር ወይም ራስ)።

***ቀነተ**

**መቀነት** ስ ከፈትል የተሰራ የሴቶች የወገብ መታጠቂያ።

**መቀነቷን ፈታች** በልጃገረድነት የመጀመሪያ ባል አገባች።

**መቀነትማ** ቅ የሆዱና የጀርባው መካከለኛ ዙሪያ መቀነት የሚመስል ቅርፅ የያዘ ነጭ መስመር ያለበት (ፍየል)።

**መቀነቻ** ስ 1. መታጠቂያ፥ ወገብ ማሰሪያ ቀበቶ፥ ሰቅ፥...። 2. ኮርቻ ወደ ግራና ቀኝ እንዳይዋልል አጥብቆ የሚይዝ፥ በፈረስና በበቅሎ ሆድ ላይ የሚታሰር ዘለበት ያለበት ጠፍር(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)።

**ቅናት** ስ 1. ሰቅ፥ ቀበቶ፥ መታጠቂያ። 2. መነኩሲዎች፥ ባህታዊዎች፥... ወገባቸውን ጠልፈው በአንገታቸው የሚያጠልቁት፥ በደረት በኩል መስቀልኛነት ያለው ሰንሰለት ወይም ጠፍር።

**ቀነዘረ** ግ 1. ፈጥኖ ደረሰ፥ ያለጊዜው አደገ፥ ፋፋ (ተክል፥ አዝመራ፥...)። 2. ሴሰነ፥ በአንድ ሴት የማይረጋ፥ የማይወሰን ሆነ።

**ቅንዝር** ስ ከፍ ያለ የዝሙት፥ የፍትወት ስሜት።

**ቅንዝረኛ** ቅ (ስድብ፥ ነውር) ሴሰኛ፥ ዘማዊ፥ አመንዝራ።

***ቀነዘነዘ**

**ቅንዝንዝ (ቀነዝናዛ)** ቅ (ስድብ) አርፎ፥ ረግቶ የማይቀመጥ።

**ቅንዝንዝ አለ** ግ ተቅነዘነዘ።

**ቅንዝንዝ አደረገ** ግ አቅነዘነዘ።

**ተቅነዘነዘ** ግ ተንቀዠቀዠ፤ እረፍት፥ እርጋታ አጣ።

**አቅነዘነዘ** ግ አንቀዠቀዠ፤ እረፍት፥ እርጋታ ከለከለ።

**ቀነዘፈ** ግ 1. ቆረጠ፥ ቀነጠሰ፥ ዘነጠፈ፥ ገነጠለ (የተክልን፥ የዛፍን ቅርንጫፍ)።

**ቅንዛፊ** ስ የዛፍ ምልማይ፥ ግንጣይ።

**ቅንዝፍ ቅንዝፍ አለ** ግ ዱብ ዱብ አለ፥ ወረደ(እንባ)።

**ተቀነዘፈ** ግ ተቀነጠሰ፥ ተገነጠለ፥ ተዘነጠፈ።

**ቀነዝናዛ** "*ቀነዘነዘ" ስር "**ቅንዝንዝ**" ን ተመ.

**ቀነደለ** ግ 1. ቀነደበ፥ በጣ፥ ቆረጠ (ቅንድብን)። 2. መታ፥ ደበደበ።

**ቅንድል** ቅ የተቀነደለ፥ የተቀነደበ፥ የተበጣ (ቅንድብን)።

**ተቀነደለ** ግ ተበጣ፥ ተቆረጠ፥ ተቀነደበ።

***ቀነደረ**

**ተሽቀነደረ** ግ 1. የኩራት አለባበስና አካሄድ አሳየ። 2. ተቀናጣ፤ ዘለለ (በደስታ)።

**አሽቀነደረ** ግ አቀናጣ፤ አዘለለ (በደስታ)።

**ቀነደሸ** ግ 1. ሰበረ፥ አነከተ፥ መታ፥ ቀነደበ (ራስን፥ ቀንድን፥ ቅንድብን)። 2. አረጀ፥ ተንቋቋ፥ ጎበጠ።

**ቅንዳሻም** ቅ (ስድብ) ያረጀ፥ የጎበጠ (ሰው)።

**ቀነደበ**[1] ግ 1. ቅንድብን፥ የአይንን ቆብ በጣ። 2. አናትን፥ ቀንድን፥...መታ። 3. ቅንድብን ላጨ፥ ነቀለ።

**መቀንደቢያ** ስ ቅንድብን እየነቀሉ የሚፈለገውን ቅርፅ እንዲይዝ ለማድረግ የሚያገለግል የውበት እቃ።



መቀንደቢያ

**ቅንድብ** ስ ከአይን በላይ አግድም የሚበቅለው ፀጉር ወይም ፀጉሩ የሚበቅልበት ቦታ። በአይን ቆብ ወይም በአይን መሸፈኛ (ክዳን) ጠርዝ ዙሪያ ያለውም ፀጉር ቅንድብ ይባላል(ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

**ቀነደበ**[2] ግ በጉጉት ጠጣ። *ሳንድ ብርሌ ጠጅ ቀነደበና ሄደ።*

**ቀነዳ** ግ ደረቀ፥ ከረረ። *እገሌ ወገቡ ቀንድቶ ጎንበስ ቀና ማለት ሳቅቶታል።*

**ቀንዳ ቀንዳ አለ** ፈጠን ፈጠን ብሎ ተራመደ፥ ሄደ፥ ተሽቀነጠረ። 2- ቀደም ቀደም አለ (በአነጋገር)።

**አቀነዳ** ግ 1. አደረቀ፥ አከረረ። 2. መታ (በሃይል)።

***ቀነጀ**

**መቀናጆ** ስ ከሌላ ሰው በሬ ጋር እየተጣመረ የሚያርስ አንድ በሬ፣ አጣማጅ።

**ቅንጅት** ስ 1. ዝግጅት፥ ቅንብር፥ ጥንቅር። 2 ግንኙነት፥ ጥምረት።

**ተቀናጀ** ግ 1. ተጣማጅ ወይም አጣማጅ አገኘ፥ ከሌላ በሬ ጋር ተጎዳኘ፣ ተጣመደ። 2. ተጣመረ። 3. ተቀናበረ፥ ተስተካከሉ ተዘጋጀ።

**አቀናጀ** ግ 1. አንዱን በሬ ከራሱ፥ ሁለተኛውን ከሌላ አምጥቶ ጠመደ። 2. አጣመረ። 3. አቀናበረ፥ አስተካክሉ አዘጋጀ።

***ቀነጠረ**

**ተሽቀነጠረ** ግ በሃይል ርቆ ተወረወረ፥ ተስፈነጠረ።

**አሽቀነጠረ** ግ አርቆ በሃይል ወረወረ፥ ጣለ።

**ቀነጠሰ** ግ 1. በጠሰ፥ ቆረጠ፥ ጎመደ። *ሳንገቱን በጎራዴ ቀነጠሰው።* 2. የጎመንን፥ የሳማን ቅጠል ከግንዱ፥ የበርበሬን ዛላ ከቂንጡ እየለየ ቆረጠ፥ ቀነጠበ።

**ቅንጥስ አለ** ግ 1. በአጭር ተቀጨ፥ ሞተ። 2. ተቀነጠሰ።

**ተቀነጠሰ** ግ ተቆረጠ፥ ተቀነጠበ።

**ቀነጠበ** ግ 1. በትንሹ ቆረጠ፥ ከጫፍ ቀነጠሰ። 2. በጥቂቱ ወሰደ፥ አነሳ።

**መቀንጠቢያ** ስ በጥጥ መንደፊያ(ደጋን) ላይ የተወጠረን ጅማት ለማንዘር የሚያገለግል የቅል አንገት ቁራጭ(ስእሉን ደጋን ስር ተመ.)።

**ቅንጣቢ** ስ በልኳንዳ ቤቶች ውስጥ ከየብልቱ በትንሽ በትንሹ ተቆርጦ የተጠራቀመ ቁርጥራጭ ስጋ።

**ተቀነጠበ** ግ ከጫፉ ላይ በትንሹ ተበጠሰ፥ ተቆረጠ።

**ተቀነጣጠበ** ግ ተቆራረጠ፥ ተበጣጠሰ፥ ተቀነጣጠሰ።

**ቀነጣ** ግ ኮራ፥ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፥ ታበየ።

**ቅንጡ** ቅ ቀብራራ፥ ቅምጥል።

**ቅንጦት** ስ 1. ከመጠን ያለፈ ድሎት፥ ምቾት። 2. የመንቀባረር፥ የመንደላቀቅ ሁኔታ።

**የቅንጦት እቃ** ስ ለህይወት ወይም ለኑሮ እጅግም አስፈላጊ ያልሆነና ድሎት፥ ምቾት ለማግኘት ሲባል የሚገዛ ውድ እቃ።

**ቅንጦተኛ** ቅ ደልቃቃ፥ ቀብራራ።

**ተቀናጣ** ግ 1. ተቀማጠለ፥ ተኩራራ፥ ቀበጠ። 2.ከሚያስፈልገው በላይ (የማይችለውን፥ የማይገባውን) ላድርግ አለ።

**አቀናጣ** ግ 1. አቀማጠለ፥ አኩራራ፥ አንደላቀቀ። 2. አቀበጠ።

**ቀነጨረ** ግ 1. ሳያድግ፥ ሳይፋፋ ባለበት ጠና፣ ጠነከረ፥ ከረረ። 2. ደረቀ፥ ጠነከረ። *ቆሎው ቀንጭሯል።*

**ቀንጫራ (ቅንጭር)** ቅ ሳያድግ፥ ሳይፋፋ የቀረና በዚያው ባለበት ሁኔታ የጠነከረ፥ የከረረ፣ ድባኖ።

**ቀነጨበ** ግ 1. ቆነጠረ፥ ቆንጥሮ ወሰደ። 2. በገበጣ ጨዋታ ላይ ጀማሪ ሆነ፥ የጅመራውን ዙር ተጫወተ።

**ቅንጫቢ** ስ የተቆነጠረ፥ የተቀነጨበ ጥቂት ነገር።

**ቀነፈ** ግ 1. የልብስን ጫፍ ዳር ዳሩን አጥፎ፥ ቀልብሶ ሰፋ። 2. የቅንፍ ምልክት አኖረ።

**ቅንፍ** ስ 1. የተቀነፈ፣ ወደላይ ታጥፎ፥ ተቀልብሶ የተሰፋ ክፈፍ። 2. አንዱን ከሌላው ለመለየት፥ በአማራጭነት ለማስቀመጥ፥ ለማብራራት፥... ከአንድ ፊደል፥ ቃል ወይም አረፍተ ነገር ግራና ቀኝ የሚቀመጥ ደጋንማ ምልክት፣ ምልክቱም " ( )" ነው።

**ቅንፋት** ስ እጥፋት፥ ቅልብሳት።

**ቀኛ**[1] ግ 1. ተመቀኘ፥ ሌላው ባደረገው ወይም ባገኘው ተከፋ፥ ተናደደ። 2. ሌላው ያገኘውን መልካም ነገር በማየት ለራሱም ተመኘ። 3. የትዳር ጓደኛን ወይም ፍቅረኛን እነጠቃለሁ፥ አጣለሁ ወይም ከሌላ ጋር የፍቅር ግንኙነት

ይኖራል በሚል ስጋት የንዴት፥ የብስጭት፥ የመብከንከን ስሜት ተሰማው።

**ቀናተኛ** ቅ 1. ምቀኛ፤ ሌላው ባደረገው ወይም ባገኘው የሚከፋ፥ የሚናደድ። 2. የሚቆጭ፥ የሚቀረቀር። *የኢትዮጵያ ህዝብ ለሃገሩ ነፃነት ቀናተኛ ነው።* 3. የቅናት ስሜት ያለበት።

**ቅናት** ስ 1. የምቀኝነት ስሜት፤ ሌላው ባለው፥ በሚያገኘው ወይም በሚያደርገው መከፋት፥ መናደድ። 2. በሌላው መልካም ነገር የመደሰትና ለራሱም የመመኘት ስሜት።3. የትዳር ጓደኛን ወይም ፍቅረኛን አጣለሁ፥ እነጠቃለሁ፥...በሚል ስጋት የሚፈጠር የብስጭት፥ የመከፋት፥ የንዴት ስሜት ወይም አድራጎት።

**ቅናተኛ** ቅ የቅናት ስሜት ያለበት።

**አስቀና** ግ 1. ለቅናት መነሻ ምክንያት ሆነ፥ ወደ ቅናት ገፋፋ። 2. ያደረገው ወይም የተደረገው፥ የተሰራው መልካም ነገር በሌላው ላይ የበጎ ቅናት ስሜት አሳደረ፥ አጓጓ፥ አተጋ።

**ቀና²** ግ 1. ቀጥ አለ፥ ረታ (የጎበጠው፥ የተጣመመው)። 2. ቀጥ አለ፥ ቆመ፥ ተነሳ (ተጋድሞ የነበረው)። 3. ተሳካ፥ ተከናወነ፥ ሰመረ። *የሄድክበት ቀናኝ*። 4. በመታረስ ወይም መኖሪያ በመሆን እንዲያገለግል ተደረገ፥ ለማ (ቦታ)። 5. እርሻ ለመደ፥ ተማረ፥ ሰላ፥ ተንከባከበ (ወይፈን)። 6.ገባ፥ ሰረፀ። *ትምህርቱ ቀናው* ። 7. አሻረ፥ አዳነ። *ከሰው ቀናው*። 8. ተስተካከለ፥ ታረመ።ቅ 9. ገር፥ የዋህ። 10. ምቹ፥ ቀላል። 11. ጥሩ፥ ደግ፥ ተንኮል የሌለበት (*አስተያየት ወይም አስተሳሰብ*)። 12. አስቸጋሪ ያልሆነ፥ ጠማማነት የሌለው፥ ቀጥታ የሆነ።

**ቀና በቀና/ቀና ለቀና** አንፃር ለአንፃር፥ ፊት ለፊት። *ቀና በቀና ተናገረ።*

**ቀና አለ** ግ 1. ቀጥ አለ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረው)። 2. እንደመቆም፥ እንደመነሳት አለ ተጋድሞ የነበረው)።

**ቀና አደረገ** ግ አቀና፥ ቀጥ አደረገ (ጎብጦ የነበረውን)። 2. እንደማቆም እንደማንሳት አደረገ (ተጋድሞ የነበረውን)።

**ቅናት** ስ የድምፅን ተነሽነት የሚያሳይ የያሬዳዊ ዜማ ምልክት።ምልክቱም(ʕ)ነው።

**ቅን** ቅ 1. ደግ፥ ገር፥ ክፋት፥ ተንኮል የሌለው (ሰው)። 2. ጥሩ፥ ገር የሆነ፥ ክፋት የሌለው (ሃሳብ፥ አስተያየት)።

**ቅኝ [ግዛት]** ስ በሌላ አገር መንግስት የተወረረና በወራሪው መንግስት ቁጥጥር ስር የሚተዳደር፥ ነፃነቱን ያጣ አገር።

**ቅኝ አገዛዝ** ስ ሌላን አገር በመውረር የብዝበዛና የጭቆና አስተዳደር የማካሄድ ፖሊሲ።

**ቅኝ ገዢ** ስ ሌላን አገር በወረራ በመያዝ በቁጥጥር ስር አድርጎ የሚያስተዳድር መንግስት።

**ተቃና** ግ 1. ቀጥ እንዲል ተደረገ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረው)። 2. ተሳካ፥ ሰመረ። *እድሉ ተቃና።*

**አቀና** ግ 1. ሸጠ (እህልን)። 2. አቅጣጫ ያዘ፥ አመራ። *ፊቱን ወደ ሰሜን አቀና።* 3. ለመኖሪያ፥ ለእርሻ፥ ለአስተዳደር ምቹ እንዲሆን አደረገ፤ አለማ (ቦታን፥ አገርን)።

**አቅኚ( አቅኝ)** ቅ አልሚ (አገርን፥ ቦታን)።

**አቃና** ግ 1. ቀጥ አደረገ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረውን)። 2.አሳካ፥ አሳመረ፥ ጥሩ አደረገ። *እድሉን አቃናለት*። 3. አስተካከለ፥ አረመ።

**ቀናተኛ** "ቀና¹" ስር ተመ.

**ቀናነሰ** "ቀነሰ" ስር ተመ.

**ቀን** ስ 1. (ብ.ቁ. **ቀናት**) ሃያ አራት ሰአታት የሚሆን የብርሃንና የጨለማ ጊዜ። *አንድ አመት ሶስት መቶ ስድሳ አምስት ቀናት አሉት*። 2. ከጠዋት እስከ ማታ ያለው የብርሃን ጊዜ። *ቀን ቀን እየተጓዝን ማታ ማታ ከድንኳን እናድር ነበር*።3. ወቅት፥ ጊዜ። *ያጣም ያገኝና ያገኘም ያጣና፥ ያስተዛዝናል ይሄ ቀን ያልፍና።* 4. ሰአት፥ ጊዜ። *ቀኑ እንዴት ይርቃል?* 5. የተወሰነ፥ የተጠበቀ ጊዜ፥ ቀጠሮ። *ቀኑ ደርሶ ነው የሞተው /የመውለጃዋ ቀን ደርሷል።*

**ቀኑ ስንት ነው?** የወሩ ስንተኛው እለት ነው?

**ቀኑ ነደደ** የእለቱ የፀሃይ ሙቀት በረታ፥ አየለ፥ ቃጠሉ ሆነ።

**ቀኑ ከበደ** ደመና ሆነ፤ ጨፈገገ፥ ሰማዩ ጠቆረ።

**ቀኑ ደረሰ** የመሞቻው፥ የመጥፊያው ጊዜ ተቃረበ፥ መጣ።

**ቀን ሆነ** ረፈደ፥ ወደእኩለ ቀን ተጠጋ።

**ቀን ሰጠ** 1. ጊዜን በማራዘም ፋታ ሰጠ። 2. ጊዜው፥ ወቅቱ አመቸ፤ የፈለጉትን ለማድረግ አስቻለ።

**ቀን ቆረጠ** ጊዜ፥ ቀጠሮ ወሰነ።

**ቀን ወጣ** 1. የችግር ጊዜ አልፎ የብልፅግና፥ የጥጋብ ጊዜ ተተካ። 2. ዝናቡ ቆመ፥ ፀሃይ ወጣ፥ ብራ ሆነ።

**ቀን ወጣለት** ከችግር ተገላገለ፥ አለፈለት፥ ተመቸው።

**ቀን ጎደለበት** የመከራ፥ የአደጋ፥ የችግር ቀን ሆነበት፥ አደጋ አጋጠመው።

**ቀነ ጎደሎ (የቀን ጎደሎ)** ለአደጋ፥ ለመከራ የሚዳርግ መጥፎ አጋጣሚ የሚያጋጥምበት ቀን።

**ቀን ጣለው** ደሀየ፥ ተቸገረ (ቀድሞ ሃብታም የነበረው)።

**ቀኗ ደረሰ** የመውለጃዋ ጊዜ ተቃረበ።

**ቀን ለቀን** ተው.ግ. በቀን፥ ብርሃን ባለበት ጊዜ።

**ቀን በቀን** ተው.ግ 1. ሁል ቀን፥ ሁልጊዜ። 2. በቀን፥ ብርሃን ባለበት። *ቀን በቀን ሌባ ከቤቱ ገብቶ ዘረፈው።*

**ቀነ ቀጠሮ** ስ የቀጠሮ እለት (የፍርድ ቤት፥...)።

**ቀን መቁጠሪያ** ስ የአመቱ ወራትና ቀናት የሚውሉባቸውን እለታት ለመቁጠርና ለመለየት የሚያስችል ሰሌዳ፥ ሰንጠረዥ።

**የቀን ሰራተኛ/ሙያተኛ** ስ በቋሚነት የተቀጠረበት ስራ የሌለውና በቀን ክፍያ የሚያገለግል የጉልበት ሰራተኛ፤ ሽቃይ፤ ኩሊ።

**የቀን ተማሪ** ስ ቀን ቀን በመደበኛ የትምህርት ሰአት ትምህርቱን የሚከታተል ተማሪ።

**የቀን ጅብ** ምህረት የለሽ፥ ጨካኝ፥ እናት አይምሬ (ያገኘውን ከመንጠቅ፥ ከመብላት፥ ከመግደል የማይቆጠብ)።

**ቀነኛ (የቀንኛ)** ስ (በገጠር አካባቢ የሚባል) ምሳ።

**ቀንበር (ቀምበር)** ስ በእርሻ ጊዜ በሁለት በሬዎች ትከሻ ላይ የሚያርፍና ከሞፈሩ ጋር በምራን የሚያያዝ የግብርና እቃ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

**ቀንበር ተሸከመ** መከራ፥ ስቃይ ተቀበለ።

**የ--ቀንበር** የ--- ሸክም፥ ጫና። *የባርነት ቀንበር።*


**ቀንበጥ(ቀምበጥ)** ስ በጣም ለምለም የሆነው ቅጠል የሚገኝበት የዛፍ ወይም የተክል ጫፍ፥ እፅቅ።

**ቀንዘል** ስ የዛፍ፥ የተክል ቅርንጫፍ።

**ቀንደኛ** "ቀንድ" ስር ተመ.

**ቀንዲል** ስ መቅረዝ።

**ቀንድ** ስ በእንስሳትና በአራዊት ራስ ላይ ሹል ሆኖ የሚበቅል ጠንካራ አካል።




ቀንድ

**ቀንዱን አለው** 1. በቁጣ፥ በስድብ፥... ዝም አሰኘው፥ አሳፈረው። 2. አናቱን፥ ጭንቅላቱን መታው፥ ቀነደበው።

**ቀንደ መለከት** ስ ከቀንድ የተበጀ መለከት።

**ቀንድ አወጣ /አበቀለ** ተናደደ።

**ቀንድ አውጣ (ቀንዳውጣ)** ስ ልብሱ የዛጎል አይነት የሆነ፥ እየተሳበ የሚሄድ፥ ለስላሳ አካል ያለው፥ በክረምት በብዛት የሚታይ ትል።



ቀንድ አውጣ

**የቀንድ ከብት** ስ የበሬና የላም አጠቃላይ ስም። እንደ በሬና ላም ያሉትን እንስሳት ከጋማ ከብቶች ለመለየት የሚያገለግል ስም።

**የቀንድ ዋንጫ** ስ ከቀንድ የተበጀ ዋንጫ።

**ቀንደኛ** ቅ ዋነኛ፥ ግንባር ቀደም (በአብዛኛው ለመጥፎ ድርጊት)።

**ቀንዳም** ቅ ቀንዱ ረዥም የሆነ (በሬ፥...)።

**ቀንጃ** "*ቀነጀ" ስር ተመ.

**ቀንጠልባ** ቅ ለፍላፊ፥ ቀባጣሪ፥ ወሬኛ።

**ቀንጠፋ** ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ፥ እሾህ ያለው የእፀዋት አይነት።

**ቀንጠ** "ቈንጠ[1]" ን ተመ.

**ቀንጫራ** "ቀነጨረ" ስር ተመ.

**ቀኖት** ስ የብረት ችንካር፤ ምስማር።

**ቀኖና** ስ 1-(ክር.) ሱባኤ። 2- ህግ፥ ደንብ፥ ስርአት (የቤተክርስቲያን)። 3- የማይለወጥ፥ የማይሻሻል ህግ፥ ደንብ፥ መመሪያ (ፍልስፍና)።

**ቀኖና ያዘ** ሱባኤ ገባ።

***ቀኘ(ቀነየ)**

**ቅኔ** ስ 1. የተለያዩና የተወሰኑ የዜማ ምጣኔዎች ያሉት፥ እንደ ግጥም ቤት የሚመታ፥ ይዘቱ ውበትና ጥልቅ ምስጢር እንዲኖረው ተደርጎ በልዩ ልዩ የቅኔ መንገድ አይነቶች የሚቀናበርና በትምህርት አማካይነት የሚቀሰም ስነ ቃላዊ ድርሰት። 2. ምስጢር አዘል ንግግር።

**ቅኔ ሰጠ** ለምስጋና፥ ለአክብሮት፥... የሚሆን ቅኔ አበረከተ።

**ቅኔ ቆጠረ** 1. ቅኔ አዘጋጀ። 2. ቅኔ አወቀ፥

ተማረ (በመጠኑ)።
**ቅኔ ነጠቀ** ባለቅኔው አዘጋጅቶ በማሰማት ላይ ካለው ቅኔ ውስጥ ድንቁን ክፍል (ሰንኙ) ሌላው አድማጭ ቀድሞ ተናገረ፥ ሞላ።
**ባለቅኔ** ቅኔ የሚያውቅ፥ የተማረ።
**ቅኔ ማህሌት** ስ በቤተክርስቲያን ውስጥ መዘምራን በመቋሚያ፥ በከበሮና በፀናፅል የሚታጀበውን የምስጋና ዝማሬ የሚያሰሙበት ክፍል።
**ቅኔ ቤት** ስ የቅኔ ትምህርት ቤት።
**ተቀኘ** ግ 1. የመጀመሪያውን ደረጃ የቅኔ ትምህርት ጨርሶና ራሱን ችሎ ቅኔ ለመድረስ ቻለ። 2. ቅኔ አዘጋጅቶ አቀረበ፥ ሰጠ፥ ተናገረ፥ አሰማ።
**አስቀኘ** ግ ቅኔ አስተምሮ እንዲቀኝ አደረገ።
**ቀኝ** ስ 1. የግራ ተቃራኒ፥ አንድ ሰው ፊቱን ወደ ሰሜን ሲያደርግ በስተምስራቅ በኩል የሚገኘው የሰውነት ክፍል፥ አቅጣጫ። 2. (ዘይ.) ምቹ፥ ቀና፥ የማያስቸግር።
**ቀኞች** ስ ወግ አጥባቂ ወይም አድሃሪ የፖለቲካ መስመር ተከታዮች።
**[በ] ቀኝ አውለኝ** በደህና፥ በሰላም አውለኝ።
**ቀኛዝማች** ስ 1. በጦርነት ጊዜ ከዋናው መሪ (ከፊታውራሪው) በስተቀኝ በኩል ባለው የጦር ግንባር ለሚሰለፍ የጦር አለቃ የሚሰጥ የቀድሞ ማእርግ ስም። 2. ቀደም ባለው ጊዜ ለአንዳንድ ባላባቶችና ሃብታሞች ይሰጥ የነበረ የማእርግ ስም።
**ቀኝ እጅ** ስ 1. በስተቀኝ በኩል የሚገኘው የሰው አንደኛው እጅ። 2. መከታ፥ መመኪያ፥ አለኝታ፥ ደጋፊ። *ለገሌ ቀኝ እጁ ነው።*
**ቀኝ እጄን ሰጥቼሃለሁ/አውሼሃለሁ** እንደኔ ሆነህ ምታልኝ፥ ደብድብልኝ።
**ቀኝ ክንፍ** ስ (ፖለ.) ወግ አጥባቂ።
**ቀኝ ጌታ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) ማእርጉ ከርእሰ ደብር በታችና ከግራ ጌታ በላይ የሆነ፥ በቅኔ ማህሌት ውስጥ በስተቀኝ በኩል በመቆም ስርአቱን የሚቆጣጠር ሹም።
**የቀኝ ዳኛ** ስ በፍርድ ስራ ጊዜ ከመሃል ዳኛው በስተቀኝ በኩል የሚቀመጠው ዳኛ።
**ቀወለለ** ግ ቀውላላ ሆነ።
**ቀውላላ (ቀወለል)** ቅ 1. ቁመተ ረዥም። 2. ዘዋሪ፥ ወዲያና ወዲህ የሚል።
**ተንቀዋለለ** ግ 1. ረዘመ፥ ቁመቱ አደገ። 2. ወዲያና ወዲህ አለ፥ ዞረ፥ ያለስራ ተንከራተተ።
**አንቀዋለለ** ግ 1. አረዘመ፥ ቀውላላ አደረገ። 2. አንከራተተ፥ ወዲያና ወዲህ ያለስራ አዞረ።
***ቀወመ**
**መቃወሚያ** ስ መከላከያ።
**ቅዋሜ** ስ አለመስማማት፥ ተቃውሞ።
**ተቃወመ** ግ 1. አለመስማማቱን ገለጠ፥ ነገሩን ሳይቀበል ቀረ፥ ተቃረነ።
**ተቃዋሚ** ቅ 1. ተቀናቃኝ፥ ባላንጣ። 2. ተፃራሪ፥ አማራጭ ሃሳብ ያለው (ሰው)።
**ተቃውሞ** ስ አለመስማማት፥ ቅዋሜ።
**የተቃውሞ ሰልፍ** ስ አንድን ነገር፥ ሃሳብ፥ ድርጊት፥... ለመቃወም የሚደረግ ሰልፍ።
**ቀወሰ** ግ አበደ፥ አእምሮው ተነካ፥ ወፈፈ ሆነ።
**ቀውስ** ስ 1. እብድ፥ ንክ፥ ወፈፌ። 2. የነገሮች መሳከር፥ መዘበራረቅ፥ ውዥንብር።
**ተቃወሰ** ግ 1. ተናጋ። 2. ተምታታ፥ ተሳከረ፥ ተዘባረቀ።
**አቃወሰ** ግ 1. አናጋ፥ አበላሸ። 2. አምታታ፥ አሳከረ፥ አዘባረቀ።
***ቀወቀወ**
**ቀውቃዋ(ቀወቀው)** ቅ ከውካዋ፥ ቀዠቃዣ፥ የማያርፍ።
**ቀውቀውቱ** ዝ.ከ.
**ተንቀወቀወ** ግ ተንከወከወ፥ ተንቀዠቀዠ።
**አንቀወቀወ** ግ አንከወከወ፥ አንቀዠቀዠ።
**ቀውላላ** "ቀወለለ" ስር ተመ.
**ቀውስ**[1] "ቀወሰ" ስር ተመ.
**ቀውስ**[2] **[እሳት]** ስ በህዳር የሚወጣ የኮከብ ስም። በተጨማሪ ኮከብ ቆጠራን ተመ.
**ቀውቀውቱ** "*ቀወቀወ" ስር ተመ.
**ቀውቃዋ** ዝ.ከ.
**ቀውጢ** ቅ ሽብር፥ ሁከት የበዛበት አስቸጋሪ፥ ክፉ (ጊዜ)። *ቀውጢ ቀን/ ቀውጢ ዘመን።*
***ቀዘመዘመ**
**ቅዝምዝም** ስ ውዝግዝግ፥ ምዝግዝግ።
**ተቅዘመዘመ** ግ በአየር ላይ ተውዘገዘገ፥ ተምዘገዘገ (ለምሳሌ ዱላ፥ ዘንግ)።
**አቅዘመዘመ** ግ በአየር ላይ አውዘገዘገ፥ አምዘገዘገ (ዱላን፥ ዘንግን)።
**ቀዘቀዘ** ግ 1. በረደ፥ ሙቀቱን አጣ። *ቡናው ቀዘቀዘ።* 2. ብርድ ሆነ። *ሌሊቱ ቀዘቀዘ።* 3. (ዘይ.) ቀነሰ፥ አነሰ (ጨዋታው፥ ገበያው፥ ጦርነቱ፥...)።
**ቀዝቃዛ** ቅ 1. የበረደ፥ የቀዘቀዘ፥ ሙቅ ያልሆነ። 2. (ዘይ.) ያልደመቀ፥ ያልተጧጧፈ።
**ቀዝቃዛ ጦርነት** ስ የራስን ጥቅም ለማስከበር፥ ሃይልን ለማጠናከርና አንዱ በሌላው ላይ ስጋት፥ ውጥረትና ውዝግብ ለመፍጠር፥

በመንግስታት መካከል የሚካሄድ፥ የመሳሪያ ውጊያ የሌለበት፥ ልዩ ልዩ አይነት ጥቃት፥ ዘመቻ (ድንበር አካባቢ ጦር መሳሪያ ማከማቸትና የጦር ልምምድ ማድረግ፥ የስለላ፥ የሃሰት መረጃ የመናኘት ተግባር)።

**ቅዝቃዜ** ስ ብርድ።

**ተቀዛቀዘ** ግ የብርድ ስሜት ተሰማ።

**ማቀዝቀዣ** ስ ምግብን፥ መጠጥን፥ መድሃኒትንና የመሳሰለውን ነገር ለተወሰነ ጊዜ ሳይበላሽ አቀዝቅዞ የሚያቆይና ፈሳሽ ነገርን ወደ በረዶነት ሊለወጥ የሚችል፥ በሳጥን ወይም በቁምሳጥን ቅርፅ የተሰራ የቤት እቃ፤ ፍሪጅ፥ በረዶ ቤት።

**ቀዘባ** ስ 1. ፍሬ ሊይዝ የተቃረበ የስንዴ፥ የገብስ ፥...ቡቃያ፥ ሰብል። 2.(ዘይ.) ዛላው፥ ቁመናውያማረ፥ የተዋበ፤ ለግላጋ፥ ሰታ።

**ቀዘነ** ግ 1. ቀጭን አይነምድር ተቀመጠ፥ ኮሳ፥ ተፀዳዳ። 2. (ዘይ.) ፈራ፥ ሰጋ፥ ተርበደበደ።

**ቅዘን** ስ ቀጭን አይነ ምድር፥ ተቅማጥ።

**ቅዘን በቅዘን ሆነ** በጣም ፈራ፥ ተርበደበደ።

**ቅዘን ነዳው "ተቅማጥ ነዳው"** ን ተመ.

**ቅዘናም** ቅ (ስድብ) ፈሪ፥ ጸርጻራ፥ ሃሞተ ቢስ፥ ቦቅቧቃ።

**ቀዘዘ** ግ ፈዘዘ።

**ቀዛዛ** ቅ ፈዛዛ፥ የቀዘዘ።

**ቅዝዝ አለው** ፈዘዘ፥ ቀፈፈው።

**ቀዘፈ** ግ በውሃ ላይ በታንኳ፥ በጀልባ፥...ለመሄድ ወይም ለመዋኘት እንዲያስችለው በመቅዘፊያ ወይም በእጅ ውሃውን ወደ ሂዋላው ግራና ቀኝ ገፋ።

**መቅዘፊያ** ስ ታንኳን፥ ጀልባን፥... በውሃ ላይ ለመቅዘፍ፥ ለመምራትና ውሃውን በመግፋት በሚገኝ ተቃራኒ ሃይል ታንኳው ወይም ጀልባው ወደፊት እንዲሄድ ለማድረግ የሚረዳ፥ ከጫፉ ጠፍጠፍ ያለ እቃ፤ ትርክዛ።

**ቀዛዛ "ቀዘዘ"** ስር ተመ.

**ቀዝቃዛ "ቀዘቀዘ"** ስር ተመ.

***ቀዠቀዠ**

**ቀዥቃዣ (ቀዠቀዥ)** ቅ (ስድብ) ከውካዋ፥ አንድ ቦታ ረግቶ የማይቆይ፥ ከለፍላፋ።

**ቀዥቀዥ አለ** ግ ተንቀዠቀዠ።

**ቅዥቅዥ አለ** ግ በጣም ተንቀዠቀዠ።

**ተንቀዠቀዠ** ግ ተንከወከወ፥ ተከለፈለፈ፥ ተቅለበለበ።

**አንቀዠቀዠ** ግ አንከወከወ፥ አከለፈለፈ፥ አቅለበለበ።

***ቀየመ(ቄመ)**

**ቂም** ስ በደል የተፈፀመበት ሰው፥ በተፈፀመበት በደል ምክንያት የሚይዘው የቁጭት፥ የጥላቻ ስሜት፤ ቁርሾ።

**ቂሙን ቀረፈ** ቂሙን ተወ።

**ቂሙን ተወጣ** ተበቀለ፥ የበቀል እርምጃ ወሰደ።

**ቂም አበቀለ** ተቀያየመ፥ ተቃቃረ።

**ቂም ያዘ** 1. አቄመ፥ በተደረገበት በደል ምክንያት የቁጭት፥ የጥላቻ፥ የበቀል ስሜት አደረበት። 2. ቶሎ አልድን አለ፥ አቀበረ፥ አመረቀዘ (ቁስል)።

**ቂም በቀል** ስ 1.ቂምን ለመወጣት የሚወሰድ ወይም የተወሰደ ርምጃ። 2. በቂም ላይ የተመሰረተ ጥላቻ፥ ክፉ ሃሳብ።

**ቂመኛ** ቅ 1.ቂም የሚይዝ፤ የተፈፀመበትን በደል የማይረሳ። 2. ቂም የያዘ፤ የተፈፀመበትን በደል ያልረሳ ጠበኛ፥ ደመኛ። *እኔና እሱ ቂመኞች ነን።*

**ቅያሜ** ስ በፀብ፥ በጥል፥ ባለመስማማት ምክንያት የሚፈጠር ቅሬታ፥ የጥላቻ ስሜት።

**ቅይም አለ** ግ 1. ክፍት አለው ተቀየመ። 2. በድንገት ከፊቱ ላይ የመቀየም፥ ቅር የመሰኘት ስሜት አሳየ። 3. ጠላ፥ ተጠየፈ።

**ተቀየመ** ግ በደረሰበት ወይም በተፈፀመበት በደል ምክንያት ተከፋ፤ ጥላቻ፥ ቅሬታ አደረበት አኮረፈ።

**ተቀያየመ** ግ እርስ በርስ አንዱ በሌላው ቅር ተሰኘ፥ ተኮራረፈ።

**አቄመ** ግ 1. በተደረገበት በደል ምክንያት የቁጭት፥ የጥላቻ፥ የመበቀል ስሜት አደረበት። 2. ቶሎ አልድን አለ፥ አቀበረ፥ አመረቀዘ (ቁስል)።

**አቀያየመ** ግ አጣላ፥ አኮራረፈ።

**አቀያያሚ** ቅ ከሌላው ጋር የሚያጣላ፥ የሚያጋጭ (ነገር፥ ጉዳይ)።

**አስቀየመ** ግ 1. ቅር አሰኘ፥ አስከፋ፥ እንዲቀየም አደረገ። 2. መጥፎ ሆነ፥ አስጠላ፥ አስጠየፈ (መልኩ፥ ስራው፥...)።

**አስቀያሚ** ቅ (ስድብ) አስጠሊታ፥ መጥፎ፥ አስከፊ፥ አስጠያፊ (መልክ፥ ስራ፥...)።

**ቀየረ** ግ 1. ለወጠ፥ ሌላ አደረገ። 2. ተካ። *ዘበኛውን የሚቀይረው ሰው ሳልተገኘም*። 3. ተለወጠ፥ ሌላ ሆነ (መልኩ፥ ቀለሙ፥...)። 4. ተበላሸ፥ ለወጠ (ጣእሙ፥ ሽታው፥...)። 5. አዛወረ፥ ከነበረበት ቦታ ለወጠ።

**መቀየሪያ** ስ መለወጫ፤ ቅያሪ፥ (በትርፍነት ያለ)።

**ቅያሪ (ቅያሬ)** ስ 1. ዝውውር (የስራ ቦታ)።

2. በአንድ ነገር ምትክ የሚሰጥ፥ የሚወሰድ ወይም የሚያገለግል መለወጫ::

**ቅይር አለ** ግ በጣም ተቀየረ፥ ተለወጠ፥ ፊት ከነበረበት ሁኔታ ተለየ::

**ቀያየረ** ግ አንዱን በሌላ ተካ፤ ለዋወጠ::

**ተቀየረ** ግ 1. ተለወጠ፥ ሌላ ሆነ:: 2. ፊት ከነበረበት ሁኔታ፥ መልክ፥ ጠባይ፥... የተለየ ሆነ:: 3. ተዛወረ፥ ለወጠ (ለስራ፥...)::

**ተቀያሪ** ቅ 1. ተተኪ፥ ተለዋጭ፥ ምትክ:: 2. ሊለወጥ፥ በሌላ ሊተካ የሚችል::

**ተቀያየረ** ግ 1. እርስ በርስ አንዱ የሌላውን ወሰደ፥ ተለዋወጠ:: 2. ፊት ከነበረበት ሁኔታ፥ መልክ፥ ጠባይ፥... የተለየ ሆነ:: 3. ተተካካ፥ ተለዋወጠ::

**ተቀያያሪ** ቅ ተለዋዋጭ፥ የሚቀያየር::

**ቀየሰ** ግ የቦታን ርቀት፥ ስፋት፥ ከፍታ፥ አቅጣጫ በሜትር፥ በገመድ፥ በልዩ ልዩ መሳሪያ ለካ፥ ሰፈረ፥ መጠነ፥ ገመገመ::

**ቀያሽ** ስ የቅየሳ ስራ ባለሙያ::

**ቅየሳ** ስ የተወሰነ የቦታን ርቀት፥ ስፋት፥... በተለያዩ ዘመናዊ መሳሪያዎች የመለካት ጥበብ፥ ዘዴ፥ ተግባር::

**ቅያስ** ስ ልክ፥ መጠን፥ ንድፍ (የቦታ፥ የመንገድ፥ የቤት፥...)::

**ተቀየሰ** ግ ተለካ፥ ተመተረ (መንገድ፥ ቤት ለመስራት)::

**ቀየደ** ግ 1. አሰረ፥ ጠፈረ፥ ሰነከለ( የከብት እግርን):: 2. ኩልታፋ፥ ለንባዳ አደረገ፤ መናገር ከለከለ (አንደበትን)::

**መቀየጃ** ስ ማሰሪያ ገመድ፥ ጠፍር::

**ቅይድ** ቅ የታሰረ፥ የተሰነከለ::

**ቀየጠ** ግ ቀላቀለ፥ ደባለቀ::

**ቅይጥ** ቅ 1.ቅልቅል፥ ድብልቅ:: ስ 2. የተለያዩ እህሎችን በመደባለቅ የተዘጋጀ እንጀራ::

**ቅይጥ አለ** ግ ተቀየጠ::

**ተቀየጠ** ግ ተቀላቀለ፥ ተደበላለቀ::

**አቀያየጠ** ግ አቀላቀለ፥ አደበላለቀ::

**ቀያሽ** "**ቀየሰ**" ስር ተመ.

**ቀያቴ** "**ቀላ**" ስር ተመ.

**ቀያየረ** "**ቀየረ**" ስር ተመ.

**ቀይ** "**ቀላ**" ስር ተመ.

**ቀደመ** ግ 1. አለፈ፥ ከፊት ሆነ (በሩጫ፥ በአካሄድ፥...):: 2. መጀመሪያ ሆነ:: *ከእንጀራው ወጡ ቀደመ::* 3. ሌላው ከማድረጉ በፊት እሱ አደረገ፥ ሰራ:: 4. (ዘይ.) ከመመታቱ በፊት አስቀድሞ እሱ መታ (በጥል ላይ)::

**በቀደም** ተው.ግ. አሁን ለታ፥ በቅርብ፥ ካለፉት ቀናት ውስጥ ባንዱ::

**ቀድሞ** ተው.ግ ድሮ፥ ጥንት፥ ፊት::

**ቀድሞውኑ** ፊቱኑ፥ መጀመሪያውኑ:: *ቀድሞውኑ ተናገሬ ነበር::*

**መቅድም** ስ በመፅሃፍ የመጀመሪያ ገፆች ላይ የሚፃፍ፥ አብዛኛውን ጊዜ ስለመፅሃፉ አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ ፅሁፍ::

**ቀደምት** ቅ የቀደሙት፥ የድሮዎቹ፥ የጥንቶቹ፥ የመጀመሪያዎቹ::

**ቀዳሚ** ቅ 1. ፊት መሪ:: 2. የቀደመ:: 3.ጀማሪ::

**ቀዳማ**[1] ስ 1.የመጀመሪያ እርሻ፥ ጭፍለቃ፥ እዳሪ ማውጣት:: 2.የኮርቻ የፊተኛ ድጋፍ:: ቀዳማይ እየተባለም ይጠራል(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)::

**ቀዳማዊ** ቅ አንደኛ፥ የመጀመሪያ::

**ቅደም ተከተል** ስ ተራ፥ ቀዳሚና ተከታይ::

**ቅድመ አያት** ስ የአያት እናት ወይም አባት፤ ሁለተኛው አያት::

**ቅድሚያ** ስ ከሁሉም በፊት የመሆን፥ የመገኘት፥ የማግኘት እድል፥ መብት::

**ቅድሚያ ክፍያ** ስ አንድን እቃ ለመግዛት ወይም አንድን አገልግሎት ለማግኘት አስቀድሞ የሚከፈል ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍያ::

**በቅድሚያ** ተው.ግ. በመጀመሪያ::

**ቅድም** ስ ከጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰአታት በፊት ያለው ጊዜ::

**ቀደም ቀደም አለ** ቸኮል ቸኮል አለ፤ ጠደፍ ጠደፍ አለ፤ ተንቀሳቀሰ::

**ቀደም ብሎ** ተው.ግ. አስቀድሞ፥ በፊት::

**ተቀደመ** ግ 1. ታለፈ፥ ወደሂላ ሆነ:: 2. (ዘይ.) ሳይመታ ተመታ:: 3. እሱ ከማድረጉ በፊት ሌላ ወገን ፈጥኖ አደረገ ወይም ሰራ::

**ተቀዳሚ** ቅ ቀዳሚ፥ በኩር፥ የመጀመሪያ::

**ተቀዳደመ** ግ ተሳለፈ፥ ፊትና ሂላ ሆነ::

**ተሽቀዳደመ** ግ 1. በሩጫ፥ በግልቢያ፥... አንዱ ሌላውን ለመቅደም ተወዳደረ፥ ተፎካከረ:: 2. ቸኮለ፥ ፈጠነ፥ ቀደመ:: *ላይሆንም እያልኩት ተሽቀዳድሞ ሂሳቡን እሱ ከፈለ::*

**አቀዳደመ** ግ አስተላለፈ፥ ፊትና ሂላ አደረገ::

**አስቀደመ** ግ አሳለፈ፥ ፊት አደረገ፥ ቅደሚያ ሰጠ::

**አስቀድመኝ** መጀመሪያ እኔን ግደለኝ (ከምወዳቸው በፊት)::

**አስቀድሞ** ተው.ግ. መጀመሪያ፥ ቀደም ብሎ፥ ከሁሉ በፊት::

**አሸቀዳደመ** ግ በሩጫ፥ በግልቢያ፥... አወዳደረ፥ አፎካከረ።

**እሽቅድድም (እሽቅድምድም)** ስ የሩጫ፥ የግልቢያ፥... ውድድር፥ ፉክክር።

**ቀደሰ** ግ 1. ስርአተ ቅዳሴን ለማካሄድ በተዘጋጀው ስጋወደሙ ላይ ተገቢውን ፀሎትና ምስጋና በማቅረብ ራሱም ቆርቦ ምእመናንን አቆረበ። 2. አነፃ፥ አጠራ፥ ባረከ። 3. ጀመረ።

**ቀዳሽ** ስ የቅዳሴ ስነ ስርአት የሚያከናውን ቄስ ወይም ዲያቆን።

**መቅደስ** ስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት ብቻ የሚገቡበት፥ ታቦቱና መንበሩ የሚገኙበትና ቅዳሴ የሚቀደስበት ክፍል።

**ቅዱስ** (ብ.ቁ.**ቅዱሳን**፤ አን.**ቅድስት**፤ አን. ብ.ቁ. **ቅዱሳት**) ቅ 1. የተቀደሰ፥ የተባረከ፥ የነፃ፥ የበቃ፥ ንፁህ፥ ብሩክ። 2. ጠባየ መልካም። 3. ርኩስ ያልሆነ።

**ቅዳሴ** ስ ስልጣነ ክህነት ባላቸው ቀሳውስት፥ ዲያቆናት፥...አማካይነት በስጋወደሙ ላይ በዜማና በንባብ የሚፀለይ ፀሎት፤ ፀሎቱ የተፃፈበት መፅሃፍም ቅዳሴ ይባላል።

**ቅዳሴ ወጡ** ቅዳሴውን ፈፀሙ፥ አበቁ።

**ቅዳሴ ገቡ** ቅዳሴ ጀመሩ።

**ቅዳሴገባ** የቅዳሴውን ስነስርአት ከሚያከናውኑት አንዱ በመሆን ወደ መቅደስ ገባ።

**ቅዳሴ ጠበል** ስ ከቅዳሴ ስነስርአት በሂላ ምእመናን በፀበል መልክ የሚቀምሱት የተቀደሰበት ውሃ።

**ቅድስና** ስ ቅዱስነት፥ ንፅህና፥ ብሩክነት።

**የተቀደሰ** ቅ የተከበረ፥ የተባረከ።

**አስቀደሰ** ግ የቅዳሴ ስነስርአት በሚካሄድበት ቦታ ተገኝቶ የፀሎቱ ተካፋይ ሆነ።

**አስቀዳሽ** ስ በቅዳሴ ስነስርአት ላይ ተገኝቶ የፀሎቱ ተካፋይ የሚሆን ምእመን።

**ቀደደ** ግ 1. ሰነጠቀ፥ ተለተለ፥ ሸረከተ (ጨርቅን፥ ወረቀትን)። 2. በሳ፥ ሸንቆረ፥ ነደለ። 3. ከፈተ፥ ጀመረ።

**ቀዳዳ** ቅ 1. የተሰነጠቀ፥ የተሸረከተ። *ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ*፡2. ብስ፥ ሽንቁር። 3.(ዘይ.፥ ስድብ) ምስጢር፥ ነገር የማይቋጥር፤ ወሬኛ (ሰው)።

**ቀዶ ህክምና** ስ በአደጋ ወይም በበሽታ ምክንያት የተጎዳን አካል በመቅደድና በመስፋት ህክምና የመስጠት ዘዴ፤ ኦፕራሲዮን።

**ቅዳጅ** ስ ከጨርቅ፥ ከወረቀት፥... ተቀዶ የወጣ ብጫቂ፥ ብጣቂ፥ እራፊ፥ ቁራጭ።

**ቅድ** ስ 1. የልብስ ስፌት የአቀዳደድ አይነት። *ሽንጥላ ቅድ ቀሚስ*። 2. (ዘይ.) ምስጢር የማይቋጥር፥ ወሬኛ።

**ተቀደደ** ግ 1. ተሸረከተ። 2. (ዘይ.) ዋሸ፥ ውሸት ነገር አወራ።

**ተቀዳጅ** ቅ በቀላሉ ሊቀደድ፥ ሊሸረከት የሚችል።

**ተቀዳደደ** ግ በእርጅና ወይም በሌላ ምክንያት ተበጫጨቀ፥ ተሸረካከተ።

**አስቀደደ** ግ ልብስ ለማሰፋት በልኩ አስቆረጠ፥ በልኩ እንዲሰፋለት አደረገ።

**ቀዳ** ግ 1. ፈሳሽ ነገርን፥ ለምሳሌ ውሃን ከወንዝ ወይም ፈሳሹ ከአለበት ቦታ በእቃ አድርጎ በተወሰነ መጠን ጨለፈ፥ ወሰደ። 2.አንቆረቆረ፥ ጨመረ፥ ሰጠ። *ላላፊው ሁለት ብርሌ ጠጅ ቀዳልኝ*። 3. አመጣ። *ውሃ ከቀዳች በሂላ ወደ ገበያ ሄደች*። 4. ገለበጠ (ፅሁፍን ወይም ሌላን ነገር ከሌላው ላይ)። 5. ቀረፀ (ድምፅን)። 6. ኮረጀ።

**ቀዳው** በብዛት አወረደው፥ አቸኀደጎደው። *ዝናቡን ቀዳው/ወሬውን፥... ቀዳው*።

**መቅጃ** ስ 1. መጥለቂያ፥ መጭለፊያ፤ ፈሳሽ ነገር ከአንዱ ወደሌላው የሚገለበጥበት ወይም የሚወሰድበት እቃ። 2. ውሃ የሚቀዳበት ስፍራ፥ ምንጭ፥ ኩሬ፥ ወንዝ፥...። 3. በቴፕ፥ በሸክላ፥... የሚቀረፀውን ድምፅ መቀበያ፥ ማስተላለፊያ መሳሪያ።

**ቅድ** ስ ከአንድ መፅሃፍ ተውጣጥቶ በከፊል የተፃፈ ፅሁፍ። *ቅድ ድጓ*።

**ቅጂ** ስ 1. ጠላ ተጠምቆ፥ ጠጅ ተጥሎ፥ ቅቤ ተነጥሮ፥... የሚገኘው ውጤት፥ የተጣራው ክፍል። *አንድ ጋን ጠላ አራት እንስራ ቅጂ ይወጣዋል*። 2. ከሌላ የተገለበጠ፥ የተወሰደ ፅሁፍ ወይም የተቀረፀ ድምፅ። 3. የመጀመሪያውን መስሉ የተባዛ፥ የተገለበጠ፥ የተቀረፀ (ፅሁፍ፥ ደብዳቤ፥...)፤ ኮፒ።

**ተቀዳው** 1. ወጣው። *ጋኑ አራት እንስራ ጠጅ ተቀዳው*። 2. ብዙ ፈሰሰው። *እንባ ተቀዳው*።

**ቀዳሚ** "**ቀደመ**" ስር ተመ.

**ቀዳማ** ዝ.ከ.

**ቀዳማዊ** ዝ.ከ.

**ቀዳማይ** "**ቀደመ**" ስር የ"**ቀዳማ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ቀዳሚት** "**ቅዳሜ**" ን ተመ.

**ቀዳሽ** "**ቀደሰ**" ስር ተመ.

**ቀዳዳ** "**ቀደደ**" ስር ተመ.

***ቀዳጀ**

**ተቀዳጀ** ግ አገኘ፥ ተጎናፀፈ (ድልን፥ ክብርን፥ ዘውድን)።

**አቀዳጀ** ግ ሰጠ፥ አስገኘ፥ አጎናፀፈ (ድልን፥ ክብርን፥...)::

**ቀጋ** ስ እንጨቱና ፍሬው የፅጌረዳ ተክል የሚመስል፥ እሾህ ያለው የእፀዋት አይነት:: ፍሬውም ቀጋ ይባላል::

**ቀጠለ** ግ 1. ተቋርጦ የነበረውን ስራ፥ ድርጊት፥... እንደገና ጀመረ፥ ማካሄድ ያዘ፥ ገፋ:: 2. ተቋርጦ የነበረው ስራ፥ ድርጊት፥... እነደገና ተጀመረ:: 3. የጀመረውን ስራ ፥ ድርጊት፥... ሳያቋርጥ አካሄደ፥ በዚያው ገፋ:: 4. የተጀመረው ስራ፥ ድርጊት፥... ሳይቋረጥ ተካሄደ፥ በዚያው ገፋ:: 5. ጨመረ፥ አከለ፥ ከፍ አደረገ (ቁመትን፥ ርዝማኔን) :: 6. ከፍ አለ፥ ጨመረ፥ በዛ:: *የኢታው ዋጋ ቀጠለ*: 7. አያያዘ፥ አገናኘ፥ ቋጠረ (የተበጠሰን፥ ለየብቻ የነበረን፥ የተለያየን ነገር):: 8. ተከተለ፥ ለጠቀ፥ ተራ ያዘ:: *ከዚህ ቀጥሎ ሌላ ይመጣል*:: 9. አገባ፥ መስመር ዘረጋ(የውሃ፥ የኤሌትሪክ፥...)::

**ቀጥል** ሂድ፥ አድርግ፥ ጀምር::

**ቀጠሳ** ስ 1. ከወለላ በቀር ከዳና ቀለህ የሌለበት የማር እንጀራ:: 2. በግንብና በካብ ቅጥር ላይ የተቀመጠ የድንጋይ ክዳን፥ ድምድማት:: 3. "ቀፀላ" ን ተመ.

**ቅጥል (ቅፅል)** ቅ 1. የተቀጠለ:: 2. "ቅፅል"ን በፊደል ተራው ተመ.

**ቅጥይ (ቅጥያ)** ስ 1. ቅርንጫፍ፥ አፅቅ:: 2. በሌላ ነገር ላይ የተቀጠለ፥ የተጨመረ፥ የታከለ፤ ዋና ያልሆነ::

**ቀጣጠለ** ግ 1. የተለያየውን ወይም የተበጣጠሰውን እርስ በርሱ አያያዘ፥ ቋጠረ:: 2. ጨማመረ፥ አከለ (ወሬን)::

**ቅጥልጥል** ቅ የተያያዘ፥ ያልተቋረጠ:: *ቅጥልጥል ፅሁፍ / ቅጥልጥል ቤት::*

**ተቀጣይ** ቅ ተጨማሪ ሆኖ የተያያዘ ወይም የሚያያዝ::

**ተቀጥላ (ቲቀፅላ)** ስ 1. ተጨማሪ፥ ተደራቢ፥ ትርፍ ነገር:: 2. በሌላ ዛፍ ላይ ጥገኛ ሆኖ ወይም ተጣብቆ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::

**ተቀጣጠለ** ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተያያዘ፤ ያልተቋረጠ ወይም ቅጥልጥል ሆነ::

**አቀጣጠለ** ግ አንዱን ከሌላው ጋር አያያዘ፥ ቀጣጠለ::

**ቀጠረ**[1] ግ በየተወሰነ ጊዜ በሚሰጥ ክፍያ ወይም ደሞዝ ስራ ለማሰራት ከሰራተኛ ጋር ተዋዋለ፤ ሰራተኛ ወሰደ፥ አስገባ::

**ቀጣሪ** ስ አሰሪ (ግለሰብ፥ ድርጅት፥...)::

**ቀጣሪና አስቀጣሪ** ስ አሰሪና ሰራተኛን የሚያገናኝ አዋዋይ፤ ደላላ::

**ቅጥር** ስ 1. የተቀጠረ፤ ለግለሰብ፥ ለድርጅት ፥...በክፍያ ወይም በደመወዝ የሚሰራ:: 2. አቀጣጠር፤ የአቀጣጠሩ ሁኔታ፥ ክንዋኔ:: *ቅጥሩ የሚከናወነው በዋናው መ/ቤት በኩል ነው::*

**ቅጥረኛ** ስ አንድ ነገር እንዲፈፅም፥ እንዲሰራ በክፍያ ወይም በጥቅም የተገዛ (ብዙውን ጊዜ ለወንጀል ስራ):: *በቅጥረኛ ተገደለ*:

**ተቀጣሪ** ቅ በገንዘብ ወይም በሌላ ጥቅም ተዋውሎ ለግለሰብ፥ ለድርጅት፥... የሚሰራ፥ ግልጋሎት የሚሰጥ::

**ቀጠረ**[2] ግ ቦታና ጊዜ ወስኖ ነገረ (አንድ ነገር ለማድረግ፥ ለመገናኘት፥...)::

**ቀጠሮ** ስ አንድ ነገር ለመስራት፥ ለመገናኘት፥... የሚደረግ የቦታ፥ የጊዜ ውሳኔ:: *የትና መቼ እንደምንገናኝ ቀጠሮ እናድርግ*: 2. ባለጉዳዮች የተስማሙበትና የወሰኑት የመገናኛ ቦታና ጊዜ:: *ቀጠሮህ የትና መቼ ነው?*

**ቀጠሮ ሰጠ** ጊዜና ቦታ ወስኖ ነገረ፥ ቀጠረ (ለመገናኘት፥ አንድ ነገር ለማድረግ)::

**ቀጠሮ ተቀበለ** የትና መቼ መገኘት እንዳለበት አወቀ፥ የቀጠሮው ጊዜና ቦታ ተወስኖ ሲነገረው ተስማማ::

**ቀጠሮ አከበረ** በቀጠሮው ሰአት በቦታው ተገኘ::

**ቀጠሮ አክባሪ** ቅ በተቀጠረበት ወይም በተቃጠረበት ቦታ በጊዜው የሚገኝ::

**ቀጠሮ አፈረሰ** በቀጠሮው ሰአት በቦታው ሳይገኝ ቀረ::

**ቀጠሮ አፍራሽ** ቅ በቀጠሮው የማይገኝ::

**ቀጠሮ ያዘ** የሚገናኝበትን ቦታና ጊዜ ወሰነ፥ አስወሰነ::

**ቀጠሮ ጠየቀ** ቀጠሮ እንዲሰጠው አመለከተ፥ አሳሰበ::

**ተቀጣጠረ (ተቃጠረ)** ግ አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመገናኘት ቦታና ጊዜውን በመወሰን ተስማማ::

**መቃጠሪያ** ስ ቀጠሮ የሚደረግበት መገናኛ ቦታ::

**አቃጠረ** ግ 1. ወንድና ሴትን ለወሲብ ወይም ለፍቅር ስራ አገናኘ፥ አስማማ:: 2. አሳበቀ፥ ወሬ አቀበለ::

**አቃጣሪ** ስ (ስድብ) 1.ወንድና ሴትን ለፍቅር ስራ የሚያገናኝ::2. አሳባቂ፥ ወሬ አቀባይ::

**አስቀጠረ** ግ ጉዳዩ የሚታይበትን ቀን አስወሰነ::

**ቀጠረ**[3] ግ አጠረ፥ ከበበ፥ ከለለ::

**ቅጥር(ቅፅር)** ስ አጥር::

**ቅጥር ግቢ (ቅፅረ ግቢ)** ስ በአጥር የተከለለ ግቢ፥ የተከበበ ቦታ::

**ቀጠሮ "ቀጠረ[2]"** ስር ተመ.

**ቀጠቀጠ** ግ 1. አንድን ነገር ለመስበር፥ ለማጉበጥ፥ ለማቅናት፥ ለመጠፍጠፍ፥... በመዶሻ ወይም በሌላ መሳሪያ ደጋግሞ መታ:: 2.ወቀጠ፥ አደቀቀ፥ ሰባበረ:: 3. ደጋግሞ መታ፥ ደበደበ፥ ጨፈጨፈ:: *ሰውየውን እንደእባብ ቀጠቀጠው*:: 4. መታ፥ ጉዳት አደረሰ:: *መዶሻው ጣቱን ቀጠቀጠው::* 5. አኮላሸ፥ ወቀጠ (የወይፈንን፥ የበግን፥ የዘር ማመንጫ):: 6. አንኳኳ፥ ደጋግሞ በሃይል መታ (በርን፥ ግርግዳን፥...):: 7. ጎዳ፥ አሰቃየ:: *በሽታ ቀጠቀጠው::*

**ቀጥቅጦ ገዛ** ጨቁኖ፥ ረግጦ ገዛ::

**ቀጥቃጭ** ስ (የን.አነ.) ብረትን በማቅለጥና በመቀጥቀጥ የተለያዩ ነገሮችን የሚሰራ የእደጥበብ ባለሙያ::

**ቅጥቃጤ** ስ የሌሊት ቅዠት::

**ቅጥቅጥ** ስ 1. ለመብራትነት የሚያገለግል የተቀጠቀጠ እንጨት:: ቅ 2. የተኮላሸ፥ የተወቀጠ (በሬ፥ ፍየልና በግ):: 3. በመደብደብ፥ በመመታት ወይም በሌላ አደጋ ምክንያት የህመም ስሜት ያለበት አካል ወይም ገላ::

**እንቅጥቃጭ (ቅጥቃጭ)** ስ ገብስና ስንዴን የመሳሰለ እህል፥ ተወቅጦ ወይም ተከክቶ ሲበጠር ወይም ሲንቀረቀብ ተለይቶ የሚወጣው ትንንሹና ስብርባሪው ክፍል::

***ቀጠቀጠ**

**ቀጥቃጣ(ቀጠቀጥ)** ቅ 1. በህመም ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የሚንቀጠቀጥ፥ የሚንዘፈዘፍ:: 2. ስስታም፥ ገብጋባ፥ ንፉግ፥ ቆጥቋጣ:: 3. ፈሪ፥ ቡከን::

**ተንቀጠቀጠ** ግ 1. በፍርሃት፥ በብርድ፥ በበሽታ፥... አካሉ ራደ፥ ተንዘፈዘፈ፥ ተርገፈገፈ:: 2. ሰሰተ፥ ተንገበገበ::

**አንቀጠቀጠ** ግ 1. አራደ፥ አንዘፈዘፈ፥ አርገፈገፈ (ፍርሃት፥ ብርድ፥ በሽታ):: 2.አሰሰተ፥ አስገበገበ:: *አንድ ብር ለመስጠት ምን አንቀጠቀጠህ::*

**አንቀጥቅጦ ገዛ** ሰጥ ለጥ እንዲሉ አድርጎ፥ አስጨንቆ ገዛ::*የአውራጃውን ህዝብ አንቀጥቅጠው ይገዙት ነበር::*

**ቀጠበ** ግ 1. ለካ፥ መጠነ፥ ምልክት አደረገ (ሽማኔ ድርን):: 2. ወሰነ፥ መጠነ (ለምሳሌ እድሜን፥...)::

**መቀጠቢያ** ስ በክንድ የተመጠነ የሸማኔ መለኪያ፤ ድሩ ላይ ምልክት ማድረጊያ እንጨት፥ ዘንግ::

**ቅጥብ** ስ 1. እየተሰራ ባለ የሸማ ድር ላይ በመቀጠቢያ ተለክቶ፥ ተመጥኖ የተደረገ ምልክት:: 2. የእድሜ መጨረሻ፥ ወሰን:: *ቅጥቡ ሲሞላ ሞተ::*

**ቅጥባት** ዝ.ከ.

**ቅጥጥብ** ስ ዝብብት፥ ሽሙጥ::

**ተቀጣጠበ** ግ ተዘባበተ፥ አፌዘ፥ አሽሟጠጠ::

**ቀጠነ** ግ 1. አነሰ፥ ሳሳ፥ ቀነሰ፥ ሰለለ (አካል):: 2. ውፍረት፥ ልድላዴ አጣ፤ ወደ ውሃነት ተጠጋ (ፈሳሽ ነገር)::

**ቀጭን (ቀጪን)(ብ.ቁ.ቀጫጭን)** ቅ 1. ውፍረት የሌለው፥ የሳሳ፥ የሰለለ (አካል):: 2. ውፍረት፥ ልድላዴ የሌለውና ወደ ውሃነት የተጠጋ (ፈሳሽ):: 3. ለቁመቱ ተመጣጣኝ የሆነ በቂ ውፍረት የሌለው (ሰው)::

**ቀጭን እመቤት** *ራሷን የቻለች ሃብታም ሴት::*

**ቀጭን ጌታ** *ራሱን የቻለ ሃብታም ሰው::*

**ቀጭን ሰጥር** ስ 1.ከጎድን ሁሉ የምትቀጥን ቀጭን የጎን አጥንት:: 2. እንደውጋት አድርጎ የሚያም የወገብ ላይ በሽታ::

**ቀጭን ድምፅ** ስ ጎርናና ያልሆነ ወይም እንደፋጨት ያለ ድምፅ::

**ቀጭን ፈታይ** ቅ በፈትል ስራ ባለሙያ የሆነች፥ በቀጭኑ የመፍተል ችሎታ ያላት (ሴት)::

**ቀጠና** ስ የረሃብ ዘመን፤ ችጋር::

**ቀጠጠ[1]** ግ 1.እንዳይበላለጥ አድርጎና አስተካክሎ ሸለተ፥ አጨደ፥ ቆረጠ፤ ቁመቱን አሳጠረ (ለጠጉር፥ ለሳር፥...)::2. ጉብጠትን፥ ጠማማነትን እያነፀ፥ እየቀረፀ አስተካከለ፥ አሳመረ::

**ቀጠጠ[2]** ግ ነፋ፥ ቀበተተ፥ አሳበጠ (ሆድን)::

**ተቀጠጠ** ግ ተነፋ፥ ተቀበተተ፥ አበጠ::

**ቀጠጥና** ስ ቅርፃቸው የአህያ ጆሮ የሚመስስል ሻካራና አመድማ የሆኑ ሰፋፊ ቅጠሎች ያሉት የእፅዋት አይነት፤ የአህያ ጆሮም ይባላል::

**ቀጠጦ** ስ የማሽላ አይነት::

**ቀጠፈ[1]** ግ 1. ቆረጠ፥ በጠሰ፥ ቀነጠበ (የዛፍ፥ የተክል ቅጠልን፥...):: 2. (ዘይ.)ቀሰፈ፥ ያለጊዜው ገደለ፥ ቀጨ::

**ተቀጠፈ** ግ 1. ተበጠሰ፥ ተቆረጠ፥ ተቀነጠበ:: 2.(ዘይ.) ተቀጨ፥ ተቀሰፈ፥ ያለጊዜው ሞተ::

**ቀጠፈ[2]** ግ አበለ፥ ዋሸ::

**ቀጣፊ** ቅ ዋሾ፥ አባይ፥ አጭበርባሪ::

**ቅጥፈት** ስ ውሸት፥ እብለት፥ ሃሰተኛ ቃል::

**ቀጣጠፈ** ግ አበለ፥ ዋሸ፥ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ::

**ቅጥፍጥፍ አለ** ግ ዋሸ፥ ወሻከተ::

**ቀጣ** ግ 1. ላደረገው ጥፋት ወይም ላደፋሰው በደል አጥፊውን ገንዘብ አስከፈለ፥ አሰረ፥ መታ፥...:: 2. አሰቃየ፥ አጎሳቆለ:: *በአለማችን*

ላይ ረሃብ የቀጣው ህዝብ ቆጥር ቀላል አይደለም:: 3. ከጥፋት እንዲታረምና በስነስርአት እንዲያድግ ገሰፀ፥ ተቆጣጠረ፥ ቆነጠጠ (አሳዳጊ ልጅን፤ ታላቅ ታናሽን):: 4. (ስፖ.) ዳኛ አጥፊ ቡድንን ወይም ተጫዋችን ለተወሰነ ጊዜ ከጨዋታ (ከውድድር) አገደ፥ አስወጣ ወይም ሌላ ውሳኔ ሰጠ::

**መቅጫ** ስ *መግረፊያ፥ መደብደቢያ* (አለንጋ፥ አርጩሜ፥...)::

**ቅጣት** ስ ጥፋት በፈፀመ ግለሰብ፥ ቡድን ወይም ድርጅት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ (የእስር፥ የገንዘብ ክፍያ፥...)::

**[የ]ቅጣት ምት** ስ (ስፖ.) ከፍፁም ቅጣት ክልል ውጭ፥ ከሁለት ቡድኖች የአንደኛው ቡድን ተጫዋች ጥፋት ሲፈፅም (ለምሳሌ ኳስን በእጅ በመንካት፥ በመጋፋት፥ በመጥለፍ፥ አንድን ተጫዋች ለሁለት በመያዝ፥... የመሳሰሉ ጥፋቶች ሲፈፀሙ) ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ ምት::

**ቅጣተኛ** ቅ ቅጣት የተቀበለ ወይም የተበየነበት::

**ተቀጣ** ግ 1. ላደረገው ጥፋት ወይም ለፈፀመው በደል ገንዘብ ከፈለ፥ ታሰረ፥ ተመታ፥ ተገደለ ወይም ሌላ አይነት ጉዳት ደረሰበት:: 2. ተሰቃየ፥ ተጎሳቆለ:: *ህዝቡ በረሃብ ተቀጣ*: 3.(ስፖ.) አጥፊው ቡድን ወይም ተጫዋቹ ለተወሰነ ጊዜ ከጨዋታ (ከውድድር) ታገደ፥ ወጣ ወይም ሌላ ውሳኔ ተወሰነበት:: 4.(ዘይ.) ተሸነፈ፥ ድል ሆነ:: 5. ከጥፋት እንዲታረምና በስነስርአት እንዲያድግ በየጊዜው ምክር፥ ተግሳፅ ወይም ሌላ ቅጣት ተሰጠው:: *ተቀጥቶ ያደገ ልጅ ነው::* 6. ቀደም ሲል በደረሰበት ቅጣት ወይም ችግር ምክንያት ጥፋቱን እንዳይደግም ትምህርት ወሰደ::

**መቀጫ(መቀጮ)** ስ ጥፋተኛ የሚከፍለው ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር:: *ያለብህን እዳ በወቅቱ ካላጠናቀቅህ መቀጫ ትከፍላለህ::*

**መቀጫ ጣለ** ቅጣት በየነ፥ ወሰነ::

**መቀጣጫ** ስ 1. ጥፋቱ ወይም ስህተቱ ዳግም እንዳይፈፀምና ለአጥፊውም ሆነ ለሌላው ሰው ትምህርት (ማስፈራሪያ) እንዲሆን የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከባድ ቅጣት:: 2. መዘባበቻ::

**ቀጣሪ "ቀጠረ"** ስር ተመ.

**ቀጣኒት** ስ ትንሽ ጉልማ መሬት::

**ቀጣና** ስ 1. በገደልና በገደል መካከል ያለ የሰውና የከብት መሂጃ፥ መተላለፊያ ቀጭን መንገድ:: 2. የተወሰኑ ቦታዎችን ወይም አካባቢዎችን የሚያጠቃልል መልክአምድራዊ ክልል::

**ቀጣጠለ "ቀጠለ"** ስር ተመ.

**ቀጣጠፈ "ቀጠፈ"** ስር ተመ.

**ቀጣጥይ "ቅጣጥይ"** ን ተመ.

**ቀጣፊ "ቀጠፈ[2]"** ስር ተመ.

**ቀጤማ "ቄጠማ"** ን ተመ.

**ቀጥ**

**ቀጥታ** ቅ ጠማማ ወይም ወልጋዳ ያልሆነ::

**[በ] ቀጥታ** ተው.ግ. ወደሌላ ቦታ ሳይኬድ:: *በቀጥታ ወደ ስራ ላስኪያጅ ቢሮ ሄደ::* 2. ፊት ለፊት፥ በግልፅ፥ ሳይድበሰበስ (ቅኔነት፥ አሽሙር፥... በሌለበት አነጋገር):: *ምክንያት ከምታበዛ በቀጥታ ለምን አልችልም አትልም?*

**ቀጥታ ስልክ** ስ በማዞሪያ በኩል ያልሆነ፥ ወደተፈለገበት ቦታ በቀጥታ መደወል የሚያስችል ስልክ::

**ቀጥተኛ** ቅ ያልተጣጣመ፥ ያልተወላገደ፥ ትክክለኛ የሆነ (መስመር፥ መንገድ፥...):: 2. ግልፅ የሆነ፥ እውነተኛ፥ ትክክለኛ (ሰው):: 3. በሌላ በኩል ወይም በተዘዋዋሪ ያልሆነ:: *በመካከላችን ቀጥተኛ ግንኙነት አለ::*

**ቀጥ አለ** ግ 1. ቆመ፥ ተገተረ:: 2. መንቀሳቀሱን ተወ፥ ረጋ:: 3. ጎበጠ፥ ተጣሞ፥ ተወላግዶ የነበረው ተስተካከለ፥ ቀና:: 4. ስነስርአት ያዘ (በቅጣት፥ በተግሳፅ፥ በምክር፥...የተነሳ):: 5. መስራት አቆመ (በብልሽት ወይም በሌላ ምክንያት):: *ሰአቴ ቀጥ አለች*: 6. ተቋረጠ፥ ቆመ፥ ተወ:: *ዝናቡ ቀጥ አለ::* 7. መንገዳገዱን ተወ፥ ሚዛኑን ጠበቀ:: *ህፃኑ ቀጥ ብሉ መሄድ ጀመረ::*

**ቀጥ ብሎ** ተው.ግ. ወዲያ ወዲህ ሳይል፥ ሳያመነታ::*ቀጥ ብሉ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ::*

**ቀጥ አደረገ** ግ 1. አቆመ፥ ገተረ:: 2. እንዳይንቀሳቀስ አደረገ:: 3. ጎብጦ፥ ተጣሞ ፥ተወላግዶ የነበረውን አስተካከለ፥ አቃና:: 4. ስነስርአት አስያዘ (በመቅጣት፥ በመገሰፅ፥ በመምከር፥...):: 5. እንዳይሰራ አደረገ:: *ሞተሩን ቀጥ አደረገው::* 6. አቋረጠ፥ አቆመ፥ አስተወ:: *መድሃኒቱ ሳሉን ቀጥ አደረገለት::*

**ቀጥ አድርጎ** በደንብ አስተካክሎ፥ ያለችግር:: *ስራውን ቀጥ አድርጎ የሚሰራው እሱ ነው::*

**ቀጥቃጣ "*ቀጠቀጠ"** ስር ተመ.

**ቀጥቃጭ "ቀጠቀጠ"** ስር ተመ.

**ቀጨ[1]** ግ 1. አክርማን፥ ስንደዶን ከአንጓው ወይም ከቅልጥሙ ላይ እየሰበረ ሰበሰበ::2. በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ አደጋ የአካል መናጋት፥ የስር መዞር፥ ወለምታ፥... አደረሰ:: *ህፃኑን ስትሸከም በጥንቃቄ ካላነሳህው ልትቀጨው ትችላለህ::* 3. (ዘይ.) ሁ-ቀሰፈ፥ ገደለ (በልጅነት):: ለ- ከመጀመሪያው በአጭሩ አስቀረ፥ አሳጠረ (ነገርን፥ ሃሳብን፥...)::

**ቅጭት** ስ በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ

አደጋ የደረሰ የአካል መናጋት፥ የስር መዞር፥ ወለምታ።

**ተቀጨ** ግ 1. በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ አደጋ የአካል መናጋት፥ የስር መዞር፥ ወለምታ፥ ... ደረሰበት። 2. (ዘይ.) ሀ-ተቀሰፈ፤ በልጅነት፥ ያለእድሜው ሞተ። ለ-ከመጀመሪያው በአጭሩ እንዲቀር ተደረገ (ሃሳብ፥ ነገር፥...)።

**ቀጨ**[2] ግ እጅን፥ ከንፈርን፥...ሰነጣጠቀ፥ ሰነታተረ (ብርዱ፥ ውርጩ፥...)።

**ቀጭ** ስ በብርድ፥ በውርጭ የሚመጣ የእጅ፥ የከንፈር፥...መሰነጣጠቅ።

**ቀጨለ "ቃጨለ"** ን ተመ.

**ቀጨመ** ግ ቅጫም ያዘ፥ አፈራ።

**ቅጫም(ቅማጭ)** ስ የጤፍ ፍሬ የሚያካክልና ነጣ ያለ የቅማል እንቁላል።

**ቅጫማም** ቅ (ስድብ) ቅጫም ያለበት፥ ንፅህናውን የማይጠብቅ።

***ቀጨመ**[1]

**ቀጨማ(የቀጨማ)** ስ የጠፋ ከብት ይዞ ላመጣ ወይም ላሳደረ፥... የከብቱ ባለቤት የሚከፍለው ገንዘብ፤ የጅብ አፍም ይባላል።

**ቀጨም አደረገ** ግ አፈፍ፥ ለቀም አደረገ፥ ያዘ።

***ቀጨመ**[2]

**ቅጭም አለ** ግ ከሃዘን፥ ከድንጋጤ፥... የተነሳ ፊቱ ኩስትር፥ ቁጥር፥ ቅይም የማለት ወይም የመከፋት መልክ አሳየ።

**አቀጨመ** ግ ከሃዘን፥ ከድንጋጤ፥... የተነሳ ፊቱን አከፋ፥ አጠቆረ፥ ቋጠረ።

**ቀጨሞ** ስ ፍሬው ሲቃምሱት የሚጎመዝዝና የኩሶ መድሃኒት ነው የሚባል የእፀዋት አይነት።

**ቀጨቀጨ** ግ 1. በጥርሱ ሰባበረ፥ አደቀቀ፥ ፈጨ። 2. ደጋግሞ ነከሰ፥ በላ።

**ተንቀጫቀጨ** ግ 1. እርስ በርሱ በመጋጨት ወይም በንቅናቄ የተነሳ ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ ሰጠ (ብረታ ብረት፥...)።

**አንቀጫቀጨ** ግ እርስ በርስ በማጋጨት ወይም በማንቃነት ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

**ቀጨጨ** ግ በሚገባው መጠን ሳያድግ፥ ሳይወፍር ቀረ።

**ቀጫጫ** ቅ 1. ኮስማና፥ ኮሳሳ፥ ደቃቃ (ለእፀዋት)። 2.(ስድብ) አጭር፥ ቀጭን (ለሰው)።

**ቀጭ "ቀጨ[2]"** ስር ተመ.

**ቀጭ**

**ቀጭ አለ (እቀጭ አለ)** ግ ምስማር በመዶሻ ሲመታ፥ ድንጋይና ድንጋይ ሲጋጭ፥ ደረቅ እንጨት ሲሰበር፥... የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ።

**ቀጭ አደረገ (እቅጭ አደረገ)** ግ ድንጋይና ድንጋይ ሲጋጭ፥ ደረቅ እንጨት ሲሰበር የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

**ቀጭ ቀጭ አደረገ** ግ 1. ቆረጠመ (ቆሎን)። 2. መታ፥ ቀጠቀጠ (ለምሳሌ ምስማርን፥ ቆርቆሮን፥...)።

**ቀጭ ቀንቧ አለ** የአካሄድ ሁኔታን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ቀጭ ቀንቧ እያለች መጣች።*

**ቀጭቋ አለ (እቀጭ እቋ አለ)** በቀጭኑ የሚሰማን የጫማ ኮቴ ድምፅ አይነት አሰማ።

**ቀጭኔ** ስ ቁመቱ ከአራዊት ሁሉ የሚበልጥ፥ አንገቱ ብቻ ሁለት ሜትር ያህል የሚረዝም፥ ቆዳና ፀጉር የለበሱ ሁለት ቀንዶች፥ ረዥም ፀጉር ያለው ጭራ፥ ከረር ያለ ሻካራ ጋማ፥ ስንጥቅ ሸሆና፥ ግንባሩ ላይ ቀንድ መሰል ነገር ወይም ጉንቁል ያለው ቀላ ያለ ቡናማ ሆኖ ነጣ ያሉ መስመሮች የተሰበጣጠሩበት ዥንጉርጉር መልክ ያለው፤ የዛፍ ቅጥቋጦና ሳር የሚመገብና በአፍሪካ የሚገኝ ታላቅ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ቀጭን "ቀጠነ"** ስር ተመ.

**ቀፀለ** ግ 1. የተማረውን መንፈሳዊ ትምህርት እንዳይረሳው በየጊዜው መላልሶ አነበበ፥ ደገመ፥ አዜመ። 2. ተማረ፥ አጠና። *ድጓ የቀፀለው በልጅነቱ ነው።*

**ቅፀላ** ስ (ቤ.ክህ.) ጥናት።

**አስቀፀለ (አስቀጠለ)** ግ መንፈሳዊ ትምህርትን አስተማረ፥ አስጠና።

**ቀፀላ** ስ ካህናት በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ወይም ለፊት መሸፈኛ የሚያደርጉት ስስ ሻሽ።

**ቀፈረ** ግ ጆሮን አቆመ፥ ዘረጋ፥ ቀሰረ፥ አቀና (ለማዳመጥ)።

***ቀፈረረ**

**ቀፍራራ(ቀፈረር)** ቅ 1. ርዝማኔው የሚያስቀይም። 2- ከርፋፋ።3. ከፍራራ።

**ቅፍርር አለ** ግ 1.ተንቀፈረረ፥ በሚያስቀይም ሁኔታ ረዘመ። 2. ተንከፈረረ።

**ተንቀፈረረ** ግ 1. በሚያስቀይም ሁኔታ በጣም ረዘመ። 2. ተንከረፈፈ። 3. ተንከፈረረ።

**አንቀፈረረ** ግ 1. በሚያስቀይም ሁኔታ በጣም አረዘመ። 2. አንከረፈፈ። 3.አንከፈረረ።

**ቀፈቀፈ** ግ 1. (ዘይ.) ብዙ ወለደ። 2. ጠረበ፥ ከረከረ (እንጨትን...) 3. መለመለ (የዛፍ ክንፍን፥ ቅርንጫፍን፥...)።

**ቀፈቀፈች** ግ የታቀፈችውን እንቁላል ፈለፈለች፤ ጫጩት አወጣች(ዶሮ)።

**መቀፍቀፊያ** ስ የሚጠረብበት፥ የሚከረከርበት፥ የሚመለመልበት መጥረቢያ።

**ተቀፈቀፈ** ግ 1. ተፈለፈለ፥ ወጣ (ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ)። 2. በብዛት ተወለደ።

**ቀፈታም** "ቀፈት[2]" ስር ተመ.

**ቀፈት[1]** **(ቀፈድ፥ ቅፍንድ)** ስ ዙሪያውን ችካል የሚወጠርበት የቁርበት ቀዳዳ ወይም ብስ።

**ቀፈት[2]** ስ ትልቅ ሆድ፤ ቦርጭ።

**ቀፈታም (ቀፈዳም)** ቅ (ስድብ) 1. ሆደ ዘርጣጣ፥ ቦርጫም። 2. (ዘይ.) በልቶ የማይጠገብ።

**ቀፈደደ** ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ጠፈረ። 2. ነፋ፥ ወጠረ፥ ቀበተተ (ሆድን)።

**ቅፍድድ (ቅፍድ)** ቅ የተወጠረ፥ የተቀፈደደ (ሆድ)።

**ተንቀፈደደ** ግ ሆዱ ትልቅ ሆነ፥ ተንዘረጠጠ።

***ቀፈደደ**

**ቀፈደድ (ቀፍዳዳ)** ቅ (ስድብ) ፍጥነት፥ ቅልጥፍና የሌለው፤ ከርፋፋ።

**ተንቀፈደደ** ግ ተንከረፈፈ።

**አንቀፈደደ** ግ አንከረፈፈ።

**እንቅፍድ** ቅ (ስድብ) የተንቀፈደደ፥ ከርፋፋ።

**ቀፈዳም** "ቀፈት[2]" ስር ተመ.

**ቀፈድ** "ቀፈት[1]" ን ተመ.

**ቀፈፈ[1]** ግ ጫፍ ጫፉን በመቁረጥ አስተካከለ፥ ከረከመ (ብራናን፥ ቆዳን፥ ቅልን፥...)

**ቅፈፍ** ስ 1. ተከርክሞ የወጣ ቁራጭ (የብራና፥ የቁርበት፥ የቅል፥...) ቁራጭ። 2. አካባቢ፥ ክልል፥ ሰበካ።

**ቅፉፊ** ቅ ተቆርጦ የወጣ፥ ቁራጭ።

**ቀፈፈ[2]** ግ መንደር ለመንደር እየዞረ የእለት ጉርሱን ለመነ፥ ሰበሰበ) የቆሎ ተማሪ፥ ለማኝ)።

**ቀፈፋ** ስ ምግብ ለማግኘት መንደር ለመንደር እየዞሩ የሚደረግ ልመና።

**ቀፋፊ** ቅ ለማኝ።

**አቀፈፈ** ግ አለመነ፥ ተዘከረ፥ ለለማኝ ሰጠ።

**ቀፈፈ[3]** ግ ስሜትን፥ ሰውነትን ደስ አልል አለ፥ አስጠላ፥ ጨፈገገ፥ ከበደ።

**ቀፋፊ** ቅ (ስድብ) ደስ የማይል፥ አስጠሊታ፥ አስቀያሚ።

**ቀፈፋ** "ቀፈፈ[2]" ስር ተመ.


**ቀፋፊ[1]** ዝ.ከ.

**ቀፋፊ[2]** "ቀፈፈ[3]" ስር ተመ.

**ቀፍራራ** "*ቀፈረረ" ስር ተመ.

**ቀፍዳዳ** "*ቀፈደደ" ስር "ቀፈደድ" ን ተመ.

**ቀፎ** ስ 1. ከመቃ፥ ከሃረግ ወይም ከቀጫጭን እንጨት (ከቀጨሞ፥ ከከትክታ፥...) ተወሳስቦ የሚሰራ የንብ ቤት። 2. (ዘይ.) ውስጠ ክፍት፤ ባዶ ነገር።



*ቀፎ 1ኛ ፍቺ*

**ቀፎ ለቀፎ** ስጋ ለስጋ፥ ውስጥ ለውስጥ። *ሰውየውን የመታው ጥይት ቀፎ ለቀፎ ሄዶ ስለወጣ አጥንቱ ደህና ነው፤ አልተሰበረም።*

**ቀፎ ቆራጭ** ስ ከቀፎ ውስጥ ማርን የሚቆርጥ ሰው።

**ቁ** የ"ቀ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ቁላ** ስ 1. (ነውር) የሰውና የእንስሳ ወንዴ አባለዘር፤ የወንዴ ብልት ዘንግ፤ ወይም ዘንጉና ፍሬዎቹ ባንድ ላይ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. መቀርቀሪያ፥ የመዝጊያ መወርወሪያ። *የመዝጊያ ቁላ*። 3. ለመደወያ እንዲያገለግል በደወልና በቃጭል ጉያ የሚንጠለጠል ብረት። *የመረዋ ቁላ*።

**ቁላ ቀረሽ** (ነውር) ወንዳወንድ የሆነች ሴት።

**የቁላ ከብት** ስ ያልተወቀጠ፥ ያልተኮላሸ ከብት።

**ቁሌታም** "ቆላ[1]" ስር ተመ.

**ቁሌት** ዝ.ከ.

**ቁልል** "ቆለለ" ስር ተመ.

**ቁልሊታ** ዝ.ከ.

**ቁልምጫ** "*ቆለመጠ" ስር ተመ.

**ቁልቁለት** "*ቆለቆለ" ስር ተመ.

**ቁልቁል** ዝ.ከ.

**ቁልቋል** ስ 1. በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅልና የሚበላ ፍሬ ያለው እሾሃም የእፀዋት አይነት፤ የባህር ቁልቋልና መንካ ቁልቋልም ይባላል። 2. በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፥ ወተት የሚመስል ፈሳሽ የሚወጣው፥ እሾህ ያለው



*ቁልቋል 2ኛ ፍቺ*

ወይም የሌለው የእፀዋት አይነት።
**ቀልቢጥ** ስ ከቁና የሚያንስ የእህል መስፈሪያ፤ ቃጤ።
**ቀልጭልጭ "*ቆለጨ"** ስር ተመ.
**ቀልፍ "ቆለፈ"** ስር ተመ.
**ቀልፍልፍ** ዝ.ከ.
**ቀመት "ቆመ"** ስር ተመ.
**ቀመና** ዝ.ከ.
**ቀማር "ቆመረ"** ስር ተመ.
**ቀማርተኛ** ዝ.ከ.
**ቀም "ቆመ"** ስር ተመ.
**ቀምጣ "ቆመጠ"** ስር ተመ.
**ቀምጤ** ስ አንጓ ያለውና እንደ ሰርዶ መሬት ላይ የሚተኛ የሳር አይነት።
**ቀምጥማጭ "ቆመጠ"** ስር ተመ.
**ቀምጥምጥ** ዝ.ከ.
**ቀምጥና** ዝ.ከ.
**ቀምጭር (ቀንጭር)** ስ ሸማኔ ጫፉ ላይ ብስ ያለውን የሸማ መጠቅለያ እንጨት የሚሰካበት አናቱ ሹል የሆነ አጭር ችካል(ስእሉን ሸማኔ ስር ተመ.)።
**ቀረን(ቆረን) "ቆረነ"** ስር **"ቆረን"**ን ተመ.
**ቀረንጮ (ቀርንጮ፥ ቆረንጮ)** ስ ያለቀ፥ የደቀቀ አሮጌ ዝተት፤ እላቂ ጨርቅ ወይም ደላጎ።
**ቀሪት** ስ ተቀማጭ ገንዘብ፥ ቅርስ፥ ጥሪት።
**ቀራ** ስ ድፍን ጥቁር ወይም በጀርባውና በደረቱ ላይ ወይም በራሱ ላይ ብቻ ነጭ ያለበት የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።
**ቀራ ይጮህበታል** ባዶ፥ ጠፍ ነው (ቦታ፥ አገር)።
**የቀራ መላከተኛ** ተልኮ የማይመለስ፥ በዚያው የሚቀር።
**የቀራ ጩሀት** ሰሚ የሌለው ጩሀት፥አቤቱታ።
**የቀራ ምሳ** ስ ፍሬው ሲበስል ቀይ የሚሆን የሃረግ አይነት፤ የአሞራ ምሳም ይባላል።
**የቀራ ወስፌ** ስ የእፀዋት አይነት።
**ቀራሽ "ቆረሰ"** ስር ተመ.
**ቀራን "ቁርአን"** ን ተመ.
**ቀራኛ "*ቆረኘ"** ስር ተመ.
**ቀራጫም "ቆረጠ"** ስር ተመ.
**ቀራጭ** ዝ.ከ.
**ቀሬማ** ስ 1. እህል የማያበቅል መሬት። 2.

(ዘይ.) ጨባጣ፥ አይን የማይገባ አጭር (ሰው)።
**ቀር**[1] ስ የብረት ቆብ።
**ቀር**[2]
**ቀር አለ** ግ በገበጣ ጨዋታ ላይ አንድ ጠጠር ሲይዝና ባዶ ቤት ሲያጋጥመው ጠጠሯን አስቀምጦ አረፈ፥ ተራ ለሌላው ሰጠ።
**ቀር**[3] **"ቆረረ**[2]**"** ስር ተመ.
**ቀርምቢ "ቀርንቢ"** ን ተመ.
**ቀርምባጥ "ኩርምባጥ"** ን ተመ.
**ቀርስ "ቆረሰ"** ስር ተመ.
**ቀርስራሽ** ዝ.ከ.
**ቀርሾ (ቅርሾ)** ስ ቂም።
**ቀርሾ ያዘ** ቂም ያዘ።
**ቀርቀምባ** ስ ከገመድ የተሰራ ጠርሙስ መስል የአሳ መያዣ።
**ቀርቀራ** ስ ፍሬው የሚበላ፥ በቆላ አካባቢ የሚበቅል እሾህ ያለው ዛፍ፤ ፍሬውም ቀርቀራ ይባላል።
**ቀርቆሳ "ቆረቆሰ**[1]**"** ስር ተመ.
**ቀርበት** ስ 1. የተለፋ የከብት ቆዳ። 2. የገላ ቆዳ (ሽፋን)።
**ቀርበተ ሞኝ** ለማያውቀው ሰው ሲያዩት ሞኝ የሚመስል (ሰው)።
**ቀርበት ፋቂ "ፋቀ"** ስር **"ፋቂ"** ን ተመ.
**ቀርባ (ቀርምባ)** ስ የሚያስታውክ፥ የሚያስቀምጥ፥ ሰውነትን የሚያደርቅ ድንገተኛ በሽታ።
**ቀርባብቻ "*ቆረበበ"** ስር **"ቆርባብቻ"** ን ተመ.
**ቀርባን "ቆረበ"** ስር ተመ.
**ቀርብቻ "*ቆረበበ"**ስር **"ቆርባብቻ"**ን ተመ.
**ቀርብጭታ "ቆረበጨ"** ስር ተመ.
**ቀርንቢ (ቀርምቢ)** ስ ለመታረድ የደረሰ የፍየል ወጠጤ።
**ቀርንባጥ "ኩርንባጥ"** ን ተመ.
**ቀርንዳድ (ቀርንድድ)** ቅ ቀርንጭጭ፥ ከርዳዳ፥ ቀጥርጥር (ፀጉር)።
**ቀርንጫጭ** ቅ 1. ቀርንዳድ፥ ከርዳዳ፥ ቀጥርጥር (ፀጉር)። 2. (ዘይ.) ነጭናጫ (በአመል)።
**ቀርንጮ "ቀረንጮ"** ን ተመ.
**ቀርንፉድ "ቅርንፉድ"** ን ተመ.
**ቀርአን (ቀራን)** ስ የእስልምና ሃይማኖት ቅዱስ መፅሃፍ።
**ቀርዝ** ስ 1. የበሬ ወይም የወይፈን ብልት (አባለዘር)። 2. ወሸላ፤ ያልተገረዘ የወንድ ብልት።

**ቁርዛም** ቅ (ስድብ) ወሸላ።
**ቁርዬ** ስ እግረ ረዥም አሞራ፤ ሽመላ (በብዛት ሆኖ የሚዘምት)።
**ቁርጠት** **"ቆረጠ"** ስር ተመ.
**ቁርጠኛ** ዝ.ከ.
**ቁርጣ** ዝ.ከ.
**ቁርጥ** ዝ.ከ.
**ቁርጥማት** **"ቆረጠመ"** ስር ተመ.
**ቁርጥራጭ** **" ቆረጠ"** ስር ተመ.
**ቁርጩ [ደሃ]** ቅ አንዳች ነገር የሌለው (ሰው)።
**ቁርጭምጭሚት** ስ በቅልጥምና በጫማ መጋጠሚያ ግራና ቀኝ ከተረከዝ ከፍ ብሎ በስተጎን በኩል የሚገኝ ጉጥ መሰል የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።
**ቁርጭኝ** ስ ከትልቅ መፅሃፍ የተውጣጣ አጭር ፅሁፍ።
**ቁርፍድ** **"ቆረፈደ"** ስር ተመ.
**ቁስ**
**ቁሳቁስ** ስ ልዩ ልዩ የቤት እቃ።
**ቁሳዊ** ቅ ቁስአካላዊ።
**ቁስአካላዊ** ቅ (ፍል.) ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከሀሊና የሚያስቀድም።
**ቁስአካላውያን** ስ ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከሀሊና የሚያስቀድመውና ሃሳባዊነትን የሚቃወመው የፍልስፍና ፈርጅ ተከታዮች።
**ቁስአካላዊነት** ስ ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከሀሊና የሚያስቀድምና ሃሳባዊነትን የሚቃረን የፍልስፍና ፈርጅ።
**ቁስለት** **"ቆሰለ"** ስር ተመ.
**ቁስለኛ** ዝ.ከ.
**ቁስል** ዝ.ከ.
**ቁሻሻ** **"ቆሸሸ"** ስር **"ቆሻሻ"** ን ተመ.
**ቁሸቢያም** **"ቆሸበ"** ስር ተመ.
**ቁሽብ** ዝ.ከ.
**ቁቁ**
**ቁቁታ** ስ ኡኡታ፥እሪታ፤ የድረሱልኝ ጩሀት።
**ቁቁ አለ** ግ ኡኡ፥ እሪ አለ፤ የድረሱልኝ ጩሀት አሰማ።
**ቁቅ**
**ቁቅ አለ** ግ ቀጠን ያለ የፈስ ድምፅ ተሰማ።
**ቁቅ አደረገ** ግ በትንሹ ፈሳ፤ ቀጠን ያለ የፈስ ድምፅ አሰማ።
**ቁባት (እቁባት)** ስ ቅምጥ፤ ውሽማ።
**ቁቤላ** ስ የዝሆን ጊደር።

**ቁብ** ስ ደንታ፥ ግድ። *የፈለግሁውን ብትሆን ቁብ የለኝም።*
**ቁብየለሽ** ቅ ደንታ ቢስ፥ ግድ የለሽ።
**ቁብ̈**
**ቁብ አለ** ግ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወይም ፈረስና በቅሎ ጀርባ ላይ ወጣ፥ ተቀመጠ፤ ጉብ አለ።
**ቁብ̈ ቁብ̈ አለ** ግ የጫማ ኮቴ ድምፅ እያሰማ ተራመደ።
**ቁብላ** ስ ወይፈን።
**ቁቲት (ቁጢት)** ስ የነጠላ፥ የጋቢ፥ የኩታ፥...ዘርፍ፤ የሚቋጨው ክፍል።
**ቁቲት በጣሽ** (የን.እነ.) ሽግኔ።
**ቁትቻ** **"ቆተቸ"** ስር ተመ.
**ቁቻ** ስ የእንጉዳይ አይነት።
**ቁና** ስ ለእህል መስፈሪያ (መለኪያ) የሚያገለግል የስፌት እቃ(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።
**ቁናሳም** **"ቆነሰ"** ስር ተመ.
**ቁናስ** ዝ.ከ.
**ቁንቁኔ** **"ቆነቆነ"** ስር ተመ.
**ቁንቁን** **"ቆነቆነ"** ስር **"ቁንቁኔ"** ን ተመ.
**ቁንን** **"ቆነነ"** ስር ተመ.
**ቁንዲ** **"ቁንዶ"** ን ተመ.
**ቁንዳላ** **"ቆነደለ"** ስር **ቆንዳላ"** ን ተመ.
**ቁንድድ** **"ቆነደደ[1]"** ስር ተመ.
**ቁንድዶ** **"ቆነደደ"** ስር **"ቁንድድ"**ን ተመ.
**ቁንዶ (ቁንዲ)** ቅ ባለሙያ (ሴት)።
**ቁንዶ በርበሬ** ስ በሻይ፥ በወጥ፥... ውስጥ የሚገባ የቅመም አይነት።
**ቁንጅና** **"ቆነጀ"** ስር ተመ.
**ቁንጢጥ** **"ቆነጠጠ"** ስር **"ቁንጥጫ"** ን ተመ.
**ቁንጣሪ** **"ቆነጠረ"** ስር ተመ.
**ቁንጣራ** ስ ፈንጣ።
**ቁንጣን** ስ ብዙ ከመብላት የተነሳ ሆድን የሚወጥር፥ የሚያስጨንቅ የህመም ስሜት።
**ቁንጣናም** ቅ (ስድብ) ያለልክ በልቶ ሆዱ የተነፋ፥ የሚጨነቅ።
**ቁንጥር ቁንጥር አለ** **"*ቆነጠረ"** ስር ተመ.
**ቁንጥንጥ** **"*ቆነጠነጠ"** ስር ተመ.
**ቁንጥጫ** **"ቆነጠጠ"** ስር ተመ.
**ቁንጫ** **"ቆነጨ"** ስር ተመ.
**ቁንጫጪት** **"ቁጫጭ"** ን ተመ.

**ቀንጭር**[1] **"ቀምጭር"** ን ተመ.

**ቀንጭር**[2] **(ጭንቀር)** ስ አብዛኛውን ጊዜ በጉንጭና በአፍንጫ አካባቢ የሚወጣ የቆስል አይነት፤ ሻህኝ::

**ቀንጮ** ስ 1. ዙሪያውን ከተላጨ በሂላ መሃል አናት ላይ የሚቀር የልጅ ፀጉር:: 2. የሳር ቤት ከዳን አናት (ጉልላት የሚቀመጥበት):: 3.(ዘይ.) ዋነኛ፥ የበላይ፥ ታዋቂ፥...::

**ቀንፅል "ቆነፀለ"** ስር ተመ.

**ቀዘማ "ቆዘመ"** ስር ተመ.

**ቀዝር "ቆዘረ"** ስር ተመ.

**ቀዳማ "አቀማዳ"** ን ተመ

**ቀጊያም (ቀጋም) "ቆጋ"** ስር ተመ.

**ቀግ** ዝ.ከ.

**ቀጠባ "ቆጠበ"** ስር ተመ.

**ቀጡ "*ቆጣ"** ስር ተመ.

**ቀጢ** ስ የቡና ቅጠል (ሲደርቅ ታምሶ እንደ ሻይ ቅጠል ተፈልቶ የሚጠጣ)፤ መጠጡም ቀጢ ይባላል::

**ቀጢሳ "ኩቲሳ"** ን ተመ.

**ቀጢት "ቀቲት"** ን ተመ.

**ቀጢጥ አለ "ቆጠጠ"** ስር ተመ.

**ቀጣ "*ቆጣ"** ስር ተመ.

**ቀጣጥ "ቆጠጠ"** ስር ተመ.

**ቀጥር "ቆጠረ"** ስር ተመ.

**ቀጥር "ቋጠረ"** ስር ተመ.

**ቀጥርጥር** ዝ.ከ.

**ቀጥቋጦ "ቆጠቆጠ"** ስር ተመ.

**ቀጥብ "ቆጠበ"** ስር ተመ.

**ቀጥጥር "ቆጠረ"** ስር ተመ.

**ቀጨት "ቋጨ"** ስር ተመ.

**ቀጫጭ (ቀንጫጪት)** ስ መጠኗ አነስተኛ የሆነ፥ መልኳና ቅርጿ ጉንዳን የሚመስል ነፍሳት::

**ቀጭ**

**ቀጭ ብድግ አለ** 1. ተሽቆጠቆጠ፥ ወዲያ ወዲህ አለ (እንግዳን ለማስተናገድ):: 2. ተንቆራጠጠ::

**ቀጭ ነው** በጣም ይመስላል (ከ __ ጋር አንድ አይነት ነው ለማለት የሚነገር):: *አሁን የተወለደው ልጅ አባቱን ቀጭ ነው::*

**ቀጭ አለ** ግ ተቀመጠ፥ ኖረ::

**ቀጭ ብዬ** ስ አጭር የማሽላ አይነት::

**ቀጭ አደረገ** ግ አስቀመጠ፥ አኖረ::

**ቀጮት "ቆጨ"** ስር ተመ.

**ቀፋሮ "ቆፈረ"** ስር ተመ.

**ቀፍ**

**ቀፍ አለች** ግ እንቁላል መጣል አቀማ ተቀመጠች፥ ጭር አለች፤ ጭክ አለች (ዶሮ)::

**ቀፍ ቀፍ አለች** ግ ቀፍ ቀፍ የሚል ድምፅ አሰማች፤ ጨከከች (ዶሮ)::

**ቂ** የ"ቀ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ቂላቂል"ቂለ"** ስር ተመ.

**ቂል** ዝ.ከ.

**ቂመኛ "*ቀየመ"** ስር ተመ.

**ቂም** ዝ.ከ.

**ቂብ**

**ቂብ አለ** ግ 1. ቁብ፥ ጉብ አለ:: 2. ቁጢጥ አለ::

**ቂን**

**ቂን ቂን አለች** ግ (ተራ.አነ.) ልታይ ልታይ አለች::

**ቂንድ** ስ የማሽላን፥ የበቆሎን፥... ፍሬ ከቆረቆንዳው ጋር የሚያያዘው ክፍል::

**ቂንጥር** ስ (ነውር) 1. በሴት ብልት አፍ አካባቢ በላይ በኩል የሚገኝ ቆም ያለ እንጥል መስል አካል:: 2. የሴት አባለ ዘር፤ ብልት::

**ቂንጥራም** ቅ (ነውር፥ ስድብ) ደካማ፥ ፈሪ፥... ለማለት የሚነገር::

**ቂጣ** ስ 1.ዱቄት በወፍራሙ በውሃ ተለውሶ ሳይቦካ ወዲያውኑ የሚጋገር የምግብ አይነት:: 2. በደንብ ያልተጋገረና አይን የሌለው እንጀራ:: 3. ወፍራም፥ ፊተ ከባዳ:: *ቂጣ ፊት ነው::* 4. (ዘይ.) በአስተሳሰብ ያልበሰለ (ሰው)::

**ቂጥ** ስ 1. ከወገብ በታች በስተሂላ በኩል ወጣ ብሎ የሚታይ የአካል ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.):: 2. አካላዊ የኩስ መውጫ፤ ፊንጢጣ:: 3. እንደ እንስራ፥ ብርሌ፥ ጣሳ፥ ብርጭቆ፥... ያሉ እቃዎች የታችኛ ክፍል፤ መቀመጫ:: 4. የመጨረሻ፥ የታችኛ ክፍል:: *የሸንኮራ አገዳ ቂጥ::*

**ቂጡ ቄጠማ ቆረጠ** 1. ከፍርሃት የተነሳ ሰውነቱ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ:: 2. በጣም ተደሰተ::

**ቂጡን ጣለ** 1. ልብሱ ተቀዶ ሰውነቱ ታየ (በተለይ ከወደቂጡ):: 2. አጣ ነጣ፥ ደሀየ::

**ቂጥ ለቂጥ ገጠመ** ተስማማ፥ አበረ፥ አብሮ ሆነ (ለማደም፥ ለማሴር፥...)

**ቂጥ ላሰ** (ነውር፥ የን. አነ.) ተለማመጠ::

**ቂጣም** ቅ ቂጠ ትልቅ::

**ቂኞ**

**ቂጥ አለ** ግ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ተቀመጠ፥ ቁብ አለ::

**ቂጥጥ አለ** ዝ.ከ.

**ቂጥ አደረገ** ግ ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስቀመጠ ፥ አኖረ::

**ቂጥጥ አደረገ** ዝ.ከ.

**ቂጥኝ** ስ ተላላፊ ከሆኑና ሰውነትን ከሚያቆሳስሉ የአባለዘር በሽታዎች አንዱ::

**ቂጥኛም** ቅ (ስድብ) ቂጥኝ ያለበት፥ የያዘው::

**ቃ**[1] የ"ቀ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ቃ**[2]

**ቃ አለ** ግ 1. ደረቅ፥ ቀንበር፥ በሰል አለ (ለቂጣ፥ ለዳቦ):: 2. በመሰበር፥ በመጋጨት፥... "ቃ" የሚል ድምፅ አሰማ::

**ቃ አደረገ** ግ 1. ደረቅ፥ ቀንበር፥ በሰል አደረገ (ለቂጣ፥ ለዳቦ):: 2. በመሰበር፥ በመጋጨት፥..."ቃ" የሚል ድምፅ እንዲሰማ አደረገ::

**ቃቃ አለ** ግ "ቃቃ" የሚል ድምፅ አሰማ::

**ቃቃ አደረገ** ግ "ቃቃ" የሚል ድምፅ እንዲሰማ አደረገ::

**ቃቃታ** ስ "ቃቃ" የሚል ድምፅ፥ ኳኳታ::

**ተንቃቃ** ግ 1. እሳት ወይም ፀሃይ ላይ ቆየ፥ ደረቀ፥ ቀነበረ:: 2. "ቃቃ" የሚል ድምፅ ሰጠ፤ ተንቋቋ:: 3. የተወሰነ ቦታ ላይ ሆኖ አንድን ነገር ረዘም ላለ ጊዜ በመጠበቅ ተንገላታ፥ ተሰቃየ:: *እሱ ይመጣል ብዬ በመጠበቅ ብዙ ተንቃቃሁ::*

**አንቃቃ** ግ 1. ከሳት ወይም ከፀሃይ ላይ አቆየ፥ አደረቀ፥ አቀነበረ:: 2. "**ቃቃ**" የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፤ አንቋቋ:: 3. አስቆየ፥ አስጠበቀ፥ አንገላታ:: *በቀጠሮው ሰአት ባለመገኘቱ እንግዶቹን ፀሃይ ላይ አንቃቃቸው::*

**ቃለቀንዳ "ቀለቀንዳ"** ን ተመ.

**ቃለአጤ "ቀላጤ"** ን ተመ.

**ቃሊም**[1] ስ የወንዝ ወይም የጅረት ዳር፥ ደገፍ፤ ከከንፈሩ እስከ ውሃው ያለው ቦታ፤ ድንጋግ::

**ቃሊም**[2] **(ቃሊብ)** ስ በትንባሆ መጠጫ (በጋያ) አናት ላይ ያለው የትንባሆና የእሳት ማስቀመጫ::

**ቃል (ብ.ቁ.ቃላት)** ስ 1. አንድን ፅንሰ ሃሳብ ለመወከል በድምፅ የተነገረ ወይም በፅሁፍ የሰፈረ የድምፅ ምልክቶች ቅንብር፥ አነስተኛው የአረፍተ ነገር ክፍልፋይ:: 2. ስለአንድ ነገር የተባለ፥ የተነገረ፥ የተፃፈ ሃሳብ፥ አስተያየት፥ መልእክት፥...:: *ቃሉ የእሱ ነው::* (በነጠ.ቁ.ብቻ) ትእዛዝ፥ መመሪያ:: *ልጁ ከአባቱ ቃል አይወጣም /የንጉስ ቃል አይሻርም*:: 4. ድምፅ:: *ቃሉ ተዘግቷል::* 5.እግዚአብሔር ወልድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ:: *በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ::*

**ቃሉ ተዛነፈ** እፈፅማለሁ፥ አደርጋለሁ፥... ያለውን ሳይፈፅም ቀረ::

**ቃሉን አከበረ /ጠበቀ** 1. እፈፅማለሁ፥ አደርጋለሁ ያለውን ፈፀመ፥ አደረገ፥ በቃሉ ፀና:: 2. ትእዛዙን፥መመሪያውን ፈፀመ::

**ቃሉን አጎደለ** አደርጋለሁ ብሎ የገባውን ቃል አፈረሰ፥ ሳይፈፅም ቀረ::

**ቃሉን አጠፈ** የተናገረውን ሳይፈፅም ቀረ፥ ካደ::

**ቃል ለምድር ለሰማይ** በተናገርኩት እፀናለሁ ለማለት የሚነገር መሃላ::

**ቃል ለቃል** ፊት ለፊት፥ በግንባር በመገናኘት:: *ሰዎቹ ተገናኝተው ቃል ለቃል ተነጋግረዋል::*

**ቃል ሰጠ** 1. ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መለሰ፥ መሰከረ (በፍርድ ቤት፥ በሚኒ.ያ፥...):: 2. ቃል ገባ፥ አረጋገጠ፥ እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጠ::

**ቃል ተቀበለ** ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወይም ምስክር የሰጠውን ቃል፥ ቃል ተቀባዩ መዝገበ::

**ቃል ተቀባይ** ስ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወይም ምስክር የሰጠውን ቃል መዝጋቢ፥ ፀሃፊ ::

**ቃል አቀባይ** ስ ዜና አስተላላፊ::

**ቃል አሰረ** ተፈጣጠመ፥ ቀለበት አደረገ፥ ቃልኪዳን ገባ (ለጋብቻ)::

**ቃል ማሰሪያ** ስ ለመጋባት ውል የሚፈፀምበት፥ ቃልኪዳን የሚገባበት፥ ቀለበት የሚደረግበት ስነስርአት፤ ፍጥምጥም::

**ቃል አጠረው/አነሰው** ሁኔታው ከባድ፥ ጉልህ፥ አስደናቂ፥ አስደሳች፥ ...ከመሆኑ የተነሳ ተመጣጣኝ የሆነ መግለጫ ወይም ቋንቋ አነሰው::

**ቃል ገባ** አንድ ነገር ለማከናወን ወይም ለመፈፀም ተስማማ፥ ውል ገባ፥ ተስፋ ሰጠ::

**ቃልዎ ይድረሰኝ** ከቃልዎ አልወጣም፥ ግዝት ይሁንብኝ ለማለት በቁስ ፊት የሚነገር የመሃላ ቃል::

**ቃለ መሃላ** ስ 1. አንድ ሰው ሲምል የሚናገረው የመሃላ ቃል:: 2. አንድን አላማ ከግብ ለማድረስ ወይም አንድን ተግባር በቅንነትና በታማኝነት ለማከናወን ከልብ እንደሚጥሩ ለማረጋገጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ስነስርአት ላይ የሚገባ ቃል ኪዳን::

**ቃለ መሃላ ፈፀመ** 1. አንድን ነገር እፈፅማለሁ፥ አደርጋለሁ በማለት ቃል ገባ:: 2. ቃል ኪዳን ገባ::

**ቃለ መጠይቅ** ስ 1. ስለ አንድ ጉዳይ መረጃ፥ አስተያየት፥ ትምህርት ለማግኘት በሁለት ወገኖች (ጠያቂና ተጠያቂ) መካከል የሚደረግ ጥያቄና መልስ:: 2. አንድን ሰራተኛ ለመቅጠር የሚደረግ የቃል ፈተና::

**ቃለ ምልልስ** ስ 1. ከልዩ ልዩ ጉዳዮች አስተያየት ወይም ትምህርት ለማግኘት በሁለት ወገኖች (ጠያቂና ተጠያቂ) መካከል የሚደረግ ጥያቄና መልስ ያለበት ውይይት:: 2. (ፍል.) ክርክር:: 3. (ስነ ፅ.) በገፀ ባህርያት መካከል የሚደረግ የንግግር ልውውጥ::

**ቃለ ቡራኬ** ስ የማሳረጊያ ፀሎት::

**ቃለ አጋኖ** ስ መገረምን፥ ማጋነንን፥ ማዳነቅን፥...የሚያመለክት ቃል:: *ኣቤት! /ወይ ጉድ!*

**የቃለአጋኖ ምልክት** ስ የማጋነን ምልክት ስም:: ምልክቱም "!" ነው::

**ቃለ እግዚአብሄር** ስ የእግዚአብሄር ቃል፥ መንፈሳዊ ትምህርት::

**ቃለ ጉባኤ** ስ የአንድን ስብሰባ ውይይትና ውሳኔ የያዘ ፅሁፍ (ብዙውን ጊዜ የሰብሰባውን ቦታ፥ ጊዜና አጀንዳ፥ የአባላት ስም ዝርዝር ይጨምራል)::

**ቃለጉባኤ ያዘ/ተቀበለ** ግ በስብሰባ ላይ የሚሰነዘሩትን ፍሬ ነገሮች መዘገብ፥ ፃፈ::

**ቃል በቃል** 1. በጥሬው እንዳለ፥ ለአንድ ቃል አንድ ትርጉም በመስጠት:: 2. የተነገረው ወይም የተፃፈው እንዳለ፥ በሙሉ:: *የተነገረውን ሁሉ ቃል በቃል ይዞታል::*

**ቃል አባይ** ቅ ዋሾ፥ ቀጣፊ፥ ቃሉን የሚያጥፍ::

**ቃልኪዳን** ስ አንድን ነገር ለማድረግ የተገባ ቃል፥ የተሰጠ ተስፋ::

**ቃልኪዳን አሰረ** አጨ፥ ለጋብቻ ውለታ ፈፀመ::

**ቃልኪዳን ገባ** አንድ ነገር ለመፈፀም ተስፋ ሰጠ፥ ውል ገባ::

**የቃል ኪዳን ቀለበት** ስ የጋብቻ ቀለበት::

**የቃላት ልውውጥ** የሃይለቃል ምልልስ::

**የቃላት አሰካክ** የቃላት ቅንብር፥ አገባብ::

**የቃል ትምህርት** ስ (ቤ.ክህ.) በቃል የሚጠና (የሚማሩት) የንባብ፥ የዜማ ትምህርት::

**ቃልቻ** ስ አውቃለሁ፥ አድናለሁ ባይ፤ ጠንቋይ፥ ባለዛር::

**ቃመ** ግ 1. በርከት አድርጎ ወደ አፉ አስገባ፥ በላ (ጥራጥሬን፥ ዱቄትን፥...):: 2. ለበሰ፥ ተሸፈነ (በዱቄት፥ በአመድ፥...):: 3. በላ፥ አኘከ (ጫትን)::

**ቃሚ** ቅ አዘውትሮ ጫት የሚበላ፥ የጫት ሱሰኛ::

**ቃሚያ** ስ በአንድ ጊዜ ሊቃም የሚችል መጠኑ አንድ ጉንጭ የሚሆን እንደ ቆሎ ያለ ምግብ::

**ቅሞ (ቃሞ)** ስ ብዙውን ጊዜ ጥርስ ለሌላቸው ሰዎች የሚዘጋጅና እየተቃመ የሚበላ በቆሎ መልክ ተሰናድቶ የተፈጨ ገብስ::

**አቃመ** ግ በብዛት ሰጠ:: *ጉቦ አቃመው::*

***ቃረ**

**ቃር** ስ በጨጓራ መታወክ ወይም በምግብ አለመስማማት የተነሳ በደረት አካባቢ የሚሰማ የማቃጠል ስሜት::

**ቃር አያውቅሽ** ታሞ የማያውቅ፥ ጤናማ ሆኖ የሚኖር(ሰው)::

**አቃረ** ግ የቃር ስሜት ተሰማ::

**ቃረመ** ግ 1. ሰብል ከታጨደ ወይም ከተነቀለ በሂላ የወዳደቀውን ወይም የረገፈውን ዛላ ወይም ፍሬ ከማሳው ላይ ለቀመ፥ ሰበሰበ:: 2. ከዚህም ከዚያም ትንሽ ትንሽ ሰበሰበ፥ አጠራቀመ:: *ከዘመዶቹ የቃረመውን ገንዘብ ልብስ ገዛበት::* 3. (ዘይ.) አንድ በአንድ፥ ተራ በተራ ሁሉንም ገደለ:: *ጠላቶቹን ቃረማቸው::*

**ቃራሚ** ቅ ቃርሚያ የሚሰበስብ፥ የሚለቅም (ሰው)::

**ቃርሚያ (ቀርም፥ ቅራሚ)** ስ ሰብል ከታጨደ ወይም ከተነቀለ በሂላ በማሳው ላይ የሚቀረው የወዳደቀ የሰብሉ ዛላ ወይም ፍሬ፤ ተለቅሞ በአንድነት የተከማቸውም ዛላ ወይም ፍሬ ቃርሚያ ይባላል::

**ቃርሞሽ** ዝ.ከ.

**ቃሪያ** ስ 1. ያልቀላ፥ ያልበሰለ የበርበሬ እሸት ዛላ፥ ቃሪያ በርበሬም ይባላል:: 2. እንጭጭ፤ ገና ያልበሰለ፥ ያልደረሰ (ፍራፍሬ):: 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ ያልበሰለ (ሰው)::

**ቃሪያ በርበሬ** ስ የቃሪያን አንደኛ ፍቺ ተመ.

**ቃሪያ ጥፌ** ስ በውስጥ እጅ ጀርባ ወይም በአይበሉባ የሚደረግ ጥፊ ወይም ምት፤ በተጨማሪ "ጥፌ"ን ተመ.

**ቃራሚ "ቃረመ"** ስር ተመ.

**ቃሬ** ስ ከጎንና ከጎን ያለውን ፀጉር ተላጭቶ በመሃል ራስ ከግንባር እስከ ማጅራት የሚወርድ ቁንጮ(ለአሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)::

**ቃሬዛ** ስ 1. ቁስለኛን፥ ሬሳን ወይም ለመሄድ የማይችል ህመምተኛን ተሸክሞ ለማጓጓዝ የሚያገለግል፥ እግር በሌለው አልጋ ቅርፅ የሚዘጋጅ መሸከሚያ፥ ወሰካ፤ ወሳንሳ:: 2. በሙታን ስም የሚዘጋጅና ፀሎተ ፍትሃት ለሚያደርጉ ካህናት የሚቀርብ ምግብና መጠጥ፤

ድግስ። 3. ከእንጨት ወይም ከሸንበቆ የሚሰራ የድግስ መብሊያ ገበታ። በተጨማሪ አቆልቋይና አውራጅን ተመ.



*ቃሬዛ 1ኛ ፍቺ*

**ቃር** "* **ቃረ**" ስር ተመ.

**ቃርሚያ** "**ቃረመ**" ስር ተመ.

**ቃርሞሽ** ዝ.ከ.

***ቃሰተ**

**አቃሰተ** ግ ከድካም፥ ከስቃይ፥... የተነሳ ሲተነፍስ የመጨነቅ አተነፋፈስ ወይም ድምፅ አሰማ፤ አቃተተ።

**ቃቃ** ግ ጎመጀ፥ ሰየ፥ ፈለገ።

**አቃቃ** ግ አጎመጀ።

***ቃቃረ**

**ተቃቃረ** ግ ተቀያየመ፥ ተሸካከረ።

**አቃቃረ** ግ አቀያየመ፥ አሸካከረ።

**ቃቃታ** "**ቃ**" ስር ተመ.

**ቃቄጳ** ስ ግትቻ፥ እላቂ (የሰፌድ፥ የእንቅብ፥...)።

**ቃበዘ** ግ አንድ ነገር ለማየት፥ ለመስማት፥... ወዲያና ወዲህ ሄደ፥ ተራወጠ፥ ባከነ።

**ቀበዝባዛ (ቅብዝብዝ)** ቅ አንድ ነገር ለማየት፥ ለመስማት፥... ወዲያና ወዲህ የሚራሯጥ፥ የሚባክን።

**ቅብዝብዝ አለ** ግ በጣም ተቅበዘበዘ።

**ተቅበዘበዘ** ግ ባከነ፥ ባዘነ፥ ናወዘ፥ ወዲያ ወዲህ ተሯሯጠ።

**አቅበዘበዘ** ግ አባከነ፥ አባዘነ፥ አናወዘ፥ ወዲያና ወዲህ አሯሯጠ።

**ቃባ** "**ቀባ**" ን ተመ.

**ቃብድ** "**ቀብድ**" ን ተመ.

**ቃተተ** ግ 1. የጭንቅ ትንፋሽ ተነፈሰ፥ አቃሰተ። 2. ተንከራተተ፥ ለፋ፥ ደከመ፥ ዞረ።

**ቃታ** ስ በሩጫ፥ በህመም፥...ምክንያት የሚፈጠር የሲቃ አተነፋፈስ።

**አቃተተ** ግ 1. ቃተተ፥ አቃሰተ። 2. አለፋ፥ አደከመ፥ አንከራተተ።

**ቃተኛ** ስ ቅቤና ድልህ (አዋዜ) አንድ ላይ ተለውሶ የተቀባ ትኩስ እንጀራ።

**ቃታ**[1] ስ የጠመንጃ፥ የሽጉጥ፥...ጥይት ማስነሻ፥ መተኮሻ(ለእሱን ሽጉጥ ስር ተመ.)።

**ቃታ ሳበ** ጥይት ተኮሰ።

**ቃታ**[2] "**ቃተተ**" ስር ተመ.

**ቃና** ስ 1. የምግብ፥ የመጠጥ ጣእም። 2. የድምፅ ወይም የሙዚቃ ለዛ፥ ወዘና፥ ጣእም።

**ቃና ዘገሊላ** ስ 1.ኢየሱስ ክርስቶስ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገበት የቦታ ስም። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቃና ዘገሊላ የተፈፀመውን ተአምር ለማስታወስ በየአመቱ ጥር 12 ቀን የሚከበር በአል።

**ቃንዛ** ስ የደም ስርን የመጠዝጠዝ፥ የመንዘር ህመም።

**ቃኘ**[1] ግ ወዲያና ወዲህ አየ፥ ተመለከተ፥ ማተረ፥ ጎበኘ፥ ሰለለ።

**ቅኝት** ስ የተወሰነ አካባቢን የማየት፥ የመሰለል ድርጊት።

**ተቃኘ** ግ ተጎበኘ፥ ተዳሰሰ።

**ቃኘ**[2] ግ 1. እንደ ክራር፥ በገና፥... ያሉ የሙዚቃ መሳሪያ ጅማቶች (ክሮች) እያንዳንዳቸው ልዩ ሙዚቃዊ የድምፅ ቃና እንዲኖራቸው፥ ጅማቶቹን በመወጠርና በማላላት ቅንብራቸውን አስተካከለ። 2.በዜማ አለ፥ አሰማ።

**ቅኝት** ስ 1. የሙዚቃ መሳሪያ ክሮችን በማጥበቅ ወይም በማላላት የሚፈለገውን የድምፅ ቃና እንዲያወጡ የማስተካከል ድርጊት። 2. የሙዚቃ መሳሪያ ክሮች የተቃኙበት የተወሰነ ሙዚቃዊ የድምፅ ስልት (ለምሳሌ አምባሰል፥ ባቲ፥...)።

**ተቃኘ** ግ ተነቃቃ፥ ተመራ። *ለእምሮው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ደራሲ።*

**ቃዛ** ስ ስጋ ለመምተር የሚያገለግል የሸንበቆ ስነጣቂ።

**ቃዠ** ግ 1. የተዘበራረቀና የማይጨበጥ ህልም አየ። 2. በእንቅልፍ ላይ እያለ ጮሀ፥ አላዘነ ወይም እንዳች ነገር ተናገረ። 3. (ዘይ.) ያልተስተካከለ ወይም የተዘበራረቀ ነገር ተናገረ፥ አወራ።

**ቅዠት** ስ 1. የተዘበራረቀና በትክክል ለማስታወስ የማይቻል ህልም። 2. በእንቅልፍ ላይ እያሉ የማላዘን፥ ጩሀት የማሰማት ወይም እንዳች ነገር የመናገር ድርጊት። 3. (ዘይ.) የተዘበራረቀ፥ የማይጨበጥ ወይም ሊታመን የማይችል ወሬ።

**ቅዠታም** ቅ (ስድብ) ዘባራቂ፥ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር የሚናገር።

**አቃዠ** ግ 1. የተዘበራረቀና የማይጨበጥ ህልም አሳየ። 2. በእንቅልፍ ልብ አስጮሀ፥ አስጨነቀ፥ አስለፈለፈ።

**ቃዲ** ስ 1. በእስልምና ሃይማኖት የሃይማኖቱ ተከታዮች መንፈሳዊ ዳኛ። 2. የሸሪአ ፍርድ ቤት

ዳኛ ወይም አቃቢ ህግ::

**ቃዳ** ስ ገዝም፥ እመም (የተወሰነ የእርሻ መሬት ስፋት፥ ልክ)::

***ቃጠለ**

**ቃጠሎ** ስ 1. በእሳት የመያያዝና የመንደድ አደጋ:: *ቃጠሎው በሀይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ::* 2.(ዘይ.) ለፍላፊ፥ ምላሰኛ:: *ሴትየዋ ቃጠሎ ናት::*

**ቅጥል አለ** ግ 1. በጣም ተቃጠለ፥ አረረ፥ ከሰለ:: 2. በጣም ተበሳጨ፥ ተማረረ፥ ተናደደ፥ ተቆጨ::

**ቅጥል አደረገ** ግ 1. አቃጠለ፥ አሳረረ፥ አከሰለ:: 2. አበሳጨ፥ አስቆጨ፥ አናደደ::

**ተቃጠለ** ግ 1. በእሳት ነደደ፥ ጋየ፥ ወደመ፥ አረረ፥ ከሰለ:: 2. በፀሃይ ብዛት ወይም በውሃ እጦት፥... የተነሳ ደረቀ፥ አረረ (ተክል):: 3.(ዘይ.) በጣም ተናደደ፥ በገነ:: 4. የጊዜ ገደቡ ከማለፉ የተነሳ ከአገልግሎት ውጪ ሆነ:: *በተወሰነው ቀን ባለመሄዱ ለአስቴዲየም መግቢያ የገዛው ቲኬት ተቃጠለ::* 5. ተሰቃየ፥ ተንገበገበ (በውሃ ጥም፥ በፍቅር፥...):: 6. በውስጡ ያለው ብርሃን ሰጪ ሽቦ በመርገፉ አምፖሉ ብርሃን መስጠቱን ወይም መብራቱን አቆመ:: 7. ተፈጀ፥ ተለበለበ ( በእሳት፥ በግለት፥ በበርበሬ፥...):: 8. አላግባብ ባከነ፥ ጠፋ፥ አለቀ (ጊዜ፥ ገንዘብ፥...):: 9. (ዘይ.) በጩሀት፥ በጫጫታ፥... ብዛት ታወከ፥ ተረበሸ:: *ሰፈሩ በጫጫታ ተቃጠለ::*

**ተቀጣጠለ** ግ ተያያዘ፥ ተለኮሰ፥ ጀመረ (እሳት፥ ነገር፥...)::

**አቃጠለ** ግ 1. አነደደ፥ አጋየ፥ አከሰለ፥ አሳረረ (በእሳት):: 2. ፈጀ፥ ተኮሰ፥ ለበለበ (እሳት፥ በርበሬ፥...):: 3. የፀሃይ ብዛት ወይም የውሃ እጦት አደረቀ፥ አሳረረ (ለምሳሌ ተክልን):: 4. (ዘይ.) አናደደ፥ አበገነ:: 5. አንገበገበ (ውሃ ጥም፥ ፍቅር፥...):: 6. አላግባብ አባከነ፥ አጠፋ፥ ጨረሰ (ጊዜን፥ ገንዘብን፥...):: 7. በነገር፥ በጩሀት፥... አወከ፥ ረበሸ::

**አቀጣጠለ** ግ ለኮሰ፥ አያያዘ (እሳትን፥ ነገርን፥...)::

**ቃጣ** ግ 1. ፈለገ፥ ከጀለ፥ ዳዳ (አንድ ነገር ለማድረግ):: 2. አንድ ነገር ለማድረግ እጁን አነሳ፥ ሰነዘረ::

**ተቃጣ** ግ 1.ታለመ፥ ታቀደ:: 2. ተሞከረ::

**ቃጤ** ስ 1. ከቀና አነስ ያለ የእህል መስፈሪያ፥ መለኪያ:: 2. ለቆሎ ወይም ለመጠነኛ ምግብ ማቅረቢያ የሚያገለግል አነስተኛ የስፌት እቃ(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)::

***ቃጨለ(ቀጨለ)**

**ቃጭል** ስ መሃሉ ላይ ከተንጠለጠለ ትንሽ ብረት ጋር ሲጋጭ የሚጮህ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ በዋንጫ ቅርፅ የተበጀ፥ እጀታ ወይም ማንጠልጠያ ጆሮ ያለው አነስተኛ የብረት ወይም የነሃስ መረዋ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::



ቃጭል

**ቅጭል አለ** ግ አነስተኛ የሆኑ ብረታ ብረቶች ሲጋጩ የሚሰጡትን አይነት ድምፅ ሰጠ::

**ቅጭል አደረገ** ግ የቃጭል አይነት ድምፅ አሰማ፣ አቃጨለ::

**ቅጭልጭል** ስ እንደ ጥቃቅን ብረታብረቶች፥ ሰብርባሪ ጠርሙሶች፥... ያሉ ነገሮች እርስ በርስ ሲጋጩ የሚሰጡትን አይነት ድምፅ የሚሰጥ ቁሳቁስ::

**ተቃጨለ** ግ ተመታ፥ ተደወለ፥ ድምፅ እንዲሰጥ ተደረገ (ደወሉ፥ ቃጭሉ፥...)

**ተቅጨለጨለ** ግ 1. ተቃጨለ:: 2. እርስ በርስ ከመገጫጨት የተነሳ ቃጭል የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ::

**አቃጨለ** ግ 1. የቃጭሉን እጀታ ወይም ጆሮ ይዞ በመወዝወዝ እንዲጮህ ወይም ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ:: 2. የቃጭል አይነት ድምፅ ሰጠ፥ አሰማ::

**አቅጨለጨለ** ግ እንደቃጭል አጮሀ፥ የቃጭል አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ::

**ቃጫ** ስ ለገመድና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ጭረት (ቀጫጭን ክር፥ ፀጉር) የሚወጣው የተክል አይነት፣ ከላይ ከተጠቀሰው ተክል የሚገኘው ጭረትም ቃጫ ይባላል::

**ቃጭል** "ቃጨለ" ስር ተመ.

**ቃጭማ** ስ ቅጠሉ ሰፋፊ፥ ግንዱ ውስጥ ከፍት፥ ፍሬው ዘይት አዘል የሆነ የእፀዋት አይነት :: ጉሎ እየተባለም ይጠራል::

**ቃፊር** ስ የጠላትን እንቅስቃሴ ለመሰለልና ለመጠቆም የተመደበ የጥበቃ ጓድ ወይም ወታደር::

**ቄ** የ"ቀ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ቄለ** ግ ሞኝ ሆነ::

**ቂል** ቅ ሞኝ፥ ጅል::

**ቂላቂል** ቅ ሞኛ ሞኝ፥ ጅላጅል፥ በቀላሉ

ሊታለል የሚችል።

**አቈለ** ግ 1. አሞኘ፡ አታለለ። 2. ሞኝ አደረገ፥ አጀለ።

**ቈራ** ስ የእርድ ከብቶች፡ በጎች፡… እየተወሰዱ የሚታረዱበት ቦታ፤ እርድ የሚያከናውን ድርጅት።

**ቈስ** "**ቀሰሰ**[1]" ስር ተመ.

**ቈብ** ቅ ገና መውለድ ያልጀመረችና ለመውለድ የሚያበቃ የእድሜ ደረጃ ላይ የደረሰች (እንስት ዶሮ፥ በግ፥ ፍየል፥…)።

**የቈብ ልጅ** ስ 1. ከቈብ በግ ወይም ፍየል፥… የተወለደ ግልገል ወይም ልጅ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ባለጌ፥ ያልተቀጣ፡ ስነስርአት የሌለው ልጅ።

**የቈብ [ዶሮ] እንቁላል** ስ ቈብ ዶሮ የጣለችው ወይም የወለደችው እንቁላል።

**ቈንጥ** ስ 1. የአነጋገር፥ የአለባበስ፡ የአሰራር፥… ለየት ያለ ሁኔታ። 2. አቃቂር።

**ቈንጥ አወጣ** 1. የተለየ ሁኔታ አበጀ፡ ፈጠረ፥ አሳየ (በአነጋገር፡ በአለባበስ፡…) 2አቃቂር አወጣ፥ ነቀፈ።

**ቈንጠኛ** ቅ ዘናጭ፥ በአለባበስ ወይም በሌላ ከሌላው ለየት የሚልበት ነገር ያለው።

**ቈንጦ** ቅ ሽቅርቅር።

**ቈንጠ**[1] (**ቀንጠ**) ስ ትንንሽ ቆላፋ እሾህ ያለው የዛፍ አይነት።

**ቈንጠ**[2] "**ቈንጥ**" ስር ተመ.

**ቈደር** ስ (ኢ.ኦ.ተቤ.) ቀሳውስት ንስሃ ለሚቀበለው ምእመን የሚያደርጉለት ፀሎትና የንስሃ ጥምቀት፤ የሚፀልዩበት መፅሃፍም [መፅሃፉ] ቈደር ይባላል።

**ቈደር ተጠመቀ** የንስሃ ጥምቀት ተጠመቀ።

**ቈጠማ (ቀጤማ)** ስ በወንዝ፥ በምንጭ ዳርና ዳር ወይም ውሃነት ባለው ቦታ ላይ መለል ብሎ የሚበቅል፥ ከብ ቅርፅ ያለውና ወፍራም የሆነ የሳር አይነት።

**ቈጦ** ስ ቃሪያ።

**ቅ** የ "**ቀ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ቅለት** "**ቀለለ**" ስር ተመ.

**ቅሉ** እንኳን። *ለበላይ ቢያመለክትም ቅሉ ሊሳካለት አልቻለም።*

**ቅላት** "**ቀላ**[1]" ስር ተመ.

**ቅላጥቤ (ቀላጥቤ)** ቅ (ስድብ) ከለፍላፊ፥ በነገር ሁሉ አለሁ አለሁ የሚል።

**ቅሌ** "**ቀላ**[2]" ስር ተመ.

**ቅሌታም** "**ቀለለ**" ስር ተመ.

**ቅሌት** ዝ.ከ.

**ቅል** ስ 1. በውስጡ ትናንሽ የፍሬ ዘሮችን የያዘ፥ ክብና ውስጠ ክፍት የሆነ ትልቅ ፍሬ የሚጥል ወይም የሚያፈራ፤ መሬት ላይ ተንሰራፍቶ ወይም በአጥርና በዛፍ ላይ እየተንጠለጠለ የሚያድግ ሃረግማ የተክል አይነት፤ ፍሬውም ቅል ይባላል። 2. ከዚሁ ፍሬ ለውሃ መቅጃና መያዣ ወይም ለጥራጥሬ፥ ለሽሮ፥ ለድልህ፥ ለቅቤ፥… ማኖሪያ የሚዘጋጅ እቃ፤ ቅምጫና፥ ዋምራ።

**ቅሌን ጨርቄን አለ** ሰበብ፥ ምክንያት አበዛ።

**ለየቅል (እየቅል)** ተው.ግ. ለየብቻ፥ ለየራስ፥ ለየግል። *ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል።*

**ቅል ራስ** (ስድብ) የማያመዛዝን፤ አእምሮው ባዶ የሆነ፥ እውቀት የሌለው።

**ቅል አንገት** ስ መቀንጠቢያ።

**ቅልልሞሽ** "**ቀለበ**[2]" ስር "**ቅልልቦሽ**" ን ተመ.

**ቅልልቦሽ** "**ቀለበ**[2]" ስር ተመ.

**ቅልሞሽ** "**ቀለበ**[2]" ስር "**ቅልቦሽ**" ን ተመ.

**ቅልስልስ** "***ቀለሰለሰ**" ስር ተመ.

**ቅልሽልሽታ** "***ቀለሸለሸ**" ስር ተመ.

**ቅልቅል** "**ቀላቀለ**" ስር ተመ.

**ቅልበሳ** "**ቀለበሰ**" ስር ተመ.

**ቅልብ** "**ቀለበ**[1]" ስር ተመ.

**ቅልብልብ** "***ቀለበለበ**" ስር ተመ.

**ቅልብሳት** "**ቀለበሰ**" ስር ተመ.

**ቅልብሽ**

**ቅልብሽ አለው** አቅለሸለሸው፥ አጥወለወለው፤ ክልብሽ አለው።

**ቅልብጭ ያለ** "**ቀለበጨ**" ስር ተመ.

**ቅልቦሽ** "**ቀለበ**[2]" ስር ተመ.

**ቅልውጥ** "**ቀላወጠ**" ስር ተመ.

**ቅልጣን** "**ቀለጠ**" ስር ተመ.

**ቅልጥልጥ** ዝ.ከ.

**ቅልጥማም** "**ቀለጠመ**" ስር ተመ.

**ቅልጥም** ዝ.ከ.

**ቅልጥጥ** "***ቀለጠጠ**" ስር ተመ.

**ቅልጥፍና** "**ቀለጠፈ**" ስር ተመ.

**ቅመማ** "**ቀመመ**" ስር ተመ.

**ቅመማ ቅመም** ዝ.ከ.

**ቅመም** ዝ.ከ.

**ቅሚያ** "**ቀማ**" ስር ተመ.

**ቅማላም** "**ቀመለ**" ስር ተመ.

**ቅማል** ዝ.ከ..

**ቅማት "ቅማያት"** ን ተመ.

**ቅማንጅር (ቅማንኽር)** ስ በቅንድብ÷ በሽፋል÷... ላይ የሚወጣ እንደ መኽርገር የሚጣበቅ ትንንሽ ተባይ፤ ቅጫም::

**ቅማንጅራም** ቅ (ስድብ) ቅማንጅር የያዘው÷ ያለበት::

**ቅማያት (ቅማት)** ስ የቅድም አያት አባት ወይም እናት፤ ሶስተኛ አያት::

**ቅማጫም "*ቀመጠ"** ስር ተመ.

**ቅማጭ "*ቀጨመ"** ስር **"ቅጫም"** ን ተመ.

**ቅሟጭ "*ቀመጠ"** ስር ተመ.

**ቅም**

**ቅምአላለውም** አልበቃውም÷አልጠቀመውም::

**ቅም ቅም አለው** ጣመው÷ ጨምር ጨምር አሰኘው::

**ቅምሆ** ስ እስከጆሮ የሚሰማ የጉሮሮ ህመም፤ ለቅዳ፤ ቶንሲል::

**ቅምምጦሽ "ቀመጠ"** ስር **"ቅምጦሽ"** ን ተመ.

**ቅምሻ "ቀመሰ"** ስር ተመ.

**ቅምቅማት "ቀመቀመ[1]"** ስር ተመ.

**ቅምቡርስ "ቅንቡርስ"** ን ተመ.

**ቅምብቻ "ቅንብቻ"** ን ተመ.

**ቅምቦ "ቅንቦ"** ን ተመ.

**ቅምድምድ "*ቀመደመደ"**ስር **"ቀመድማዳ"** ን ተመ.

**ቅምጥ "አይን"** ስር **"አይናር"**ን ተመ.

**ቅምጥ "*ቀመጠ"** ስር ተመ.

**ቅምጥል "*ቀማጠለ"** ስር ተመ.

**ቅምጦሽ "*ቀመጠ"** ስር ተመ.

**ቅምጫና** የ **"ቅል"** ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

**ቅሞ (ቃሞ)** ስ ፍሬው የሚበላ የእፀዋት አይነት፤ ፍሬውም ቅሞ ተብሎ ይጠራል::

**ቅሪላ** ስ ለመጫኛ÷ ለጠፍር÷...የሚያገለግል የተለፋ የበሬ ቆዳ::

**ቅሪት "ቀረ"** ስር ተመ.

**ቅራሚ "ቃረመ"** ስር ተመ.

**ቅራሞ** ዝ.ከ.

**ቅራሪ "ቀረረ"** ስር ተመ.

**ቅራቅንቦ** ስ ኩሳንኩስ÷ ኮተት::

**ቅራተኛ "ቀራ[1]"** ስር ተመ.

**ቅራት** ዝ.ከ.

**ቅራና** ስ 1. የቀርቃባ ጠፍር:: 2. ለምራን÷ ለቀርቃባ ወይም ለመጫኛ የሚሆን ጠፍር ሊወጣው የሚችል የተለፋና ገና በጠፍር መልክ ያልተሸነሸነ የበሬ ቆዳ::

**ቅራኔ "*ቀረነ"** ስር ተመ.

**ቅራፊ "*ቀረፈ"** ስር ተመ.

**ቅሬ[1]** ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት::

**ቅሬ[2]** ስ የ**"እድር"** ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

**ቅሬታ "ቀረ"** ስር ተመ.

**ቅር**

**ቅሬታ (ቅርታ)** ስ 1. ያለመስማማት÷ ያለመደሰት ስሜት::

**ቅሬታ ተሰማው** ቅር ተሰኘ::

**ቅር ተሰኘ** 1. ያለመርካት÷ ያለመደሰት ስሜት ተሰማው:: 2. ተቀየመ:: 3. አዘነ÷ ተከዘ÷ ተከፋ::

**ቅር አለው** 1. ሳይረካ÷ የልቡ ሳይደርስ÷ ደስ ሳይለው ቀረ፤ ቅሬታ ተሰማው:: 2. የተሟላ ለመሆን ትንሽ ተጨማሪ አስፈለገው:: *ስፍሩ ቅር ላለው::*

**ቅር ቅር አለው** ከመለያየት÷ ከመራራቅ ወይም የለመደውን ከማጣት ወይም ከአንዳች ነገር መጓደል የተነሳ ቅሬታ አደረበት፤ የመናፈቅ ስሜት ተሰማው፤ አንድ ነገር ትዝ አለው::

**ቅር አሰኘ** 1. አሳዘነ÷ አስቀየመ:: 2. ቅሬታ አስከተለ::

**ቅርምት "*ቀረመተ"** ስር ተመ.

**ቅርስ** ስ 1. የተካበተ ሃብት÷ ጥሪት:: 2. እንደ ሃውልት÷ ህንፃ÷ የእደጥበብ ውጤቶች÷... የመሳሰለ የአንድን ሃገር ጥንታዊ ታሪክና ባህል የሚያንፀባርቅ÷ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈና የሚተላለፍ ቋሚ መረጃ::

**ቅርሻታም "ቀረሸ"** ስር ተመ.

**ቅርሻት** ዝ.ከ.

**ቅርሾ "ቁርሾ"** ን ተመ.

**ቅርቃር "ቀረቀረ"** ስር **"መቀራቅር"** ን ተመ.

**ቅርቃብ "ቀረቀበ"** ስር **"ቀርቃባ"** ን ተመ.

**ቅርቅፍት** ስ ለመሄጃ አመቺ ያልሆነ÷ በደንብ ያልቀና÷ ድንጋያማ÷ ወጣ ገባ መንገድ::

**ቅርበት "ቀረበ"** ስር ተመ.

**ቅርብ** ዝ.ከ.

**ቅርታ "ቅር"** ስር **"ቅሬታ"** ን ተመ.

**ቅርናታም "ቀረና"** ስር ተመ.

**ቅርናት** ዝ.ከ.

**ቅርንጥስ** ስ የተጣጣፈ አሮጌ ጨርቅ፤ ጭርንቁስ፤ ደባደቦ::

**ቅርንጫፍ** ስ 1. በዛፍ ወይም በማንኛውም እፅዋት ግንድ ዙሪያ ከታች እስከ አናት ድረስ ጋደም ጋደም እያለ የሚበቅል፥ የዛፍ ወይም የእፅዋት ክንፍ። 2. የአንድ ዋና አካል ቅጥያ፥ ዘርፍ።

**ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት** ስ ከዋናው መስሪያ ቤት ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ ላይ የሚገኝና ዋናው መስሪያ ቤት የሚያከናውነውን ተመሳሳይ ስራ የሚያከናውን የዋናው መስሪያ ቤት አካል፤ ዘርፍ።

**ቅርንፉድ (ቁርንፉድ)** ስ ጥሩ ሽታና ጣእም ያለው የቅመም አይነት።

**ቅርጫ** "ቀረጠ" ስር ተመ.

**ቅርጫት** ስ ከሸንበቆ፥ ከቀርከሃ፥ ከሃረግ፥... የሚበጅ ለእቃ መያዣና ማጓጓዣ የሚያገለግል የቤት እቃ።

**ቅርጫት ኳስ** ስ አምስት አምስት ተጫዋቾችን በያዙ ሁለት ቡድኖች መካከል፥ ከመሬት አስር ጫማ ያህል ከፍታ ባለው ምሰሶ ላይ በተሰቀለ የተቃራኒ ቡድን ቅርጫት ውስጥ ኳስን በእጅ እየወረወሩ ለማስገባት የሚካሄድ የውድድር ጨዋታ አይነት፤ ኳሱም ቅርጫት ኳስ ይባላል(ስእሉን ኳስ ስር ተመ.) ።

**ቅርፃ ቅርፅ** "ቀረፀ" ስር ተመ.

**ቅርፅ** ዝ.ከ.

**ቅርፊት** "ቀረፈ" ስር ተመ.

**ቅርፍርፍ** ዝ.ከ.

**ቅስም** ስ አካላዊ ገፅታ፥ ወዘና፤ ብርታት፥ ጥንካሬ።

**ቅስሙ ተሰበረ** 1. ተስፋ በመቁረጥ ሀሊናዊ ክብሩ፥ ጥንካሬው ወደቀ፥ ስሜቱ ተጎዳ። 2. አካላዊ ጥንካሬው፥ ወዘናው ጉዳት ላይ ወደቀ።

**ቅስር** "ቀሰረ" ስር ተመ.

**ቅስቀሳ** "ቀሰቀሰ" ስር ተመ.

**ቅስቃሴ** "*ቀሰቀሰ" ስር ተመ.

**ቅስና** "ቀሰሰ[1]" ስር ተመ.

**ቅስፈት** "ቀሰፈ" ስር ተመ.

**ቅሽምድምድ** "ቀሸመደ" ስር ተመ.

**ቅሽር** "ቀሸረ" ስር "ቀሽር"ን ተመ.

**ቅቅል** "ቀቀለ" ስር ተመ.

**ቅቅታም** "ቀቀተ" ስር ተመ.

**ቅቅት** ዝ.ከ.

**ቅበላ** "*ቀበለ" ስር ተመ.

**ቅቡጭ**

**ቅቡጭ አለ** ግ እንስ፥ ጉድል አለ፤ በቶሎ፥ በድንገት እልቅ አለ።

**ቅባት** "ቀባ" ስር ተመ.

**ቅቤ** ዝ.ከ.

**ቅብ** ዝ.ከ.

**ቅብቃብ** "ቀበቀበ[2]" ስር ተመ.

**ቅብቅብ** "ቀበቀበ[1]" ስር ተመ.

**ቅብቅቦ** ስ ሳይጠበስ የሚበላ፥ በጨው የታሸ የማሽላ እሸት።

**ቅብብል** "*ቀበለ" ስር ተመ.

**ቅብብሎሽ** ዝ.ከ.

**ቅብትት** "ቀበተተ" ስር ተመ.

**ቅብአ መንግስት** "ቀባ" ስር ተመ.

**ቅብአ ቅዱስ** ዝ.ከ.

**ቅብአ ኑግ** ዝ.ከ.

**ቅብአ ክህነት** ዝ.ከ.

**ቅብዝብዝ** "ቃበዘ" ስር ተመ.

**ቅብድድ** "ቀበደደ" ስር ተመ.

**ቅብጠት** "ቀበጠ" ስር ተመ.

**ቅብጥብጥ** ዝ.ከ.

**ቅትር** "ቀተረ[1]" ስር ተመ.

**ቅትርት** "ቀተረ[2]" ስር ተመ.

**ቅናሽ** "ቀነሰ" ስር ተመ.

**ቅናተኛ** "ቀና[1]" ስር ተመ.

**ቅናት[1]** ዝ.ከ.

**ቅናት[2]** "ቀና[2]" ስር ተመ.

**ቅናት[3]** "*ቀነተ" ስር ተመ.

**ቅኔ** "*ቀኘ" ስር ተመ.

**ቅን** "ቀና[2]" ስር ተመ.

**ቅንስናሽ** "ቀነሰ" ስር ተመ.

**ቅንቀና** "ቀነቀነ[2]" ስር ተመ.

**ቅንቅናም** "ቀነቀነ[1]" ስር ተመ.

**ቅንቅን** ዝ.ከ.

**ቅንቡርስ (ቅምቡርስ)** ስ እርጥበት ባለው ከሲ መሬት ወይም ተቆልሎ በከረመ አዛባ ውስጥ የሚገኝ ወፈር ያለ ነጭ ትል።

**ቅንብር** "*ቀነበረ" ስር ተመ.

**ቅንብብ** "ቀነበበ" ስር ተመ.

**ቅንብቻ (ቅምብቻ)** ስ ከስንደዶ ስፌት ወይም ከቆዳ የሚዘጋጅ የኩተት ማስቀመጫ፥ መክተቻ።

**ቅንብቻ ሆድ** ጉስር ያለች ትንሽ ቦርጭ ያለው (ሰው)።

**ቅንቦ(ቅምቦ)** ስ ትላልቅ ፍሬ ያለው፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና በበረሃ የሚገኝ የእፅዋት አይነት።

**ቅንዛፌ** "ቀነዘፈ" ስር ተመ.
**ቅንዝረኛ** "ቀነዘረ" ስር ተመ.
**ቅንዝር** ዝ.ከ
**ቅንዝንዝ** "*ቀነዘነዘ" ስር ተመ.
**ቅንዳሻም** "ቀነደሸ" ስር ተመ.
**ቅንድል** "ቀነደለ" ስር ተመ.
**ቅንድብ** "ቀነደበ[1]" ስር ተመ.
**ቅንጅት** "*ቀነጀ" ስር ተመ.
**ቅንጡ** "ቀነጣ" ስር ተመ.
**ቅንጣቢ** "ቀነጠበ" ስር ተመ.
**ቅንጣት** ስ 1. ነጠላ፥ አንድ ብቻ የሆነ:: 2.ትንሽ::
**ቅንጥ** ስ በአይንና በጆሮ መካከል አካባቢ ላይ የሚገኝ አካል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::
**ቅንጠተኛ** "ቀነጣ" ስር ተመ.
**ቅንጠት** ዝ.ከ.
**ቅንጫቢ** "ቀነጨበ" ስር ተመ.
**ቅንጬ** ስ ከስንዴ ወይም ከገብስ ወይም ከአጃ ክክ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::
**ቅንጭር** "ቀነጨረ" ስር "ቀንጫራ" ን ተመ.
**ቅንጭብ** ስ ሲቆረጥ ወተት የሚመስል ፈሳሽ የሚወጣው በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::
**ቅንፋት** "ቀነፈ" ስር ተመ.
**ቅንፍ** ዝ.ከ.
**ቅኝ** "ቀኘ[2]" ስር ተመ.
**ቅኝት[1]** "ቃኘ[1]" ስር ተመ.
**ቅኝት[2]** "ቃኘ[2]" ስር ተመ.
**ቅዋሜ** "*ቀወመ" ስር ተመ.
**ቅው**
**ቅው አለ** ግ የመጋጨት፥ ኳ የማለት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ::
**ቅው ቅው አለ** ዝ.ከ.
**ቅው ቅው አደረገ** ግ የማጋጨት፥ የማንኳኳት፥ የመቀጥቀጥ ድምፅ አሰማ::
**ቅዝናም** "ቀዘነ" ስር ተመ.
**ቅዝን** ዝ.ከ.
**ቅዛዛ** ስ የብርሌ፥ የብርጭቆ፥... መስታወት ወይም ስሊዳው::
**ቅዝምዝም** "*ቀዘመዘመ" ስር ተመ.
**ቅዝቃዜ** "ቀዘቀዘ" ስር ተመ.
**ቅዝዝ አለው** "ቀዘዘ" ስር ተመ.

**ቅዥታም** "ቃዠ" ስር ተመ.
**ቅዥት** ዝ.ከ.
**ቅያሜ** "*ቀየመ" ስር ተመ.
**ቅያሪ (ቅያሬ)** "ቀየረ" ስር ተመ.
**ቅያስ** "ቀየሰ" ስር ተመ.
**ቅይድ** "ቀየደ" ስር ተመ.
**ቅይጥ** "ቀየጠ" ስር ተመ.
**ቅደም ተከተል** "ቀደመ" ስር ተመ.
**ቅዱሳት** "ቀደሰ" ስር "ቅዱስ" ን ተመ.
**ቅዱሳን** ዝ.ከ.
**ቅዱስ** "ቀደሰ" ስር ተመ.
**ቅዳሜ** ስ በአርብና በእሁድ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሰባተኛ ወይም መጨረሻ ቀን፤ ቀዳሚትም ይባላል::
**ቅዳም ሹር (ስኡር)** ስ በስቅለት ማግስት የሚውለው ቅዳሜ ስም::
**ቅዳሴ** "ቀደሰ" ስር ተመ.
**ቅዳጅ** "ቀደደ" ስር ተመ.
**ቅድ** ዝ.ከ.
**ቅድ** "ቀዳ" ስር ተመ.
**ቅድመአያት** "ቀደመ" ስር ተመ.
**ቅድሚያ** ዝ.ከ.
**ቅድም** ዝ.ከ.
**ቅድስት[1]** "ቀደሰ" ስር "ቅዱስ" ን ተመ.
**ቅድስት[2]** ስ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በተለይ ክብ ቅርፅ ይዘው በተሰሩት ህንፃዎች ውስጥ በመቅደሱና በቅኔ ማህሌቱ መካከል ያለው ቦታ::
**ቅድስና** "ቀደሰ" ስር ተመ.
**ቅጅ** "ቀዳ" ስር ተመ.
**ቅጠል** ስ 1. ከግንዱ ላይ ለምለም ሆኖ የሚበቅል፥ ብዙውን ጊዜ ቀለሙ አረንጓዴ፥ አካሉ ስስ የሆነ የእፀዋት አካል ክፍል :: 2. ነጠላ፥ አንድ ብቻ (ለወረቀት)::
**ቅጠላ ቅጠል** ስ 1. አይነቱ የተለያየ ብዙ ቅጠል:: 2. እንደ ጎመን፥ ሰላጣ ላሉና ለሚበሉ የተክል አይነቶች የጥቅል መጠሪያ::
**ቅጠል በጣሽ** ስ (የን.አነ.) ቅጠላ ቅጠሎችን እየሰበሰበ በመቀመም የባህል መድሃኒት የሚያዘጋጅ (ሰው)::
**ቅጠል የለሽ** ስዛ ቢስ፥ ንግግሩ ጣእም የሌለው::
**ቅጠልማ** ቅ ቀለሙ ቅጠል የሚመስል፤ አረንጓዴ::
**ቅጠልያ** ዝ.ከ.

**ቅጣተኛ "ቀጣ"** ስር ተመ.

**ቅጣት** ዝ.ክ.

**ቅጣጥይ (ቀጣጥይ)** ስ በመጨረሻ የሚወጣ መንጋጋ::

**ቅጥ** ስ ስርአት፤ ደንብ::

**ቅጡ ጠፋው** 1.የሚያደርገውን አጣ፥ ተደናገረው:: 2. ስርአት አጣ::

**በቅጥ(በቅጡ)** በደንብ፤ በስነስርአት፥ በትክክል::

**አለቅጥ (ያለ ቅጥ)** ከመጠን በላይ::

**ቅጥ የለሽ** የተበላሸ፤ ስርአት ያጣ::

**ቅጥል "ቀጠለ"** ስር ተመ.

**ቅጥልጥል** ዝ.ክ.

**ቅጥረኛ "ቀጠረ"** ስር ተመ.

**ቅጥራን** ስ 1. መጣብቅ ወይም ሙጫነት ያለው ዝፍት:: 2. ሬንጅ፤ ካትራሚ::

**ቅጥር[1] "ቀጠረ[1]"** ስር ተመ.

**ቅጥር[2] "ቀጠረ[3]"** ስር ተመ.

**ቅጥር ግቢ** ዝ.ክ.

**ቅጥቃጤ "ቀጠቀጠ"** ስር ተመ.

**ቅጥቃጭ "ቀጠቀጠ"** ስር **"እንቅጥቃጭ"** ን ተመ.

**ቅጥቅጥ "ቀጠቀጠ"** ስር ተመ.

**ቅጥባት "ቀጠበ"** ስር ተመ.

**ቅጥብ** ዝ.ክ.

**ቅጥይ(ቅጥያ) "ቀጠለ"** ስር ተመ.

**ቅጥጥብ "ቀጠበ"** ስር ተመ.

**ቅጥፈት "ቀጠፈ[2]"** ስር ተመ.

**ቅጫማም "ቀጨመ"** ስር ተመ.

**ቅጫም** ዝ.ክ.

**ቅጭት "ቀጨ[1]"** ስር ተመ.

**ቅፀላ "ቀፀለ"** ስር ተመ.

**ቅፅ** ስ ጥራዝ፤ ተከታታይነት ያለውና በተለያየ ጥራዝ የተዘጋጀ መፅሃፍ::

**ቅፅል** ስ 1. (ሰዋ.) ከስምንቱ የንግግር ክፍሎች የአንደኛው ስም:: 2. የአንድን ነገር ጠባይ ወይም መልክ ወይም መጠን፥... ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል (ለምሳሌ *ደግ ሰው፥ ቀይ ልጅ ፥ ጥቂት* ገንዘብ በሚለው ውስጥ *"ደግ"፥ "ቀይ"፥ "ጥቂት"* ቅፅል ናቸው)::

**የቅፅል ስም** ስ ከግብሩ ወይም ከባህርዩ ወይም ከመልኩ፥... የተነሳ በዋናው መጠሪያ ስም ላይ እንደ ተጨማሪ ሆኖ የሚያገለግል ስም::

**ቅፅረ ግቢ "ቀጠረ[3]"** ስር **"ቅጥር ግቢ"** ን ተመ.

**ቅፅር "ቀጠረ[3]"** ስር **ቅጥር"** ን ተመ.

**ቅፅበት** ስ አፍታ፥ በጣም አጭር የሆነ የጊዜ ልክ::

**ቅፅበተ አይን** ስ አይን እንደ መከደን ብሎ እስኪገለጥ ድረስ ያለና እጅግ በጣም አጭር የሆነ የጊዜ ልክ::

**በቅፅበት (ከመቅፅበት)** ተው.ግ. እጅግ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ፥ ወዲያውኑ::

**ቅፈፍ "ቀፈፈ[1]"** ስር ተመ.

**ቅፍለት** ስ አንዱ ከሌላው ሂላ በመሆን እንደሰንሰለት ተቀጣጥሎ የሚጓዝ የተጫኑ የነጋዴ ግመል መንጋ::

**ቅፍንድ "ቀፈት"** ን ተመ.

**ቅፍድድ (ቅፍድ) "ቀፈደደ"** ስር ተመ.

**ቆ** የ **"ቀ"** ፊደል ሳብእ ዘር::

**ቆለለ** ግ 1. ከመረ፥ አነባበረ፥ አደራረበ፥ በአንድ ላይ ሰበሰበ:: 2. አበዛ፥ ጨመረ፥ ከመጠን በላይ ከፍ አደረገ (ዋጋን፥...)::

**ቁልል** ቅ ክምር::

**ቁልልታ** ስ ጉብታ፥ ከአካባቢው ተለይቶ እንደ ኮረብታ ከፍታ ያለው መሬት::

**ቆለመመ** ግ ጠመዘዘ፥ ቀለሰ፥ አጎበጠ::

**ቆልማማ** ቅ 1. ጎባጣ፥ ቅልስ:: 2.(ዘይ.) ጠማማ፥ ወልጋዳ (ለጠባይ)::

**ተቆላመመ** ግ 1. ተጠማዘዘ፥ ተጣመመ፥ ተወላገደ:: 2. አልገጥም፥ አልስማማ አለ፥ አስቸገረ፥ እምቢ አለ::

**አቆላመመ** ግ አጠማዘዘ፥ አጎበጠ፥ አጣመመ::

***ቆለመጠ**

**ቁልምጫ** ስ የመውደድ፥ የመለማመጥ፥ የማባበል፥ የማሞካሸት፥ የማወደስ፥... አነጋገር ወይም አጠራር::

**የቁልምጫ ስም** ስ ዋናውን የመጠሪያ ስም ቅርፅ ለወጥ አድርጎ ለመጥራት የሚያገለግል፥ በቤተሰብ ወይም በጓደኛ አማካይነት የሚወጣ የፍቅር ስም:: ለምሳሌ አበበን "አቤ"፥ ዘነበችን "ዘኑ" እንደማለት ያለ አጠራር::

**ተቆላመጠ** ግ በቁልምጫ ተጠራ፥ ተሞካሸ::

**አቆላመጠ** ግ በቁልምጫ ጠራ፥ አሞካሸ::

**አቆላማጭ** ቅ አሽቃባጭ::


**ቆለቆለ** ግ ወደታች ወረደ፥ ዝቅ አለ::

**ቁልቁል** ተው.ግ. ወደታች፥ ዝቅ ወዳለ ቦታ::

**ቁልቁለት** ስ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚወስድ ተዳፋትነት ያለው መንገድ፥ ቦታ::

**ቆልቋላ** ቅ ተጸፋትነት ያለው፥ ዘቅዛቃ::
**ተቆለቆለ** ግ ቁልቁል ሄደ፥ ወደታች ወረደ::
**ተሽቆለቆለ** ዝ.ከ.
**አቆለቆለ** ግ 1. ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሄደ፥ አዘቀዘቀ፥ ወደታች ወረደ:: 2. ቀነሰ፥ ዝቅ አለ፥ ወረደ (ዋጋ)::
**አቆልቋይ** ስ 1. ወደታች የሚሄድ፥ ወራጅ:: 2. በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው ሊመገብበት የሚችል ሞላላ ገበታ፣ አውራጅ፣ አቆልቋይ ገበታም ይባላል::
**አሽቆለቆለ** ግ 1. ወደታች ወረደ፥ ቁልቁል ሄደ:: 2. ዝቅ አለ፥ ቀነሰ፥ ወረደ (ዋጋ)::
**ቆለቆል** ስ መርዛማ የሆነና ወተት የሚመስል ነጭ ፈሳሽ የሚወጣው፥ በቆላማ ቦታ የሚገኝ፥ ቁልቋል መሰል የእፀዋት አይነት::
**ቆለኛ** "ቆላ[2]" ስር ተመ.
**ቆለጥ** ስ ከወንዴ ብልት መባቀያ ስር ከረጢት መሰል በሆነ የአካል ክፍል ውስጥ የሚገኝ፥ ወንዴ ዘርን የሚያመነጭና ጥንድነት ያለው ፍሬ የሚመስል አካል::
**ቆለጣም** ቅ (ዘይ.) ትእቢተኛ ጎረምሳ::
***ቆለጨ**
**ቆለጭ** ቅ አይነ መልካም፥ አይነ ከብላላ::
**ቁልጭ አለ** ግ 1. ጠራ፥ ንፁህ ሆነ:: 2.ወለል ብሎ፥ ግልፅ ሆኖ ታየ:: 3. ይፋ ወጣ፥ ግልፅ ሆነ::
**ቁልጭ ያለ** ቅ 1. ያማረ፥ የጠራ፥ ንፁህ የሆነ:: 2. ግልፅ የሆነ::
**ቁልጭ አደረገ** ግ 1. አጠራ፥ ንፁህ አደረገ:: 2. ግልፅ አደረገ::
**ቁልጭ ቁልጭ አለ** ግ ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ በማንከባለል አየ፥ ተመለከተ::
**ቁልጭ ቁልጭ አደረገ** ግ ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥...የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ በማንከባለል አየ፥ ተመለከተ::
**ቁልጭልጭ** ቅ ውብ፥ መልካም፥ አይናማ::
**ቁልጭልጭ አለ** ግ ተዋበ፥ ፀዳ፥ አማረ::
**ቁልጭልጭ አደረገ** ግ አስዋበ፥ አፀዳ፥ አሳመረ::
**ተቁለጨለጨ** ግ 1. ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑ ወዲያና ወዲህ እየተንከባለለ አየ፥ ተመለከተ:: 2. ተዋበ፥ አማረ::
**አቁለጨለጨ** ግ 1. ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ እያንከባለለ አየ፥ ተመለከተ:: 2. አስዋበ፥ አሳመረ:: 3. አጓጓ፥ አስጎመጀ::

**ቆለፈ** ግ 1. በርን፥ ሳጥንን፥... በቁልፍ ዘጋ፥ እንዳይከፈት አደረገ:: 2. የሸሚዝን፥ የኮትን፥ የቀሚስን፥ የኪስን፥...ክፍተት በአዝራር፥ በቻርኔላ(በዚፕ)፥... አያያዘ፥ ገጠመ፥ ዘጋ:: 3. አጎበጠ፥ ቀለሰ:: 4. አንቆ ያዘ፥ አልለቅ፥ አላንቀሳቅስ አለ::
**ቁልፍ** ስ 1. የበር፥ የሳጥን፥...መዝጊያ እንዳይከፈት አንቆ ወይም ጠርቅሞ የሚይዝ፥ ከብረታ ብረት የሚሰራ እቃ፣ ጓንጓቸር::2. የቁልፍ መክፈቻ እና መቆለፊያ:: 3. አዝራር:: 4. (ዘይ.) ዋነኛ፥ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችል ወይም የሚያስችል (ሰው፥ ቦታ፥...):: ቅ 5. በቁልፍ የተቆለፈ፥ የተዘጋ:: *ቤቱ ቁልፍ በመሆኑ መግባት አልተቻለም::*




ቁልፍ

**ቆላፋ** ቅ ከወደጫፉ የተቀለሰ፥ የተቆላመመ (እንጨት ወይም ብረት)::
**ቁልፍ** ቅ (ዘይ.) ዝግ፥ መናገር የማይችል::
**ቆላለፈ** ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አጠላለፈ፥ አወሳሰበ፥ አያያዘ:: 2. ቆለፈ::
**ቁልፍልፍ** ቅ አንዱ ከሌላው ጋር የተጠላለፈ፥ የተወሳሰበ፥ የተያያዘ::
**መቆለፊያ** ስ 1. ቁልፍ ወይም ጓንጓቸር:: 2. የ"ቁልፍ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 3. እንደ አዝራር ያለና በቁልፍነት የሚያገለግል ማንኛውም ነገር::
**ተቆለፈ** ግ 1. ተዘጋ፥ ተገጠመ:: 2. ጎበጠ፥ ታጠፈ፥ ተቀለሰ::
**ተቆላለፈ** ግ 1. ተጠላለፈ፥ ተሳሰረ፥ ተወሳሰበ፥ ተያያዘ (አንዱ ከሌላው ጋር):: 2. አንድም ሳይቀር ሁሉም ተቆለፈ፥ ተዘጋ::
***ቆለፈ**
**ቆለፈት** ስ የወሸላ ሽፋን፣ ሸለፈት፥ ልምቡጥ::
**ቆለፈታም** ቅ (ስድብ) ሸለፈታም፣ ወሸላ፥ ያልተገረዘ (ወንድ)::
**ቆላፍ** ቅ 1. ያልተገረዘ፥ ወሸላ:: 2. የአህዛብ ወገን፥ አረማዊ::
**ቆላ[1]** ግ 1. ምጣድን እሳት ላይ አድርጎ

በማስማትና በላዩ ላይ እንደ ጥራጥሬ ያሉ የምግብ አይነቶችን በማስቀመጥና በማመስ አበሰለ:: 2. ከሰሚ ምጣድ ላይ የተደረገን ጥራጥሬ ወይም ሌላን ነገር በመቁያ አመሰ፥ አገላበጠ:: 3. አቃጠለ፥ ፈጀ (በሽታ፥ ፀሃይ፥ ረሃብ፥ ችጋር፥ ጥይት፥...):: 4. አቃረ፤ አቃጠለ(ልብን):: 5. ወዘወዘ፤ ወነወነ፥ ነቀነቀ (ውሻ፥ ድመት፥... ጅራትን)::

**ቆላው** (ነውር) የወሲብ ፍላጎት አቅነዘነዘው::

**መቁሊያ (መቁያ)** ስ ከሰሚ ምጣድ ላይ የተነዛን ጥራጥሬ፤ ቡና፤... እንዳያር እያመሱ ወይም እያገለባበጡ ለማብሰል የሚረዳ ከጭፋ ቆልመም ያለ እንጨት ወይም ብረት፤...።

**ቁሌት** ስ እንደ ሽንኩርት፤ በርበሬ፥ ቅመም፥ ዘይት ያሉትን ከትንሽ ውሃ ጋር አንድነት አድርጎ በማብሰል የሚዘጋጅና በርከት ብሎ ለሚሰራው ወጥ እንደ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል የወጥ ጅምር፤ ውጥን::

**ቁሌታም** ቅ (ነውር፤ ስድብ) ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ያለው::

**ቆሎ** ስ ከሰሚ ምጣድ ላይ ተደርጎና ታምሶ የበሰለ ጥራጥሬ::

**የቆሎ ተማሪ** ስ እየለመነ ከየመንደሩ የሚያገኘውን ቁራሽ እንጀራ፥ እንዲሁም ጥራጥሬውን በቆሎ መልክ እያዘጋጀ በመመገብ እንደ ንባብ፤ ዜማ፥ ቅኔ፥... ያሉትን የትምህርት አይነቶች የሚቀዕል የቤተክህነት ተማሪ::

**ተቆላ** ግ (ነውር) የወሲብ ፍላጎት ተነሳበት::

**ተቁላላ** ግ 1. ወጥ ለመስራት በቀዳሚነት የሚፈለገው ቅመም (ሽንኩርት፥ ቅባት፥ በርበሬ ወይም ማቁላሊያ) እሳት ላይ በተጣደ ድስት ውስጥ ተደርጎ እየተማሰለ ተቀቀለ፥ የወጡ የመጀመሪያ ደረጃ ስራ ተከናወነ:: 2. (ዘይ.) ተጉላላ::

**አቁላላ** ግ ወጥ ለመስራት በቀዳሚነት የሚፈለገውን ቅመማቅመም ወይም ማቁላሊያ እሳት ላይ በተጣደ ድስት ውስጥ ጨምሮ እያማሰለ ቀቀለ፥ አበሰለ::

**ማቁላሊያ** ስ እንደ አብሽና በሶብላ፥... ያሉ ቅመሞች ተጨምረውበት የተዘጋጀ የሽንኩርት ዱቄት::

**ቆላ**[2] ስ አቀማመጡ በጣም ዝቀተኛና ሞቃታማ የሆነ ቦታ፥ ሃገር፤ የደጋ ተቃራኒ::

**ቆላና ደጋ ረገጠ** 1. ሲራመድ ሚዛኑን ስቶ እዚህና እዚያ ማዶ ረገጠ፥ ተግተረተረ:: 2. ያልተስተካከለ ነገር በመናገር ዘባረቀ፥ ዘላበደ::

**የቆላ ቁስል** ስ እየሞቀሞቀ የሚያስቸግርና ቶሎ የማይድን የቁስል አይነት::

**የቆላ ዝንብ** ስ በጣም ቆላማ በሆነ አካባቢ የሚገኝ፥ ከብቶችን እየነደፈ የሚገድል መርዛማ የዝንብ አይነት::

**ቆለኛ** ቅ 1. በቆላ የሚኖር:: 2. ሽክላ በመስራት ወይም ቆዳ በመፋቅ፥ በማልፋትና በማለስለስ ወይም ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ብረታብረቶችን በመስራት የሚተዳደር የእጅ ባለሙያ::

**ቆላማ** ቅ ቆላነት ያለው፥ ሞቃታማ::

**ቆላለፈ** "ቆለፈ" ስር ተመ.

**ቆላፋ** ዝ.ከ.

**ቆላፍ** "*ቆለፈ" ስር ተመ.

**ቆሌ** ስ የአንድን ሰው ወይም አካባቢ ደህንነት ይጠብቃል ወይም ግርማ ሞገስ ይሰጣል ተብሎ የሚታሰብ እንደ ውቃቢ፥ ዛር፤ ከራማ፥ አድባር፥... ያለ የባእድ አምልኮ መንፈስ::

**ቆሌ ገፈፈ** በጣም አስደነገጠ::

**ቆሌው ተገፈፈ** ውቃቢ ራቀው፤ ግርማ ሞገሱን አጣ፤ በጣም ደነገጠ::

**ባለ ቆሌ** ቅ ውቃቢ፥ ዛር ያለበት (ሰው)::

**ቆሌቢስ** ቅ 1. ግርማ ሞገስ የሌለው፥ ጥላ ቢስ፥ ከውካዋ:: 2. ረድኤት የለሽ::

**ቆልማሚት** ስ በጣም ረዥም ቅልጥምና ቆልማማ የሆነ ረዥም አንገት ያለው፥ በአብዛኛው መልኩ ነጭ የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ በሃይቆች አካባቢ በመንጋ ሆኖ የሚገኝ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

**ቆልማማ** "ቆለመመ" ስር ተመ.

**ቆልቋላ** "ቆለቆለ" ስር ተመ.

**ቆሎ** "ቆላ[1]" ስር ተመ.


**ቆመ** ግ 1. ከተቀመጠበት ተነሳ፥ ብድግ አለ:: 2. ተገተረ:: 3. ተገታ፥ ታገደ:: 4. እንቅስቃሴው፥ ሂደቱ ተቋረጠ፥ መስራቱን ተወ:: *ሰአቱ ቆመ::* 5. አበቃ፥ አለቀ፥ ተፈፀመ:: *ንግግሩ እንደቆመ ትርኢቱ ይቀጥላል።* 6. ጠበቃ፥ ወኪል፥ አጋዥ ሆኖ ተከራከረ:: *ለሰላም እንቆማለን::* 7. ረገጠ:: *እግሬ ላይ ቆመ::* 8.ተሰራ፥ተቋቋመ፥ ተመሰረተ፥ ተተከለ:: *ትምህርት ቤት ቆመ/ ሃውልት ቆመ::*

**ቆሚ ቀረች** ባል ሳታገባ ቀረች::

**ቆሞ ቀር (ቁሞ ቀር)** ቅ (ስድብ) ባል ሳታገባ ጊዜው ያለፈባት::

***መቆሚያ*** ቅ መጨረሻ፥ ማለቂያ:: *ወሬው መቆሚያ የለውም::*

***መቋሚያ*** ስ ብዙውን ጊዜ ካህናት በቤተክርስቲያን ውስጥ



*መቋሚያ*

የሚደገፉበት፥ ዝማሜ የሚዘሙበት፥ የሚመረኩዙትና በስተ አናቱ በኩል ለመደገፊያነት እንዲመች ሆኖ የተሰራ ምርኩዝ::

**በቁሙ (በቁም)** ተው.ግ. 1. በህይወት እያለ:: 2. ሳይቀመጥ፥ እንደቆመ፥ ሳያርፍ:: 3. ሳይነቀል፥ ሳይታጨድ፥ ሳይሰበሰብ፥ ሳይወቃ፥ በተዘራበት እርሻ ላይ እንዳለ::*ሰብሉን በቁሙ ሸጠው::*

**በቁሙ ሞተ** 1. መጥፎ፥ አሳዛኝ ነገር ደረሰበት ወይም ተፈፀመበት:: 2. በጣም ተጎሳቆለ፥ ከሰውነት ተራ ወጣ::

**በቁሙ የሞተ** ቅ እርባና የሌለው፤ ራሱን ያዋረደ፤ መንፈስ ደካማ::

**ቁም ለቁም** (ስድብ) 1. ቀውላላ፥ ረዥም፥ ከርፋፋ:: 2. ስራ መስራት የማትወድ፥ ገልቱ፥ ሰነፍ:: 3. በወርዱ ወይም በጎኑ ሳይሆን በቁመቱ::

**ቁምሳጥን** ስ ቁመቱ ረዘም ያለና የቤት በር የመሰለ መዝጊያ ያለው፥ ብዙውን ጊዜ ለልብስ መስቀያና ማስቀመጫ የሚያገለግል ትልቅ ሳጥን::

**ቁም ስቃይ** ተው.ግ. ከፍ ያለ ስቃይ፥ ጭንቅ፥ መከራ::

**ቁም ስቅሉን አየ** መከራ ተቀበለ፥ተሰቃየ::

**ቁም ነገር** ስ ፍሬ ያለው ወይም ጠቃሚ የሆነ ነገር፥ ሃሳብ::

**ቁም ንባብ** ስ በቤተክህነት የንባብ ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚሰጥ ፈጠን ያለ የአነባበብ አይነት::

**[የ] ቁም እስር** ስ ከተወሰነ የቦታ፥ የሃገር ክልል ወይም አካባቢ ውጭ መንቀሳቀስ የማይፈቀድበት የእስር አይነት፤ ግዞት::

**ቁም ከብት** ስ እንደ በግ፥ ፍየል፥ በሬ፥ ላም፥... ያለ የቤት እንስሳ ሃብት::

**ቁም ዜማ** ስ (ቤ.ክህ.) የድጓ ዜማ::

**ቁም ፅህፈት** ስ ብዙውን ጊዜ በመቃ ብእር በብራና ላይ የሚፃፍ ጉልህና ውብ የሆነ የእጅ ፅሁፍ::

**ቁመት** ስ 1. የርዝመት መጠን:: 2. ከእግር እስከ አናት ድረስ ያለው ርዝመት::

**ቁመና** ስ የሰውነት ወይም የአካል ቅርፅ፥ አቋም::

**በቁመና** 1. በህይወት እያሉ:: 2. በአካል ቅርፅ፥ በአቋም:: 3. ሳይሰበሰብ በተዘራበት እርሻ ላይ እንዳለ:: *ሰብሉን በቁመናው ሸጠው::*

**ቋሚ** ስ 1. ከእንጨት በሚሰራ የቤት ግድግዳ ዙሪያ አልፎ አልፎ የሚተከል ቀጥ ያለ ጠንካራ እንጨት::ቅ 2. አሳላፊ፥ አስተናጋጅ፥ አስተናባሪ:: 3. በህይወት ያለ (የሚች ዘመድ፥ ቤተሰብ፥ ወገን):: 4. ዘላቂ::

**ቋሚ ሰራተኛ** ስ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና መደበኛ ተቀጣሪ የሆነ ሰራተኛ::

**ተቆመ** ግ (ቤ.ክህ.) በዜማ ተባለ፥ ተፀለየ:: *ሰአታት ተቆመ::*

**ተቋም** ስ ልዩ ምርምርና ጥናት የሚካሄድበት፥ የልዩ ልዩ ሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበት ድርጅት::

**ተቋቋመ** ግ 1. ተመሰረተ:: 2. ስር ሰደደ፥ ተጠናከረ፥ ደረጀ:: *እስኪቋቋሙ ድረስ ኑሮ ያስቸግራል::* 3. መከተ፥ ተከላከለ:: 4. ተሟገተ፥ ተከራከረ::

**መቋቋሚያ** ስ አንድን ተግባር ለማካሄድ የሚያስፈልግ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት፤ መነሻ ሃብት::

**አቆመ** ግ 1.ብዙ እንዲቆም፥ እንዲቆይ አደረገ፥ አስቆመ:: 2. ብድግ፥ ቀጥ አደረገ:: 3. ገታ፥ አገደ፥ ከለከለ፥ አስቀረ:: 4. ገተረ:: 5. እንዳይሰራ፥ እንዳይንቀሳቀስ አደረገ:: 6. የመሄድ፥ የመምጣት፥ የመጓጓዝ እንቅስቃሴ አቋረጠ:: 7. መሰረተ፥ አቋቋመ:: 8. አበቃ፥ ፈፀመ::

**አቋም** ስ 1. ማንኛውም ነገር ከእድሜ፥ ከጥንካሬ፥...አኳያ ሲገመገም የሚገኝበት ሁኔታ፥ አኳኋን:: 2. አንድን ጉዳይ አስመልክቶ የሚወሰድ የራስ አስተያየት፥ አመለካከት፥ ፍላጎት፥ ውሳኔ::

**የአቋም መግለጫ** ስ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በተደረገ ስብሰባ ላይ የተላለፉ የውሳኔ ነጥቦችን ይዞ የሚወጣ መግለጫ::

**አቋም ወሰደ** አንድን ጉዳይ በተመለከተ አንድ አይነት አመለካከት፥ ውሳኔ ያዘ::

**አቋቋመ** ግ 1. መሰረተ፥ ሰራ፥ አበጀ:: 2.አደራጀ፥ አጠናከረ፥ አበረታታ፥ አገዘ፥ ረዳ:: *ልጆቱ ንግድ ቤት ከፍታ እንድትሰራ ያቋቋሟት ወላጆቿ ናቸው::* 3. ወላጆች ልጃቸውን ክርስትና በሚያስነሱበት ቦታ በመገኘት አብሮ ስርአቱን አከበረ፥ ተከታተለ::

**አቋቋም** ስ 1. የመቆም ሁኔታ (ቀጥ በማለት ወይም ባለማለት):: 2. መዘምራን ከመቋሚያ ውዝዋዜ፥ ከፀናፅልና ከከበሮ ድምፅ ጋር እያቀናጁና እያስማሙ የሚያዜሙት የማህሌት ዜማ፤ ትምህርቱም አቋቋም ይባላል::

**አስቆመ** ግ 1. ብዙ አስጠበቀ (በመንገድ ላይ):: 2. አሳገደ፥ አስከለከለ:: 3. እንዲያቆም ወይም እንዲቆም አደረገ::

**ቆመረ** ግ ቁማር ተጫወተ::

**ቁማር** ስ ገንዘብን፥ ንብረትን አሲዘው በጨዋታ ብልጫ ተከከር አንዱ ሌላውን ለመርታትና የተያዘውን ለመውሰድ ወይም ለመብላት የሚደረግ ጨዋታ::

**ቁማርተኛ** ስ አዘውትሮ ቁማር የሚጫወት ሰው።

**ቆመጠ** ግ 1. ቆማጣ አደረገ፥ አካልን አጎደለ (ቁምጥና ወይም ደዌ ስጋ)። 2. ጎመደ፥ ጎረደ፥ በጠሰ፥ ቆረጠ። 3. በዱላ መታ፥ ነረተ። 4. (ዘይ.) አሳነሰ፥ ቀነሰ፥ አጎደለ። *ወፍጮው እህሉን ቆምጦ አስቀረው።*

**ቆምጦ ቀጥል** ቅ ውሸታም፣ ያልሆነውን ሆነ፥ ያልተደረገውን ተደረገ ብሎ የሚያወራ።

**ቁምጣ** ስ 1. ከጉልበት በላይ የሚውል አጭር ሱሪ። 2. የኩንታል አጋማሽ የሚሆን ጆንያ።

**ቁምጥና** ስ መላ ሰውነትን የሚያቆስል፥ የሚቆራርጥ ደዌ ስጋ።

**ቆመጥ** ስ አጭርና ወፈር ያለ ዱላ።

**ቆማጣ** ቅ (ስድብ) በደዌ ስጋ አካሉ የቆሰለ፥ የተቆረጠ፥ የተጎዳ (ሰው)። 2. አጭር፣ ሰንካላ፣ ጎደሎ።

**ቁምጥ አለ** ግ 1. ተቆመጠ። 2. እሁለት ተከፈለ፥ ግምስ አለ። 3. (ዘይ.) ሳይታሰብ በድንገት መጠኑ አነሰ፥ ቀነሰ።

**ቆማመጠ** ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ቆመጠ፥ አቆሰለ (ደዌ ስጋ)። 2. ቆራረጠ፥ ጎራረደ።

**ቁምጥምጥ (ቆመጥማጣ)** ቅ (ስድብ) ቆማጣ።

**ቁምጥምጥ አለ** ግ ተቆማመጠ።

**ቁምጥማጭ** ቅ ቁርጥራጭ።

**ተቆመጠ** ግ 1. ደዌ ስጋ (ቁምጥና) ያዘው፥ ቆሰለ፥ ቆማጣ ሆነ። 2. ተቆረጠ፥ ተጎመደ።

**ተቆማመጠ** ግ 1. በቁምጥና ህመም ቆሳሰለ፥ አካሉ በቁስል ተበጣጠሰ። 2. ተቆራረጠ፥ ተጎማመደ።

**ቆሞስ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ)ስልጣነ ክህነቱ ከኤጲስቆጶስ በታች የሆነ የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አባት።

**ቆረመ** ግ ጭንቅላትን በትንሹ መታ፥ ለኮፍ አደረገ፥ ኮረኮመ።

***ቆረመደ**

**ቆርማዳ (ቆረመድ)** ቅ የተጎሳቆለ፥ ጨባጣ፥ ድህነት ያጠቃው።

**ተቆራመደ** ግ 1. ተኮማተረ፥ ተኮራመተ፥ ተጨበጠ፥ ቆረፈደ። 2. በችግር፥ በድህነት ተጎሳቆለ፥ ተሰቃየ።

**ተቆረማመደ** ግ ተቆራመደ።

**አቆራመደ** ግ 1. አኮማተረ፥ አኮራመተ፥ አቆረፈደ። 2. በችግር ፥ በድህነት አጎሳቆለ፥ አሰቃየ።

**አቆረማመደ** ግ አቆራመደ።

**ቆረረ**[1] ግ በቀጭኑ ኮለል ብሎ ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)።

**ቁርር ብሎ ወረደ** ግ ቆረረ።

**መቁረርት** ስ ብዙውን ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የቅዳሴ ፀበል የሚያድሉበት እንደማንቆርቆሪያ ያለ እቃ፣ ኩስኩስት።

**ቆረረ**[2] ግ እጅግ በጣም በረደ፥ ቀዘቀዘ።

**ቁር(ቆራ)** ስ እጅግ በጣም ሃይለኛ የሆነ ቅዝቃዜ፥ ውርጭ።

**ቆረሰ** ግ ገመሰ፥ ከፈለ፥ ቀረደደ፥ ሸረፈ (እንጀራን፥ ዳቦን፥...)።

**ቁራሽ** ቅ 1. የእንጀራ ክፋይ ወይም ሽራፊ። 2. ትንሽ። *ቁራሽ መሬት አለችኝ።*

**ቁርስ** ስ ብዙውን ጊዜ ጧት የሚበላ መጠነኛ ምግብ።

**ቁርስራሽ** ቅ ብዙ ቁራሽ፥ ሽርፍራፊ።

**ተቆረሰ** ግ ተገመሰ፥ *ተከፈለ፥ ተቀረደደ፥* ተሸረፈ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)።

**ተቋረሰ** ግ ተካፈለ፥ ተጋራ (ምግብን)።

**አቋረሰ** ግ አካፈለ፥ አጋራ፥ አሳተፈ (ምግብን)።

***ቆረሰሰ**

**ቆርሳሳ(ቆረሰስ)** ቅ ከርፋፋ፥ ዘገምተኛ፥ ቀርፋፋ።

**ተንቆረሰሰ** ግ ቀስ እያለ ተራመደ፥ አዘገመ፥ ተንቀረደደ።

**አንቆረሰሰ** ግ በቀስታ አራመደ፥ አስኬደ፥ አንቀረደደ።

**ቆረቆረ** ግ 1. ወጋ፥ ጎረበጠ፥ አሳመመ፥ ምቾት ነሳ (አይንን፥ ገላን)። 2. መታ፥ አንኳኳ (በርን፥ ጠረጴዛን፥...)። 3. ቆጨ፥ ቅር አሰኘ፥ አሳዘነ፥ ከነከነ (ነገር፥ ድርጊት፥ ሁኔታ)። 4. ጀመረ፥ መሰረተ፥ ሰራ (መንደርን፥ ከተማን)። 5. በመቆርቆሪት እየታገዘ የሽክላን ቀዳዳ በሞራና በጨርቅ ጠቀጠቀ፥ ደፈነ፥ ቀዳዳው እንዳያፈስ መረገ። 6. በሹል ብረት ወይም በመቆርቆሪት በሳ፥ ነደለ፥ ሸነቆረ። 7. በትካዜ መንፈስ መሬትን መታ መታ አደረገ፥ ጫረ።

**መቆርቆሪት** ስ 1. የብረት፥ የቆርቆሮ፥... መብሻ፥ መሸንቆሪያ፥ እንዲሁም የተሸነቆረ ሽክላን በጨርቅና በሞራ እየጠቀጠቁ ለመድፈን የምታገለግል ሹል ብረት። 2. አነስተኛ መዶሻ።

**ተቆረቆረ** ግ 1. አዘነ፥ ቅር ተሰኘ፥ ተቆጨ። 2. ተጀመረ፥ ተመሰረተ፥ ተሰራ (መንደር፥ ከተማ)።

**ተቆርቋሪ** ቅ አሳቢ፥ አዛኝ፥ የሚቆጭ።

**አይቆረቁሬ** ክፋት፥ ተንኮል የማያውቅ፥ ጥሩ

ጠባይ ያለው፥ ሰው የማያስቀይም።

***ቆረቆረ**

**ተንቆረቆረ** ግ 1. ፈሳሽ የሆነ ነገር በቀጭኑ ወረደ፥ ፈሰሰ። 2. ተቀዳ። *ጠጁ በጠርሙስ እየተንቆረቆረ ተቀምጧል።*

**አንቆረቆረ** ግ 1. ፈሳሽ የሆነን ነገር በቀጭኑ ቀዳ፥ ከአንዱ እቃ ወደ ሌላው እቃ አስተላለፈ። 2. ዘለግ ባለና በሚያስደስት ድምፅ አዜመ። *ዜማውን አንቆረቆረው።*

**ማንቆርቆሪት** ስ ፈሳሽነት ያለውን (እንደ ዘይት፥ ጋዝ፥...ያለን) ነገር ከአንዱ እቃ ወደ ሌላው ያለማፍሰስ በትክክል ለማዛወርወይም ለመቅዳት የሚረዳ እንደ ቅል አንገት ጠበብ ያለ ቀዳዳ ወይም ጡት ያለው እቃ።



ማንቆርቆሪት

**ማንቆርቆሪያ** ስ ብዙውን ጊዜ ለጠላና ለጠጅ ማደያ የሚያገለግል፥ በውስጡ ያለውን ፈሳሽ ወደ ሌላ እቃ ውስጥ ያለማፍሰስ ለማዛወር የሚረዳ እንደ ጀበና ያለ ጡት ያለው፥ ከኒኬል ወይም ከሌላ ማእድን የሚሰራ የቤት እቃ።

**ቆረቆር** ስ ራስ ላይ ጉብ ጉብ ብሎ የሚወጣ የቀስል ህመም አይነት።

**ቆረቆራም** ቅ (ስድብ) ቆረቆር ያለበት።

**ቆረቆሰ**[1] ግ በገና ጨዋታ ጊዜ ጨዋታውን ጀመረ፥ ባረከ (እሩሩን በገና ዱላ በመምታት)።

**ቁርቆሳ** ስ ጅመራ (የገና ጨዋታ ወይም የጠብ)።

**ተቆራቆሰ** ግ 1. በገና ጨዋታ ላይ ዱላና ዱላን በማጋጨትና እሩርን በመምታት ጨዋታውን ጀመረ። 2. ተጋጨ፥ ተጣላ፤ ጠብ፥ ጦርነት ጀመረ፥ አጫረ።

**አቆራቆሰ** ግ 1. የገና ጨዋታ ተጫዋቾች (የቡድን አባቶች) በግብ አማካይ ቦታ ላይ ሆነው እሩሩን እኩል ተሻምተው በመምታት ጨዋታውን እንዲጀምሩ አደረገ፤ እንደ ዳኛ ሆኖ የጨዋታውን አጀማመር ስርአት ተቆጣጠረ። 2. አጣላ፥ አጋጨ፥ እንዲተናኮሱ፥ እንዲጣሉ አደረገ።

**አቆራቋሽ** ስ 1. የገና ጨዋታ ተጫዋቾችን የጨዋታ አጀማመር ስርአት የሚቆጣጠር ሽማግሌ፥ ዳኛ። 2. (ዘይ.) አንዱን ከሌላው ጋር የሚያጣላ፥ የሚያጋጭ፥ ነገረኛ (ሰው)።

**ቆረቆሰ**[2] ግ አረጀ፥ ተቆራመደ፥ ቆረቆዘ።

**ቆርቋሳ** ቅ (ስድብ) ያረጀ፥ የተቆራመደ።

**ቆረቆንዳ** ስ 1.ፍሬዎቹ ተፈልፍለው ከላዩ ላይ ከተወሰዱ በሂላ የሚቀረው የበቆሎ ፍሬዎች ተሸካሚው አካል። 2. (ዘይ.+ ስድብ) ለዛው ያለቀ፥ የተጧጠጠ (ሽማግሌ፥ አሮጊት)።

**ቆረቆዘ** ግ 1. ቀጨጨ፥ ጫጫ፥ ከሰመነ። 2. ደሀየ።

**ቆርቋዛ (ቆረቆዝ)** ቅ ከስማና፥ ቀጫጫ።

**አቆረቆዘ** ግ 1. አቀጨጨ፥ አከሰመነ። 2. በዘበዘ፤ አደሀየ።

**አቆርቋዥ** ቅ በዝባዥ፥ ሌላው የደከመበትን የስራ ውጤት ያለአግባብ የሚወስድ።

**ቆረበ** ግ (ክር.) 1. የክርስቶስን ስጋ በላ፥ ደሙን ጠጣ፤ ስጋ ወደሙ ተቀበለ። 2. ስጋ ወደሙ በመቀበል በአንድ የትዳር ጓደኛ ተወሰነ።

**ቆራቢ** ቅ (ክር.) 1. ስጋ ወደሙ የሚቀበል ወይም የተቀበለ። 2. ትዳሩ ወይም ጋብቻው በቁርባን ወይም በስጋ ወደሙ የተወሰነ።

**የቆራቢ እራት** ስ (ክር.) የሟች ቤተሰብ በሟች ስም አዘጋጅተው ለቀዳሽ ካህናት የሚሰጡት ምግብና መጠጥ፤ ጠበል ጠዲቅ።

**ቁርባን** ስ (ክር.)1. ስጋ ወደሙ። 2. የሟችን ስም እየጠሩ በቤተክርስቲያን ፀሎት ለሚያደርጉ ካህናት እንዲሁም ለድሆች ይሰጥ ዘንድ በሟች ቤተሰብ የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ፤ ጠበል ጠዲቅ፤ መክፈልት።

**ተቆረበ** ግ (ክር.) 1.በቤተክርስቲያን የቅዳሴ ስነስርአት ተካሄደ፥ ተቀደሰ። 2. የቁርባን ስርአት ተካሄደ፥ ተከናወነ፥ ስጋ ወደሙ ለምእመናን ተሰጠ።

**አቆረበ** ግ (ክር.) 1. ስጋ ወደሙ ሰጠ፥ አቀበለ (ካህን)። 2. ወደ ቤተክርስቲያን ወስዶ ስጋ ወደሙ እንዲቀበል አደረገ (ቤተሰብ ልጅን ወይም እቅመደካማ የሆነን ሰው)።

**አቁራቢ** ቅ (ክር.) ለቆራቢዎች ስጋ ወደሙ ያቀበለ ወይም የሚያቀብል ካህን።

**ያቁራቢ** ስ (ክር.) ለአቁራቢዎች (ለቀደሱና ስጋ ወደሙ ላቀበሉ ካህናት) የሚሰጥ ምግብና መጠጥ ወይም ገንዘብ።

**አስቆረበ** ግ (ክር.) 1. በቤተክርስቲያን ተገኝቶ የቅዳሴው ስነስርአት እስኪያልቅ ድረስ የፀሎቱ ተካፋይ ሆነ። 2. ፀበል ፃዲቅ በሟች ስም እያዘጋጀ ለካህናትና ለነዳያን በመስጠት የሟችን ስም በፀሎት አስጠራ፥ በሟች ስም ቅዳሴ አስቀደሰ።

**አስቆራቢ** ቅ (ክር.) በሟች ስም ቅዳሴ እንዲቀደስ፥ ቁርባን እንዲቆረብ በማድረግ የሟችን ስም በፀሎት የሚያስጠራ (የሟች ቤተሰብ)።

***ቆረበበ**

**ቆርባብቻ (ቁርባብቻ፥ ቁርብቻ)** ስ ከቆዳ ወይም ከጨርቅ የተሰራ ከረጢት።

**ቆርባባ (ቆረበብ)** ቅ ጎርባባ፥ ኮርፋፋ።

**ተንቆረበበ** ግ ተንኮረፈፈ፥ ተንጎረበበ።

**አንቆረበበ** ግ አንኮረፈፈ፥ አንጎረበበ።

**ቆረበጨ** ግ አተረ፥ አበጠ፥ ጎረበ፥ ውሃ ያዘ፥ ወይም አዘለ (የሰውነት ቆዳ)።

**ቁርብጭታ** ስ እትራት፥ እበጥ።

**አቆረበጨ** ግ ቆረበጨ።

**ቆረባ** ግ ደረቀ፥ ገረረ።

**ቆርባ ቆርባ አለ** ግ ተንቆራባ።

**ተንቆራባ** ግ እንደ ደረቀ ቆዳ ተንኳኳ፥ ተንጓጓ።

**አንቆራባ** ዝ.ከ.

**ቆርባብቻ "ቆረበበ"** ስር ተመ.

**ቆረነ** ግ 1. ወሰን፥ ድንበር ለመከለል ድንጋይ ተከለ፥ ምልክት አበጀ። 2. ሰብሉን አጭዶ በማንሳት ማሳው ቆረን እንዲሆን አደረገ።

**ቆረን (ቁረን)** ስ 1. ጤፍ፥ ስንዴ፥ ገብስ፥… ከታጨደ በሗላ ማሳው ላይ የሚቀረው የሰብሉ አገዳ። 2. ሰብሉ ታጭዶ ባዶውን የቀረ ማሳ።

**ቆረንጮ "ቁረንጮ"** ን ተመ.

***ቆረኘ**

**ቁራኛ** ስ 1- ከዳኛ ዘንድ እስኪደርስ ወይም እስኪፈረድ ድረስ፥ እግሩ ወይም እጁ ከጠላቱ እግር ወይም እጅ ጋር እንዲጣመር ተደርጎ ከጠላቱ ጋር በአንድነት ይታሰር የነበረ ሰው። 2.(ዘይ.) የማይለቅ፥ አብሮ የሚኖር እንደ ዛር፥ ርኩስ መንፈስ ያለ በሽታ።

**ተቆራኘ** ግ 1. እጁ ወይም እግሩ ከጠላቱ እግር ወይም እጅ ጋር እንዲጣመር ተደርጎ ታሰረ። 2. (ዘይ.) አልተውም፥ አልለይም፥ አልነጠልም ብሎ አብሮ ሆነ።

**አቆራኘ** ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አጣምሮ አሰረ። 2. ከ___ጋር አብሮ እንዲኖር፥ ከእርሱ እንዳይለይ፥ እንዳይነጠል አደረገ።

***ቆረዘዘ**

**ቁርዝዝ አለ** ግ ተንቆረዘዘ።

**ተንቆረዘዘ** ግ ሊወርድ፥ ሊፈስ ተቃረበ፥ ተንጠለጠለ (እንባ፥ ጤዛ፥…)።

**አንቆረዘዘ** ግ ሊያወርድ፥ ሊያፈስ፥ ሊያዘንብ ተቃረበ፥ አዘለ (ደመና ዝናብን፥ አይን እንባን፥…)።

**ቆረጠ** ግ 1. በጣ፥ ሰነበጠ፥ ሰነጠቀ፥ ቀደደ (ስለት አካልን)። 2. ጎመደ፥ ጎረደ፥ በጠሰ። 3. መደመደ፥ አሳጠረ፤ ከረከመ፥ አስተካከለ (ፀጉርን፥ አታክልትን፥…)። 4. ወሰነ፥ ጨከነ (አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ)። 5. ከተሰጠው ጥቅል ገንዘብ ላይ ለእቃው ወይም ለአገልግሎቱ መከፈል ያለበትን ያህል ሂሳብ ቀንሶ ወሰደ (ገንዘብ ተቀባይ)። 6. ገዛ ወይም ሸጠ (ትኬትን)። 7. ወሰነ፥ በየነ፥ አሳጠረ (ነገርን)። 8. የቀጠሮ ቀን ወሰነ፥ አበጀ። *ቀን ቆረጠ*፡ 9. ቀጠፈ (ቅጠልን፥ ፍሬን ከዛፍ ላይ)። 10.ማርን ከቀፎ ሰበሰበ፥ አወጣ። *ማር የሚቆረጠው በምን ወር ነው?* 11. ጨረሰ፥ ፈፀመ (በመስራት ላይ የነበረን ሽማ፥ ስፌት)።12. አመመ፥ አሰቃየ። *ሆዴን ቆረጠኝ።* 13. (ዘይ.) ቆጨ፥ ከነከነ። *ሗላ ሆድህን ከሚቆርጥህ አሁን ተናገረውና ይወጣልህ።*

**ቆርጦ ቀጥል** ቅ ውሸታም፤ ወሬው የማይታመን (ሰው)።

**መቁረጪት** ስ አነስተኛ መቀስ።

**መቁረጫ** ስ 1. ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለት ያለው መሳሪያ። 2. የመጨረሻ ልጅ። *መቁረጫዬ ሴት ልጅ ናት።*

**ቁራጭ** ቅ የአንድ ነገር ክፋይ፥ ጉማጅ፥ ብጣሽ።

**ቁራጫም** ቅ (ስድብ) ምናምንቴ፥ የሰው ጎደሎ፤ ብጣሻም።

**ቁርጣ** ስ በመጀመሪያው እርሻ ጊዜ መሬቱ የታረሰው ከታች ወደ ላይ ከላይ ወደታች እየተባለ ከሆነ፥ በድጋሚው ጊዜ የዚህ ተቃራኒ የሆነ አቅጣጫ ተከትሎ የሚደረግ የአስተራረስ አይነት።

**ቁርጥ** ቅ 1. እርግጠኛ፥ ትክክለኛ። *ቁርጡ አልታወቀም።* 2. የማይቀር፥ መደረግ ያለበት፥ የመጨረሻ ውሳኔ። *ዘንድሮ ቁርጥ ነው፤ ትዳር እመሰርታለሁ።* ስ 3. ሳይቀቀል ወይም ሳይጠበስ ጥሬውን የሚበላ የከብት ስጋ፤ እርጥብ ወይም ቁርጥ ስጋም ይባላል።

**ቁርጥ ስራ** ስ በተወሰነ ገንዘብ የሚሰራ የተወሰነ የስራ መጠን።

**ቁርጠት** ስ የሆድ ውስጥ የህመም ስሜት አይነት።

**ቁርጠኛ** ቅ 1. እርግጠኛ። 2. ወደሗላ የማይል፥ የማያወላውል (አንድ ነገር ለማድረግ)።

**ቁርጠኛ ዘመድ** ስ ታማኝ፥ የማይከዳ፥ ለክፉ ጊዜ የሚደርስ ዘመድ፥ ወዳጅ።

**ቆራጣ** ቅ (ስድብ) 1. አካለ ጎደሎ፥ አካሉ ሙሉ ያልሆነ። 2. እንከን ያለበት፥ ያልተሟላ፥ ጎደሎ (ነገር)።

**ቆራጥ** ቅ ደፋር፥ ጎበዝ፥ የማያወላውል፥ በውሳኔው የሚፀና።

**ቁርጥራጭ** ቅ ብጥስጣሽ፥ ክፍልፋይ፥ ከተቆራረጠ ነገር ላይ የተራረፈ።

**ቁርጥርጥ አለ** ግ ተቆራረጠ።

**ቁርጥርጥ አደረገ** ግ አንድን ነገር ብዙ ቦታ ላይ ቆረጠ፥ ጎመደ።

**ተቆረጠ** ግ ተጎረደ፥ ተጎመደ፥ ተበጠሰ።

**ተቆራጭ** ቅ 1. በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ወይም የሚሰጥ መተዳደሪያ ገንዘብ (ለምሳሌ ለወላጅ ወይም ለልጅ ማሳደጊያ)፡፡ 2. ከሙሉ ሂሳብ ወይም ገንዘብ ላይ ተከፋይ ሆኖ የቀረ ወይም የሚቀር (ገንዘብ)፡፡

**ተቆራረጠ** ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ተቆረጠ፥ ተበጠሰ፥ ተጎመደ፡፡ 2. በጠብ፥ በቂም ወይም በሌላ ምክንያት ተለያየ፥ ተራራቀ፥ ግንኙነት አቆመ፡፡

**ተቋረጠ** ግ 1. ቆመ፥ ቀረ፡፡ *መብራት ተቋረጠ*፡፡ 2. የተወሰነ ስራ ለመስራት ተዋዋለ፥ ተኮናተረ፡፡

**ተቋራጭ** ስ ውለታ በመዋዋል የተወሰነ ስራ እየተረከበ የሚሰራ፤ ተኮናታሪ፡፡

**አቆረጠ** ግ አቆመ፥ ተወ (ለምሳሌ ዝናም፥ የወር አበባ)፡፡

**አቆራረጠ** ግ 1. አቀያየመ፥ አጣላ፡፡ 2. በአጭር፥ በአቋራጭ መንገድ ሄደ፡፡

**አቆራራጭ** ቅ 1. አጭር (መንገድ)፡፡ 2. የሚያጣላ፡፡

**አቋረጠ** ግ 1. አቆመ፥ ተወ፡፡ *ትምህርቱን አቋርጦ ስራ ያዘ*፡፡ 2. በአጭር መንገድ ሄደ፤ አሳበረ፡፡ 3. ተሻገረ፥ ሰንጥቆ አለፈ፡፡ *ወንዙን፥ አቋርጦ ሄደ*፡፡ 4. አደናቀፈ፥ በንግግር መሃል ጣልቃ ገባ፡፡

**ማቋረጫ** ቅ 1. አጭር የሆነ (መንገድ)፡፡ 2. ማለቂያ፥ መጨረሻ፡፡ *ወሬው ማቋረጫ የለውም*፡፡

**አቋራጭ [መንገድ]** ስ ወደሚሄዱበት ቦታ በቶሎ የሚያደርስ አጭር መንገድ፡፡

**በአቋራጭ** በአጭሩ፤ ባልታሰበ፥ ባልተገመተ ዘዴ፥ አኳኋን፥ መንገድ፡፡ *በአቋራጭ ስልጣን አገኘ*፡፡

**አስቆረጠ** ግ 1. አስጨረሰ፥ የመጨረሻውን ቃል ወይም ሃሳብ አገኘ፥ አስወሰነ፡፡ 2. ገዛ (ትኬትን)፡፡

**ቆረጠመ** ግ 1. በጥርስ ሰባበረ፥ አደቀቀ፥ በላ (ጥራጥሬን፥ አጥንትን)፡፡ 2. አመመ (ሰውነትን)፡፡

**ቁርጥማት** ስ የእግርን፥ የእጅን፥... ውስጠኛ ክፍል የሚገተግት የህመም አይነት፡፡

***ቆረጠጠ**

**ቆርጣጣ (ቆረጠጥ)** ቅ ከጭንቀት፥ ከንዴት፥...የተነሳ ቆጭ ብድግ፥ ሄድ መጣ፥ ገባ ወጣ የሚል፥ የሚቁነጠነጥ(ሰው)፡፡

**ቆርጠጥ ቆርጠጥ አለ** ግ ከጭንቀት፥ ከንዴት፥... የተነሳ ቆጭ ብድግ፥ ሄድ መለስ፥ ወጣ ገባ አለ፤ ተቁነጠነጠ፤ ተንቆራጠጠ፡፡

**ተንቆራጠጠ** ግ ከጭንቀት፥ ከንዴት፥... የተነሳ ቆጭ ብድግ፥ ሄድ መለስ፥ ወጣ ገባ አለ፥ ተቁነጠነጠ፡፡

**አንቆራጠጠ** ግ 1. አንጎራደደ፥ ወዲያና ወዲህ አሰኘ፥ አላሳርፍ አለ፡፡ 2. ወዲያና ወዲህ ወሰደ፥ ከቦታ ወደቦታ አዘዋወረ፥ አንድ ቦታ ላይ እንዳይቆይ አደረገ፡፡ 3. (ዘይ.) አስጨነቀ፥ አሰቃየ፡፡

**ቆረጨመ (ቀረጨመ)** ግ ቆረጠመ፥ አደቀቀ፥ ሰበረ (በጥርስ)፡፡

**ቆረፈደ** ግ ደረቀ፥ ሻካራ ሆነ፥ ልስላሴ አጣ፡፡

**ቆርፋዳ (ቆረፈድ)** ቅ 1. የደረቀ፥ ሻካራ፡፡ 2. (ዘይ.) አመለ መጥፎ፥ ገታራ፡፡

**ቁርፍድ** ቅ ቆርፋዳ፡፡

**ተቆራፈደ** ግ 1. ደረቀ፥ ሻከረ፥ ልስላሴ አጣ፡፡ 2. ጠባዩ መጥፎ ሆነ፡፡ 3. በችግር ተቆራመደ፡፡

**አቆራፈደ** ግ በችግር አቆራመደ፥ አማቀቀ፡፡

***ቆረፈፈ**

**ቆረፋፍ (ቆርፋፋ)** ቅ ኮርፋፋ፡፡

**ተንቆረፈፈ** ግ ተንኮረፈፈ፡፡

**አንቆረፈፈ** ግ አንኮረፈፈ፡፡

**ቆሪ (ቆሬ)** ስ በጣባ ወይም በደቅ አምሳያ እንደ ዋንዛ ካለ ግንድ እየተጠረበ የሚሰራና ለውሃ መያዣ፥ ለማስታጠቢያ፥... የሚያገለግል የቤት እቃ፤ ገበቴ፡፡



*ቆሪ*

**ቆራ**[1] ግ 1. በሰለት ሰውነት ላይ በጣ፥ ምልክት አደረገ፡፡ 2. በብትር መታ፤ ቆረመ፡፡ 3. በትንሹ ላጨ፤ በቀረ፡፡

**ቆራ**[2] **"ቆረረ**[2]**"** ስር **"ቁር"** ን ተመ.

**ቆራቢ** **"ቆረበ"** ስር ተመ.

**ቆራጣ** **"ቆረጠ"** ስር ተመ.

**ቆራጥ** ዝ.ከ.

**ቆሬ** **"ቆሪ"** ን ተመ.

**ቆርማዳ** **"*ቆረመደ"** ስር ተመ.

**ቆርሳሳ** **"*ቆረሰሰ"** ስር ተመ.

**ቆርቆሮ** ስ 1. በቀላሉ ሊተጣጠፍ የሚችልና የሚብለጨለጭ እንደ ብረት ያለ የማእድን አይነት፡፡ 2. ከላይ ከተጠቀሰው የማእድን አይነት የሚሰራ ስስ የሆነ የጣሪያ መክደኛ፡፡ 3. ከላይ ከተጠቀሰው የማእድን አይነት በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ፥ በውስጡ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገሮችን

ለመያዝ የሚያገለግል እቃ።

**ቆርቆሮ ራስ** ቅ (ዘይ.፥ ስድብ) ደደብ፣ ማስተዋል፥ ማመዛዘን የሚሳነው።

**ቆርቆሮ ቤት** ስ ጣሪያው በቆርቆሮ የተሸፈነ ወይም ጣሪያውም ግድግዳውም በቆርቆሮ የተሰራ ቤት።

**የቆርቆሮ ምግብ** ስ በፋብሪካ ውስጥ የሚዘጋጅና በቆርቆሮ ውስጥ እየታሸገ ለተጠቃሚው የሚቀርብ ምግብ።

**ቆርበባ** "*ቆረበበ" ስር ተመ.

**ቆርኪ (ቆርኬ)** ስ ከቆርቆሮ የተሰራ የጠርሙስ አፍ ማሸጊያ፣ መክደኛ።



ቆርኪ

**ቆርኬ** ስ ከትከሻው ከፍ ከዳሌው አጠር የሚል፥ ቀላ ያለ ቡናማ መልክ ያለው፥ ጫፋቸው ወደ ውስጥ ጎበጥ የሚሉ ቀንዶች ያሉት፥ ጠበብ ያለ ረዥም ፊትና ከቀንዶቹ መነሻ ላይ ጉብር ያለ አጥንት ያለው፥ ሳረበል የሆነና በቆላ አካባቢ በመንጋ የሚኖር የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ቆርጣጣ** "*ቆረጠጠ" ስር ተመ.

**ቆርፋዳ** "ቆረፈደ" ስር ተመ.

**ቆርፋፋ** "*ቆረፈፈ" ስር ተመ.

**ቆሮ** "አባ ቆሮ" ን ተመ.

**ቆሰለ** ግ 1. በጦርነት፥ በጠብ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ ላይ ጉዳት ደረሰበት፣ ተላጠ፥ ተወጋ፥ ደማ፥...። 2. ቁስል ያዘ፥ አበጀ (አካል)። 3. (ዘይ.) በሃዘን፥ በንዴት፥ በመጥፎ ነገር፥... ምክንያት ስሜቱ ተጎዳ፥ ተነካ፥ በጣም ተናደደ።

**ቁስል** ስ 1.በመቆረጥ፥ በመወጋት፥... ምክንያት ተጎድቶ የሚደማ ወይም የሚመግል የሰውነት ክፍል። 2. (ዘይ.) ቁርሾ፥ ቂም፣ መጥፎ ትዝታ፥ እንከን። *በመካከላቸው የኖረ ቁስል አለ።*

**ቁስሉ ደረቀ** 1. ሻረ፥ ዳነ።2. ቁርሾው ተተወ፥ እርቅ ወረደ።

**ቁስለ ስጋ** ስ የአካል መቁሰል፣ ቁምጥና፥ ደዌ ስጋ።

**ቁስለት** ስ ንዝንዝ፥ ጭቅጭቅ፣ ንዴት ፥ ብስጭት።

**ቁስለኛ** ስ በጦርነት ወይም በሌላ አደጋ ምክንያት አካሉ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰው።

**ተቆሳሰለ** ግ (ዘይ.) ተጣላ፥ ቂም ተያያዘ።

**ተቋሰለ** ዝ.ከ.

**አቁስል** ቅ አናዳጅ፥ አብግን። *ልጁ ኣቁስል ነው።*

**ቆሰቆሰ** ግ 1. ማገዶን ወደ እሳት ውስጥ ገፋ፥ ጨመረ። 2. (ዘይ.) ጫረ፥ ጀመረ (ነገርን፥ ጠብን)።

**መቆስቆሻ** ስ ማገዶን (ደቃቅ እንጨትን፥ ፍግን) ወደ እሳት ውስጥ መግፊያ፥ መጥቀሻ (ቀላፋ እንጨት ወይም ብረት)።

**ቆስቋሽ** ቅ 1. ማገዶን (እንጨትን፥ ኩበትን፥...) ወደ እሳት ውስጥ የሚገፋ፥ የሚጨምር። 2. (ዘይ.) ጠብ ጫሪ።

**ተቆሳቆሰ** ግ ተማታ፥ ተዋጋ፥ ተገዳደለ፥ ተፋጀ፥ ተላለቀ።

**አቆሳቆሰ** ግ አማታ፥ አዋጋ፥ አፋጀ፥ አስተላለቀ።

**ቆሸመደ** ግ ከሳ፥ አቅመ ቢስ ሆነ።

**ቆሽማዳ (ቆሽመድ)** ቅ (ስድብ) አቅመቢስ፥ ደቃቃ፥ ከሲታ።

**ቆሸሸ** ግ አደፈ፥ ዕዳት አጣ፥ ንፅህና ጎደለው።

**ቆሻሻ (ቁሻሻ)** ቅ 1.ንፅህና፥ ዕዳት የሌለው። ስ 2. ጥራጊ፥ እድፍ፥ ጉድፍ። 3. (ዘይ.፥ ስድብ) ሀ- ንፅህናውን ወይም ዕዳቱን የማይጠብቅ። ለ- በግብሩ፥ በጠባዩ ብልሹ የሆነ፥ ልክስክስ።

**የቆሻሻ መኪና** ስ ተጠራቅሞ የሚቆየውን ቆሻሻ ሰብስቦ እየወሰደ ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ በሚገኝ በተወሰነ ቦታ ላይ የሚጥል መኪና።

**የቆሻሻ መጣያ** ስ 1. የሚያስቀይሙ፥ ለጤና ጠንቅ የሆኑና በቆሻሻ ደረጃ የሚታዩ ነገሮች እየተወሰዱ የሚጣሉበት ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ የሚገኝ የተወሰነ ቦታ። 2. እንደ ቅርጫት፥ በርሜል፥... ያለ ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ።

**ተንቋሸሸ** ግ ተጥላላ፥ በመጥፎነት ወይም በቆሻሻነት ታየ።

**አንቋሸሸ** ግ የአንድን ነገር መጥፎነት ወይም ቆሻሻነት በመናገር አጥላላ፥ አናናቀ፥ አኪያኪያስ።

**ቆሽቆሸ** ግ 1. ከመጠን በላይ ደረቀ፥ ገረረ። 2. (ዘይ.) በጣም አረጀ፥ ሰውነቱ ደረቀ።

**ቆሽቋሻ (ቆሽቆሽ)** ቅ 1. ከመጠን በላይ ከመድረቁ የተነሳ በቀላሉ ሊሰበር የሚችል። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) በጣም ከማርጀቱ ወይም ከመጎዳቱ የተነሳ ሰውነቱ የደረቀ፥ አቅም የሌለው፣ ቀሽማዳ።

**ተንቆሻቆሸ** ግ 1. ከመጠን በላይ ደረቀ፥ ገረረ። 2. በጣም ከማርጀቱ የተነሳ ሰውነቱ ደረቀ፣ አቅመ ቢስ፥ ቀሽማዳ ሆነ፣ ጠነጠነ።

**አንቆሻቆሸ** ግ 1. ከመጠን በላይ እንዲደርቅ፥

እንዲገር አደረገ። 2. አደቀቀ፥ ሰባበረ፥ አንኳኳ (የተጎዳ ሰውነትን በማሸት ወይም በመጫን)።

**እንቁሸቁሸ** ቅ ደራቁቻ፥ ደቃቃ፥ አቅመ ቢስ።

**ቆሸበ** ግ የምግብ ፍላጎት አሳጣ፥ ከለከለ።

**ቆሻባ (ቁሽብ)** ቅ ምግብ የማይደፍር፥ በሚገባ የማይበላ።,

**ቁሽቢያም** ዝ.ከ.

***ቆሸበለ**

**ተንቆሻበለ** ግ ተቀማጠለ።

**አንቆሻበለ** ግ አሸበለበለ፥ አቀማጠለ።

**ቆሽንዳ** ስ ከሲታ፥ ደራቁቻ።

**ቆሸደ** ግ ደረቀ (እንጀራ)።

**ቆሽድ** ስ የደረቀ እንጀራ፤ ኩቸሮ።

**ቆሻሻ "ቆሸሸ"** ስር ተመ.

**ቆሻባ "ቆሸበ"** ስር ተመ.

**ቆሽማዳ "ቆሸመደ"** ስር ተመ.

**ቆሸቋሻ "ቆሸቆሸ"** ስር ተመ.

**ቆሽት** ስ በአፈጣጠሩ ከጨጓራ ጋር የተያያዘ ሆኖ የደቀቀና የላመ ምግብ የሚገኝበት ከረጢት መሰል የሰውነት ክፍል።

**ቆሽቱ አረረ** በጣም ተናደደ፥ ተበሳጨ።

**ቆሽት አንድድ** አናዳጅ፥ አብሻቂ።

**ቆቀር** ስ ትንሽ ፍሬ ወይም አንኳር(የእጣን፥ የአፈር፥...)።

**ቆቅ** ስ 1. መጠኗ ዶሮ የሚያህል፥ በጫካ የምትኖር፥ ሰዎች በወጥመድ እየያዙ እንደ ዶሮ የሚበሏት የአእዋፍ ዝርያ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ንቁ፥ ጠርጣሪ፥ ጠንቃቃ፥ ብልጥ።

**ቆቅማ** ቅ ሀብረ ቀለሙ ቆቅ የሚመስል።

**ቆበር** ስ በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት በአፍ ዙሪያ የሚታይ አረፋ መሰል ምራቅ።

**ቆበሩን ደፈቀ** 1. ከአፉ ብዙ ምራቅ ወጣ ወይም አወጣ (ብዙውን ጊዜ በህመም ምክንያት)። 2. (ዘይ.) የማይጥምና ተገቢ ያልሆነ ነገር ተናገረ፥ ለፈለፈ።

**ቆበራም** ቅ (ስድብ) ቆበር ያለበት፥ ቆበር የሚደፍቅ።

***ቆበቆበ**

**አቆበቆበ** ግ 1. አጎረበ፥ አጎበጎበ፥ አቆረበጨ። 2.አኩበኩበ፥ ዝግጁ ሆነ (ለመሄድ፥ ለመናገር፥...)።

**አቆብቋቢ** ቅ ለመሄድ፥ ለመናገር፥... የተከለ፥ ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ላይ ያለ።

**ቆባ**[1] ስ የአተር፥ የባቄላ፥...ፍሬሽፋን፤ እንቁሪባ።

**ቆባ**[2] ቅ 1. ለፍላፊ፥ ምላሰኛ። 2. ንቁ፥ ባለሙያ (ሴት)።

**ቆብ** ስ 1. ከጨርቅ ወይም ከክር የሚሰራና መነኩሴ ወይም መንፈሳዊ ሰው ራሱ ላይ የሚደፋው አስኬማ። 2. ለፀሃይ ወይም ለብርድ መከላከያ ራስ ላይ የሚደረግ ኮፍያ።



*ቆብ 1ኛ ፍቺ*

**ቆቡን ቀደደ/ጣለ** ምንኩስናውን ትቶ አለማዊ ሆነ፤ ስልጣኑን አፈረሰ።

**ቆብ ደፋ** 1. ቆብ ራሱ ላይ አደረገ፥ ራሱን ወይም ጭንቅላቱን በቆብ ሸፈነ። 2. መነኮሰ፤ ቆብ ጫነ።

**ቆብ ጫነ** መነኮሰ።

**የቆብ ተዝካር** ስ የመነኩሱ ሰዎች በመነኩሱበት እለት ወይም በመነኩሱ በአርባኛው ቀን ወይም በየአመቱ፥ በሞተ ሰው አምሳያ ፀሎተ ፍትሃት ከተደረገላቸው በሃላ ለካህናትና ለነዳያን የሚያበሉት ድግስ፤ ተዝካር።

**የቆብ አባት** ስ አንድ ሰው በሚመነኩስበት ጊዜ፥ በተዘጋጀለት ቆብ ላይ ፀሎት አድርጎ ቆቡን ራሱ ላይ የሚደፋለት ድንግላዊ መነኩሴ፤ አመንኳሽ።

**ቆቦ** ስ በፍሬው መሸፈኛ ውስጥ ነጭ ሃር የሚመስል ባዘቶ ያለው፥ በቆላ የሚገኝና ውተታም የሆነ የእፅዋት አይነት።

***ቆተቸ**

**ቁትቻ** ስ ውርርድ።

**ተቆታቸ** ግ ተወራረደ።

**አቆታቸ** ግ አወራረደ።

**ቆቻ** ስ ብርታት፥ ጥንካሬ።

**ቆቻ ዋለ** ከቀትር በፊት ከአንድ በሬ ጋር፥ ከቀትር በሃላ ደግሞ ከሌላው በሬ ጋር በመጠመድ ምንም ድካም ሳያሳይ ቀኑን ሙሉ በጥንካሬ አረሰ (ጎበዝ የሆነ በሬ)።

**ቆነሰ** ግ በጣም ገማ፥ ሸተተ፥ ከረፋ፥ ጠነባ።

**ቁናስ** ስ ግማት፥ ክርፋት።

**ቁናሳም** ቅ (ስድብ) ግማታም፥ ክርፋታም።

**ቆነቆነ**[1] ግ ነቀዘ፥ ጠነጠነ።

**ቁንቁን (ቁንቁኔ)** ስ ነቀዝ፤ ጥንጣን፤ አንዳንድ የደረቀ የእንጨት አይነቶችን ውስጣዊ አካል እየቦረቦረ በመብላት ለብልሽት የሚዳርግ

የትል ወይም የነፍሳት አይነት።
**ቆነቆነ**[2] ግ ሰሰተ፥ ቀቀተ።
**ቁንቋና** ቅ ስስታም፥ ንፉግ፥ ቅቅታም።
**ተቆናቆነ** ግ ሰሰተ፥ ተንቆጣቆጠ።
**ቆነቆነ**[3] ግ በጥቃቅኑ ከተፈ፥ መተረ።
**መቆናቁን** ስ ዱለት።
**ቆነነ**[1] ግ ጎነጎነ፥ ሸረበ፥ ታታ (ፀጉርን፥ ጥራን፥...)።
**ቆናኝ** ስ ፀጉር ሰሪ፤ ሹሩባ ሰሪ።
**ቆነነ**[2] ግ ጀነነ፥ ኮፈሰ፥ አኮራ። *ምን ይቆንንሃል ራመድ ራመድ በል አንጂ።*
**ቁንን** ቅ ጅንን፥ ኩሩ።
**ተቆነነ** ግ ተጀነነ፥ ተኮፈሰ፥ ኮራ።
**ቆነነ**[3] ግ እየለካ፥ እየመጠነ፥ እየሰፈረ ሰጠ (የቀለብ እህልን፥ድርጎን)።
**መቁነን** ስ በገዳም ውስጥ በማህበር ለሚኖሩ መነኮሳት በቀን አንድ ጊዜ ተለክቶና ተመጥኖ ወይም ተሰፍሮ የሚሰጥ ምግብ፥ ድርጎ።
**ቆናኝ** ቅ መቁነን እየለካ ለድርጎኛ የሚሰጥ፥ አዳይ፥ አከፋፋይ።
**ተቆነነ** ግ መቁነን ታደለ፥ ተሰጠ፤ መቁነን አገኘ፥ ተቀበለ።
**ቆነደለ** ግ ሹሩባ ሰራ፥ ጎነጎነ፥ ቆነነ (ፀጉርን)።
**ቁንዳላ (ቁንዳላ)** ስ ሹሩባ የተሰራ ፀጉር።
**ቆነደደ**[1] ግ ሹሩባ ሰራ (ጎፈሬ ሆኖ የቆየውንና እስከዚህም ርዝማኔ የሌለውን ፀጉር እየሳበ)።
**ቁንድድ(ቁንድዶ)** ስ 1. የአጭር ፀጉር ሹሩባ። ቅ 2. ጎፈሬ ሆኖ የቆየውን ፀጉር ሹሩባ ያደረገች፥ የተሰራች። 3. ፀጉረ አጭር።
**ቁንዳዳ** ቅ አጭር፥ ሻካራና ቁጥርጥር ፀጉር።
**ቆነደደ**[2] ግ 1.በጅራፍ፥ በአለንጋ ገረፈ፤ በለበቅ መታ። 2. አሰቃየ (ብርድ፥ ረሃብ፥...)። 3. (ዘይ.) ቀጣ። *ጥፋተኛውን መቶ ብር ቆነደደው።*
**ቆነጀ** ግ አማረ፥ ተዋበ፤ መልከመልካም ሆነ።
**ቆነጀች** ለአቅመ ሄዋን ደረሰች።
**ቁንጅና** ስ ውበት፥ ደምግባት፥ መልከ መልካምነት።
**የቁንጅና ሳሎን** ስ የሴቶችን ፀጉር የሚተኩስ፥ የሚሰራና የውበት አገልግሎት የሚሰጥ ንግድ ቤት።
**ቆንጆ** ቅ 1.ውብ፤ ጥሩ፤ ሸጋ፥ ያማረ። ስ 2.ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ።
**ተቆነጃጀ** ግ ተዋበ፥ አማረ፥ ራሱን አስዋበ፥ አሳመረ።
**አቆነጀ** ግ አስዋበ፥ አሳመረ።
**ቆነጎለ** "ጎነቆለ" ን ተመ.

**ቆነጠረ** ግ 1. በጥቂቱ አነሳ (ለመውሰድ ወይም ለመስጠት)። 2. ወጋ፥ ቆነጠጠ፥ ቦጨቀ።
**ቁንጣሪ** ስ ብዛት ካለው ነገር ላይ በጥቂቱ ወይም በትንሹ ተከፍሎ የተነሳ፤ ጥቂት፥ ትንሽ ነገር።
***ቆነጠረ**
**ቁንጣራ** ቅ በትንሽ ነገር በመቆጣት ተነስቶ በፍጥነት የሚሄድ፤ ቁጡ።
**ቁንጥር ቁንጥር አለ** ግ ቆጣ ቆጣ አለ፤ በንዴት፥በቁጣ መንፈስ ተራመደ።
**ተቆናጠረ** ግ በቁጣ መንፈስ፥ በንዴት ተናገረ ወይም ተራመደ።
**አቆናጠረ** ግ ቆጣ ቆጣ አሰኘ፥ አስደረገ ወይም በቁጣ መንፈስ አራመደ።
***ቆነጠነጠ**
**ቁንጥንጥ (ቆነጥናጣ)** ቅ ቅብጥብጥ፥ ሰውነቱ አንድ ቦታ ላይ ረግቶ የማይቀመጥ።
**ቁንጥንጥ አለ** ግ ተቁነጠነጠ፥ ተቅበጠበጠ።
**ቁንጥንጥ አደረገ** ግ አቁነጠነጠ፥ አቅበጠበጠ።
**ተቁነጠነጠ** ግ ተቅበጠበጠ፥ እረፍት፥ እርጋታ አጣ።
**አቁነጠነጠ** ግ አቅበጠበጠ፥ እረፍት፥ እርጋታ አሳጣ።
**ቆነጠጠ** ግ 1. በእጅ ጣቶች ወይም በሌላ ነገር ሰውነትን አጥብቆ በመያዝ አሳመመ። 2. በእግር ጣቶች አጥብቆ ያዘ (እርካብን፥ መሬትን)። 3. በጉጠት፥ በመቆንጠጫ አጣብቆ ያዘ። 4.(ዘይ.) ቀጣ፥ ስርአት ይዞ እንዲያድግ አደረገ(ልጅን)። 5. ቆጥቦ፥ ሰስቶ ያዘ፤ አጠራቀመ (ሃብትን፥ ገንዘብን፥...)። 6.(ዘይ.) የሴቷን ገላ በጣት በመቆንጠጥ ለፍቅር ጉዳይ እንደሚፈልጋት ምልክት ሰጣት።
**ቆንጥጣለች** አርግዛለች።
**ቁንጥጦ አጠበ** ልብሱን፥ ጨርቅን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ቆሻሻ የነካውን ክፍል ብቻ አጠበ።
**መቆንጠጫ** ስ 1. ፍምን ወይም የጋለ ብረትን ቆንጥጦ ለመያዝና ከአንድ ቦታ ወደሌላው ለማዘዋወር እንዲረዳ የሚዘጋጅ፥ መንታ ጫፍ ያለው በንዳ ወይም ብረት። 2. ገመድ ላይ የተሰጣ ልብስ እንዳይወድቅ፥ ከገመዱ ጋር አጣብቆ እንዲይዝ ሆኖ የተሰራ መንታ ጫፍ ያለው እንጨት ወይም ሌላ ቁሳቁስ።
**ቁንጥጫ (ቁንጢጥ)** ስ 1. በአመልካች ጣትና በአውራ ጣት አማካይነት ሰውነትን በሃይል አጥብቆ የመያዝና የማሳመም ድርጊት። 2. የእጆችን የመዳፍ ጀርባዎች በጣት ቆንጥጦ

በመያዝና አንዱን በአንዱ ላይ በማነባበር፥ እንዲሁም የተነባበሩትን በማለያየትና እንደገና ድርጊቱን በመድገም የሚካሄድ የልጆች ጨዋታ።

**ቆንጠጥ አለ** ግ ጠንቀቅ፥ ክስተር አለ።

**ተቆነጠጠ** ግ ተቀጣ፥ ስነስርአት እንዲኖረው ተደረገ።

**ተቆንጥጦ ያደገ** አስተዳደጉ መልካም የሆነ፥ ጨዋ፥ ስነስርአት ያለው።

**ያልተቆነጠጠ** ባለጌ፥ ስነ ስርአት የሌለው (ልጅ)።

**ተቆናጠጠ** ግ 1. በጣቶቹ ሰውነትን አጥብቆ በመያዝ አሳመመ። 2. ተደላደለ፥ መሰረት ያዘ፥ ተቋቋመ (ለኑሮ)።


**መቆናጠጫ** ስ መቋቋሚያ፥ መነሻ (ገንዘብ)።

**አቆናጠጠ** ግ አቋቋመ፥ አደላደለ፥ አጠናከረ (አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ)።

**ቆነጥናጣ** "*ቆነጠነጠ" ስር "ቁንጥንጥ"ን ተመ.

**ቆነጨ** ግ ቁንጫ አፈራ፥ ፈጠረ፥ ቁንጫ ሆነ (ቤቱ)።

**ቁንጫ** ስ ተፈናጣሪና ዘላይ የሆነች፥ ቅማል የምታህል፥ ብዙውን ጊዜ ዕዳቱ በሚገባ ባልተጠበቀ መኖሪያ ቤት ውስጥ የምትገኝ ጥቁር ቡናማ ተባይ።



ቁንጫ

**ቆነፀለ** ግ ስለ አንድ የእውቀት ዘርፍ በጥቂቱ ወይም በቁንፅሉ አወቀ፥ ተማረ፥ ተረዳ።

**ቁንፅል** ቅ ሙሉነት የሌለው፥ ጎዶሎ።

**ቁንፅልፅል** ቅ ያልተሟላ፥ ብዙ ነገር የጎደለው።

**ቆናኝ**[1] "ቆነነ[1]" ስር ተመ.

**ቆናኝ**[2] "ቆነነ[3]" ስር ተመ.

**ቆንሲል** ስ የአገሩን መንግስት በመወከል በሌላ አገር የሚቀመጥ ተወካይ፣ ጉዳይ ፈፃሚ።

**ቆንቋና** "ቆነቆነ[2]" ስር ተመ.

**ቆንዳላ** "ቆነደለ" ስር ተመ.

**ቆንዳዳ** "ቆነደደ" ስር ተመ.

**ቆንጆ** "ቆነጀ" ስር ተመ.

**ቆንጣራ** "*ቆነጠረ" ስር ተመ.

**ቆንጥር** ስ የሚነካውን ሌላ አካል ወይም ገላ የሚበጭቅ ቆላፋ እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት።

**ቆዘመ** ግ 1. አዘነ፥ ተከዘ። 2. አለቀሰ፥ የሃዘን እንጉርጉሮ አንጎራጎረ።

**ቁዘማ** ስ 1. ሃዘን፥ ትካዜ። 2. ልቅሶ፥ የሃዘን እንጉርጉሮ።

**ቆዘረ** ግ ነፋ፥ ጎሰረ፥ ቀበተተ (ሆድን)።

**ቁዝር** ቅ ሆዱ ጉስር፥ ዝርጥጥ ያለ።

**ቁዝር አለ** ግ ሆዱ ጉስር፥ ቅብትት አለ፤ ተቆዘረ።

**ተቆዘረ** ግ ሆዱ ተቀበተተ፥ ተጎሰረ።

**ቆየ** ግ 1. ኖረ። *ሰውዬው እዚህ አገር ብዙ ጊዜ ቆይቷል።* 2. ጠበቀ። *ቆየኝ እየመጣሁ ነው።* 3. ዘገየ፥ ጊዜ አሳለፈ። *በጣም ቆይቶ መጣ።*

**የቆየ** ቅ 1. ብዙ ጊዜ የሆነው፥ የሰነበተ። 2. የድሮ የጥንት፥ በፊት ጀምሮ የነበረ፥ የኖረ።

**ቆይ** [ብቻ] ዛቻን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ቆይ እንዳሾፍክ አትቀርም።*

**መቆያ** ስ በምሳና በእራት መካከል የሚበላ አነስተኛ መጠን ያለው ምግብ፤ መክሰስ፤ የእራት መጸረሻ።

**ቆይታ** ስ በአንድ ጉዳይ ላይ በምስጢር ለመምከር፥ ለመነጋገር የሚደረግ አጭር ስብሰባ (ብዙውን ጊዜ በተከበሩ ሰዎች መካከል)። 2. በአንድ ቦታ፥ አገር፥... ሆኖ የሚያልፍ ወይም የሚያሳልፉት የተወሰነ የጊዜ መጠን። *በናዝሬት ቆይታዬ ደስተኛ ነበርኩ።* 3. ከተወሰነ ሰው ጋር ወይም ከተወሰነ ቦታ ሆኖ የተወሰነ ጊዜ ማሳለፍ።

***ቆደሰ**

**መቋደሻ** ስ የዶሮ ጨጓራ።

**ተቋደሰ** ግ 1. ተካፈለ፥ ተጋራ፥ ተቋረሰ። 2. ቀመሰ፥ አፉን አሟሸ።

**አቋደሰ** ግ1. አካፈለ፥ አጋራ፥ አቋረሰ። 2-. አቀመሰ፥ አለከፈ።

**ቆዳ** ስ 1. ከሰው ወይም ከማንኛው የእንስሳ ስጋ በስተላይ የሚገኝ የስጋ ሽፋን፥ ልባስ። 2. ከእንስሳ ስጋ ላይ የተገፈፈና ከስጋው ተለይቶ ለብቻው የተደረገ የስጋ ሽፋን፤ ቁርበት፥ አንጋሬ፥ ሌጠ። 3. የፍራፍሬ ሽፋን፥ ልጣጭ። 4. (ዘይ.) ነገር ቶሎ የማይገባው፤ ደደብ።

**ቆዳ መሬት** ስ ለምነት የሌለው፥ ቢዘሩበት የማያበቅል መጥፎ መሬት።

**የቆዳ ስፋት** ስ የአንድ ቦታ፥ ክልል፥ ሃገር፥... ጠቅላላ ስፋት።

**የቆዳ በሽታ** ስ በሰውነት ቆዳ ላይ የሚወጣ ማንኛውም አይነት ህመም (እከክ፥ ቁስል፥...)።

**ቆጋ** ግ 1. በጅራፍ ገረፈ፥ ሸነቆጠ፥ ቆነደደ። 2. የጅራፍን ጫፍ (ቁግን) አበጀ። 3. (ተራ.አነ.) ሸጠ።

**ቁግ** ስ የገመድ ጅራፍ ጫፍ(ስእሉን ጅራፍ ስር

ተመ.)::

**ቁጊያም (ቁጋም)** ቅ (ስድብ) ከሲታ::

**ቆጠረ** ግ 1. አንድ፥ ሁለት፥...እያለ የአንድን ነገር ብዛት ለይቶ አወቀ (በማስላት፥ በማካፈር ወይም ነገሮችን አንድ በአንድ በማሰብ፥ በማየት፥ በመንካት፥...):: 2. የቁጥሮችን ስም (1፥2፥3፥...) በየተራ ጠራ:: 3. ጥቅም ላይ የዋለን የመብራት፥ የውሃ፥... መጠን፥ ልክ መዘገበ (ሰራተኛው ወይም ቆጣሪው):: 4.አዘጋጀ (ቅኔን)::

**እንደ___ ቆጠረ** እንደ___አየ፥ ተመለከተ:: *እኔንም እንደ ሰው ቆጥረህ ቸርነትህን አደረግክልኝ ፈጣሪዬ?*

**ከ___ ቆጠረ** ከ ___መደበ:: *እሱንም ከሰው ቆጠርከው?*

**መቁጠሪያ** ስ አንድን የፀሎት ቃል ስንት ጊዜ መላልሰው መጥራታቸውን ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ፀሎተኞች እንደ ዶቃ በክር ሰክተው የሚይዙት፥ ቅርፁ ድቡልቡል ሆኖ መጠኑ ዳቦ ቆሎ የሚያክል፥ ብዛቱ እንደየፀሎተኛው ፍላጎት የሚወሰን፥ ከእንጨት ወይም ከሌላ ነገር የሚዘጋጅ የፀሎት መገልገያ እቃ::

**መቁጠሪያ ቁጥር** ስ ከአንድ ጀምሮ ያሉ አሃዛዊ ቁጥሮች (1፥2፥3፥...)::

**ቆጠራ** ስ የገባውን፥ የወጣውንና በእጅ ላይ ያለውን ንብረት ለይቶ ለማወቅና ለመመዝገብ የሚደረግ እቃን የመቁጠር ተግባር፤ የንብረት ቆጠራም ይባላል::

**ቆጣሪ** ስ አገልግሎት ላይ የዋለን የመብራትና የውሃ መጠን በየጊዜው መዝግቦ የሚይዝ፥ ከውሃ ቧንቧው አፍ አጠገብ እንዲሁም ከመብራት መስመር መቀበያ ላይ የሚደረግ መሳሪያ::

**የቆጣሪ [ግብር]** ስ ጥቅም ላይ ከዋለ የውሃ ወይም የመብራት ፍጆታ ዋጋ ሌላ፥ ለቆጣሪው እቃ ተብሎ በግብር መልክ የሚከፈል ገንዘብ::

**ቁጥር** ስ 1. መጠን፥ ልክ፥ ብዛት:: *የህዝቡ ቁጥር ምን ያህል ነው?* 2. መጠንን፥ ልክን፥ ብዛትን፥...የሚያሳይ ምልክት (እንደ 1፥2፥3፥...):: 3. እንደ መለያ የሚያገለግል አሃዝ:: *ቁጥሩ___ የሆነ ሸሚዝ::* 4. የአንድ ነገር የርዝመት፥ የስፋት፥... መጠን፥ ደረጃ:: *የጫማህ ቁጥር ስንት ነው?* 5. ሂሳብ፥ ስሌት (የመደመር፥ የመቀነስ፥ የማባዛት፥ የማካፈል አሰራር፥ ትምህርት)::

**በቁጥር ነው** ጥቂት ነው:: *ያላየሁቸው አገሮች በቁጥር ናቸው::*

**በ___ ቁጥር** በ___ጊዜ ሁሉ:: *በመጣ ቁጥር ይጠይቀኛል::*

**ከቁጥር አይገባም** ትንሽ ነው፥ አይረባም፥ እንዳለም አይታሰብ::

**ከቁጥር ወጣ** 1. ተለየ፥ ተገለለ፥ ተባረረ፥ ተወገደ (ከማህበር፥ ከቡድን፥... አንድነት):: 2. እንደሰው ወይም እንደ ቁምነገር የማያየው ታጣ፥ ጠፋ::

**ቁጥጥር** ስ የአንድን ነገር ሁኔታ የመከታተል፥ የመጠባበቅ፥ የመቆጣጠር ተግባር::

**[በ፥ከ] ቁጥጥር ስር አዋለ /አደረገ** በስልጣኑ፥ በፍላጎቱ፥ በትእዛዙ፥... ስር እንዲሆን አስገደደ::

**ተቆጠረ** ግ 1. ታሰበ፥ ተሰላ፥ ቁጥሩ ተነገረ፥ ታወቀ:: 2. ታየ፥ ታሰበ፤ ተገመተ:: *እንደ ስህተት ተቆጠረ::* 3. በነጥብ ተያዘ፥ ታሰበ:: 4. ተዘረዘረ፥ ተነገረ:: *ተቆጥሮም አያልቅ::*

**ተቆጣጠረ** ግ 1. ተከታተለ፥ ተጠባበቀ:: 2. አንድን ነገር ወይም ቦታ በይዞታው ስር አደረገ በቁጥጥሩ፥ በፍላጎቱ ስር እንዲውል አስገደደ::

**መቆጣጠሪያ** ስ የአንድን ነገር ተግባር፥ እንቅስቃሴ፥ ሁኔታ፥... ለመከታተል፥ ለመቆጣጠር፥... የሚያስችል ዘዴ፥ መንገድ፥ መሳሪያ::

**ተቆጣጣሪ** ስ አንድ ተግባር በአግባቡ መፈፀሙን፥ ንብረት በአግባቡ መያዙን፤ ደንብና ስርአት በወጉ መጠበቁን የሚከታተል ሰው::

**ተቋጠረ** ግ ዘሩን ወይም ትውልዱን በመቁጠር የእነማን ወገን መሆኑን ለማስረዳት አንዱ ለሌላው ተናገረ፥ አወራ፤ እገሌን የወለደው እገሌ ነው እያለ የዘመዶቹን ስም በየተራ ጠራ::

**የተቋጥሮ ዝምድና** ስ የሩቅ ዝምድና፤ ዝምድናው እንደ አጎትና አክስት በጣም ቅርብ ያልሆነ የትውልድ ግንኙነት::

**አቁጣሮ** ስ በመቁጠሪያ አማካኝነት የሚደረግ ፀሎት::

**አቆጣጠር** ስ የቆጠራ፥ የስሌት መንገድ:: *እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር/ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር::*

**ቆጠበ** ግ 1. ቶሎ እንዳያልቅ በጥንቃቄ ያዘ፥ ተጠቀመ፤ አጠቃቀሙን በጥቂቱ፥ በመጠኑ፥ በልኩ፥... አደረገ:: 2. በየጊዜው ትንሽ ትንሽ በማስቀመጥ ገንዘብ አጠራቀመ::

**ቁጠባ** ስ ገንዘብን፥ ንብረትን፥... በአግባቡ በስነስርአቱ የመገልገል ወይም በመጠን በመጠኑ የመጠቀም ድርጊት::

**የቁጠባ ሂሳብ** ስ በየጊዜው ጥቂት በጥቂት ባንክ ውስጥ በማስቀመጥ የሚጠራቀምና ወለድ ሊያስገኝ የሚችል ገንዘብ::

**የቁጠባ ቤት** ስ በአነስተኛ ወጪ በመንግስት እቅድ የሚሰራ ቤት::

**ቁጥብ** ቅ ብዙ ከመናገር፥ ከማድረግ የታቀበ፥ ራሱን በራሱ የጠበቀ፥ የተቆጣጠረ::

**ቆጣቢ** ቅ ብዙ የማያጠፋ፥ የማያባክን

(ገንዘብን፥ ንብረትን፥...)።

**ተቆጠበ** ግ ተጠበቀ፥ ተወ፤ አንድን ነገር ከማድረግ፥ ከመፈፀም ራቀ፥ ራሱን ተቆጣጠረ።

**ቆጠቆጠ**[1] ግ 1. አቃጠለ፥ ለበለበ፥ ፈጀ፤ የተላጠ ቁስል ውሃ ወይም ሌላ ነገር ሲነካው የሚሰማውን የህመም አይነት ስሜት ተሰማ። 2. (ዘይ.) አንገበገበ፥ ቆጨ፥ የቁጭት ስሜት ተሰማ።

**ቆጠቆጠ**[2] ግ 1. የዛፍን ቅርንጫፍ፥ ክንፍ፥ ቅጥያ መለመለ። 2. ቁጥቋጦን፥ ቅጠላ ቅጠልን መነጠረ።

**ቁጥቋጦ** ስ 1. በተፈጥሮ ቁመናው እንደ ዛፍ ትልልቅ (ረገርጎርም)፥ ወፍራም ያልሆነና እንደ ቀጋ፥ አጋም፥... ያለ የእፅዋት አይነት። 2. አዲስ በተቆረጠ የዛፍ ጉቶ ወይም ጉራጅ ላይ የሚበቅል የዛፍ ለጋ ቅጣይ፥ ቀንበጥ።

**አቆጠቆጠ** ግ አለመለመ፥ አፈጠፈጠ፥ አጀፈጀፈ።

***ቆጠቆጠ**[1]

**ቆጥቋጣ (ቆጠቆጥ)** ቅ ገብጋባ፥ ስስታም፥ ቆንቋና።

**ቁጥ ቁጥ** ተው.ግ. የመቆናቆን፥ የስስት፥ የቆጣቢነት አድራጎት። *ሲሰጥ ለጋስ ነው ቁጥቁጥ አያውቅም።*

**ቁጥቁጥ አለ** ግ ተስገበገበ፥ ሰሰተ፤ ተንቆጣቆጠ።

**ተንቆጣቆጠ** ግ ተስገበገበ፥ ሰሰተ፤ ቁጥቁጥ አለ።

**አንቆጣቆጠ** ግ አቆናቆነ፥ አሰሰተ።

***ቆጠቆጠ**[2]

**ተንቆጠቆጠ** ግ አሸበረቀ፥ አጌጠ፥ አማረ፥ ተዋበ።

**አንቆጠቆጠ** ግ አሸበረቀ፥ አስጌጠ፥ አሰዋበ።

**እንቁጥቁጥ** ቅ ያሸበረቀ፥ ያጌጠ።

**ቆጠቆጥ** "***ቆጠቆጠ**[1]" ስር "**ቆጥቋጣ**" ን ተመ.

**ቆጠጠ** ግ 1. ኮሳ፥ ቁጣጥ ጣለ። 2. ጎበበ፥ ቆበበ፤ ጉብ፥ ጉች ብሎ ታየ።

**ቁጣጥ** ስ በጣም ትንሽና ለስላሳ የሆነ የጨቅላ (ጥጃ፥ ግልገል፥ ልጅ) ኩስ።

**ቁጢጥ አለ** ግ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በእግሮቹ ጫፎች በቋፍ ሆኖ ተቀመጠ።

***ቆጣ**

**ቁጡ** ቅ ንዴተኛ፤ በትንሹ ነገር ሁሉ የሚበሳጭ፥ ቶሎ የሚናደድ።

**ቁጣ** ስ 1. የንዴት የመበሳጨት፥ የመናደድ፥ ሃይለቃል የመናገር፥ የማኩረፍ አድራጎት። 2. ምክር አዘል ተግሳፅ፤ ዘለፋ። 3. (ዘይ.) መአት፥ መቅሰፍት፥ ውርጂብኝ።

**ቆጣ አለ** ግ ሲቀምሱት ጣእሙ ኮምጠጥ፥ ኮስተር፥ በሰል አለ (ጠላ፥ ጠጅ፥ ቅቤ)።

**ተቆጣ** ግ 1. ተናደደ፥ ተበሳጨ፤ በቁጣ ስሜት ተናገረ። 2. ተቀየመ፥ አኩረፈ። 3. ምክር አዘል በሆነ አነጋገር ገሰፀ፥ ሰደበ፥ ዘለፈ (አባት ልጁን፥ ታላቅ ታናሽን፥...)። 4. ቆጣ አለ። 5. በተለያየ ምክንያት ሰውነት ወይም ገላ አበጠ፥ ተጉረበረበ፥...።

**ተቆጭ** ስ መካሪ፥ ተቆጣጣሪ። *ተቆጭ የሌላቸው ልጆች መጨረሻቸው ላያምር ይችላል።*

**ተቆጣጣ** ግ መከረ፥ መካከረ። *የተጣሉትን ልጆች ተቆጣጥቶ አስታረቃቸው።*

**አስቆጣ** ግ 1. አናደደ፥ አበሳጨ። 2. ቁጣ እንዲደርስበት፥ እንዲቆጡት አደረገ። 3. አስቀየመ፥ አስኮረፈ። 4. እንዲቆጣ አደረገ።

**ቆጣሪ** "**ቆጠረ**" ስር ተመ.

**ቆጣቢ** "**ቆጠበ**" ስር ተመ.

**ቆጥ** ስ አራት እግሩ መሬት ውስጥ የተተከለና ከፍታው ረዥምም የሆነ የእንጨት አልጋ (ብዙውን ጊዜ በገጠር ገበሬዎች ቤት የሚገኝ)።

**ቆጣስር (ቆጥ አስር)** ስ ሚስት ያጨ ወንድ ልጅ የጋብቻቸው ወግ ተጠናቆ ጎጆ ከመውጣታቸው በፊት ከሚስቱ ወላጆች ዘንድ ተቀምጦ ለተወሰኑ አመታት እነርሱን ያገለግልበት የነበረ ጥንታዊ የጋብቻ ውል አይነት፥ ደንብ ወይም ስርአት።

**ቆጥቋጣ** "***ቆጠቆጠ**[1]" ስር ተመ.

**ቆጨ** ግ ከነከነ፥ ቅሬታ አሳደረ፥ ፀፀተ።

**ቁጭት** ስ 1. ፀፀት፥ ንዴት፥ መቆርቆር። 2. ቂም፥ ቁርሾ። *አጋጣሚ ጠብቆ ቁጭቱን ተወጣ።*

**ቁጭቱን ተወጣ** አስቀይሞት ወይም አናዶት የነበረውን በመበቀል ረካ፥ ንዴቱን አበረደ።

**ተቆጨ** ግ ቅር ተሰኘ፥ ተናደደ፥ ተቆረቆረ፤ ተፀፀተ።

**አስቆጨ** ግ አስፀፀተ፥ ቅር አሰኘ፥ አናደደ።

***ቆጨቆጨ**

**ቆጭቋጫ** ቅ ነጭናጫ፥ ብስጩ።

**ተንቆጫቆጨ** ግ ተነጫነጨ፥ ተበሳጨ።

**አንቆጫቆጨ** ግ አነጫነጨ፥ አበሳጨ።

**ቆፈረ** ግ 1.ማሰ፥ ጎደፈረ፥ ጫረ (መሬትን)። 2.(ዘይ.) ጎረጎረ፥ ፈለፈለ፥ መረመረ (የተደበቀ ነገርን ለማግኘት፥ ለማውጣት)።

**መቆፈሪያ** ስ እንደ ዶማ፥ ድጅኖ፥ አንካሴ፥... ያለ መሬትን የመማሻ መሳሪያ።

**ቁፋሮ** ስ 1. በዶማ አማካይነት መሬትን የማረስ፥ የመጎድፈር ድርጊት። 2. በዶማ

አማካይነት የተቆፈረ መሬት::

**ቆፋሪ** ቅ 1. በዶማ መሬትን የሚጎደፍር፥ የሚያርስ:: ስ 2. ዶመኛ፤ መሬትን ለማረስ ለመጫር በዶማ የሚገለገል ሰው::

**ቁፍርፍር አለ** ግ ተቆፋፈረ::

**ተቆፈረ** ግ ተማሰ፥ ተጎደፈረ፥ ተጫረ፥ በዶማ ታረሰ::

**ተቆፋፈረ** ግ ፈላለሰ፥ እዚህም እዚያም ተማሰ፥ በዶማ ታረሰ::

**ቆፈነን** ግ እጅንና እግርን ያዘ፥ አላንቀሳቅስ አለ፥ አደነዘዘ (ብርድ)::

**ቆፈን** ስ እጅንና እግርን የሚይዝ፥ የሚያደነዝዝ ብርድ፥ ቅዝቃዜ::

**ቆፈናም** ቅ 1. በጣም ብርዳም ወይም ቀዝቃዛ የሆነ (ቦታ):: 2. (ስድብ) ሰውነቱ በቆፈን የደነዘዘ፥ ከርፋፋ:: 3. (ዘይ.) ስስታም፥ ሲሰጥ እጁ በስስት የሚንቀጠቀጥ::

***ቆፈጠነ**

**ቆፍጣና** ቅ ንቁ፥ ቀልጣፋ፤ ኩሩ::

**ቆፋሪ "ቆፈረ"** ስር ተመ.

**ቆፍ**

**ቆፍ ቆፍ አደረገ** ግ የመቆርቆር፥ የማንኳኳት፥ የመምታት አይነት ድምፅ አሰማ::

**ቆፍጣና "*ቆፈጠነ"** ስር ተመ.

**ቋ**[1] የ **"ቀ"** ፊደል ፍንዕቅ ዘር::

**ቋ**[2]

**ቋ አለ** ግ ቀጭ፥ ኳ አለ፤ የመሰበር፥ የመገጨት አይነት ድምፅ አሰማ::

**ቋሊማ** ስ የተከተፈን ስጋ በቅመም አጣፍጦ በታለበ ወተት አንጀት ውስጥ በመከተት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::

**ቋመጠ** ግ ጎመጀ፥ ጓጓ፥ ከጀለ (አንድን ነገር ለማየት፥ ለማድረግ፥ ለማግኘት)::

**አቋመጠ** ግ አጎመጀ፥ አጓጓ::

**ቋሚ "ቆመ"** ስር ተመ.

**ቋር** ስ በእንጨት አካል ላይ ተድቦልቡሎ ወይም አትሮ የሚታይ የእንጨት ጉጥ::

**ቋራም** ቅ ቋር ያለበት (እንጨት)::

**ቋርፍ** ስ ብዙውን ጊዜ መናኞች የሚመገቡት ከዱር እፅዋት ፍራፍሬና ስራስር የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::

**ቋሮ** ስ ራሰ ትልቅ አሳ::

**ቋቁቻ** ስ ብዙውን ጊዜ በሰው ፊት፥ አንገት፥ ደረት ላይ የሚወጣ የቆዳ በሽታ አይነት::

**ቋቅ**

**ቋቅ አለ** ግ 1. አስመለሰ፡ አስታወከ:: 2. (ዘይ.) ሰለቸ፥ አስጠላ:: *ስራው አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ቋቅ ብሎታል::*

**ቋቅ እስኪለው** እስኪያንገፈግፈው፥ እስኪሰለቸው::

**ቋቋ**

**ቋቋቴ** ስ የፍሬ መያዣውን ከረጢት በጣም አጣብቀው ሲጫኑት ከረጢቱ የፍንዳታ ድምፅ በማሰማት የሚተረተር የእፅዋት አይነት::

**ቋ ቋ አለ** ግ ተንቋቋ::

**ተንቋቋ** ግ 1. ቋቋ የሚል የድምፅ አይነት አሰማ::2. በጣም ከማርጀቱና ሰውነቱ ከመግረሩ የተነሳ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሰውነቱ ቋቋ የሚል ድምፅ አሰማ::

**አንቋቋ** ግ ቋቋ የሚል የድምፅ አይነት አሰማ ወይም እንዲሰማ አደረገ::

**ቋተ** ግ አንድ ቦታ ላይ ተጠራቀመ፥ ተከማቸ (ለምሳሌ ፍሳሽ ውሃ)::

**ቋት** ስ 1.እህል ሲከካም ሆነ ወይንም ሲፈጭ ከወፍጮው ላይ የሚወርደው ክክ ወይም ዱቄት የሚከማችበት፥ ከባህላዊው የቁም ወፍጮ ጋር ተያይዞ ከጭቃ ወይም ከሸክላ የሚሰራ ማጠራቀሚያ:: 2. መጠራቀሚያ፥ መከማቻ:: *ሰውየው የበሽታ ቋት ነው::*(ዘይ.) ሆድ:: *ቀን ከሌት የሚሰራው ቋቱን ለመሙላት ነው::*

**ቋቱ ጠብ አይልም** 1. አይጠራቀምም:: 2. አይሟላም፤ አይሳካም::

**ከቋት ከቋቱ** ከስር ከስሩ፥ ወዲያው ወዲያው፥ ሳይቆይ::

**አቋተ** ግ 1. የሚፈጨውን እህል ከወፍጮው አናት አካባቢ አደረገ፥ ወይም የሚፈጨውን እህል በወፍጮው ማቋቻ ላይ ደቀነ:: 2. አንድ ቦታ ላይ ተከማቸ፥ ከተተ (በመፍሰስ ላይ ያለ ፈሳሽ ነገር)::

**ማቋቻ** ስ የሚፈጨው እህል የሚቀመጥበት (የሚደቀንበት) የወፍጮው የላይኛው ጠርዝ፥ ወይም አናቱ::

**ቋንቁራ** ስ መንገደኛ የሚሸከመው ቅራቅንቦ፤ ሰባራ ስንጥሩ፥ ጥቃቅኑ እቃ ሁሉ ባንድ ላይ (ቅሉ፥ አገልግሉ፥...)::

**ቋንቋ** ስ 1. ሰዎች እርስ በርስ ለመግባቢያነት የሚገለገሉበት፥ ሃሳባቸውን፥ ስሜታቸውን የሚገልፁበት፥ ስርአት ያለው የድምፆች የቃላት፥... ጥንቅር:: 2. የአንድ ቡድን፥ ሃገር፥ ብሄረሰብ፥... አባላት ለመግባቢያነት የሚገለገሉበት የቋንቋ ቅርፅ ወይም አይነት:: *የቤም ቋንቋ /አማርኛ ቋንቋ/ የአፍ መፍቻ ቋንቋ::* 3. የአገላለፅ መንገድ:: *ሃሳቡን ተውና ቋንቋውን ብቻ አርምልኝ/ ገንዘቡን እንደማይከፍል በማያሻማ ቋንቋ ነገራቸው::* 4.

የተወሰነ የህዝብ ክፍል እርስ በርስ ለመግባባት የሚገለገልበት ቃል ወይም ሃረግ፥...። *የኦሮሞ ቋንቋ /የሌቦች ቋንቋ።*

**ቋንቋ** "ቋንጃ" ን ተመ.

**ቋንዶ [ሃረግ]** ስ ጠንካራ የሃረግ አይነት።

**ቋንጃ (ቋንቋ)** ስ ከጉልበት በስተሂላ በባትና በጭን መካከል የሚገኝ መታጠፊያው ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ቋንጃ ቆራጭ** ስ የሰው ሃብትና ንብረት የሚዘርፍ፥ በሰዎች ላይ ግፍ የሚፈፅም፥ ወንጀለኛ፤ ሽፍታ፥ ወንበዴ።

**ቋንጣ**[1] ስ 1. በቀጭኑ ተዘልዝሉና ገመድ ወይም ሽቦ ላይ ተሰቅሉ እንዲደርቅ የሚደረግ የእንስሳት ስጋ። 2.ስ የበሰለና የደረቀ የበለስ ወይም የዋርካ ፍሬ። 3.(ዘይ.) ከሲታ ወይም በጣም ቀጭን የሆነ (ሰው)።

**ቋንጣ እግር** እግረ ቀጭን የሆነ (ሰው)።

**ቋንጤ ወንበር** ስ በጠፍር የተሰራና፥ መደገፊያ ያለው የእንጨት ወንበር።

**ቋንጣ**[2] ስ በእንዝርት አናት ላይ የሚሰካ፥ ቆላፋ የሆነ ቀጭን ሽቦ።

**ቋኛት** ስ ከሃረግ ወይም ከመቃ የሚሰራ የአሳ መያዣ ሞላላ ቅርጫት።

**ቋዝመን** ስ እንደ ጩቤ ያለ አነስተኛ ካራ።

**ቋያ** ስ የደረቀና ያልታጨደ የበረሃ ሳር።

**የቋያ እሳት** ስ በቋያ ላይ የሚነሳና ከፍተኛ የመቀጣጠል ፍጥነት ያለው የሰደድ እሳት።

**ቋድ** ስ እንደዛብ አራት ማእዘንነት ያለው የሃር፥ የጠፍር፥... ጉንጉን።

**ቋጠረ** ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አያያዘ፥ አቆራኘ፥ አጠላለፈ (ለምሳሌ አንድን ገመድ ከሌላ ገመድ ወይም ከሌላ ነገር ጋር)። 2. በጨርቅ ወይም በሌላ በተመሳሳይ ነገር ጠቅልሉ፥ ሸፍኖ አሰረ። *እረኛው ምሳውን በልብሱ ቋጥሮ ሄደ /ሴትዮዋ ሳንቲሞቿን በመሃረብ ቋጥራ ኣስቀመጠች።* 3. በውስጡ ያዘ፥ አዘለ፥ አቆረ። *የእሳት ነበልባል የገረፈው ገላው ውሃ ቋጠረ።* 4. አፍኖ ያዘ፥ ተቆጣጠረ። *ከስብሰባ ላይ ተነስቶ መውጣት ስለፈራ ሽንቱን ቋጥሮ ዋለ።* 5. አጠራቀመ፥ አካበተ፥ አኖረ። *ትንሽ ጊዜ ነግዶ ደህና ገንዘብ ቋጥሯል።* 6. አሴረ፥ ተበተበ (ነገርን)።

**ቋጠረች** ፀነሰች፥ አረገዘች።

**መቋጠሪያ** ስ 1. ማሰሪያ (ገመድ)። 2.መከተቻ፥ መያዣ፥ መጠቅለያ (ከረጢት፥ ስልቻ፥ ጨርቅ፥...)።

**መቋጠሪያው ተበጥሷል** ፈሱን መያዝ፥ ወይም መቆጣጠር አይችልም፤ በመጣበት ጊዜ ሁሉ ይፈሳል።

**ቁጥር** ስ እስር። *ቋጥሩ የጠበቀ ነው፤ ኣይፈታም።*

**ቁጥርጥር** ቅ 1. እርስ በርሱ የተያያዘ፥ የተሳሰረ (ነገር)። *ፀጉሩ ቁጥርጥር ብሏል፤ ተበጥሮም ኣያውቅ።* 2. ብዛት ያለውና ተቋጥሮ ተቋጥሮ የተቀመጠ እቃ። *ሴትዮዋ የገዛችውን ቅመማ ቅመም ለያይታ ከቋጠረች በሂላ ቁጥርጥሩን በአንድነት ተሸክማ ሄደች።*

**ቁጥርጥር አለ** ግ እርስ በርስ ተጠላለፈ፥ ተያያዘ፥ ተተባተበ፥ ተወሳሰበ።

**ቋጠሮ** ስ 1.እስር (የገመድ፥ የጨርቅ፥...)። 2. የተቋጠረ።

**ተቋጠረ** ግ 1. ታሰረ። 2. ኣብሮ ሆነ፥ አልነጠል ኣለ። 3. ደደረ፥ ጓጎለ።

**ተቆጣጠረ** ግ እርስ በርስ ተጠላለፈ፥ ተተባተበ፥ ተወሳሰበ።

**ቋጥኝ** ስ መጠኑ በጣም ትልቅ የሆነና መሬት ላይ ጉብ ብሉ የሚገኝ ድንጋይ።

**ቋጨ** ግ 1. የነጠላን፥ የጋቢን፥....ጫፍ ወይም ዘርፍ ገመደ፥ አከረረ፤ ፈተለ። 2. (ዘይ.) አንድን ሃሳብ፥ነገር፥ ጉዳይ፥... ከውሳኔ ወይም ከውጤት ላይ አደረሰ፤ አጠቃለለ፥ ደመደመ።

**ቁጨት** ስ 1. የነጠላን፥ የጋቢን፥...ጫፍ ወይም ዘርፍ የመግመድ፥ የማከረር ወይም የመፍተል ተግባር። 2. የተገመደ ወይም የተፈተለ የነጠላ፥ የጋቢ፥... ጫፍ ወይም ዘርፍ።

**ቋጨራ** ስ ለቤት ክዳን ስራ እንዲያመች በገብስ ነዶ መጠን የሚታሰር ሰንበሌጥ፥ ጓሳ፥...።

**ቋጫ** ስ ከስንደዶ ወይም ከአክርማ የሚሰፋ የወተት ማለቢያ፤ ጮጮ።

***ቋፈ**[1]

**ቋፍ** ስ ጫፍ፤ ጠርዝ፥ ኣፋፍ። *ቋፍ ላይ ኣትቀመጥ፤ ትወድቃለህ።*

**በቋፍ [ላይ] ነው** ትንሽ ሰበብ፥ ምክንያት ይበቃዋል (ኣንድ ነገር ለመሆን፥ ለማድረግ፥...)።

***ቋፈ**[2]

**ተቋፈ** ግ ተቆነነ፥ ተጀነነ (በአካሄድ፥ በአነጋገር፥...)።

**አቋፈ** ግ ቆነነ፥ ጀነነ፥ ቀስ አደረገ።

**አስቋፈ** ዝ.ከ.